# ክርስቶስ የተገለጠ የእግዚአብሔር ምስጢር ነው

እናመሰግናለን፡ ወንድም ነቪል። እግዚአብሔር ይባርክህ። ራሶቻችን ለጸሎት እንዳቀረቀርን ለአፍታ እንቆማለን።

2 ቸር የሰማይ አባት ሆይ፡ ዛሬም በዚህ ማለዳ ቃልህን እንድንማር ስለ ምሕረትህ እና ስለ መንፈስ ቅዱስ ምሪት፡ ዛሬ በሕብረት አንድ ሆነን፡ ቃልህ ለመማር መገናኘት እንዳለብን ስለገባን፡ ይህም በአሁኑ ዘመን እንዴት መኖር እንዳለብን፡ ምናልባትም ዘመኑን ማወቅ እንችል ዘንድ ነው። እንድናውቀው የሚገባንን ቃልህን ለማወቅ፡ ወደ እያንዳንዱ ቃልህ እንዲመራን፡ ሐሳባችን እና ልባችን የሚመራ ቅዱስ ምሪትህን እንጠይቃለን፡ ብቻህን የእግዚአብሔርን ቃል የምትገልጥ መሆንህን፡ እያወቅን፡ እና፡ ለምትናገረው ቃል፡ ልባችን ተቀባይ እንዲሆን፡ እንደበታችንም እንድትከፍተው፡ ትክክል ባልሆነ ነገር ላይም አንደበቶቻችን እንድትዘጋ እንጠይቅሃለን።

3 አሁንም ጌታ ሆይ እቺ ትንሽ ቤተክርስትያን ትቼ ወደ ሌላኛው የምድር ጥግ በምሄድበት ጊዜ፡ ጌታ ሆይ፡ በአንተ ፊት አቀርባቸዋለሁ። እነኚህ፡ የልቤ ትርታ፡ የልቤ ደስታ፡ ብያቸዋለሁና። በመንፈስ እና በእውነት ቃል የተወለዱልህ፡ ብቸኞቹ ልጆችህ——ናቸውና። ጌታ ሆይ፡ እንድትባርካቸው፡ እንዲሁም በክርስቶስ የፍቅር ገመድ አስረህ አጥብቀህ እንድትጠብቃቸው እጸልያለሁ።

4 የተወደደው ፓስተራችንን፡ እረኛውን ባርከው። በቃልህ መንፈስ ቅዱስ ቀብተህ እንድትገልጥለት፡ እና መንጋውን እንዲመግብ፡ እንጸልያለን።

5 ያኔ፡ በቅርብ ጊኢዜ፡ ስለዚች ድንኳን፡ ራእይ ስታሳየን፡ በጣም ተፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ ይመጣልና፡ ምግብን አከማችሁ ብለህ ነግረኸን ነበር። ወንድማችን ሶዝማን እና ወንድም ዉድስ አገር አቋርጠው ለመሻገር ተዘጋጅተው፡ ባየናቸው ጊዜ... አንተ ግን፡ “ለጊዜው ይህ ምግብ በዚህ ስፍራ አከማቹት።” እንዳልከን ጌታ ሆይ፡ ያልከንን ለማድረግ በቅድስና ሞክሬአለሁ።

6 አሁንም፡ በዚህ ማለዳ፡ በተማርነው ትምህርት፡ ጌታ ሆይ፡ አምላክ መሆንህን፡ እንዲሁም ቃልህ እና እውነትህ መሆኑን፡ እንድታሳይ እጸልያለሁ። ጌታ ሆይ፡ ህዝቡ፡ ከአምላክ ጸጋ እንደሚሆን፡ ተመግቦ ይፋፉ ዘንድ፡ እንዲሁም በዚ ዘመን ለእኛ ያለውን፡ ታላቁን የአምላክ ምህረት መሆኑን ይገነዘቡ ዘንድ ይህን አድርግልን። አባት ሆይ፡ ዛሬ በዚ ስፍራ የተገኙትን እንዲሁም መገኘት የተመኙትን ሁሉ ባርካቸው። ክብር ሁሉ ለአንተ ይሁን፡ በኢየሱስ ስም እንጸልያለን። አሜን።

ጌታ ሁላችሁም ይባርካችሁ።

7 እንግዲህ አሁን እንደማምነው፡ ከመጀመራችን በፊት፡ ከአቶ ኮሊንስ ቤተሰብ፡ ህጻን ልጅ መጥቷል። ቀደም ብየ አባትየውን አነጋግሬዋለሁ፡ ለጌታ——

አደራ የሚሰጥ ህጻን አላቸው። በቀጥታ እሱን እናደርጋለን፡ ወንድም ወይም እህት ኮሊንስ፡ እንዳቸው፡ የህጻኑን ልጅ አደራ የመስጠቱን ስርዓት ማከናወን እንድንችል ህጻኑን ልጅ አቅፈው ወደዚህ ያመጡታል።

8 ይህ ለምን እንደሚሆን፡ ታውቃላችሁ፡ እነኚህ፡ የክርስቶስ አካል... ታማኝ፡ አባላት፡ ናቸው። “ስለ ህንጻው” ተናግሬ እንደማላውቅ፡ እስተውሉ። “የክርስቶስ አካል፡” ይህ... ይሄኛው አካል፡ የአካሉ ክፍል ነው።

9 ስለዚህም አደራ ሊሰጡት የፈለጉትን ልጅ ይዘው መጥተዋል። ይህም—ህጻናትን ማቀፍ፡ ባለቤቴ ሁልጊዜ የምትቀናብኝ ሥራ—ይህ ይመስለኛል። እህ-ሃህ። ወንድም ነቪለ፡ ከቻልክ፡ ወደፊት ብትመጣልን።

10 የመጀመርያ ስምህ ማን ነበር ወንድሜ? [አባትዬው “ክላይድ ነው፡” አለ።—አርታዒ።] እነኚህ ወንድም እና እህት ክላይድ ኮሊንስ ይባላሉ፡ የውድ ወንድማችን የሬቨረንድ ዊላርድ፡ ኮሊንስ ወንድም ነው። እንደማየው የኮሊንስ ቤተሰብ እየበዛ ነው፡ እንደው፡ የሚያምር ልጅ ነው።

11 ስንት ጊዜ ሆነው፡ እህት ኮሊንስ? [እናትዬውም “አራት ወር ገደማ፡” አለች።—አርታዒ።] አራት ወር ገደማ። ስሙስ ማን አላችሁት? [“ማርክ ዴቪድ።”] ማርክ ዴቪድ። ቆንጆ ስም ነው። ቆንጆ ልጅ ይመስላል። እንደው፡ ትልቅ ልጅም ነው፡ እባካችሁ።

12 እዚህ ያሉ እናቶች እንዲህ ዓይነቱ ልጅ እንደሚያደንቁ አውቃለሁ። አሻንጉሊት ነው አይደል?

በጣም ጥሩ፡ አሁን ራሶቻችን ዝቅ እንዳደረግን።

13 የሰማይ አባት ሆይ፡ እነዚህ ወጣት አባት እና ወጣት እናት፡ ጌታ አምላክ በመጠበቃቸው ምክንያት ስለ አንድነታቸው ወደ እጃቸው የተረከቡትን፡ ይህን ድንቅ የሰው ጨቅላ ይዘው መጥተዋል። ይህን ድንቅ ልጅ ለሰጣቸው ለእምላክ ክብር ይሆን ዘንድ ሁሉን ለሚችል አምላክ በትህትና ሊያስረክቡት፡ በመልካም ጤና ያለው ወንድ ልጅ፡ እንዲያሳድጉ፡ ወደ ሰጣቸው እንዲያስረክቡ፡ ህጻን ማርክ ዴቪድን ይዘው መጥተዋል።

14 ጌታ ሆይ፡ አባት እና እናት ባርካቸው። በቤታቸው፡ ቡህቃቸው ባዶ አይሁን፡ እንስራቸውም በፍጹም አይድረቅ። ጌታ ሆይ፡ ለጨቅላው ማሳደግያ ይሰራ ዘንድ፡ አባትየውን ጤናን ስጠው፡ እናትየውም የተዘጋጀች ትሁን፡ ጌታ ሆይ፡ ጨቅላውን በጌታ ምክር እያሳደጉ፡ ለማስተማር፡ ልባቸው የተዘጋጀ ይሁን። ይሁን፡ ጌታ ሆይ።

15 ይህ የተወደደ ጨቅላ፡ ማርክ ዴቪድ፡ ከእጃቸው ወደ እኔ፡ ተቀብዬዋለሁና። ከቤተክርስትያኑ ሽማግሌ ጋር በመሆን፡ መላ ህይወቱ፡ ለክርስቶስ ኢየሱስ አገልግሎት ይሆን ዘንድ፡ ለአንተ አስረክባለሁ። ይሁን፡ ጌታ ሆይ። ከህይወቱም ክብር ይሁንልህ። አንተን ደስ የሚያሰኝ ከሆነ፡ እስከ ጌታ ኢየሱስ መምጣት ድረስ፡ ረጅም እድሜ ይሁንለት። እንግዲህ፡ ከሆነም፡ በሚመጣው ዘመን፡ የጌታ የእግዚአብሔር መልእክት የሚሸከም ይሁን። ይሁንለት። ጤናን ስጠው፡ ደስተኛም ይሁን፡ በጌታ ፊት ቅን የሆነውን ያደርግ ዘንድ፡ ልቡ ሁልጊዜ የተዘጋጀ ይሁን። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ልጁን ለአንተ፡ አደራ ሰጠን። አሜን።

16 እግዚአብሔር ይባርካችሁ። እህት ኮሊንስ፡ እና ይህን ጨቅላ፡ አንተንም ወንድማችን ኮሊንስ፡ ጌታ ይባርካችሁ። ጌታ ከእናንተ ጋር ይሁን።

**አምጡአቸው**፡ አንድ ላይ እንዘምር፡

አምጡአቸው፡ አምጡአቸው፡
ከሀጢአት ማሳ አምጡአቸው፡
አምጡአቸው፡ አምጡአቸው፡
ታናናሾቹን ወደ ኢየሱስ አምጡአቸው።

17 ደስ ይላል። አያችሁ፡ ዲያብሎስ እድል ከማግኘቱ በፊት ወደ ኢየሱስ አምጡአቸው። ከዛ በኋላ ስለ ህይወት አገልግሎት ለሱ የተዘጋጁ ይሆኑለታል።

18 የዳች ቤተሰብ እንዳቸው፡ ዛሬ እዚ መምጣታቸውን፡ አለመምጣታቸውን፡ የሚያውቅ ሰው አለ እንዴ፡ እህት ዳውች? ወንድም ብራውን፡ እዚ ነህ፡ ወንድም ብራውን? የሰ፡ እሰይ። ወንድም ዳውችስ... አብሮን አለ? አሹ! [ወንድም ቶም ብራውን ስለ ወንድም ዊልያም ዳውች ሁኔታ አስተያየት ሰጠ—አርታዒ።] ወንድም ዳውች አምልጦን ነበር። አያችሁ፡ ምን እንላለን ምንስ እንመልሳለን፡ ጌታ ትኖራለህ ካለው ዘመን ጀምሮ አሁን ሀያ-አንደኛው ዓመቱ ይዟል። እግዚአብሔር መኖር እንደሚችል ከነገረው ጊዜ በላይ፡ ያልታቀደ የህይወት ዘመን እየኖረ።

19 ባለፈው ማለዳ፡ ሊሞት—ተቃርቦአል ተብሎ ተደውሎልን፡ እየተሯሯጥን ደረስን። ጌታ ግን ለሱ መልካም ሆነለት፡ አዳነውም። እንደሚመስለኝ፡ ተዘጋጅቶ—የጌታን መምጣት እየተጠባበቀ ነው። ግን፡ ታውቃላችሁ፡ እርስ በርስ ተያይዘናል። እንደው... ሽማግሌው ለኔ—እንደ አባት ነው።

20 በፊት በነበረችው አዳራሽ፡ ወደዛ አከባቢ ሲቀመጥ ትዝ ይለኛል። ያኔ... በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እያጠመቅን ሳለን፡ በውኃው ዙርያ ታላቅ ብርሃን ሲንጸባረቅ፡ ያኔ ነው የመጣው። ምርኩዝ የያዘ፡ የሰማንያ-ሰባት ወይም ሰማንያ-ሰምንት ዐመት አዛውንት ሆኖ ጠጋ ብሎ፡ በቀጥታ ወደዚህ መጣና፡ "ገብቼ መጠመቅ እፈልጋለው" አለን። አንድ ሰው ሄዶ ልብስ አመጣለት። ሌላ ጊዜ እመጣለሁ ብሎ እንኳን አላሰበም፡ ወድያው መምጣት ነበረበት፡ ወድያውኑ። በጣም—ወደድኩለት።

21 በቀደምለት፡ እያናገርኩት ነበርና፡ "ወንድም ብራንሀም፡ አሁንስ፡ ደህና እመስልሃለሁ ወይ፡" ብሎ ጠየቀኝ?

22 እኔም፡ "ለቼክ አፕ ወደ ዶክተር ሄደህ ታውቃለህ" ብየ ጠየቅኩት?

"አዎን፡ ጌታዬ፡" አለኝ።

23 እንዲህ አልኩት፡ "ሐኪሙ ስቴቶስኮፖችን በጆሮው ውስጥ ያስገባል፡ ልብህ ላይ ያደርገዋል፡ ልብህ በትክክል እየመታ መሆኑን ያያል፡ እና የኤሌክትሪክ ካርዲዮግራም፡ ከዚያም የደም ግፊት፡ የሽንት ምርመራ፡ ወዘተ፡ መሳርያዎችን በመጠቀም፡ የሰውነትህን ሁኔታ ይመረምራል። አሁን፡ የእሱ አደራረግ፡ በተለያዩ ርእስ ጉዳዮች ላይ—የተለያዩ ስፔሻሊስቶች የጻፉትን መጻህፍት፡ ያገላብጣል፡ 'ይህም **እንዲህ** ከሆነ፡ ችግሩ ይህ ነው የሚሉ መጻሕፍትን በማገላበጥ ነው።'"

24 እኔም “እንግዲህ፡ እየህ፡ እኔ የያዝኩት ብቸኛው የነፍስ ስትርዮስኮፕ፡ መጽሓፍ ቅዱስ ነው፡” አልኩት። እኔም፡ “ምርመራ አደርግልሃለሁ፡” አልኩት። እንዲህ አልኩት፡- “ዮሃንስ 5፡24 ‘ቃሌን የሚሰማ፡’ ይላል አልኩት።” እንዲህ አልኩት፡ “ቁጭ ብሎ መሰማት ብቻ አይደለም። መቀበል ነው፡ እየህ፡ ስትቀበለው፡ ታምነዋለህ። የሆነ ነገር ከውስጥህ ትክክል ነው አለህ። አንተም ተቀበልከው፡ አመንከው፡ ያንተው ሆነ። የአንተው ነው፡ ‘ቃሌን፡’ ‘የሚሰማ፡ በላከኝም የሚያምን።’ ይህን ታምናለህ? ”

“እምናለሁ፡” አለኝ።

25 እንዲህ አልኩት፡ “የሐኪሞች አለቃ ያለውን ልንገርህ፡ ‘ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ፡ ወደ ፍርድም ወደ ኩነኔ ከእንግዲህ ወዲህ አይመጣም።’” “እስከማውቀው ድረስ፡ በመጽሐፍት መሰረት፡ ፈተናውን አልፈሃል፡” አልኩት።

26 ይህ ፈጽሞ የቸርች ሰው ያልሆነው፡ የአንድ መቶ አመት ገደማ፡ አዛውንት፡ የብርሀን ጸዳል በመንገዱ በፊቱ ባንጸባረቀ ጊዜ፡ ይህንን ተቀበለ። ይህች አስቀድማ የተወሰነችው ዘር አያችኋት? አሀ-ሃህ። የስ፡ ሰር። አያችሁ፡ ልክ ብርሀን ስታገኝ፡ በፍጥነት ወደ ህይወት መጣች።

27 እንግዲህ፡ ዛሬ ሞቃት እንደሆነ አውቃለሁ፡ እና፡ እንዲህ በጣም በተተፋፈጋችሁበት ጉባኤ ላይ ሁላችሁም ወደ ጉባኤው መጥራት የሚቻል አይመስለኝም። ይሁን እንጂ፡ በጌታ ጸጋ—ሁላችሁም ትቻችሁ ከመሄዴ በፊት፡ ለአጭር ጊዜ፡ ሌላ ጉባኤ እንደሚኖረን፡ እምናለሁ።

28 ስለዚህ አሁን እሮብ ስለሚጀመር ጉባኤ፡ ነገ ማታ፡ ወደ ቺካጎ መሄድ ይኖርብኛል። ከተቻለኝ፡ ተከታታይ ጉባኤዎች ከመጀመራችን በፊት እደርሳለሁ፡ ምናልባትም ጥቂት እረፍት አደርጋለሁ። እዚህም፡ እንደደረሳቸው እምናለሁ... እያየሁት ነበር። እዛም—እያስተዋወቁት ይገኛሉ። ሰሙ ማሬንጎ ይባላል... [አንድ ሰው፡ “ማሪጎልድ” አለ።—እርታዒ።]... አካባቢው፣ አዎን፡ ማሪጎልድ፡ አካባቢ፡ አዎን፡ ማሪጎልድ፡ ሜዳ ነው። ማሪጎልድ ሜዳ ከረቡዕ ምሽት ጀምሮ፡ እስከ እሁድ ድረስ፡ የሚካሄድበት ቦታ ነው። የፉል ጎስፔል ቢዝነስ ሜን—ቅዳሜ ጠዋት፡ የቁርስ ስነ ስርዐት፡ ይኖራቸዋል። እና ያንን ማስታወቂያ፡ ከየት እንዳገኙት በትክክል አላውቅም። እንጃ። ከዛ ቅዳሜ ማታ በሌን ቴክ ይካሄዳል። እዚ በማስታወቅያው—ይታየኛል።

29 እንግዲህ፡ በአቅራቢያው፡ ወይም በዙርያው ከሆናችሁ፡ ሁሌም እንደምናደርገው፡ የተለመደው የወንጌል ጉባኤ ይሆናል። አብዛኞቹ መልዕክቶች እዚሁ የተማርናቸው ትምህርቶች ይሆናሉ፡ ምክንያቱ፡ ቴፖቻችን የምንቀዳው ከዚ ሰፍራ ነውና። እዛ ምናልባት ሊያቅራሩ ይችላሉ። ከዚህ የተቀዳ መስማት ከወደዱ ግን፡ የተቀዱ ቴፖች ከፈለጉ ማዳመጥ ይችላሉ። የሚጀምረው ከዚህ ነው። ይህ ፑልፒታችን ነው።

30 ስለዚ እዛ፡ ብዙ ጊዜ ብዙም ጠለቅ ያላሉ ጉዳዮችን ነው የማነሣው፡ ምክንያቱ በልምድም ይሁን በአቀባበል ገና ስር ያልሰደዱ ስለሆኑ ነው። እዚህ ግን ጌታ እንድናገረው በልቤ ያሰቀመጠውን እንድናገር፡ ምሉ ነጻነት ይሰማኛል። ስለዚ ቴፖቻችን ሁሉ እዚህ ይቀዳሉ። እያችሁ? እና አሁንም እዚያ

ክፍል ውስጥ ናቸው፡ መቅጃ መሳርያዎቻቸው አስተካክለው፡ በመስተዋቶቹ ራሶቻቸው ብቅ ብቅ ብለው ይታያሉ።

31 አሁን፡ ስብሰባው ላይ መገኘት ከፈለጋችሁ፡ በደስታ እንቀበላችኋለን። እዛ ደርሳችሁ፡ የምትሄዱበት ከጠፋባችሁ፡ ዝም ብላችሁ፡ የፋል ጎስፔል ሰዎችን፡ መጠየቅ ትችላላችሁ፡ ወይም––ደግሞ ወንድም ካርልሰንን ጠይቁት፡ እና እሱ––ይጠቁማችኋል… ቦታውን እንዴት እንደምታገኙት፡ እሱ ወይም የፊላደልፊያ ቤተክርስትያን፡ አንዳቸውም፡ ያሳዩአቸዋል።

32 ከዛ በኋላ በሚቀጥለው ሰኞ ከሰዐት፡ ወይም ወደ ማታ አከባቢ፡ እመለሳለሁ። ሌላው ልጆቻችን ወደ ትምህርት ቤት ለመውሰድ ወዘተ፡ ማክሰኞ––ወደ አሪዞና ተመልሰን እንሄዳለን። ከዛም በኋላ መቼ ተመልሼ እንደምመጣ አላውቅም፡ ምክንያቱ፡ ጌታ፡ ማድረግ ያለብኝን እንዲመራኝ እፈልገዋለሁ።

33 በጣም የሚገርም ነገር ተፈጠረ። በርግጥም ቴፕ ውስጥ እንደተቀረጸ፡ አውቃለሁ… ምናልባት እዚህም ማስቀመጥ ያለብኝ ይመስለኛል። አሁንም ራእዮች እና የመንፈስ ቅዱስ ምሪቶች በሚታዩበት ጊዜ፡ በዚያ ቅጽበት መስራት እወዳለሁ። ይህም… አምና፡ አንድ ወሳኝ ነገር ነበር፡ በአገልግሎት ዘመኔ፡ አምና ከፍተኛ ራዕዮች የተቀበልኩበት ወቅት ነበረ፡ ያለፈው ዓመት፡ ነገሮች በብዛት የተከናወኑበት ጊዜ ነበር፡ እናንተም ከመሆኑ በፊት አስቀድሞ የተተነበየ መሆኑን ታውቃላችሁ፡ ይህም የሆነው––ልክ እንደተነገረው እንዲሁ ነው።

34 አሁንም፡ ለጉብኝት––በድጋሚ፡ እዚህ መጥተናል። እዚ ያለውም የአየር ጸባይ፡ በምገባበት ቅጽበት… ስለሚሰባብረኝ፡ በእውነት አልወደውም። እንደው… የተራራውን ጫፍ ተሻግሬ ወደዚህ ሸለቆ ሰወርድ፡ በአስር ደቂቃ ውስጥ እታመማለሁ፡ እከክ ይወጣብኛል። አየሩ፡ ራስ ምታት-ያዞረኛል፡ ሁሉንም ነገር የሚያስፈራ፡ ጨለማ ይሆንብኛል፡ እናም––በቃ መውጣት አለብኝ። አያችሁ? በቀደም ሚስቴን እየነገርኳት ነበረ…

35 ወደዚህ የሚያስመጣኝ፡ ዋናው ነገር ግን፡ እንድመጣ የሚያደርገኝ፡ እናንተ ሰዎች ናችሁ፡ አያችሁ፡ እቺ ቤተክርስትያን ናት። እውነት እላችኋለሁ፡ በህይወቴ ለስብከት ከሄድኩባቸው ሰፍራዎች ሁሉ፡ ወንጌልን ለመስበክ የምወደው ይህ ሰፍራ ነው። እና ከየትኛውም ቦታ ይልቅ በአስር እጥፍ የሚበልጥ ቴፕ ከዚህ መስራት የምንችል ይመስላል። አያችሁ? አያችሁ፡ “እግዚአብሔር በሚሰራበት ቦታ፡ በዚያ ቦታ ጽኑ፡” ብዬ የምመክራችሁ ለዚሁ ነው። ነገር ግን፡ መጀመርያ በጠራኝ ጊዜ አልታዘዝ ያልኩበት፡ ታላቁ ነገር ያ ነበር፡ በዚህም ምክንያት ተመልሼ ስገባ አከበደብኝ። መታዘዝ ከመስዋእት ይበልጣል።

36 ስለዚህ፡ በዚህ ተበርናክል ለመስበክ፡ ሁልጊዜ እመላለሳለሁ። ከከተማው ውጪ ለሆናችሁ ሰዎችም፡ ይነገራችኋል። ቢሊ ፖል እዚህ ይቀራል፡ ቢሮ ውስጥ ስለሚሆን፡ በየትኛውም ጊዜ––በሱ በኩል፡ ታገኙናላችሁ። ከዛ በኋላ ተመልሰን እንመጣለን፡ ጉባኤ… ጌታ ቢፈቅድ፡ ሰባቱ መለከቶች ቀጣይ ርዕስ ይሆናል፡ ሰባቱ የመጨረሻ መቅሰፍቶች፡ እና ጽዋዎች፡ እና የመሳሰሉት፡ በተቻለን መጠን፡ ምናልባት ትንሽ ቀዝቀዝ ያለ የአየር ሁኔታ ስናገኝ፡ ወይም የሆነ ነገር፡ ብቻ ጌታ እንደመራን እንሆናለን።

37 ሌላው፡ ባለፈው ቀን፡ ስለ አንድ ጉዳይ፡ አንድ ሰው ስለሰጠኝ አንድ—ቼክ፡ ስለ አንድ ነገር የተነሳ ጥያቄ ነበር፡ እኔን ለብቻዬ፡ ጠቅሶ፡ “ለግል” ይላል፡ “ግብሩ የተከፈለ፡ ነጻ፡” እንደሆነ በዝርዝር ተቀምጧል። እንግዲህ፡ አብረን ሄድን... ቢሊም ያንን ቼክ እንደሚያስፈልገኝ፡ ያውቃል።

38 ሄዶ ገንዘብ መውሰድ እንችል እንደሆነ ጠበቆቹን ጠየቃቸው። እንዲህ አለ፦ “ለምን፡ አሜሪካዊ ዜጋ አይደለም’ዴ። እንዴት አይችልም? አየህ፡ ‘ግብር የከፈለ፡’ ሌላው ሁሉ ‘ነጻ፡’ ነው። ዜጋ የሆነ ሁሉ ይሄንን ማድረግ ይችላል፡ አለው።”

39 እና ቢሊ፡ በዚህ ሊረካ አልቻለም፡ ስለዚህ ወደ ግል ሒሳብ አዋቂ ሄደ። እርሱም አለው፦ “እንዴ፡ በእርግጠኛነት፡ መዘርዘር ይችላል።” “የዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ ነው፡” አለው።

40 እና፡ እንደው፡ ጥሩ ነው ብሎ ማሰብ ስላልቻለ፡ ወደ መርሊ ሚለር ደወለ፡ እሱም—በኢንዲያናፖሊስ ውስጥ—የግብር ማሕበር ዋና ሐላፊ የነበረ፡ ጠበቃችን ነበር፡ አይስ እና ሚለር የሚባሉ ናቸው። እና፡ “በትክክል፡ ምንም ችግር የለውም። አየህ? በትክክል፡ ቼኩን መዘርዘር ይችላል። ለ—ለ—ለርሱ የተዘጋጀ ነው፡ ‘ለርሱ ብቻ’ ይላልና።” እኔ እችላለሁ፡ ማውጣት የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ነው፡ እና፡ በኛ ማሕተም አይቻልም...

41 አያችሁ፡ እኔ ቼኮችን መዘርዘር አልችልም። ባለፈው ያደረጉብኝ ያ ነው። አንድ ሰው፡ ወደ ጉባኤው፡ ብዙ ቼክ አምጥቶ “ይሄው፡ ወንድም ብራንሃም፡” ይላል። እኔም “ዊልያም ብራንሀም፣ ዊልያም ብራንሀም... ” እያልኩ እፈርምበታለሁ፡ እንግዲህ፡ ይህን ያህል ጊዜ ሁሉ መንግስት ራሱ ነው ጉዳዩን የሚያደርገው። እና ለራሴ እየፈረምኳቸው እና እዳዎችን ስከፍል ቆይቻለሁ፡ እነርሱ ግን በዚ ሁሉ፡ ባጠቃላይ፡ ሦስት መቶ ሺህ ዶላር ዕዳ አለብህ አሉኝ። ስለዚህ—ጫጫታው የተነሣ በዚያ ነው።

42 ልክ ቼኩን እንዳስቀመጥኩ፡ መጥፎ ድምጽ ሆነ! ወኪሉ ወድያውኑ ተመልሶ መጣና፡ ነገሩን አከበደው፡ “ክሱን ደግመን እንከፍትበታለ።” በማለት ነገሩን እጅግ ከበድ አደረገው።

43 ወንድማችን ሊ ቨይል እዚህ ቁጭ ብሏልና፡ ብናገር፡ ቅር የሚለው አይመስለኝም... ይህ የባብቲስት ምሁር ሰው ወንድም ሊ ቨይል፡ መጣ... ወንድም ሊ ቬይልን፡ በዚህ በገንዳው ውስጥ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በቀደም’ለታ ነው ያጠመቅኩት። በክርስቶስ ወንድሜ የሆነ፡ በጣም ደስ የሚል ሰው ነው። ከዚ በፊት ሰብኮን ያውቃል፡ በጣም የተማረ ሰው ነው፡ ከዛም በላይ፡ ደግሞ፡ በመንፈስ-የሚመራ ሰው ነው። ብርሃን በበራለት ጊዜ፡ ለመሸሽ አስቤ ነበር አለ፡ ይሁን እንጂ አልቻለም፡ ስለዚ በቀደም ጥዋት እዚሁ ሰፍራ አጠመቅኩት። ከዚ በላይ መዘግየት አልፈለገም ነበርና፡ ስለዚህ ወደዚህ ወርደን ልብሳችንን ለብሰን ገብተን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቀ።

44 እና፡ ያንን መልካም መንፈሳዊ መብል ከወሰደ፡ ምናልባት፡ ትንሽ እየተነጋገርን ሰጋዊ ምግብ ብንመገብ ብዬ አሰብኩ። ስለዚህ ወደ ብሉ ቦር ሄደን፡ ቁጭ ብለን፡ አወራን፡ እና የዚህን ርዕስ ጉዳይ አነሣን፡ “ሰዎች ስለ አንተ እንደዚህ እንዲናገሩ እንዴት ትፈቅዳለህ? ”

45 እንግዲህ፡ ወንድም ቬይል በህይወቴ ከማውቃቸው ምርጥ ሰዎች አንዱ ነው፡ ነገር ግን ታውቃላችሁ፡ ሁሌ እነግረዋለሁ፡ “ቃታውን ለመሳብ ሁሌ ይቸኩላል።” እናም፡ እሱን፡ ወንድም ቨይል… ምንም ማለት እንዳልሆነ፡ ተሰፋ አደርጋለሁ አልኩት። ስለዚህ… “ተረጋጋ። ወድያው ቱግ አትበል። ይሄን እያደረገ ያለው ጌታ ነው፡” አልኩት።

46 እንዲህ—አለኝ፡ “ወይ ጉድ፡ ምናልባት ለአንተ ደህና ሊሆን ይችል ይሆናል፡” አለኝ። እንደው፡ ግን፡ እሱ—እሱ… አዋቂ የቢባሉትን ሰዎች መግጠም እስከሚችል ድረስ፡ በጣም አስተዋይ ሰው—እንደሆነ አምናለሁ፡ መቋቋም እንደማይችሉት አድርጎ፡ እንዴት እንደሚያጠምድ ያውቃል። በቃ።

47 እዛው ብሉ ቦር ቁጭ ብለን ሳለን፡ “ይሄውልህ፡ ወንድም ቨይል።” አልኩት። እንዲህ አልኩት፡ “አንድ ቀን፡ ዳዊት በልጁ ከዙፋኑ፡ በጭካኔ፡ ከተወገደ በኋላ፡ ከዙፋኑ ተሰደደ፡ እስራኤልም ተከፋፈለ፡ ዳዊትም በልጁ ዙፋኑን ተወሰደበት፡ እያነባ፡ ከከተማይቱ ወጣ። የእሱን የመጨረሻው-ዘመን መልዕክት የማይወድ፡ ታውቃላችሁ፡ ሰለሱ ግድ አልሰጠውም፡ ይህ አካል ጉዳተኛ፡ የሆነው ሽማግሌ፡ ይልቁንስ እየተሳለቀበት፡ ይከተለው ነበር፡ እንዲሁ በዳዊት ላይ ይተፋበት ነበር። አንዱ ወታደር ሰይፉን መዘዘና፡ ‘በጌታየ ላይ የሚተፋውን፡ ውሻ አንገት ልቁረጠውን? ’ አለ፡ ዳዊትም፡ ‘ተወው። ጌታ አዞታልና።’ አያችሁ? ተፋበት፡ ተሳለቀበት፡ እንደገናም ተፋበት። ‘ጌታ አድርግ ብሎታል፡’” አለ። እንግዲህ፡ የታሪኩን አጨራረስ፡ እንዴት እንደነበረ እናውቃለን። ወንድም ቨይልም ይህን ለማድረግ ሞሉ ጸጋ ይጠይቃል ብሎ አሰበ።

48 እንግዲህ ተመልሰን ወደ ቢሮ እንደገባን፡ የሒሳቡ ባለሞያ ቢሊን ደወለለትና ስለዚ ጉዳይ በተመለከተ ነገረው። ከዛ ወንድም ቨይል አብሮኝ ወደ ቤት ሄደና። እንደ ገባሁ፡ ከከሰዐት ገደማ ነበር… ሚስቴን እንዲህ አልኳት። ክፍል ውስጥ ገባን። “ሃኒ፡ የምነግርሽ ነገር አለኝ፡” አልኳት።

49 ገና ከመሄዴ በፊትም እየተነጋገርንበት ነበርና። እንዲህም አለችኝ፡ “ቢል፡ ጌታ እንደላከህ፡ ሁላችንም እናውቃለን፡ተመልሰህ እንድትመጣ ግን አላዘዘህም። እሱ የነገረህ… እንግዲህ፡ ጭንቀቴ እዚህ ላይ ነው።”

50 እንዲህ አልኳት፡ “አዎን፡ ሰለ አንቺ እና ሰለ ልጆቼ ነው። እንጂ ሰለኔ ግድ የለኝም። እንደ ጌታ ፈቃድ፡ በሄድኩበት ሁሉ፡ አገለግለዋለሁ።” እናም እንደዛ ነገርኳትና፡ ወደ ኋላ ዞርኩ። ዞር ብየም፡ ኮፍያዬን ወደ ላይ ሰቀልኩት።

51 እና አንድ ሰው፡ ሰለ አንድ ነገር ተናገረ፡ “እይ፡ ይሄ ቀረጥ ሰብሳቢ! መሄድ አለብን… ” ዓይነት ንግግር በድንገት ተናገረ።

52 ለወንድም ቨይል የተናገርኩት ነገር ትዝ ሳይለኝ፡ “ተወው። ምናልባት ጌታ አድርግ ብሎት ይሆናል፡” አልኩና።

53 ተናግሬ ሳልጨርሰው፡ ወንድም ቨይል እና ሚስቴ ቁጭ ብለው ሳሉ፡ ግድግዳው ላይ የተጻፈ ብርሀን አንጸባረቀ፡ “ወደ አሪዞና ተመለስ።” የሚል ፊደላት በግድግዳው ላይ የተጻፈ፡ “ና ወደ አሪዞና ተመለስ።” እውነት ነው። ይሄው ወደ አሪዞና፡ ሄድኩ፡ አሜን።

54 እንግዲህ ይህ ሳምንት፡ የታላላቅ በረከቶች ሳምንት ሆኖልን ነበር። **ከሰባቱ ማሕተማት** በኋላ ሲጠብቁን ከነበሩ ሰዎች ጋራ፡ የግል ቃለ መጠይቆችን

አደረግን። እንደውም ያለጥርጥር፡ አንዳንዶቹ፡ ከከተማው ውጪ፡ ከአገሪቱ ዙርያ የሚደወሉ ጥሪዎች ነበሩ። ይሁን እንጂ ቃለ መጠይቁ ከመጀመሩ በፊት፡ ማለዳ ላይ በክፍል ውስጥ ቁጭ ብዬ፡ እያንዳንዱ ሊጠይቁ የሚፈልጉትን እና የሚያውቁትን ሁሉ እንድጽፍ፡ መንፈስ ቅዱስ መራኝ፡ ጥያቄዎቹን በፈለጉት መንገድ ቢያዟዙሩትም፡ ገና ሳይነግሩኝ ሕልማቸውንና ፍቺውንም እየነገርኳቸው ነበር።

55 እንግዲህ፡ ሰዎቹ ክፍል ውስጥ፡ እዚህ ጋር ይሆናሉ። እኔ ቀድሜአቸው እናገራቸዋለሁ። ከዛ በኋላ እነሱም፡ "እየህ፡ ወንድም ብራንሃም፡ እኔ **እንዲህ-እና-እንዲያ** ሆኜ።"

56 እኔም እላለሁ፦ "እንግዲህ፡ አስታውስ፡ የተሰበሰብነው ሕብረት ለማድረግ አይደለም። እርስ በርስ ሕብረት ለማድረግ ወደዚህ አልመጣንም። በአእምሮህ፡ በልብህ ውስጥ፡ እጅግ የተቸገርክበት ጥያቄ አለ—ምን እንደሆነም አታውቀውም። እና እኔ ምናልባት፡ በእግዚአብሔር እርዳታ፡ ማድረግ እችል ይሆናል።"

57 እኔም አልኩ፦ "የደቡቧ ንግሥት፡ አስቧት፡ ወደ ሰሎሞን በመጣች ጊዜ፡ አንዳንድ ጥያቄዎች ነበሯት። መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ሰሎሞን ሊመልስ ያልቻለው ያልተገለጠ ወይም የተከለከለ ነገር እንዳልነበረ ይናገራል።" እኔም እላችኋለሁ፡ "ከሰለሞን የሚበልጥ በዚህ አለ። አያችሁ? በትክክል። ጌታ ኢየሱስም ቃል ገብቶልናል፡ 'ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በተሰበሰቡበት፡ በዚያ በመካከላቸው እገኛለሁ ብሎናል። እና የሚያስቡት የትኛውንም ነገር ቢያስቡ፡ ወይም ቢመኙ፡ እንዲሁም—ቢጠይቁ፡ ይሰጣችኋል።' አሁንም አንተ ጥያቄህን እንኳን አታውቀውም፡ እንዴት ማቅረብ እንዳለብህ የማታውቀው፡ ምን ማድረግ እንዳለብህ የማታውቀው ነገር ነው።"

58 እኔም እላችኋለሁ፡ "ዳግመኛም፡ መጽሐፍ፡ እንዲህ ይላል፡ 'የእግዚአብሔር መላእክት በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራሉ፡' በሌላ አባባል አምስቱ የስሜት ህዋሳት በማይገለጡበት ዓለም ላይ ይሰፍራሉ።"

59 አምስቱ የስሜት ህዋሳት ከዚህ ዓለም ጋር ብቻ የሚገናኙ ናቸው። ስሜት ባይኖራችሁ ኖሮ፡ ምንም ባልተሰማችሁ ነበር። ስሜት ትርጉም አይሰጣችሁም ነበር፡ ሌላ ዓለም ይሆንባችሁ ነበርና። ማያ ባይኖርህ ኖሮ፡ የምትመለከተው ነገር ሁሉ ሌላ ዓለም ይሆንብህ ነበር፡ ምኑንም አታውቀውም። ስለዚህ እግዚአብሔር ለአምስቱ የስሜት ህዋሳት ብቻ አሳልፎ ሰጥቶናል።

60 አሁን ደግሞ እምነት የሚባልም ሌላ አለ። በዚህ እምነትም መሰላል ትወጣላችሁ፡ በመጨረሻም ወደ ሌላው አለም ገብታችሁ ራዕይ እስክታዩ ድረስ፡ ወደ ከፍታ ትወጣላችሁ። በዚያ ማየት ትችላላችሁ።

61 በስሜት ሕዋሳቶቻችሁ በኩል የሚሰሟችሁ ነገሮችን መረዳት የተሳኗችሁ፡ ማየት የተሳኗችሁ ከነበራችሁ፡ አሁን ግን አይናችሁ ተከፍቶ፡ ማየት ትችላላችሁ። በጭራሽ ማየት ለማይችል ሰው ይህ ሁሉ ምስጢር ይሆንበታል። ነገሩ ያለ ቢሆንም፡ ለእሱ ግን እንቆቅልሽ ይሆንበታል።

62 በዚያ ውስጥም፡ ጌታ... ከመላው አገሪቱ፡ ከየትኛውም ቦታ ለሚመጡ ሰዎች፡ ከመምጣታችን በፊት፡ ከሰሜን፡ ደቡብ፡ ምዕራብ፡ ወደ ቃለ መጠይቅ ከመድረሳቸው በፊት። ገና መናገር ሲጀምሩ፡ ሊጠይቁት ያሉትን ጥያቄ፡

የሚጠይቁትን ነገር፡ ቀድሜ እለዋለሁ፡ “እዚህ ጋር አስተውል፡” ከፍ አደርገዋለሁ፡ ከእያንዳንዱ ጥያቄ ጋር ወረቀት ተዘጋጅቶበታል፡ የሚጠይቁትን ነገር፡ እንደየአጠያየቃቸው አገልጠው ነበር፡ ለጥያቄያቸው የተሰጠ መልስም፣ ልክ እንደ ተመለሰ ተቀምጧል። ጌታ ታላቅ ነው። ሁሉንም ነገር ያውቃል። ቢሆንም፡ ግን፡ ከዛ ለመውጣት ሶስት ቀን ያህል ወሰዶብኛል፡ ምን ስለሆነ፡ በጣም-ስለሚያደክም። አሁንም፡ ከመሄዳችን በፊት፡ እንድንደግመው አስባለሁ።

63 ግለሰቦችን የምታስተናግዱበት፡ ራሱን የቻለ፡ ሂደት አለ። እንግዲህ እዚህ ጋር፡ መባል ያለበት ነገር አለ።

64 እዚህ ያሉ ሰዎች፡ ተሰውሮ የነበረውን ነገር ግን የተገለጸውን ቢያውቁት፡ እጅግ... አስከፊ ይሆን ነበር፡ እንዲሁ በዚሁ መድረክ ላይ፡ በህዝብ ፊት፡ ቢነገር ኖሮ፡ ወንጀል ሊያስፈጽም ይችል ነበር፡ አንዱ ሌላው ላይ ተኩሶ፡ እንዲገድል ያደርግ ነበር። ወህኒ ቤት ውስጥ የሚያስገባ ወንጀል፡ እና፡ ሌላ ሌላ ሁሉ...

65 መንፈስ ቅዱስ ባለበት፡ ሁለታችሁ ብቻ፡ በእንዲህ ዓይነት ስትቀመጡ ግን። መቼም የሚጠይቁኝ ሁሉ፡ የግል ጉዳያቸው እንደሆነ ይገባናል። እኔም ምስጢር አላወጣም። የነገርኳቸው ነገር ይናገሩት አይናገሩት እነሱ ራሳቸውን ይመለከታል። አያችሁ? ቃለ ምልልሱ ግን፡ በኛ መካከል ይቀራል። መንፈስ ቅዱስ፡ ጉዳያቸው ፈጽሞ፡ እስኪመልስላቸው ድረስ፡ በአንድ ጊዜ፡ አንድ ሰው ብቻ ይስተናገዳል።

66 አቤት ጸጋው፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ስለ ተሰለፉት ሰዎች ሁሉ፡ ስለ እያንዳንዳቸው፡ በህይወቴ አይቻቸው የማላውቅ ሰዎች፡ ከየአገሩ፡ ገና፡ ወደዚህ ሳይመጡ ሲነግረኝ፡ እኔ ሳስበው ይገርማል። እንደየጥያቄአቸው፡ እንደሚጠይቁት ጥያቄ መሰረት፡ መልሳቸውን እንዲያውቁት እጽፈዋለሁ።

67 የእባቡን ዘር በተመለከተ ጥያቄ ያቀረበ አንድ ወንድም ነበረ፡ መልሱን በሚገባ አልመለስኩለትም፡ ምክንያቱ ስላሳ ደቂቃዋ ሰላለቀች ነው። በወረቀቱ የነበረውን መልስ፡ በትክክል ገብቶታል ብዬ፡ ተስፋ አደርጋለሁ። መ... መጻፍ ነበረበት፡ መልሱን ጽፎ ስላልጨረሰ፡ ወረቀት ላይ የነበረውን፡ መልስ የያዘውን ጽሁፍ ሰጠሁት። ካልያዘው ግን፡ ቢሊፖል ጋር አለለት። ሰውየው እዚሁ እንዳለ አውቄአለሁ፡ ቀደም ሲል አይቼዋለሁ። እንግዲህ—የሚፈልግ ከሆነ፡ የጥያቄዎችህ ሁሉ መልሶች፡ ወረቀት ላይ ተጽፎልሃል።

68 አቤት፡ አሁንም፡ ጌታ እንዴት ድንቅ ነው! ሰው ሁሉ ደስተኛ እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ። እህ-ሀህ።

69 እስኪ አሁን ደግሞ እኔ ለመሃረቡ ስጸልይ፡ ወንድማችን ዳውንን፡ እናስበዋለን። ተወዳጅ ወንድም ነው፡ በጸሎት እንድናስበው እፈልጋለሁ።

70 ወንድም አንግረን—አይቼዋለሁ፡ እህት አንግረን ግን—አላየኋትም፡ ደህና መሆኗን ማወቅ አልቻልኩም። አዎን፡ ከጎኑ ተቀምጣለች። በጣም ጥሩ። እሺ። ደስ ብሎኛል። ምክንያቱ በቀደም ለት ማታ የ... የእርሷ፡ እና የልጇ እህት... እ... .ዳውኒንግ፡ ዳውኒንግን፡ ድንገተኛ ጉዳይ አጋጥሟቸው ተጠርተን ነበር። ከመንገድ ዳር ወጥተው፡ በጌታ ጸጋ ባይሆን ኖሮ፡ ይሄኔ በአደጋ ደቅቀው ነበርና። እንግዲህ ባቡር ተሳፍረው፡ በቀጥታ ወደ ቸርች መጥተዋል።

71 ሁላችሁም እወዳችኋለሁ። በፍጹም አልረሳችሁም። ጌታ ያውቃል። እ—ወዳችኋለሁ። በአስቸጋሪው የአየር ጸባይ፡ አገር አቋራጭ ሁሉ፡ ተሻግረዋል!

72 ከጆርጂያ፡ ከአላባማ፡ እና ከተለያዩ ቦታዎች፡ ከቴነሲ፡ እና አካባቢው የሆኑ ወንድሞች ስመለከታቸው፣ አንድ ጉባኤ ለመካፈል መኪናቸውን በየመንገዱ እያሽከረከሩ፡ ሲሄዱም፡ ሲመጡም፡ የሚንሸራተት፡ በረዶ ባለበት አቋርጠው የመጡ ናቸው።

73 ስለ ወንድም ዳው፡ ድንገተኛ ጥሪ በደረሰኝ ጊዜ፡ ሊማ፡ ኦሃዮ ይሄን ያህል ሩቅ መሆኑን አላውቅም ነበር። በቃ... ፈንጠር፡ ዘለል፡ አለፍ ብቻ መሰሎኝ ነበር። ነገር ግን፡ አቤት፡ ያን ቀን በማለዳ ነበር የተነሳሁት፡ በመንታ ሃይዌ መንገድ፡ የተፈቀደውን—የፍጥነት ወሰን ሁሉ ነድቼ፡ እስከ ከሰዓት አንድ ሰዓት ድረስ አልደረስኩም። እንደሚመስለኝም፡ ሌሎቹ ወደ መጡበት ወደ ደቡብ ይቀርባል ብዬ አስባለሁ፡ እነሱ ወደ መጡበት ወደ ሰሜን እና ወደ ምዕራብ፡ እጅግ ይቀርባል።

74 እወዳቹኋለሁ፡ እዚህ ራሴን ዝቅ ለማድረግ እጅግ የምጥረው ለዚህ ነው።

75 ከ—ቀደምቶቹ! ወንድም ክሪች እና ሌሎቹ ከኋላ ተቀምጠው ይታዩኛል፡ ይሄን ሁሉ አመታት አብረውኝ የተጓዙ ናቸው፡ ይሄን ሁሉ፡ አብረን ተጉዘናል። ከሁለት ምሽቶች በፊት ይመስለኛል፡ ሜሪ ጆ ፎቶዋን እያየሁት ነበር። ያኔ ስንገናኝ፡ የሆነች ትንሽየ ቀጫጫ ነበረች፡ አሁን ግን ይመስለኛል፡ አግብታ ልጆችም ወልዳለች። ወንድም ክሪች እና እህት ክሪች፡ ያኔ ወጣቶች፡ ባለ ጥቁር-ጸጉር ነበርን፡ እኔና ሜዳ፡ አሁን ግን ሽብተን ጎብጠናል። አያችሁ፡ እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች፡ የሚሰባችሁ—ነገር አላቸው። አያችሁ፡ አብረሀቸው ቆይ—ቆይ—ይላችኋል። አያችሁ? አይምሮአችሁን—በትውስታ የሚመልስ አንዳች ነገር አላቸው። እዚሁ ላሉ ለሌሎች እንደ ምሳሌ እየተተቀምኩባቸው ነው። ወጣት እና አዛውንት፡ ሁላችንም የጌታን መምጣት እንጠባበቃለንና።

76 ስለዚ በዚሁ ማለዳ... እንደ አምላካችን ፈቃድ፡ እግዚአብሔር፡ ረዘም ላለ ሰዓታት የሰንበት ትምህርት እንዳስተምር፡ በልቤ ትምህርት እንዳስቀመጠ እምናለሁ። አሁንም... ለተወሰነ ቀናት፡ ይህ ጉባኤ፡ የመጨረሻ ጉባኤዬ መሆኑን፡ አውቃችሁ...

77 ይሄንን ጉባኤ በተመለከተ ወንድም ኔቪል፡ በመንፈስ ቅዱስ ጥላ ስር ሆኖ፡ በሀላፊነት ይቆያልና እንድታሰቡት እፈልጋለሁ፡ በዚሁ ቤተ ክርስትያን፡ እሱ እዚሁ ይቀራል፡ ይሄንን መልዕክት እንደ እኔ—ያምናል ያስተምራልም። ትክክል። እና በማንኛውም ጊዜ ስትፈልጉ፡ ወንድም ኔቪልን ለመስማት መምጣት ትችላላችሁ፡ በእርግጥ ጥሩ ይጠቅማችኋል፡ እርግጠኛ ነኝ። የኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅ አገልጋይ ነው።

78 ኦርማን ኔቪልን ህጻን ልጅ ሳለሁ አውቀዋለሁ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መልካም ባርያ ነው፡ ወደ ጌታ በመጠጋት በቀር በሌላ በምንም አልተለወጠም። ያኔ መጀመርያ ያየሁት ጊዜ... በሱ ሜተዲስት መድረክ የተጋበዝኩ ጊዜ አስታውሳለሁ። ወደ ጉባኤ ተመልሼ እንደመጣሁ፡ "ይህ ሰው፡ አንድ ቀን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጠምቀዋለሁ፡" አልኩኝ። እንግዲህ ይሄው፡ ጠንካራ ባርያ ሆኖ፡ አሁን ከመልእክቱ ጋር እየተጓዘ ይገኛል።

79 በተጨማሪ ወንድም ኔቪል ምንም እንኳን በጉባኤው አይግለጠው እንጂ፥ በብዙ ውጣ ውረድ እና የልብ ህመም አልፎአል። ይሁን እንጂ የሰዎች ህይወት ማየት የምችልበትን ጸጋ ከጌታ የተሰጠኝ በመሆኔ፥ የሚያልፍባትን እያንዳንዷን ነገሩን ለማወቅ ችያለሁ፥ አያችሁ። በርግጥም በተለያዩ ውጣውረዶች እና ውጥረቶች፥ ወዘተረፈ አልፎአል። እናንተም ደግሞ፥ ቃል በሚያመጣ ጊዜ ኢያሱ እና ካሌብ የሙሴ እጆች እንዳበረቱ፥ እናንተም እጆቹን አበርቱ።

80 ከምንም በላይ፥ እርስ በእርስ ተዋደዱ። እርስ በእርስ ተዋደዱ። ዲያብሎስ... የፈለገውን ለማለት ይሞክር! እናንተ አንድ ታላቅ ውብ እና ድንቅ ቡድን ናችሁ፥ አያችሁ፥ ማስጠንቀቂያየን አትርሱ፥ ሰይጣን እንዲህ ሆኖ እንድትቀጥሉ አይፈልግም። በፍጹም፥ ወዳጄ። አንዱን ዒላማውን ለማድረግ፥ የቻለውን ያህል ይወረውራል። አንድ የማያምን ነቃፊ አምጥቶ፥ ከእናንተ ጋር በእርጋታ እንዲቀመጥ ያደርገዋል፥ በርጋታ እና በሌላ ሌላ አብሮ እያመለከ እንዲቀመጥ ያደርጋል፥ ከዛ በኋላ እሱን መርዛማ ነገር እየተኮሰበት፥ ቤተ ክርስትያኒቱን በዚያ ይጀምራታል። እንዳትተባበሩት። ከእንደዚሁ ዓይነት ጋር ምንም ነገር አይኑራችሁ። እርስ በእርሳችሁ ቅኖች መልካሞች ሩህሩሆች እየሆናችሁ ተዋደዱ። ያ ሰው፥ ወይም ያቺ ሴት፥ እንዲድኑ ጸልዩላቸው፥ ማንም ይሁን፥ ጸልዩላቸው። እርስ በእርስም በአንድነት ተያያዙ።

81 ከፓስተራችሁም ጋር አንድ ሆናችሁ ቆዩ። አያችሁ፥ እረኛ ነው፥ እናንተም አክብሩት። ይሄን ለመሰራት፥ በጌታ የተቀባ ነውና፥ በሁሉ ይመራችኋል።

82 አትረሱም አይደል? [ጉባኤው፥ "አሜን" አለ።—አርታዒ።] ጠላት ይመጣል። ሲመጣም፥ አብልጣችሁ በአንድነት ተያያዙ። ከዛ ጠላት ሲጠቀምበት የነበረውን ሰው ወይ ገብቶ ከእናንተ እንደ አንዱ ይሆናል ወይም ይሄድላችኋል። በቃ።

83 በመካከላችሁ ጎሳዊነት አይሁን... ወይም—እትናገሩ፥ ራሳችሁን አንድ ጎሳ አድርጉ። አንድ ነንና። "ግራ እጅ፥ ቀኝ እጅ ስላልሆንሽ፥ ተበሳጭቼብሻለሁ፥ ገንጥየ እጥልሻለሁ፥" ማለት አልችልም። ግራ እጄ ነው። እዛው በቦታው እንዲሆንልኝ እፈልገዋለሁ። ትንሿም ጣቴም እንዲሁ፥ መላ አካላቶቼ፥ በስፍራቸው እንዲቆዩልኝ እፈልጋቸዋለሁ። ጌታም እንደ አማኞች አካል፥ እርስ በእርስ እየተደጋገፍን፥ በስፍራችን፥ አብረን አንድንሆን ይፈልገናል።

84 በዚህ ዙርያ ቴፖች አሉን። የምናምነውም በተመለከተ ቴፖች አሉአችሁ። ስለ ቤተ ክርስትያን ስነምግባር፥ በእግዚአብሔር ቤተክርስትያን ውስጥ ራሳችንን እንዴት መግዛት እንደሚገባን፥ አብረን በህብረት መጥተን እንዴት በሰማያዊ ሰፍራ መገኘት እንደሚገባን የሚገልጹ ቴፖች አሉላችሁ። ቤት አትቅሩ። ጌታ በልባችሁ ከሆነ፥ ከወንድሞቻችሁ ጋር ለማምለክ፥ በሮች እንዲከፈቱላችሁ በጣም ትቸኩላላችሁ። እንዲህ—የማይሰማችሁ ከሆናችሁ ግን፥ መጸለይ እንዳለባችሁ፥ እነግራችኋለሁ።

85 ምክንያቱ፥ ያለንበት ዘመን የመጨረሻው ነው፥ መጽሐፍ ቅዱስ—እኛን፥ ሲናገር፥ ወይም ሲመክር፥ "ይልቁንስ ቀኖቹ ተቃርበው ሰናያቸው፥" በክርስትያናዊ እና በመሎኮታዊ ፍቅር እርስ በእርስ አጥብቃችሁ ተዋደዱ ይለናል፥ "በ—በ—በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ስፍራ በሕብረት በአንድነት

ሁኑ፡” ተዋደዱ። “እርስ በርሳችሁ ፍቅር ሲኖራችሁ፡ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።” ትክክል ነው። አብራችሁ ቆዩ።

86 አንድ ወንድም፡ ወይም እህት፡ ተሳስተው ካያችሁት፡ እንዲህ በሉ፡ “ጌታ ሆይ፡ መራራ ስር እንዳይበቅልብኝ፡ እሱን ይጎዳዋል—እሱን ጎድቶት፡ የክርስቶስን ህይወት እንዳላጣ እርዳኝ በሉ።” ምክንያቱ ምቀኝነት፡ እና ቅናት፡ እንዲሁም የጥላቻ መርዛማ አሲድ፡ መንፈስ ቅዱስን ከውስጣችሁ ያስሸሻልና። ከዚሁም ከጉባኤው ያሸሸዋል። የጌታን መንፈስ ይገድላል፡ እንዲርቅ ያደርገዋል፡ ፓስተራችሁንም ያሰመታል። ሁሉም ነገር ያደርጋል። አያችሁ? ፈጽማችሁ እንዳታደርጉት።

87 ይሄን ያህል በአንድነት ቅለጡ። ያ አገልጋይ... ባለፈው ማታ ራእይ አይቶ፡ እንደሰጠን ምስክርነት፡ መታጠቂያውን አንሱ፡ በራዕይ ስለመታጠቅ፡ አይቶ ነበርና። ይህም፡ በእግዚአብሔር ዕቃ ጦር ሁሉ መታጠቂያ ነው። አጠጋግታችሁ ያዟት፡ እርስ በእርስ ተጠጋግታችሁ ተጓዙ። በምንም ዓይነት ሁኔታ፡ እርስ በእርስ፡ ተዋደዱ። እርስ በእርስ መልካምን ተነጋገሩ፡ እንዳችሁ ስለሌላው መልካምን ተነጋገሩ፡ ከዛ በኋላ ጌታ ይባርካችኋል።

88 ዛሬ ጠዋት፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ በእሱ እርዳታ እና ጸጋ፡ ብዙ ጥያቄዎች ይዣለሁ፡ በተለይ ደግሞ፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሆኑትን። እንግዲህ ከመጀመራችን በፊት... መቅጃ መሳርያዎች ሲያበሩ የሰማሁ መሰለኝ። አሁን በእግዚአብሔር ጸጋ፡ መልእክቱን እናመጣለን።

በጸሎት ቃል፡ እንጀምራለን።

89 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ በማይለወጠው የእግዚአብሔር እጅ፡ ፍፁማቸው የሆነውን፡ ቃሉን፡ ይይዙ ዘንድ፡ ለዚህ የቤተክርስቲያን አካል ሰናገራቸው፡ “ተኩላዎች ይገባሉ፡” ብሎ፡ ጳውሎስ መንጋውን እንዳሰጠነቀቃቸው፡ አስጠነቅቃቸዋለሁ። ያን ጊዜ እንደሆንክ ዛሬም ያው አምላክ ነህና፣ ጠላትም ያው ነው። ይህ ኅብረት እና የፍቅር ማሰሪያው፡ በክርስቶስ ኢየሱስ በእነዚህ ሰዎች መካከል ሁል ጊዜ ይኑር።

90 ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማለዳ፡ ቃልህ ሰናነበው፡ ረዲኤትህ ይሁንልን። መንፈስ ቅዱስ ይግለጽልን፡ ቤተክርስትያኒቱ “ለቅዱሳን ፈጽሞ በተሰጠውን እምነት፡” በሙላት እንድትጸና፡ አጥብቃ ትያዝ። ከሁለት አመታት በፊት፡ “ምግቡን አከማችሁ፡” ብለህ ራእዩን እንደገለጽከው ይሁንልን፡ በራእይ ያየኋቸው፡ ጥሩ፡ ሲታዩ-የሚያማምሩ አትክልቶች በዚህ ድንኳን ውስጥ ተከማችተው አይቻለሁና፡ ዛሬ ዘንቢላችን ሞልቶ፡ ወይም፡ የሞላ ቴፕ የምንቀበልበት ዕለት ይሁን፡ (ይሁን፡ ጌታ ሆይ።) በዚህ በምንኖርበት ዘመን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚገልጽልን ይሁንልን፡ ከፊታችን ለሚጠብቀን ተግባር፡ መንፈሳዊ ጥንካሬን የሚደግፍ ጥንካሬን ማግኛ ይሁን። ሰጠን፡ አባት ሆይ።

91 ከተለያዩ አገሪቱ ክፍል መጥተው፡ በዚ ማለዳ እዚ ተገኝተዋል። እነዚህን ልጆችህ ባርካቸው። ሞቃታማ፡ እና እርጥበታማ ማለዳ፡ ቢሆንም እንኳ፡ በዚሁ ሁኔታ ሁሉ ግን የመንፈስ ቅዱስን መገኘት አሁንም ይሰማናል።

92 ሰለ ጆን ዌስሊ፡ እና ካልቪን፡ እና ሳንኪ፡ እና ኖክስ፡ ፊኒ፡ እና ከእነዚህ ውስጥ ብዙዎቹን ሰናሰባቸው፡ የኤሌክትሪክ ማቀዝቀዣ በሌለበት ሰፍራ፡ ፊታቸው ላይ ላብ እየወረደባቸው፡ ሰዎች በአዳራሽ ውስጥ ይቀመጡ ነበር።

ሴቶች፡ ነፍሶቻቸው በጌታ ቃል ለመመገብ፡ በሰርዓት ለብሰው እና ተሸፍነው፡ ቀሚሶቻቸው በላብ እስኪረጥብ ድረስ፡ ይቀመጡ ነበር። ጌታ ሆይ፡ አሁን፡ የጌታን መምጣት እየተጠባበቁ፡ በእረፍት ሰፍራ እንዳሉ፡ ይሰማናል።

93 አባት ሆይ፡ በአንድነት ጠብቀን። መንፈስ ቅዱስህም አቅጣጫ ያሳየን እንዲሁም ይምራን። አንተን የምናገለግልበት ረጅም ዘመን ሰጠን። በየአንዳንዳችን ልብ እንዲገባ፡ በዚ ማለዳ ከቃልህ የምንጠብቀውን ታላቁን መልዕክትህ ሰጠን። ጌታ ሆይ፡ ተናጋሪው ከንፈር፡ እውነት እንዲናገር አድርገው። ሰሚ ልብም እውነትን ይቀበል ዘንድ ለምለም ልብ ይሁን። በሰዎችም ፊት የሚነበቡ ደብዳቤዎች እንሆን ዘንድ፡ የሚያበሩ ታላላቅ ዘለአለማዊ ዛፎች ሆነን ማደግ ይሁንልን፡ ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን እንደተነሳና በመካከላችን እንደሚኖር ያውቁ ዘንድ ነው። ከታላቁ ክስተት ከሁለት ሺ ዓመታት በኋላ አሁንም ሴቶች እና ወንዶች፡ ወጣቶች እና ልጃገረዶች ሁሉ አሁንም የክርስቶስ የሕይወት ፍሬ በእኛ እንደሚኖር ያዩ ዘንድ፡ በፍቅር እና በመንፈስ ፍሬ የተሞሉ አድርገን። አባት ሆይ፡ ስለ አንተ ክብር፡ ይህን አድርገው። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠይቃለን። ኣሜን።

94 አሁን ከቅዱሳት መጻሕፍት የተወሰኑትን ማንበብ እፈልጋለሁ። አሁንም ብዕሮቻችሁ፡ እና ማስታወሻዎቻችሁ፡ ይዛችሁ ዝግጁ እንደሆናችሁ አምናለሁ።

95 ወንድም ኔቪል፡ እንደው፡ ተረጋግተህ ቁጭ ብለሃል። እንግዲህ... እኔ ግን ኮቴን አወልቀዋለሁ። [ወንድም ኔቪል፡ "አበጀህ፡ አሜን።" አለው።—አርታዒ።] ያ ነው... ኮቴን ሰላወለቅኩ ይቅርታ አድርጉኝ፡ እዚህ ግን—በጣም ይሞቃል።

96 እና የቆላሰይስ ሰዎች መጽሃፍ፡ ወደ ቆላሰይስ ሰዎች 1ኛ ምዕራፍ እንድትከፍቱ እፈልጋለሁ። ከዚያም ይህን እያነበብን፡ በመጀመር... ወደ ቤት ሰትሄዱ፡ የዚህን የቆላሰይስ ሰዎች ምዕራፍ በሙሉ እንድታነቡ፡ እፈልጋለው። ዛሬ ጠዋት ግን፡ ከእኔ ጋር ከ15ኛው ቁጥር፡ እስከ 29ኛው፡ ሙሉውን፡ እንድታነቡ እፈልጋለሁ።

97 እንግዲህ ጌታ ከረዳን፡ ባለፉት ዘመናት ሁሉ፡ በዚህ ሰፍራ በድንኳኑ ዓመታት፡ የነገርኳችሁ ነገሮችን ወደ ልባችሁ እንዳበራላችሁ እና እንድገልጥላችሁ ሰለፈለግኩኝ የምትችሉትን ያህል እንድትታገሱኝ እፈልጋቹኋለሁ፡ ያልኩት ሁሉ ለምን እንዳልኩት፡ ያደረግኩትስ ሁሉ ለምን እንዳደረግኩት እገልጻለሁ። ምክንያቱ ይህ ነው።

98 አሁን ከቁጥር 15 ጀምሮ።

> **እርሱም የፍጥረት ሁሉ በኵር፡ የማይታይ እምላክ ምሳሌ ነው፡**
>
> **የሚታዩትና... የማይታዩትም፡ በሰማይና፡ በምድር ያሉት ሁሉ፡ በእርሱ ተፈጥረዋልና፡ ዙፋናት ቢሆኑ፡... ወይም ጌትነት፡... ወይም አለቅነት፡... ወይም ሥልጣና፡ ሁሉ በእርሱና፡ ለእርሱ ተፈጥሮአል፡**
>
> **እርሱም ከሁሉ በፊት ነው፡ ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል።**
>
> **እርሱም የአካሉ፡ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፤ እርሱም፡ በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ፡** መጀመሪያ **ከሙታንም በኵር ነው።**

**እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር—ሙላቱ** እንዲያድርበት **ወደእልና፤**

99 አሁንም ደግሜ በ19ኛው ቁጥር ላይ ትንሽ ትኩረት ልስጥ።

**እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር ወደእልና፤**

**በእርሱም በኩል፡ በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ፡ በምድር ወይም በሰማያት፤ ያሉትን ሁሉ፡ ለራሱ፡ እንዲያስታርቅ፡ ፈቅዶአልና።**

ያ እርቅ ወዴት እንደሆነ ተመልከቱ።

**እናንተንም፡** በፊት **የተለያችሁትን ክፉ ሥራችሁንም በማድረግ በአሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አስታረቃችሁ።**

**ነውርና** ነቀፋ የሌላችሁና... **ቅዱሳን... አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ፡ አሁን በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ፤**

**ይህም** ተመሥርታችሁና **ተደላድላችሁ፡ ከሰማችሁትም ከወንጌል ተሰፋ** ሳትናወጡ፡ **በእምነት ጸንታችሁ ብትኖሩ ይሆናል፡ ያም ወንጌል ከሰማይ በታች ባለው ፍጥረት ሁሉ ዘንድ የተሰበከ ነው፡ እኔም ጳውሎስ የእርሱ አገልጋይ ሆንሁ፤**

**አሁን በመከራዬ ሰለ እናንተ ደስ ይለኛል፡ ሰለ አካሉም፡ ማለት ሰለ ቤተ ክርሰቲያን፡ በሥጋዬ... በክርሰቶሰ መከራ... የጐደለውን እፈጽማለሁ፡**

**ሰለ እናንተ እንደ ተሰጠኝ፡ እንደ እግዚአብሔር መጋቢነት የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽሜ እንድሰብክ፡ እኔ የቤተ ክርሰቲያን አገልጋይ ሆንሁ፡**

**ይህም ቃል** ከዘላለምና **ከትውልዶች ጀምሮ** ተሰውሮ የነበረ **ምሥጢር ነው፡ አሁን ግን ለቅዱሳኑ ተገልጦአል፤**

100 ይህን ጥቅሰ ደግሜ ማንበብ እፈልጋለሁ።

**ይህም ቃል ከዘላለምና ከትውልዶች ጀምሮ ተሰውሮ** የነበረ **ምሥጢር ነው፡ አሁን ግን ለቅዱሳኑ ተገልጦአል፤**

**ለእነርሱም እግዚአብሔር በአሕዛብ ዘንድ ያለው የዚህ ምሥጢር ክብር ባለ ጠግነት ምን እንደ ሆነ ሊያሰታውቅ ወደደ፤ ምሥጢሩም፡ የክብር ተሰፋ ያለው ክርሰቶሰ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው፤**

**እኛም፡ በክርሰቶሰ ፍጹም የሚሆን ሰውን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ፡ ሰውን ሁሉ እየገሠጽን፤ ሰውንም ሁሉ በጥበብ ሁሉ እያሰተማርን የምንሰብከው እርሱ ነው፤**

**ለዚህም ነገር ደግሞ፡ በእኔ በኃይል እንደሚሠራ** እንደ **እሠራሩ እየተጋደልሁ፡ እደክማለሁ።**

101 ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱሰ መሰረት በማድረግ፡ ርእሰ ለመሰጠት፡ ርዕሰን ከዚሁ መውሰድ እፈልጋለሁ፡ የተገለጠው የእምላክ ሚሰጢር

ክርስቶስ ስለሆነ፡ **ክርስቶስ የተገለጠ የእግዚአብሔር ምስጢር ነው።** በማለት ርዕስ እንድንሰጠው እፈልጋለሁ! እንግዲህ፡ ህብረት እያደረግን—በህበረት እያነበብንም፡ የሰንበት ትምህትት እንዲሆንልን በየተራው በሰርዓት አድርጌዋለሁ።

102 ይህም፡ የተሰወረ የእግዚአብሔር ምስጢር፡ ዓለም ሳይፈጠር በፊት በርሱ ዘንድ የነበረ ነው። ወደ ኋላ፡ ወደ እግዚአብሔር አሳብ መለሰ ሰንል፡ ሊፈጽመው እና ሊሰራው የፈለገው አንድ ነገር ነበረው፡ የሚያደርግበትም አሳብም ነበረው፡ ያም ደግሞ ራሱን መግለጽና መተረክ ነበረ። ምክንያቱ፡ መጀመርያ፡ ጨረቃም፣ ከዋክብትም፣ አተም፣ ሜለኩል ወይም ሌላ ምን ሳይኖር። እሱ አምላክ ነበረ። በዚያ ዘመን ግን **አምላክ** አልነበረም፡ አምላክ ማለት "የሚመለክ አካል፡" ማለት ነውና፡ እሱን የሚያመልክ ገና አልነበረምና።

103 ስለዚህ፡ በታላቅ አሳቡ፡ እነኚህን መገለጫዎቹ ሁሉ እንዲከፈቱ ፈለገ። በውስጡ ፍቅር ነበረ፡ በውስጡ አባት መሆን ነበረ፡ በውስጡ ልጅ መሆን ነበረ፡ በውስጡ አዳኝ መሆን ነበረ፡ በውስጡ ፈዋሽነት ነበረ። እነዚህን ተገልጸው የምናያቸው ታላላቅ መገለጫዎች ሁሉ፡ በአምላክ ውስጥ ነበሩ።

104 ስለዚህ፡ እንደ'ኔ አሳብ፡ መላእክት የመጀመርያ ስራው ናቸው። ከዚያም እነሱ ሲያመልኩት፡ ይህ ስራው "አምላክ" እንዲሆን አሰደረገው። ባለፉት መልዕክቶች ለመግለጽ፡ ለማስቀመጥ እንደሞከርኩት። ከዚህ ይጀምራል። እና፡ ያኔ፡ መላእክቶች እሱን ማምለክ በጀመሩ ጊዜ፡ ያ ማለት ገና በምድር ሜለኩል እንኳን ሳይኖር ነበር። ምንም ነገር አልነበረም። ሙሉ በሙሉ ጨለማ ነበረ። ጸሓይም፣ ጨረቃም፣ ከዋክብትም፣ ምንም ባልነበሩበትም፡ እሱ ግን አምላክ ነበረ። ኢዮብን ደግሞ እንደጠየቀው፡- "የዓለምን መሰረት ባደረግሁ ጊዜ አንተ ወዴት ነበርህ፡ እያችሁ፡ አጥቢያ ኮኮቦች በአንድነት ሲዘምሩ፡ የእምላክም ልጆች ሁሉ ዕልል ሲሉስ? እያችሁ? ያኔ፡ የት ነበርክ?" እያችሁ? ያ ማለት ገና ምድር ሳይኖር በፊት ነው።

105 ስለዚህ፡ እግዚአብሔር አምላክ ዓላማ እና የተሰወረ ምስጢር ነበረው። ዛሬ ማለዳ ለቤተ ክርስትያን ልናገር የምፈልገው ነገር ይህ ነው፡ ከዓለም ፍጥረት በፊት በእግዚአብሄር አምላክ አሳብ ውስጥ የነበረውን የተሰወረው ምስጢር፡ እኛ ወደምንኖርበት ዘመን በራሱ ጊዜ እንዴት እንደ ተከፈተ እናገራለሁ። እያችሁ? ከዛ በኋላ፡ ምን ምን እንደተደረገ፡ በግልጽ፡ እንደምትረዱ፡ አምናለሁ።

106 ታላቁ የእግዚአብሔር አምላክ ምስጢር፡ እንዴት፡ ምስጢር ሆነ። ምስጢራዊ አድርጎ አቆየው። አንድም የሚያውቀው አልነበረም። እያችሁ፡ አልገለጠውምና። መላእክትም ቢሆኑ ሊረዱት አይቻላቸውም። በሰባተኛው ምስጢራችን ላይ፡ ሰባተኛው ማህተም በተፈታ ጊዜ፡ ጸጥታ ሆነ የሚባለው፡ ምክንያቱ ይህ ነው። ኢየሱስ፡ በምድር በነበረ ጊዜ፡ የመምጣቱ ጊዜ መቼ እንደሆነ ለማወቅ ፈለጉ። "አይታወቅም… መቼ እንደሚሆን ልጅ እንኳን አያውቅም፡" አላቸው። እያችሁ፡ እግዚአብሔር አምላክ ይህን ሁሉ ለራሱ ጠብቆታል። ምስጢር ነው። በሰማያት ለግማሽ ሰዓት ጸጥታ የሆነበት ምክንያቱ ይህ ነው፡ ሰባቱ ነጎድጓዶችም በየድምጻቸው ተናገሩ፡ ዮሃንሰም፡ እያችሁ፡ የጌታን መምጣት እንዳይጽፍ የተከለከለበት ምክንያት ይህ ነው። እንዴት እንደሚመጣ፡

እና መቼ እንደሚመጣ፡ እስካሁን ያልገለፀው አንድ ነገር ይህ ነው። ባይገልጸው ይሻላል። አይ።

107 በመጽሓፍ ቅዱስ ባለው በጥላው ሁሉ አሳይቶታል እንዲሁም ገልጾታል። ስለዚህ፡ መላው መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቶስ ዘንድ ያለው የእግዚአብሔር ምስጢር መገለጥ ነው። አሃ! መላው መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አምላክ በመጽሓፍ ቅዱስ ውስጥ ሊፈጽመው የፈለገውን፡ የአንዱ ዓላማ መግለጫ ነው። በመጽሓፍ ቅዱስ ውስጥ የተመዘገቡ የአማኞች—ሰራዎችም፡ የእግዚአብሔር አምላክ ትልቁ ግብ ምን እንደሆነ በጥላ የሚተርኩ ናቸው፡ አሁን በዚ በመጨረሻ ቀን ገልጦታል አሳይቶታልም። በእግዚአብሔር እርዳታ፡ በዘመናት ሁሉ ጌታ በሐሳቡ ምን እንደነበረ፡ እና ምን እንደገለጸ፡ ዛሬ ማለዳ እናየዋለን።

108 ስለዚህ፡ ይህ ለማወቅ እና ወደ ህዝብ ለማምጣት መሞከር፡ ምን ያህል ታላቅ ትርጉም እንዳለው ማየት ትችላላችሁ። አያችሁ? በእናንተ በኩልም... እግዚአብሔር እንደገለጠልኝ ለማስረዳት ወደ ዝርዝር ነገር ገና አልገባሁም።

109 እንግዲህ፡ ልታስምሩበት ከወደዳችሁ። ማንበብ የምፈልጋቸው ብዙ ክፍሎች ይዣለሁ። በቅዱስ ሉቃስ—መጽሐፍ 24ኛው ምዕራፍ ላይ፡ ከሐወርያት መካከል ሁለቱ፡ መንገዳቸውን... ወደ ኤማሁስ ሲያቀኑ እንመለከታለን። ከትንሳኤው በኋላ፡ ወደ ኤማሁስ በሚወስደው መንገድ—በጉዞ ላይ ሳሉ፡ ኢየሱስ ገጠማቸው፡ በሞቱ—ምክንያት አዝነው እየጠወለጉ፣ እያነቡ፣ እና እያወሩ፣ ያሰቡት ሁሉ፡ ምንም ዋጋ እንደሌለው በመሰላቸው ነገር ላይ ሲስቃይ እንዴት እንዳዩት፡ ጌታቸውን ወሰደው ሰቀሉባቸው። እና—እያነቡ፡ መንገዳቸው ሄዱ።

110 በመንገድ እያነቡ ስሄዱ ሳሉ ድንገት ከመንገድ ዳር መጣና ስለ ክርስቶስ ያናግራቸው ጀመረ። "እናንተ ለማስተዋል የዘገያችሁ ሞኞች ሆይ፡ ነብያት ሁሉና መዝሙራትን አታውቁምን... ? " አላቸው፤ አያችሁ፡ ምን እያደረገ ነበር? እራሱን ለእነዚያ ሐዋርያት፡ ነብያት ሁሉ እና፡ መዝሙሮች ሁሉ፡ ሌሎች ሁሉ ጭምር፡ እሱን የሚተርኩ፡ መሆናቸውን ያሳያቸው ጀመረ። አያችሁ?

111 በዚህ ማለዳ፡ በስብከት መልኩ እንዳላደርገው የመረጥኩበት ምክንያት፡ አንድ ጽሁፍ እያየን፡ እየዘለልን ከመሄድ ይልቅ፡ ርዕሱን ወስደን ዝም ብለን ከማለፍ ይልቅ እንረዳዋለን ብዬ ስላሰብኩ ነው። ብናስተምር የተሻለ ነው።

112 እንግዲህ፡ ነብያት ሁሉ እና መዝሙሮች ስለ'ኔ ተናግሯል ብሏል። መልካም፡ እንግዲህ፡ ያ የሚያሳየው፡ ብሉይ ኪዳን ሁሉ፡ አዲስ ኪዳን በሙሉ፡ መዝሙሮች፡ ዝማሬዎች፡ እና የተዘመሩ መኃልየዎች ሁሉ፡ ስለሱ እንደነበሩ ያስረዳል።

113 መዝሙረ ዳዊት መእራፍ 22 ውሰዱና፡ ዘምሩት፡ ከዛም በኋላ ከሰቅለቱ ዕለት ጋር አስተያዩት። አያችሁ፡ "አምላኬ፡ አምላኬ፡ ለምን ተውከኝ? አጥንቶቼ ሁሉ፡ ተመለከቱኝ። እጆቼን እና እግሮቼን ወጉኝ።" ያኔ እነዚህን ሁሉ፡ መዝሙሮቹን በሙሉ በመቅደስ ውስጥ እየዘመሯቸው፡ ዋናውን ግን፡ ሰቀሉት። አያችሁ? አያችሁ፡ እነዚያ ታላላቅ የሐይማኖት መሪዎች፣ ታላላቅ ሰዎች፣ ታላላቅ አስተማሪዎች ሆነው፡ እጅግ የታወሩ፡ ነቢያትን እያነበቡ መዝሙሩን እየዘመሩ፣ እንፈጽመዋለን የሚሉትን ወንጀል በመፈጸም ላይ ነበሩ።

ዛሬ ጠዋትም ተመሳሳይ ነገር እየተፈጸመ ነው!

114 አሁን በደንብ ተከታተሉኝ፡ ምክንያቱ... ዛሬ ስንት ሆነ ብዬ ሰዓቱን ለማየት አልዞርም። ይህ እንዲገባችሁ እፈልጋለሁ። አያችሁ? እንድትረዱት፡ እፈልጋችኋለሁ። አያችሁ? [ጉባኤው ደስ ብሎት፡ "አሜን" አለ።—አርታዒ።]

115 እንግዲህ እንደምታዩት፡ በመሰረቱ፡ ከመጀመርያም፡ በእግዚአብሔር አምላክ ዘንድ የነበረውን የመጀመርያውን ሐሳብ፡ ከአዋቂዎች ሁሉ ሰውሮታል። ያንን የሰሙት... በጣት የሚቆጠሩ፡ በቁጥር አስቀድመው የተመረጡ፡ አስቀድመው የተወሰኑ፡ ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው። እስኪ እናንተም ከነብያት ዘመን ጀምራችሁ ቅዱስ ቃሉን መርምሩትና፡ እስከ አሁን ድረስ ተመሳሳይ ካልሆነ ተመልከቱት። አያችሁ?

116 አሁንም እዚህጋ፡ ራሱን ከነብያት እና ከመዝሙራት ጋራ እያስተያየ፡ ኢየሱስ ሁሉም ስለሱ እንደተናገሩ ነገራቸው። አያችሁ? እዚህ ጋርም የአይሁድ አስተማሪዎች፡ ራቢዎች፡ የሕግ ዶክተሮች፡ ፕሮፌሰሮች ሁሉ እነዚያ ድሮ እንዳደረጉት፡ አሁን እነዚህ ደገሙት።

117 የተናገረውን ቃል፡ አሁን አስተውሉ፡ "መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ፡ እነሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው፡" አላቸው። መጻሕፍትን መርምሩ፡ ቅዱሳን መጽሕፍት፡ መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ። ምን እያደረግኩ ይመስላቹኋል? ይህ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት መሆኑ ለእናንተ ለማሳየት ነው።

118 ባለፈው ቀን፡ በሆስፒታል ክፍል ቆመን፡ እያወራሁ፡ አንዲት እህት ስለ ሐይማኖት ተቋማት እንዳብራራላት፡ የሐይማኖት ተቋማትን፡ የሐይማኖት ተቋማት—ሰዎችን ለምን እንደምንቃወም ጠየቀችኝ።

119 አያችሁ፡ ወደ ቃሉ መመለስ አለበት፡ ምክንያቱ ቃል ራሱ እግዚአብሄር አምላክ ስለሆነ። አያችሁ? ኢየሱስም ስለ ራሱ እዚህ ጋር፡ ቃል እንደሆነ እያስተዋወቀ ነው። መቼም ቃል እርስ በርስ እንዲቃረን ማድረግ አይቻልም። "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ቃልም፡ ሥጋ፡ ሆነ!" አያችሁ?

120 እርሱም እንዲህ አለ፡ "መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ፡ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው። በእነሱ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታስባላችሁ፡" እውነትም ነው፡ "እነሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው። እኔም ስለ እነዚያ ምስክር አለኝ። ያደርጋቸዋል የተባሉልኝ ስራዎች የማላደርግ ከሆንኩ፡ እኔን አትስሙኝ። ስራዎቹን የማደርግ ከሆነ ግን፡ እኔን ባታምኑ፡ ስራዎቼን እመኑ፡ ምክንያቱ እሱ ራሱ ቃል እንደሆነ የሚመሰክሩ ናቸውና።" ኦ! ከዚህ በላይ ማብራራት የሚቻል አይመስለም። አያችሁ? መልካም። አሁን፡ "መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ።" ሙሴና ሕግ ሁሉ፣ ነብያትም፣ መዝሙሮችም፣ እና ሌሎችም ሁሉ፣ ስለ'ሱ እንደሚናገሩ ተናግሯል። መጻሕፍትም ስለሱ እንደሚመሰክሩ፡ በድጋሚ፡ ተናገራቸው።

121 የመላው መጽሐፍ ቅዱስ መሪ ተዋናይ እሱ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንብባችሁ፡ በእያንዳንዷ ቃል ክርስቶስን ማየት ካልቻላችሁ፡ ተመለሱና ደግማችሁ አንብቡ፡ አያችሁ? በእያንዳንዷ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ውስጥ፡ ክርስቶስን ማየት ካልቻላችሁ፡ ያመለጣችሁ ነገር ስላለ፡ እንደገና አንብቡት። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም ቃል ነው። በመጀመርያ "እግዚአብሔር እንዲህ ፈጠረ፡" የሚል ስታነብቡ፡ ክርስቶስ ነበረ። አያችሁ?

ከዛች ጀምሮ... በራእይ ዮሃንስ እስካለች የመጨረሻ "አሜን" ድረስ፡ እያንዷንዱ ቃል፡ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ይመሰክራል።

122 **ተረፈ ዳንኤል፣** እና መ—**መጽሐፈ መቃብያን** የሚሏቸው ተጨማሪ መጻሕፍቶችን፡ አያችሁ፡ ሙታን ማቆያ ወዘተ፡ በቅዱሳን ቃላት የሌሉ መጻሐፍቶች የሚጨማምሩት ለዚህ ነው። አያችሁ? ከሌሎቹ ጋር ቤት አይመቱም። ሙታን ማቆያ ብሎ ነገር አብሮ ሊጠረዝ አይችልም። የቅዱሳን አስታራቂነት፡ እና አማላጅነት ተቀባይነት የለውም። ከቅዱስ ቃል ጋር የሚቀላቀልበት ስፍራ የለውም። የሐይማኖት ተቋም ስፍራ የለውም። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ—ለሆነው ለሐይማኖት—አዋልድ ስፍራ የለውም። አያችሁ? እነዚህን ስትመለከቱ፡ ወደ ስዕሉ አ—አይቀርቡም። ሰዎች እነዚህን ሁሉ በማቀላቀል፡ የራሳቸውን የተዘበራረቀ—የእንቆቅልሽ—ጨዋታቸው የቀላቀሉት ለዚህ ነው። አያችሁ? በትክክል መስራት አይችሉም፡ "ትላንትና፣ ዛሬ፣ እስከ ዘለአለም ያው ነውና።"

123 ነገር ግን እነዚህ ነገሮች በሙሉ በትክክል ተቀናጅተው ከተቀመጡ፡ የውድቀት እና የዳግም ልደት ትክክለኛውን ስዕል አለው። የፍጥረትን ሙሉ ስዕል፡ እና የእግዚአብሔር አምላክ ሙሉ ዕቅድ በኢየሱስ ክርስቶስ የተገለተ ነው። አሜን! አባጣው እና ጎባጣው ሁሉ፡ በዚህ ስዕል ውስጥ በህብረት የተቀናጀ ነው። እንደው... አሁን፡ የተዘበራረቀውን የእንቆቅልሽ ጨዋታ ወደ አንድ ለማምጣት እንጂ፡ በዚህ ምክንያት ለማራከስ ከመፈለግ አይደለም።

124 በዚ ዘመን ቀፋፊ ምስል ያስያዘን ጉዳይ ይህ ነው። "አማኞች ነን፡" እያልን፡ ላም ከዛፍ በላይ ሳር ጋጠች። አይሰራም። እንዲህም ይላሉና፦ "አዎን፡ እርሱ ሁሉ በሁሉ ቢሆንም፡ ጥቂት ነገሮች ላይ ግን... ከጥቂቶች ነገሮች በቀር እንጂ፡ ትናንትና፣ ዛሬ፣ እስከ ለዘላለም ድረስ ያው ነው ይላሉ።" አያችሁ? ያኔ ምስሉን ሁሉ ታጠፉታላችሁ።

125 መጽሐፍ ቅዱስ ግን ያው ነው ብሎታል! ዮሃንስ ወንጌል 5፡ ወይም ዮሃንስ ወንጌል 14:12፡ እንዲህ ይላል፦ "በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርጋቸውን እሱም ደግሞ ያደርጋል፡" "እርሱ፡" እርሱ ማለት፡ ማንም ይሁን።

"እንዴ፡ ያ'ኮ ለሌላ ዘመን ነው።"

126 ይሄው እንደገና የተሳሳተ ምስላችሁ ይሄው ነው። አሳ በሌለበት፡ በምድረበዳ የጋለ የአሸዋ ክምር ባለበት ስፍራ፡ አሳን የሚያጠምድ ሰው ትስላላችሁ። አያችሁ? አያችሁ፡ ብዙ አሳዎች ወደሚገኙበት፡ አሳዎችን ማጥመድ ወደሚቻልበት፡ ወደ ገሊላ ባሕር ልትመልሱት ይገባል፡ አያችሁ። አያችሁ?

127 ምስሉን—በትክክል እንዲመስል ማድረግ አለባችሁ። የእግዚአብሔር ድንቅ ሥዕል ነው። ይሄን የምታዩበት አንድ መንገድ ብቻ አለ፡ ይህም ኢየሱስ ክርስቶስን ማየት ስትችሉ ብቻ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ። የመጽሐፍ ቅዱስ መሪ ተዋናይ እርሱ ነው።

128 ከዚህ ውስጥ አንድን ርዕስ ወስዳችሁ ዝም ማለት እንደማይቻላችሁ፡ መቼም ሰባኪ ይህን አንስቶ ዝም ማለቱ ይከብደዋል። ቀጥል ቀጥል የሚል ነገር ይኖረዋል፡ ይሁን እንጂ እያስተማርን ወዳለነው ነገር መመለስ ያስፈልጋል።

129 የመጽሓፍ ቅዱስ መሪ ተውኔት እርሱ ነው። በነብያት ዘንድ እርሱ ነበረ። በመዝሙሮችም እርሱ ነበረ። በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ እርሱ ነበረ። መጽሐፍ ቅዱስ ትንቢታዊ መጽሐፍ ነው። ታሪካዊ መጽሓፍ ነው። የፍቅር መጽሐፍ ነው። የ—የዝማሬ መጽሐፍ ነው። የሕይወት መጽሓፍ ነው። በዚያም ክርስቶስን ታገኛላችሁ። በነብያት ዘንድ እርሱ ነበረ። በመዝሙራት እሱ ነበረ። በታሪክ ውስጥ እሱ ነበረ። በመጽሐፍ ቅዱስም፡ ሊመጣ ያለው፡ እርሱ ነው። ስለዚህ፡ ፊተኛውም እርሱ ነበረ ኋለኛውም እርሱ ነው። ታድያ ይህ ማን ያደርገዋል? "ትላንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ዘለአለም ያው ያደርገዋል።"

130 እናንተም "ትላንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው፣" የማያደርገው ነገር፡ እየቀላቀላችሁበት፡ ወንድም ሊ፡ የት ትደርሳላችሁ? በጣም አስቀያሚ ምስል ትፈጥራላችሁ። ምክንያቱ፡ እራሱ ታሪክ ነበረ፡ አያችሁ፡ እንዲሁም ነብይ ነው፡ መዝሙረ ዳዊት እርሱ ራሱ ነው። ሁሉ ነገር ነው። እንግዲህ እሱን ሁሉ ነገር፡ እና ያው ካላደረጋችሁት በቀር፡ የሳላችሁት ምስል፡ ምን ሊመስል ይችላል? እየገባችሁ ነው? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—እርታዒ።] መልካም።

131 ቁምነገሩ እርሱ ነው! እሱ ነብያቶች ነበረ። በእነርሱ ዘንድ ነበረ። ከመዝሙረኛው ጋር ነበረ። ታሪክ ውስጥ ነበረ፡ የሚመጣውም ነገር እርሱ ነው፡ "ትላንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ዘለአለም ያው ነው።" እየጻፋችሁ ከሆናችሁ፡ ዕብራውያን 13:8። ያኔ፡ እሱ እንደዛ ከነበረ፡ አሁንም ከሆነ፡ እሱ ራስ መሆን አለበት። እኛም እናምናለን፡ እናምናለን አይደል? [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—እርታዒ።] እንግዲያስ እርሱ እንዲሁ ከሆነ፡ የንግግራችን ራስ ሊሆን ይገባል፡ የአስተሳሰባችን፣ የመዝሙራችን፣ የአካሄዳችን ራስ። ["አሜን።"] እንዲሁም የሕይወታችንም መሪ ተዋናይ መሆን አለበት። እሱ የመጽሐፍ ቅዱስ መሪ ተዋናይ ሆኖ፡ መጽሓፍ ቅዱስም በእኛ ውስጠ ከሆነ፡ እንግዲያውስ በድርጊታችን፣ በንግግራችን፣ እና በአሳባችን ሁሉ ላይ፡ ክርስቶስ መሪ ተዋናይ መሆን አለበት። ልክ ነው? ["አሜን።"] በጣም ጥሩ።

132 ይህንም የምናስብ፡ እስከ ሆንን ድረስ፡ እርሱም "በነገር ሁሉ፡" ለእኛ—ራስ ነው። ወደ ቆላስይስ ሰዎችም ተናግሯል። ለእኛ "በነገር ሁሉ፡" ራስ ሆኗልና። እርሱ ራሱ... ለእኛ "ሁሉ ነገራችን፡" እንደሆነ እንቆጥረዋለን። እናንተም፦ "ሐጢአተኛውስ?" ትላላችሁ። እርሱን ላልተቀበለው ለሐጢአተኛውም ፈራጅ እንዲሆን ተደርገዋል። ለተቀበሉት ለአማኞች ግን ክብር ሆኖአል። ስለዚህ፡ ነገሮች ሁሉ፡ "ሁሉ በእርሱ፡ ለእርሱ ሆኖአል።"

133 እንዲሁም የቀንን ክብር ለመግለጽ፡ የማታው መኖር ይጠይቃል። የክብርን ዕቃ—ፍቅር እና እንክብካቤን ለመግለጽም፡ የውርደትን እቃ መኖር ይጠይቃል። ሞራልዋን የጠበቀች ደግ—እና ረጋ ያለች፡ ትክክለኛ እመቤት ለመግለጽ፡ ክፍ ልብስ የምትለብስ ሞራልዋን የሸጠች ክፉ ሴት ታስፈልግ ነበረ። አያችሁ? የእውነተኛ አማኝ፡ የእውነተኛ ክርስቲያን፡ እውነተኛነት ለመግለጽ፡ አጭበርባሪ እና ሌባ ሰው ያስፈልግ ነበር። አማኙ፡ ማን እንደሆነ ለማየት፡ የግብዙ መኖር ይጠይቃል።

134 እንግዲህ፡ "ነገር ሁሉ በእርሱ ከሆነ።" የሆነውም ሁሉ... የሆነው፡ የተደረገውም ሁሉ፡ በእርሱ፡ ለእኛ ለሁላችን ተደረገ። እንግዲህ፡ ያ እውነት

እስከሆነ ድረስ፡ መታወቂያችንን ከእርሱ ጋር በማድረግ (ለርሱ መለየት) አለብን። እሱ ራሱ፡ ከእኛ ጋር አንድ ስላደረገ፡ እኛም ማንነታችንን፡ ከእርሱ ጋር አንድ ማድረግ ይገባናል። ከእርሱ ጋር መታወቅ አለብን። እንዴት? ለእርሱ በመኖር፡ በአፍ በናገር ብቻ አይደለም።

135 ብዙ ሰዎች በአፋቸው ይመሰክራሉና፡ አሁን'ማ... እዚህ ደረጃ ላይ ደርሷል። ክርስትያን ነህ? "ሜተዲስት ነኝ።" አሀ፡ ይሄ'ኮ ራስህን ክርስትያን ከመሆን፡ ከማድረግ ፈጽሞ የራቀ ነው። ታዲያ፡ የሜቶዲስቶች ተግባር ተመልከቱ። "ባፕቲስት ነኝ።" ታዲያ፡ የባፕቲስቶች ተግባር ተመልከቱት። "ካቶሊክ ነኝ።" ስራዎቻቸውን እዩት። አያችሁ?

136 ይሁን እንጂ ክርስትያን መሆናችሁን የምትታወቁበት ብቸኛው መንገድ ክርስቶስ ራሱን በእናንተ ዘንድ ሲወግን ነው። እዚህ ውስጥ፡ እንዴት ያለ መውጊያ ነገር አለ! በቴፕ የምታዳምጡ ሰዎችም፡ ገብቶአቿል ብየ ተስፋ አደርጋለሁ። አያችሁ? አያችሁ? አያችሁ?

"እኔ ጴንጤቆስታል ነኝ፡" ብትሉም። ምንም የሚጠቅማችሁ ነገር የለውም።

137 ክርስቶስ በእናንተ ሲኖር ነው። እናንተን የሚያውቃችሁ ያኔ ነው።

"ልሳን እናገራለሁ።" ብትለኝ፡ ዲያብሎስም፡ ይናገራል።

138 "እጮሃለሁ ብትለኝ።" ሙሐመዳውያን፡ ቡድሃውያን ሌሎቹም ሁሉ ይጮሀሉ። ህንዳውያን በእባብ ዳንስ ላይ ይጮሃሉ። አያችሁ? አዎን። ሁሉም ይጮሃሉ። ጎሳዎች፡ የሐይማኖት ልምምዶች፡ ሌሎች ሁሉም፡ ይጮኃሉ ይንከባለላሉ። በቤዝ ቦል ጨዋታ ሁሉ ይጮሃሉ ይንከባለላሉ።

139 ክርስቶስ በእናንተ ሲኖር ግን፡ ራሱን በእናንተ ውስጥ ሲገልጽ፡ ያኔ ክርስቶስ-መሣይ ትሆናላችሁ። **ክርስትያን** የሚለው ቃልም፡ "ክርስቶስን-መሣይ" ማለት ነው። መታወቂያችሁ ይሄ ነው። በጣም ጥሩ። አሁን፡ እርሱ መታወቂያችን እስከሆነ ድረስም፡ በነገር ሁሉ ለእርሱ በመኖር፡ ከእርሱ ጋር መታወቅ አለብን።

140 አስተውሉ፡ እግዚአብሔር አምላክ በዚህ በታላቁ የተሰወረው ምስጢር ውስጥ ሶስት መአዝናዊ ዓላማ ነበረው። እግዚአብሔር አምላክ፡ ዓለም ሳይፈጠር በእርሱ ዘንድ በነበረው፡ በታላቁና በተሰወረው ምስጢሩ ውስጥ፡ ሶስት መአዝናዊ ዓላማ ነበረው። እንግዲህ ዛሬ ጠዋት፡ ልናየው የምንፈልገውም፡ ይህ ሶስት መአዝናዊ ዓላማው ምንድነው ነው? አያችሁ? እንግዲህ፡ ህያው በሆነው፡ በእግዚአብሔር... እርዳታ፡ እርሱ—ራሱ እንደሚያሳየን እምናለሁ። አሁንም፡ ሶስት መአዝናዊ ዓላማ የነበረው ከሆነ፡ ይህ ሶስት መአዝናዊ ዓላማው ምን እና ምን እንደሆነ መፈተሽ እንፈልጋለን።

141 የመጀመርያው ነገር፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ ራሱን ለሰዎች ማስተዋወቅ ወይም መግለጥ መፈለጉ ነው።

142 ሰማያትንና፡ ጊዜን ዘለአለማዊነትንም የሚሞላ ጀሆቫ ሆኖ፡ ይህን ማድረግ አይሆንለትም። ለሰዎች ለመገለጥ እጅግ ሰፊ ስለሆነ፡ እጅግም ምስጢራዊ ነውና። አይሆንም። ይህ መጀመርያ የሌለው... ከመቶ ቢልዮን እና ከትሪልዮን እና ትሪሊዮኖች የብርሃን ዓመታት ጽንፍ ወዲያ ማዶ ተሻግራችሁ፡ ማለቅያ

ወደሌለው፡ ወደ ዘለአለማዊነት ስትመለሱ፡ ይህ ሁሉ የነበረው፡ እና አሁንም ያለው ታላቅ ፈጣሪ እርሱ ነው።

143 ነገር ግን ምን ማድረግ ፈለገ፡ አባት ስለነበረ፡ አባትነትን ወደደ። አባትነቱን የሚገልጽበት ብቸኛው መንገድ ደግሞ ልጅ፡ ወይም ሰው በመሆን ነበረ። ኢየሱስ በተደጋጋሚ "የሰው ልጅ፡" ሲል የነበረው ለዚህ ነው። አያችሁ፡ ብዙዎች፡ ስለ ምን እንደሚል አይረዱትም ነበር። እናንተ ግን አሁን ገብቶአቿል? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—እርታዒ።] አያችሁ? ራሱን መተረክ ወደደ። ይህም ከሶስት ማአዝናዊ ዓላማዎቹ፡ አንድ ሆኖ፡ ራሱን ለመተረክ፡ ከሰዎች ልጆች ጋር ለመወገን፡ እራሱን በክርስቶስ ለመግለጥ ነው።

144 በሁለተኛ ደረጃ፡ የአማኖች አካል በምትሆን፡ በሙሽራይቱ ላይ፡ እንዲሰለጥን፡ በሰዎች መካከል ይኖር ዘንድ ነው።

145 ይሄንን ነገር፡ በአዳም እና በሄዋን ውስጥ ማድረግ ይችል ነበር፡ ሐጢአት ግን ለያያቸው፡ ስለዚህ ያንን የሚመልስ መንገድ ያስፈልግ ነበር። ኦ፡ ማይ! ኦህ፡ እንደው... ይሄንን፡ ለእኔ፡ ሳስበው ብቻ፡ በጣም ያረካኛል። አያችሁ? የጌታ አላማ ምን እንደነበር አያችሁ? አዳምን እና ሄዋንን እንዲሁ ለምን አይተዋቸውም ነበር? እንዲያ ከሆነ'ማ፡ ሙላቱን ወይም ሙሉ መገለጫዎቹን በትክክል መግለጽ በፍጹም አይቻለውም ነበር። ምክንያቱ፡ በዚያ ሆኔታ አባት መሆን እንደሚችል፡ እውነት ነው ይችላል፡ ነገር ግን አዳኝም ደግሞ ነው። "አዳኝ እንደነበረ እንዴት አወቅህ? " ብትሉኝ፡ አዎን አዳኝ ነው፡ የግል ልምምድ ስላለኝ። አያችሁ? አያችሁ? አዳኝ ነው፡ አዳኝነቱንም መተረክ ነበረበት። መተረክ የሚችለው እንዴት ነው? በክርስቶስ በኩል ብቻ ነው። ልጅ የሚሆነው እንዴት ነው? በክርስቶስ በኩል ነው። ፈዋሽ የሚሆነው እንዴት ነው? በክርስቶስ በኩል ብቻ ነው። አያችሁ፡ ይህ ሁሉ በአንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ይጠቃለላል። ኦ፡ ማይ! ይሄንን—ሳስብ...

146 አያችሁ፡ ሳስበው፡ የእግዚአብሔርን ታላቁ ዓላማ ሳየው፡ የሐይማኖት ተቋማቶቹ—ከመስመር ሲወጡ፡ ሌላውም ሁሉ እየተፈጸመ እንዳለ ይታየኛል። ራሱን ሲገልጥ፡ ወይም፡ "የመለኮት ሙላት በስጋ ሆኖ፡" መጀመርያ፡ ራሱን በክርስቶስ ውስጥ መግለጡ ነው። ከዛም በኋላ፡ "የመለኮት ሙላት በስጋ" በሰዎች ላይ፡ ለማምጣት ነው፡ ይህም የበላይ ይሆን ዘንድ፣ አለቃ፣ እና መሪ ይሆን ዘንድ ነው።

147 ሌላኛው፡ ባለፈው፡ ማታ ላይ የሰበኩት ስብከት ካሴት ካላገኛችሁ፡ "የኢየሱስ ክርስቶስ እስረኛ፡" የሚል ስብከት ነው። እስረኛው፡ ጳውሎስ! አያችሁ? እግዚአብሔር እስረኞችሁ ሲያደርጋችሁ፡ መንፈሱ አድርግ ያለውን ከማድረግ በቀር ሌላ ዕድል አታገኙም። ጳውሎስ፡ በተማረው... በታላቅ እውቀቱ፡ አንድ ቀን፡ ታላቅ ካህን ወይም ራቢ ለመሆን በገማልኤል የተማረ ሰው ነበረ። ደግሞም ታላቅ ጉጉት ነበረው። በእውቀት የላቀ፡ በአገሪቱ የተከበረ፡ ታላቅ ባለስልጣን ነበረ። ይሁን እንጂ፡ አያችሁ፡ የቃሉ አካል ለመሆን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመተረክ፡ ይህን ሁሉ መስዋዕት ማድረግ ነበረበት። ምንም ማለቱ እንደሆን በትክክል የሚያውቅ ነበር...

148 ወንድሞች ጠርተውት፡ ወደ አንድ ስፍራ ለመሄድ ሃሳብ ነበረው፡ ይሁን እንጂ የገዛ ፈቃዱን እንዳያደርግ በመንፈስ ተከለከለ። ኦ! እንደው—

ግማሽ መንፈሳዊያን የሆኑ ሰዎች ይሄን መረዳት በቻሉ! አያችሁ? የገዛ ፈቃዱ እንዳያደርግ ተከለከለ። ማድረግ የሚችለው… "መንፈስ ከለከለኝ።" አያችሁ? የክርስቶስ እስረኛ ነውና።

149 ያቺ፡ ኮኮብ ቆጣሪ ሴት፡ ጳውሎስ ዲያብሎሱን ከሷ ገስጾ ማውጣት እንደሚችል፡ ሀይል እንደነበረው ያውቅ ነበር፡ ይሁን እንጂ ያንን ማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር ሲፈቅድለት ብቻ ነው። ከቀን ወደ ቀን ተከተለችው፡ ከኋላው እየመጣች ትጮኽ ነበር፡ አንድ ቀን ግን ከመንፈስ ፈቃድ አገኘ። ከዛ በኋላ ገሰጻት፡ በውስጧ የነበረውን መንፈስ ገሰጸ። አያችሁ? እስረኛ መሆን ምን ማለት እንደሆነ ያውቅ ነበር።

150 ሙሴ፡ ክርስቶስን እንዲያገኝ፡ እስረኛው እንዲሆን፡ እውቀቱን ሁሉ መጣል ነበረበት። እግዚአብሔር ዓለምን ሁሉ እና፡ የታላቅነቱ ብርታት ከውስጡ ጨምቆ ባወጣ ጊዜ፡ በእሳት ዓምድ መካከል ቆሞ፡ ያን ቀን ቃላት አጥሮት ዝም አለ። በፍጹም፡ መናገር አልቻለም፡ ተብታባ ነኝ ሳይቀር አለ። ያኔ እግዚአብሔር አምላክ አንድ እስረኛ ያዘ። አያችሁ? በራሳችሁ መንገድ አትሞክሩ። ከዛ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ ይሄንን ሰው ማስታጠቅ፡ ወይም፡ መሄድ የሚያስችለው በቂ ኃይል አስታጠቀው።

151 እሱም "ጌታ ሆይ፡ ያልከኝ ሁሉ ነገርኩት፡ ፈርዖን ግን እምቢ ብሏል፡" አለው።

152 እግዚአብሔርም ተናገረው፡ አለውም፡ ይህም የእግዚአብሔር ቃል ነው፡ "ይሄን፡ ብትርህን ውሰድ፡" "ወርደህ ወደ ምስራቅ በኩል ዘርጋው፡ ዝንቦችምም ጥራበት።" ዝንቦችም ተፈጠሩ፡ ምክንያቱ ፈርኦን ሊያሰቆመው ያማይችል እስረኛ ሰላገኘ። ማንም ሰው በምንም መልኩ ሊመልሰው አይቻለውም። በአምላክ ቃል ሰንሰለት የታሰረ እስረኛ፡ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ለሚል ቃል ፈጽሞ የታሰረ እስረኛ።

153 በቃ፡ እግዚአብሔር እስረኛውን እንዲህ ከያዘ! የበላይነቱን መግለጽ የሚችለው ያኔ ነው፡ አያችሁ። ከክርስቶስ ውጪ፡ ሌላ ነገር እንዳያውቅ፡ ሰውየውን፡ ወይም ግለሰቡን ይይዘዋል። ምን ለማለት እንደፈለግኩ ገባችሁ? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] በጣም ጥሩ። ይህ ሁለተኛው ነው።

154 አንደኛው፡ እግዚአብሔር፡ ራሱን በክርስቶስ በሙላት መግለጽ።

155 ሁለተኛው፡ በዚህ፡ ማለትም፡ አካሉ በሆነች፡ በሙሽራይቱ ላይ፡ የበላይነትን እንዲያገኝ፡ ይህም ራሱን በእነሱ ዘንድ ለመግለጥ በላያቸው የበላይነት እንዲይዝ ነው። በጣም ጥሩ።

156 ሶስተኛውም፡ በመጀመርያው ሰው፡ በአዳም ሐጢአት ምክንያት፡ ወድቆ የነበረውን መንግስት፡ ከህዝቡ ጋር፡ በመሸ ጊኢዜ ወደተመላለሰበት ወደተነጋገረበት፡ አብሮ ሕብረት ወደሚያደርግበት፡ ምቹ ስፍራ ለማቃናት ነው።

157 አሁን ኃጢአት እና ሞት ከህልውናው እና ከአጠቃላይ መገለጫዎቹ ለያይቶአቸዋል። ገብቶአቿል? ከዓለም ምስረታ በፊት፡ ማንነቱን፡ እና መ—መ—መገለጫዎቹን ሁሉ ለመተረክ።

158 ስለዚህ፡ እዚህ ያላችሁ የሰላሴ እምነት ተከታዮች፡ ለአንድ ደቂቃ ራሳችሁን ፈታ አድርጉ፡ አባት፣ ልጅ፣ እና መንፈሰቅዱስ ሦስት አማልክት አለመሆኑን

መመልከት ትችላላችሁ። የአንዱ እግዚአብሔር ሦስት መገለጫዎች ናቸው። አያችሁ፡ አገላለጽ ነው። አባት፡ ነበረ፡ አባት ስለነበረ፡ አባት መሆን ፈለገ። ልጅም ነበረ። መንፈስ ቅዱስም ነው። አብ እና መንፈስ ቅዱስም አንድ መንፈስ ናቸው። አይታያችሁም ወይ? ገባችሁ? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—እርታዒ።] ሦስት አማልክት አይደለም። ጣኦትን በመካከላችሁ ለማድረግ ስለፈለገ፡ ዲያብሎስ የነገራችሁ ነገር ነው። አያችሁ? በሶስት መገለጫዎች የተገለጠ አንድ አምላክ ነው። አባት ለመሆን፣ አዳኝ ለመሆን፣ ልጅ ለመሆን፣ ፈዋሽ ለመሆን፣ አያችሁ፡ አገላለጡ ናቸው።

159 በቴፕ ካሴት የሚሰሙ ሰዎች ሃሳቡን በደንብ እንዲረዱት፡ ማየት እንዲችሉ የተወሰነውን እነካካዋለሁ። ካልሆነ ርእሶቹ ሁሉ፡ የየራሳቸው ሰዓት፡ ይወስዱብኛል። ይሁን እንጂ ወደምን እየመጣሁ እንደሆነ በተወሰነ መልኩ ማየት እንደቻላችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። አያችሁ?

160 እግዚአብሔር፡ "የመለኮት ሙላት በስጋ፡" አባትም፣ ልጅም፣ መንፈስ ቅዱስም፣ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ተተረከ።

161 አሁን "የመለኮት ሙሉ ሙላት በአካል" የበላይነቱ፡ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ አድሯል። አምላክ የሚያስብለው ሁሉ፡ በክርስቶስ ዘንድ አፈሰሰው፡ በክርስቶስ ውስጥ የነበረውን ሁሉ ደግሞ፡ ወደ አማኞች፡ ወደ ቤተ ክርስትያን አፈሰሰው።

162 ወደ ሐይማኖት ተቋም አይደለም! በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ወደዛ እንገባለን፡ ከአእምሮአችሁ ውስጥ ለዘለአለም ይጠፋል፡ አያችሁ፡ እርሱ ከፈቀደልን፡ በጌታ እርዳታ ያንን የሆነበት ምክንያት፡ ምን እንደሆነ አሳያቹኋለሁ።

163 አሁን ዓላማው ምንድነው? እና፡ አሁን፡ "የመለኮት ሙላት ሁሉ በእሱ በስጋው እንዲያድር፡" አያችሁ፡ ራሱን እንደ ልጅ መተረክ ነው። ቆላይስይስን፡ እዚህ በፊቴ ተከፍቶ፡ ይዣለሁ። አያችሁ? ይህም፡ በቅዱሳን መጻሕፍት፡ የእግዚአብሔር ዓላማ ያ ነበረ። ከዛ፡ በዚህ ልጅ ህይወት፡ "ስለ መስቀሉ፡" በመስቀሉ፡ "ደም፡" ይላል እዚጋ፡ አንዲት አካልን፡ ሄዋን የምትሆን፤ ሙሽሪትን፡ ሁለተኛዋን ሄዋን ለራሱ ያስታርቅ ዘንድ ነው። እግዚአብሔርም፡ በሙሴ እና በሌሎች ያደረገውን ነገር በጥላ አደረገው። የክርስቶስ እና የሙሽራዋ ጥላ መሆናቸውን ለማሳየት፡ በአዳምና በሔዋን ያደረገው ያንኑ ነበር። እሱ ሁለተኛው አዳም ሲሆን፡ ቤተ ክርስትያን ሁለተኛዋ ሄዋን ናት።

164 ዳግማዊት ሔዋንም በቃሉ ላይ እስካመቻመቸች ድረስ፣ የመጀመርያዋ ሄዋን ያደረገችው ተመሳሳይ ድርጊት አልፈጸመችምን? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—እርታዒ።] "አይ፡ ያ'ማ ለሌላ ዘመን የተነገረ ነገር ነው፡" ለማለት ትሞክራለችና። ለሌላ ዘመን ይሁን አይሁን፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ እንደርስበታለን። "ትላንትናም፣ ዛሬም፣ እስከ ለዘለአለም ያው ሆኖ ሳለ" እንዴት፡ ለሌላ ዘመን ሊሆን ይችላል?

165 እግዚአብሔር ግን አስቦ "ከአስተዋዮችና ከጥበበኞች ዓይን ሰወረው፡ አስቀድሞ ለወሰናቸው ለሕጻናት ገለጠላቸው" እንዲቀበሉት አስቀድመው የተወሰኑ ናቸውና።

166 በዘመናት ሁሉ የታየው፡ ምክንያቱ ይህ ነው፡ ያ ብርሃን ጥቂቶችን ሲነካ፡ ይቃወሙታል፡ ያሸሹታል። ታላላቅ ሊቃውንት እና ታላላቅ ካህናት ቆመው፡ ከታላላቅ መምህራን እና ከስልጣን የተውጣጡ ሊቃውንቶች፡ እንደነ ኒቆዲሞስ የመሳሰሉት፡ በትምህርት ብዛት የተወለወሉ ነበሩ፡ ይሁን እንጂ፡ ሊረዱት አልቻሉም።

167 በዚያ ቃል የተማሩ ታላላቅ ካህናት፡ እንዲሁም ራቢዎች ሁሉ በዚያ ቆመው ነበሩ። ይኸውላችሁ፡ በእውቀት ደረጃ፡ ያውቁታል! እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፡ “እናንተ ከአባታችሁ፡ ከዲያብሎስ ናችሁ፡ የእርሱ ስራም ታደርጋላችሁ።” አሰቡት፡ ቅዱሳን ሰዎች፡ በህይወታቸው፡ እና በአባቶቻቸው ህይወት፡ ወይም በአያቶቻቸው ህይወት፡ ወይም የቅድመ-ቅመ-ቅመ-ቅመ-ቅመ አያቶቻቸውን ህይወት ላይ ጣቶቻችሁ በፍጹም ልትቀሰሩባቸው የማይቻሉ ናቸው። ቢያደርጉ ግን፡ እስኪሞቱ ድረስ በድንጋይ ተወግረው፡ በውርዴት ሞት ይገደላሉ። ኢየሱስ ግን፡ የኃይማኖት ሰዎችን፡ “የዲያብሎስ መንጋ፡” ብሎ ጠራቸው።

168 አቤት፡ አሁን፡ ታላቁ መገለጥ አሁን ነው! ዋርሳነቱን ለመመለስ፡ ለማቃናት... እነዚህ፡ እንዲሰቱ ማድረግ ነበረበት። ገባችሁ? ነጻ ምርጫ እንዲኖራቸው በማድረግ፡ ሐጢአት እንዲፈጽሙ ሊያደርጋቸው ተገባው... ይሁን እንጂ ኃጢአት እንዲያደርጉ—አድርጎአቸው፡ እንዲያደርጉት ባደረጋቸው ነገርም እየቀጣቸው፡ አምላክ ሆኖ ሊቀጥል አይችልም።

169 ነገር ግን ሰውን ከራሱ ጋር አጋር እንዲሆን አደረገው፡ ሰውንም የነጻ ምርጫ ስልጣን ላይ ሆኖ እንዲያከናውን ፈቀደለት፡ አያችሁ፡ ዛሬም እናንተን የያዘበት አያያዝ ተመሳሳይ ነው። አያችሁ? አያችሁ? እናንተም ነገሮችን በወደዳችሁት መንገድ ለማድረግ፡ ነጻ የግል ፍቃድ ያላችሁ ናችሁ። ስለዚህ፡ በዚህ ምክንያት፡ በመጀመርያ ላይ እንደዛ ካደረገ፡ ሁለተኛውም ያው መሆን አለበት፡ ሌሎቹንም ሁሉ እንዲሁ፡ ካልሆነ ግን ከጅምሩ ስህተት ነበረበት ማለት ነው። አያችሁ? ሰው ሁሉ ግን በዚያ በተመሳሳይ መሠረት ላይ ነው።

170 አሁን ይህን አስተውለን፡ ያንን መልስን ሰናመጣው፡ እንደሚወድቅ እያወቀ፡ እንደሚያደርገው እያወቀ፡ ሰውዬውን እንዲሁ እንዲያደርግ አደረገው። ታድያ ምን ጠቀመው? የአዳኝነት መገለጫው አሳየበት። የዓላማው ፍጻሜ ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ አረፈ፡ ይህም... እግዚአብሄር በገዛ ሕጉ፡ ለመሞት፡ የሞት ቅጣት ለመቀበል ፈቀደ፡ ይህም እርሱን በመቃወም ጠፍታ የነበረችውን ሚስቱን ለመቤዠት ነው።

171 ሄዋን ከቃል በተለየች ጊዜ፡ ከወዳጇ ራቀች። ቤተክርስትያን ከቃል ርቃ ወደ ሐይማኖት ተቋም በሄደች ጊዜ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ስልጣን በመቃወም፡ ከአለም የሰው ጥበብ ጋራ ዝሙትን በማድረግ ተቃወመችው። ግልጽ ነው? [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።] መጽሐፍ ቅዱስ፡ “መንፈሳዊ ዝሙት አደረገች፡” ይላታል። የትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል፡ ከተቃወማችሁ፡ ወይም ግላዊ-ትርጉም ከሰጣችሁት፡ ባላችሁ የሆነውን አምላክ በመቃወም ሙሉ በሙሉ መንፈሳዊ ምንዝርናን ማድረጋችሁ ነው። አመንዝራዎች ወደ እግዚአብሄር መንግስት አይገቡም፡ ያንን እናውቃለን። አያችሁ? አሁን፡ ተመልከቱ፡ ሄዋን መጀመርያ ያደረገችው ይህ ነው።

172 አሁን እንደገና አስታውሱ፡ አሁን፡ ሶስት መአዝናዊ ዓላማው ምን ነበር? በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል፡ ወደ አካሉ ለመምጣት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ እራሱን በመተረክ፡ የበላይነቱን ማረጋገጥ ነው። (ምን? ) ጠፍቶ የነበረውን፡ ኤደን ማቃናት። ከሰርዓት ውጪ ሆኖ የነበረው ነገር ይህ ብቻ ነበርና። ሌላው ነገሮቹ ሁሉ በሰርዓት ነበሩ።

173 ሰው እንዲወድቅ ግን፡ ሰውን በነጻ ፈቃድ ስልጣን ውስጥ፡ ማስገባት ነበረበት፡ ይህም እርሱ አዳኝ ይሆን ዘንድ፡ በውስጡ የነበረው፡ አዳኝ የመሆን መገለጫውን፡ ለማሳየት። የሆነ ነገር መጥፋት ነበረበት። እናም ሰው ወድቆ የመጥፋቱ፡ ዋናው ነገር፡ የገዛ ሕጉን በመጠቀም፡ የዚያን ሰው አዳኝ ሆነ። ጽንፈ ዓለምን፡ እና ጊዜን፡ የሚሸፍን ጆሆቫ ሆኖ፡ ይሄንን ነገርን ሊፈጽም አይቻለውም። ሰው መሆን ነበረበት። ጠፍቶ ከነበረ ሰውም ዋርሳነት ተቀበለ፡ አሜን፡ ሰው ሆነ፡ አምላክ፡ ስጋ ሆነ!

174 ሃሌ ሉያ! የተገረምኩ ከመሰልኳችሁ፡ አልተገረምኩም። ውስጥዊ ነገር ነው!

175 እግዚአብሔር፡ እኔን፡ እሱን እንዲያደርገኝ፡ ሐጢአቴን ከእኔ ወደ ራሱ ለመውሰድ፡ እግዚአብሔር ከመሆን፡ እኔን ለመሆን መጣ፡ አሜን፡ ዘለአለማዊ አባት ነውና፡ ወደ ታላቁ የወንዶች እና ሴቶች ልጆቹ ዓላማ መለሰን። አያችሁ፡ መገለጫው በውስጥ ነበረ፡ ስለዚህም ወጥቶ መታየት ነበረበት።

176 ሦስት መአዝናዊ ዓላማውን ሙሉውን አሁን አይታይም? አያችሁ፡ ራሱን ለመተረክ፡ ምን መሆን ፈለገ... እንግዲህ፡ ዓለም—ስለጠፋ፡ በመስቀሉ ደም በማስታረቅ፡ አዳኝ ለመሆን፡ እራሱን በሰው መተረክ ነበረበት። እንግዲህ፡ ያ ለመሆን፡ ራሱን ወደ ቤተክርስትያን ለመመለስ፡ እንዲሁም፡ በቤተ ክርስትያኑ ላይ የበላይ ለመሆን መሞት ነበረበት።

177 የኃይማኖት ተቋም፡ አይሆንም፡ ሊሆን አይችልም፡ ፈጽሞም ሆኖም አያውቅም፡ ወደፊትም በፍጹም እንደማይሆን፡ አስታውሱ! የበላይነቱን መያዝ አለበት፡ ይህም ቃል ነው። አሜን! አዋልድ እንዴት ይቀላቀልበታል? ይህ'ማ... የሰው ቃል የሰው ሰርዓተ ኃይማኖት ተቋም እና አዋልድ መቀበል፡ ቤተ ክርስትያኒቱን አመንዝራ ያደርጋታል። ባጭሩ፡ በራእይ 17፡ እንደ ጋለሞታ እና እንደ አመንዝራዎች ተጠቅሰዋል፡ የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስትያን እንደ ጋለሞታይቱ፡ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስትያናትም እንደ አመንዝራዎቹ ናቸው። ሰው ሁሉ ማንበብ በሚችለው ልክ ግልጽ ነገር ነው። ከፈለጋችሁ የቤተክርስትያን ዘመናት እያጠናን መጥተናልና፡ በቴፖቹ ላይ—ልትመለከቱት ትችላላችሁ። በትክክል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ካለው ከኃይማኖት ሰርዓት ጋር የሚጣመር ማንኛውም ነገር፡ በእግዚአብሔር ፊት ጋለሞታ ነው። ሔዋንም ያደረገችውን ያንኑ አድርጋለች፡ ከቃል ርቃለች፡ እርሱም ክርስቶስ ነው። ኦህ፡ ማይ! በጣም ጥሩ።

178 ዓለም ሳይፈጠር ገና በሃሳቡ የደበቀውን ምስጢሩ አሁን አይተናል። እስኪ ትንሽ ከዚህ ብናነብ ምን ይመስላቹኋል? እስኪ እናንብበው። በቂ ጊዜ አላቹን? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—እርታዒ።] እንግዲያውስ—እናነበዋለን። አሁን ሁላችንም፡ ከኤፌሶን ሰዎች መጽሐፍ፡ ለማንበብ፡ እንክፈት፡ ለማንበብም፡ በ—በ1ኛው ምዕራፍ እንጀምር። እንግዲህ አሁን የስንበት

ትምህርታችን፡ በክርስቶስ ሦስት መአዝናዊ መገለጥ እየቀጠለ ባለበት፡ እሰኪ እናንብብ።

**በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ፡ ጳውሎስ፡...**

179 በዓለም ላሉት እንዳልተላከ አስተውሉ፡ ነገር ግን፤

**... በኤፌሶን ላሉት ቅዱሳን፡ በክርስቶስ ኢየሱስም ላሉት ምእመናን፤**

180 በክርስቶስ ኢየሱስ የምትሆኑት እንዴት ነው? የቤተ ክርስትያን አባል በመሆን ነውን? [ጉባኤው "አይደለም፡" አለ።—አርታዒ።] በመወለድ! "በአንድ መንፈስ፣" አንደኛ ቆሮንቶስ 12፡ "ሁላችንም አንድ አካል እንድንሆን ተጠመቃችሁ።" አያችሁ?

181 እሺ፡ የሚናገረው በውጭ ላሉ አይደለም። ለእነኚህ ለታናናሾች ነው። ኃጢአተኛን በዚ ጉዳይ ላይ ልናወራው አንችልም፡ አንዳች አያውቅምና። ጳውሎስ ይህን ጉዳይ ሐጢአተኞች አልላከውም። እሱ ያለው፡ "ይህ በ—በ—በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት" ብሎ ላከው።

**ከእግዚአብሔር ከአባታችን፡ ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ፡ ጸጋና ሰላም፡** ለእናንተ **ይሁን።**

**የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፡** እርሱም **በክርስቶስ** (በየት? ) **በሰማያዊ ሰፍራ በመንፈሳዊ በረከቶች ሁሉ የባረከን፤**

182 "በሰማያዊ ሰፍራ።" ኦ፡ ጊዜ ቢኖረኝ እንዴት ደስ ባለኝ! በሰማያዊ ሰፍራ በተመለከተ፡ ሰማያዊ ሰፍራ ምንድነው፡ እዚሁ በመጽሐፍ ቅዱሴ አሰምሬበታለሁ። **ሰማያዊ ሰፍራ፡** ማለት "በክርስቶስ ዘንድ ያለውን የአንድ አማኝ ሰፍራ፡" የሚያስረዳ ነው፡ አያችሁ፡ በሰማያዊ ሰፍራ፡ "አማኝ በክርስቶስ ዘንድ የሚጸናበት ጽናት።"

**እርሱ እንደመረጠን**... (አዳምጡ)... **ዓለም ሳይፈጠር በፊት በእርሱ መረጠን፡...**

183 መቼ ነው የመረጠን? "ዓለም ከመፈጠሩ በፊት፣" ታላቁ ምሥጢሩ፣ ታላቁ ምሥጢሩ ድብቅ በነበረ ጊዜ።

... ዓለም **ሳይፈጠር በፊት** በክርስቶስ **መረጠን፡ በእርሱ ፊት ቅዱሳንና ነውር የሌለን** (በምን? ) **በፍቅር እንሆን ዘንድ፤**

**በኢየሱስ ክርስቶስ ለራሱ ልጆች ልንሆን** (ምን አደረገን? ) **አስቀድሞ ወሰነን፡ እንደ በጎ ፈቃዱ እንደወደደ፡**

184 "አስቀድሞ ወሰነን!" ምስጥሩ ይህ ነው። እርሱ፡ ክርስቶስ ወይም ሌላ በምድር ላይ ከመኖሩ በፊት፡ ሙሽራይቱን እንደመረጠ፡ ታላቁን ምስጢሩን ታያላችሁ። ሔዋንን እንደምትወድቅ ሰላወቀ፡ ቃሉን ካለማመን፡ እንደምትወድቅ አውቋልና፡ ያኔ የማትወድቅ ሙሽራን ግን መረጠ፡ እነርሱም ሌላው ዓለም ምንም ቢናገር ምንም ቢል ቃሉን አጽንተው የሚይዙ ይሆናሉ። ቃሉን አጥብቀው

ይይዛሉ! በዚያ ለመጽናት "በኢየሱስ ክርስቶስ ልጆች ለመሆን፡" አስቀድመው ተወስኗል፡ ቤተ ክርስቲያንን፡ ታላቅ ክብር ላለው ለዚያ መጽናት ወስናት!

185 አሁን ምስጢሩን አይታችሁታል? ምን ለማድረግ ነው? የቤተ ክርስቲያኗ ምሳሌ እንደመሆኗ መጠን፡ የወደቀችው ሔዋን ለማቃናት ነው። አሁንም አስተውሉ፡ አምላክ የአዳምን ጎን ከፍቶ፡ ከአዳም ስጋ እና ደም ሄዋንን እንዳወጣ፥ መንፈሱን ከወንዳዊ እና ሴታዊ አላቆ ሴትን አወጣና፡ በሄዋን ውስጥ አስቀመጠው። ከጎኑም አጥንትን በመውሰድ፡ ሄዋንን አበጃት፡ እግዚአብሔር አምላክም እንዲሁ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጎን፡ ደም እና ውሃን ወሰደ። ክርስቶስም ቃል ነው፡ ቃሉን በመውሰድ ቤተ ክርስትያንን፡ ሄዋንን ሰራ፡ እያችሁ፡ ከአካሉ በፈሰሰው ደም፡ ወደ ራሱ መለሳት። እያችሁት አሁን? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።]

186 ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ተሰውሮ የነበረውን፡ አስቀድሞም እስከ ፍጻሜ ድረስ በጥላ ያሳየውን፡ የእግዚአብሔር ታላቅ ምስጢር አሁን ተከፈተ። አሁን ተከታተሉ፡ እንዲህ—እንዳደረገ፡ አሁን ተገንዝበናል። በኤፌሶን፡ እንዲሁም በተለያዩ ቦታዎች እናገኘዋለን፡ ያ በቂ ነገር ይሰጣችኋል... አሁን፣ በዘመናት ውስጥ፣ ይህንን ምስጢር በዝግታ ሲገልጥ ቆይቷል። አሁን እያችሁት? አሁን፡ እዚህ ድረስ...

187 ምን አደረገ... ? ወደፊት በሚያሳየው ስእላዊው መገለጫ እንዴት ነበር? የአዳምን ጎን ከፈተውና፡ ሄዋንን የሚሰራበት የአዳም ስጋ፡ አንድን ክፍል ወሰደ። እርሱ ቃል ስለሆነ፡ ሙሽራይቱም ቃል መሆን አለባት። በሰርዓቶች ላይ መመስረት አትችልም። በኃይማኖት ተቋም ላይ መመስረት አትችልም። በመልካም ባህርይ ላይ ልትመሰረት አትችልም። ከቃሉ ጋር ብቻዋ የጸናች ልትሆን ይገባታል፡ የቃሉ አካል ናትና። የተገኘችውም ከክርቶስ ነውና። እያችሁ?

188 ንጥቀቱ፡ ሙሉውን እርግጥ ለማድረግም፡ ሉተር ተካፋይ ነበር፡ ዌስሊም ተካፋይ ነበረ፣ ነብያት ሁሉ ተካፋዮች ነበሩ። ተካፋዮች—ካልሆኑ'ማ... ይህ ሁሉ በሚሰራበት በመገለጡ የአካሉ ሙላት በመሆን፡ አካል፡ እግር፡ ጣቶች፡ እጆች፡ ወዘተ፡ እስከ ራስ ድረስ (በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ እናየዋለን)፡ እያችሁ፡ ንጥቀቱ ሙሉ የሚያደርጉት እነዚህ ናቸው። የቃሉ፡ ማለትም የክርስቶስ አካል ነው። አሜን!

189 ከዛ ውጪ፡ ጠፍታችኋል። ምን ዓይነት ሕብረት እንደሆናችሁ፡ ምን ዓይነት የኃይማኖት ድርጅት መሆናችሁ፡ እና ምን ዓይነት ግኑኝነት እንዳላችሁ አያገባኝም፡ ቃሉ በእናንተ ውስጥ ከሌለ፡ ጠፍታቿል።

190 "በእኔ ብትኖሩ፡ ቃሌም፡ ማለት ቃል በእናንተ ቢኖር፡ የምትሹትን ትጠይቃላችሁ፡" ምክንያቱ እናንተ እና ቃሉ አንድ ስለሆናችሁ። እሱ እራሱ የበላይ ሆኗል። መሪነቱን እርሱ ተቆጣጥሯል። እናንተም—እስረኞቹ ናችሁ። ዓለም ሞታባችኋለች። የቀረ ነገር የላችሁም... ሰዎች ሁሉ በተመቻቸው መንገድ ነገሮችን ያደርጋሉ፡ እናንተ ግን ማድረግ አትችሉም። እስረኞች ናችሁና። ቀንበሩ ተጠምዶባችኋል። "ቀንበሬም ቀሊል ነው።" ከክርስቶስ ጋር በቃሉ ቀንበር ተጠመዳችሁ። "አባትን የሚያስደስተው ብቻ... አደርጋለሁ። እኔ እሱ እንደሆንኩ ባታምኑ፡ እንግድያውስ ቃሉን እመኑ።" እጅግ ግልጽ! አስተውሉ።

191 አሁን አስተውሉ፡ ባለፉት ዘመናት ሁሉ፡ ቀስ በቀስ ይሄን እየለቀቀ ቆይቷል፡ ሚስጢራቱን በነብያት እና በጥላዎች፡ ቀስ በቀስ እየከፈተ ነበር። አሁን ወደዚያ አልፈን፡ ራሱን ወደ መተረክ፡ መሄድ እንችላለን።

192 ራሱን በሙሴ ተረከ። ሙሴን ተመልከቱት። የህጻናት ስደት በነበረበት ዘመን ተወለደ። ነጻ አውጪ ለመሆን ተወለደ። ኢየሱስ ወደ ግብጽ እንዳሸሹት፡ ሙሴንም በቄጤማ ውስጥ ሸሸጉት። ከዚያም መጣ። ወደ ተራራውም ወጣና፡ ትዕዛዛትን ይዞ ወረደ።

193 ኢየሱስም ወደ ተራራው ወጣ፡ የመጀመርያውም ስብከቱ፡ የተራራው ስብከት ሰበከ፡ ትዕዛዛትም ይዞ ወረደ። "የዱሮዎቹ፡ 'አታመንዝር፡' ሲሉ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፡ ወደ ሴት ያየ ሁሉ፡ የተመኛትም፡ ያመነዝራል።" ሕግ-ሰጭ፣ ካህን፣ ንጉስ፣ መሪ፣ በትክክል ነው።

194 በኃይማኖት ተቋማት መካከል፡ ማለት በወንድሞቹ መካከል በተወለደው ዮሴፍም፡ ራሱን ተርኳል። መንፈሳዊ ሰለ ነበረ፡ እግዚአብሔር ከሱ ጋር ስለነበረ። ራእዮችን ያያልና። ያለ ምክንያት፡ ጠሉት። ሕልሞችን ይፈታል። ስለዚህም ወንድሞቹ ጠሉት። በገዛ ወንድሞቹ-... በሚቀራረብ ዋጋ፡ በሠላሳ ብር ያህል ተሸጠ። ከወንድሞቹ አንዱ በሆነው፡ በአስቆሮቱ ይሁዳ፡ በሠላሳ ብር እንደተሸጠው ነው። እንዲሞት ወደ ጉድጓድ ተጣለ። አዎን። አባትየው እና ሌሎቻቸው መሞቱ ተነገራቸው። ከተወረወረበት ጉድጓድ፡ ወጥቶ፡ ወደ ፈርኦን ቀኝ ተወሰደ።

195 በእስር ቤት ውስጥ፡ በጣም ተሰቃየ! ከእርሱም—ጋር ሁለት ነበሩ... ጠጅ አሳላፊ እና ጋጋሪው። አንደኛው ዳነ፡ ሌላኛው ግን ጠፋ አልዳነም። ጠጅ አሳላፊው—ከሁለቱ አንዱ ጠፋ... አንደኛው ግን ዳነ። በመስቀል ላይ፡ በእስር ቤት በነበረ ጊዜ፡ ሰለ ኃጢአታችን በመሰቀል ላይ እንደተጠረቀ፡ እሰረኛ ሆነ፡ አንዱ ሌባ ጠፋ አንዱም ዳነ። አያችሁ፡ በትክክል።

196 በህልም ባየው ንጉሥ ፊት፡ በፈርዖን ቀኝ ሆነ። በንጉሡም እግር ሥር እንደሚቆም ራእይ አይቶ ነበርና፡ በግብፅም ያለውን ሥልጣን ሁሉ ተሰጠው። ህልሙ መፈጸሙ ግድ ነበረ። ገና በ—በእስራት በነበረ ጊዜ፡ ደጋግሞ፡ ተመራምሮበት ሊሆን ይችላል። ጢሙ አድጎ፡ ሌላ ሌላም ይሆናል፡ እርሱ ግን ተመራመረበት። አንድ ቀን ራእዩ እውን መሆን ነበረበት።

197 ቢዘገይም፡ መፈጸም ነበረበት! ትላንና ማታ፡ ወይም ከትላንትና ወዲያ ማታ፡ እሮብ ማታ ላይ በጉባኤው ላይ ተናግሬአለሁ። አያችሁ፡ መፈጸሙ አይቀርም። እግዚአብሔር ከተናገረ፡ ይሆናል። የተረጋገጠ ነብይ ስለሆነ፡ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነም፡ ይፈጸማል።

198 ቃል የሚመጣው ወደ ነቢዩ ብቻ ነው። **ነብይ** የሚለው ቃል ትርጓሜው "የተጻፈውን መለኮታዊ ቃል የሚገልጥ ማለት ነው፡" አያችሁ፡ "የወደፊቱን ነጋሪ" ወይም "ባለ ራዕይ፡" እንደ ማለት ነው። አስተውሉ። ይህም፡ ባለ ራዕይ፡ እንደምታውቁት የወደፊቱን የሚናገረው፡ አስቀድሞ በማየቱ እና ያየው ነገር በመፈጸሙ፡ መለኮታዊ ማረጋገጫ ያለው ሰው ነው። "አንድ ነብይ ቢኖር፡ እንዲህ እና እንዲያ ይሆናል ብሎ ይነግራችኋል። ያለው ካልተፈጸመ፡ እርሱን አትስሙት። ከተፈጸመ ግን እኔ ከእርሱ ጋር ነኝ። እኔ ከእርሱ ጋር ነኝና፡ ፍሩት፡

እያችሁ።” ትክክል ነው። እውነት መሆኑን ወይም አለመሆኑን የምታውቁበት ማሳያው፡ ይህ ነው።

199 እግዚአብሔር አምላክ ለህዝቡ፡ በሰዎች አልፎ፡ ቃሉን ይናገራቸዋል። አያችሁ፡ እግዚአብሔር በሰው ይናገራል። “እኔ የወይን ግንድ ነኝ፡ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ።” ግንዱ ፍሬ አያፈራም። ቅርንጫፎች ግን ይናገራሉ፡ ከግንዱ ፍሬን ያፈራሉ። አያችሁ፡ ሁሌም እንደዛው ነው።

200 ዮሴፍን ያየነው እንደሆነ፡ ያኔ፡ አስቀድሞ ዮሴፍን ሳያይ ወደ ፈርኦን መግባት ወይም መንካት የሚችል ማንም ሰው አልነበረም። “በልጁ ካልሆነ በቀር፡ ወደ አብ መምጣት የሚቻለው ሰው የለም።” ዮሴፍ ከዙፋን ሲነሣ፡ መለከት እየነፉ “ጉልበት ሁሉ ይንበርከክ! ዮሴፍ እያለፈ ነው!” ይባላል፡

201 ክብር ይሁን! አንድ ቀንም፡ የአባቱን ዙፋን ትቶ ሲወርድ፡ ጉልበት ሁሉ ይንበረከካል፡ አያችሁ፡ ምላስም ሁሉ ይመሰክራል። እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ሁሉም ይመሰክራል። እናንተም... አሁን መስክሩ። ያኔ ይረፍድባችኋል።

202 አሁን ቀደም ብዬ እንዳልኩት፡ በጥላዎች ዳዊትንም ልንወስድ እንደምንችል አስተውለናል፡ በገዛ ወገኖቹ ስለተጠላ፡ ከዙፋኑ ወርዶ፡ ወደሚታሰርበት፡ ተራራ፡ ወደ ደብረዘይት ተራራ ወጣ። ወደ እስር ቤቱ የሄደው በወንድሞቹና በገዛ ወገኖቹ ስለተጣለ ነው። እያለቀሰ፡ ወደ ላይ ወጣ። በእሱ ውስጥ የነበረውን፡ ሊገፋ የተገባውን የክርስቶስ መንፈስ፡ ኢየሩሳሌምን ሲመለከታት አለቀሰላት፡ እንዲህም አለ፡ “ኢየሩሳሌም ሆይ፡ እኔ ብዙ ጊዜ... ” የተገፋ ንጉስ። ከሰምንት መቶ ዓመት በኋላ፡ የዳዊት ልጅ በኢየሩሳሌም ተገኝቶ፡ በኢየሩሳሌም ላይ ቆመ፡ ተገፋም፡ ሰለ ኢየሩሳሌምም እያለቀሰ፡ እንዲህ አለ፦ “አሁን ግን ሰዓትሽ መጥቷል።” እውነት ነው። አያችሁ?

203 እነዚህ ጥላዎች ሁሉ፡ በምሳሌ ደረጃ ሰለሱ ይናገራሉ፡ ምስጢሩ ግን ተሰውሮ ነበር። እነዛ ሰዎች የሚያደርጉትን አያውቁም ነበር። የሚያውቁት እነዚህን ነገሮች ለማድረግ በመንፈስ መመራታቸው ብቻ ነው። አሁን፡ ለታላቁ መገለጥ፡ ሰለ መጨረሻው ቀን የታቆረ ነበርና። ይሁን እንጂ፡ እየተረከ ነበር፡ እራሱን በሙሴ፣ በዳዊት፣ በዮሴፍ፣ በኤልያስ፣ እና በሌሎች ሁሉ ተርኳል። እንደው... እነዚያን ነብያቶች ለምሳሌ መውሰድ እንችላለን፡ ሕይወታቸውን በኢየሱስ ክርስቶስ፡ በትክክል መተረኩን ማውጣት እንችላለን። ሆኖም፡ ምስጢሩን በሙላት ገልጦ አያውቅም፡ እንደ ተሰፋ ቃሉ በዘመን ፍጻሜ እንዲታወቅ ወዷልና፡ እርሱ ከመተረኩ በፊት፡ አያችሁ፡ ሙሉ ለሙሉ መረዳት እንዲቻል ነው። ሙሉውን ነገር ቢዘረግፈው ኖሮ...

204 መጽሓፍ ቅዱስ፡ በምስጢር የተጻፈ መጽሐፍ ሰለሆነ። በምስጢር ስለተጻፈ፡ አያችሁ፡ ኢየሱስ አባትን አመሰገነ።

205 የጌታ መምጣትም፡ በምስጢር ነው። መቼ እንደሚመጣ፡ እንዴት እንደሚመጣ የምናውቀው ነገር የለንም፡ ይሁን እንጂ እንደሚመጣ እናውቃለን። አያችሁ? የእግዚአብሔር ምስጢሮች ሁሉ ይህ መጨረሻው ዘመንን ሲጠባበቁ ነበር። ሌላው ከተጠናቀቀ በኋላ፡ እሱ ደግሞ ይገለጣል ያደረገው ሁሉም ያሳያል። ኦህ፡ ማይ! በጭራሽ ሙሉ ምስጢሩን ሰጥቶ አያውቅም።

206 ከሰባት ማህተሞች ጋር ሲነፃፀር፡ ልክ እንደዚህ ነው። እንግዲህ፣ እግዚአብሔር ለዚያች የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ወይም ያቺን ቤተ ክርስቲያን ዘመን ለመውጣት ማርቲን ሉተርን ሲጠቀም፣ ጆን ዌስሊን በተጠቀመ ጊዜ፡ ቀስ በቀስ ወደ ውጭ አወጣቸው፡ በእነርሱ ውስጥም ያንን የቤተክርስቲያን ዘመን እየገለጠ ነበር። እንደው... አሁን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መለስ ስንል እናየዋለን። በመጨረሻው ዘመን፡ ይህ ታላቅ ነገር የሆነበት ምክንያት ግን፡ እርሱ ይህን እዚህ ተናግሮ እነዚያን ሰባት ነጎድጓዶች አሳይቷል። እና **ላይፍ** መጽሔት ላይ **እዩት-**...

207 ያኔ **ላይፍ** መጽሔት እስከአሁን ድረስ ያላወቁትን ሊረዱት የማይችሉትን፡ ክቡ ደመና እና ያንን ብርሃን አወጡት። እዚህ ግን ከመከሰቱ ከወራት በፊት፡ "ወደዚያ ሂድና እነዚህ ምስጢራት እስኪገለጡ ድረስ ጠብቅ፡" ብሎ ተናገረን፡ ከዚያም አደርገዋለሁ ባለው መንገድ እንዲሁ ሆነ። በሥዕሉ ላይ አስተውላችኋል? በቀኝ በኩል የነበረው ያ መልአክ፡ ተገናጽፎ፡ ሲወርድ፡ ክንፎቹ ወደ ኋላ ራሱንም ወደ ጎን ዘምበል አርጎ ነበር፡ ይሄው ስዕሉ **ላይ**፡ በትክክል ይታያል። ይህ ከመሆኑ ከወራት በፊት፡ እዚህ ተነግሮን ነበር፡ ይህም፡ "ተላቅቀው የነበሩትን፡ የአማኞች አካል አንድ ለማድረግ፡ ለመግለጥ ነው።"

208 ሉተር በዘመኑ መጣ፡ ጽድቅን ብቻ እየሰበከ፡ በዘመኑ በደንብ ዘመተ። ዘመኑ ምን እንደነበረ አያውቅም ነበር። ዌስሊም እንዲሁ መጣ፡ የዘመኑ ብቻ ዘመተ። አያችሁ? ከእሱም ብዙ ጎረፉ፡ ሌሎች አብያተ ክርስትያናት ተነሱ። በዚያን ጊዜ ጴንጤቆስጤ፡ መጥተው ዘመቱ፡ እነርሱም ተደራጅተው እንደገና ወደ ሞት ቸኮሉ፡ በጥቂት ደቂቃዎች እንደምናየው፡ በቀጥታ ወደ "ሞት" ተመለሱ።

209 ከዛ በኋላ ይህ ሁሉ ምን ማለት እንደነበረ የሚገልጥ፡ የምስጢሩ መገለጥ መጣ። የመጡትንም፡ ትንንሽ አስተምህሮዎች፡ ሉተር እንዳመጣው ካቴኪዝም እና ሌላ ሌላ ነገሮች፡ ዌስሊም ያመጣቸው **ይህ፡ ያ፡** እና **ሌላው፡** እንዲሁም ሌሎች ነገሮች፡ ጴንጤቆስጤዎችም ድርጅታዊነትን እና መሳይ ነገሮች፡ እና "የአባት፣ ልጅ፣ መንፈስ ቅዱስ" ጥምቀት፡ ወዘተረፈ አስገቡ፡ ልዩነት እንዳለው ሳያውቁ ነው፡ ምክንያቱ... ከዚያም በመጨረሻው ቀን መጥቶ ምስጢራት ሁሉ አነሣቸውና በግልጥ አብራራቸው፡ ገለጣቸው። ለምን? እግዚአብሔር በልቡ ያለው ይህ ታላቅ ምስጢር የሚገለጥበት የመጨረሻው ዘመን ነውና።

210 ገብቷችኋል? [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—አርታዒ።] ካልገባችሁ፡ እንደገና ቴፑን ስሙት። ለምን ያህል ጊዜ ከእናንተ ጋር እንደምቆይ እኔ አላውቅም። አስታውሱ፡ ይህ እውነት ነው፡ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል ነው።** እውነቱ ይህ ነው። ቅዱስ ቃል ነው።

211 እንደ መጨረሻዎቹ የሰባቱ ማህተማት ሰባት ምስጢራት፡ ምስጢሮቻቸው። ማኅተሞቹ ተከፍተው፡ እያንዳንዱ ዘመን ታይተው አልፈዋል፣ እነርሱ በታትነዋቸው ያለፉት ብዙ ነገሮች ነበሩ። እግዚአብሔርም እንዲበታተን ባለመውደዱ፡ ተመልሶ መጥቶ እነዚያን የጀመሩዋቸውን ትምህርቶች፡ ከወዳደቁበት ለቀማቸው፡ አውጥቶም ሁሉንም ነገር ገለጠ። እሱ ለቤተ ክርስቲያን እንዴት የእግዚአብሔር ሦስት መአዝናዊ ዓላማ እንደነበረ፡

የክርስቶስን ምሥጢር በመግለጥ፡ አሁንም ተመሳሳይ ነገር እያደረገ ይገኛል! ኦህ፡ ማይ! እንዲታይ እያደረገው ይገኛል። እንዲገለጥ!

212 ስለ **መግለጥ፡** ዌብስተር ሲተረጉመው፡ "እንዲታወቅ ማድረግ። ማለት፡ እንዲታወቅ ማድረግ፡" ዌብስተር ሲናገር፡ በተለይ፡ "በመለኮታዊ እውነት" ይላል፡ **መገለጥ** ማለት ያ ነው። መገለጥ፡ ክርስቶስ ራሱን ለቤተክርስቲያኑ የሚያሳውቅበት መንገድ ነው።

213 ምናልባት አሁን "አሁን፡ ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ አንተ ዝም ብለህ አልክ፡" ልንል እንችላለን። ስለ ማለት፡ ዝም **ብለን**፡ አንልም።

214 እንግዲህ አስተውሉ፡ ራሱን ለጴጥሮስ ገለጠለት። ይሄን መጻፍ ከፈለጋችሁ፡ እኛም... ለማንበብ ከፈለጋችሁ፡ እና—እናነበዋለን፡ ማንበብን ከፈለጋችሁ እናነበዋለን፡ ከማቴዎስ 16:15 እና 17። እጠቅሳለሁ። ከተራራው በወረዱ ጊዜ፡ እንዲህ አላቸው፡ "ሰዎች እኔን የሰው ልጅን ማን ነው ይሉኛል? "

215 "ኦህ፡ አንዳንዶቹ፡ 'ኤልያስ' እንደሆንክ ያስባሉ፣ አንዳንዶቹም 'ከነብያት አንዱ፡' 'ኤርሚያስ፡' ወይም ሌላ ነው ይሉሃል።" የጠየቀው ግን ይህ አልነበረም።

216 እንዲህ አላቸው፡- "እናንተስ ማን እንደሆንኩ ትላላችሁ? " እየተናገረ ያለው ለቤተ ክርስትያን ነው። አያችሁ?

"ሰዎች ማን ነው ብለው ያስባሉ? "

217 ዛሬ ዛሬ፡ "የማሕበረሰባዊ ሐይማኖት፡ ፈላስፋ ነበረ። ደግ ሰው ነበረ። ትምህርቶቹ ትክክል እንደሆኑ እናምናለን ይላሉ። መኖር ያለበት ጉዳይ ነው። ብንኖርበት፡ የተሻሉ ያደርገናል ብለን እናሰባለን ይላሉ። የየራሳችን ቸርች ይኑረን፡ የ—የራሳችን ነገሮች።" እንደ ሳንታ ክላውስ፡ እንደ ሳንታ ክላውስ ታሪክ ነው።

218 የምንተርከው የቤተ ክርስትያን ትርክት አይደለም። ይህ ህይወት ራሱ ወደ እናንተ መጥቶ በራሱ የሚኖረው እንጂ፡ እናንተ የማትኖሩት ህይወት ነው፡ እናንተም፡ ለሰዋዊ ጽንስ ሐሳቦች ሁሉ ፍጹም እስረኛ ትሆናላችሁ። በመንፈስ ትመራላችሁ። እንዴት ታውቀዋለህ?

219 አሁን እናንተ፡ እንዲህ ትሉኛላችሁ፡- "እያወቀ አይምሮውን እየሳተ ነው። ይሁን ምንልባት ይሄን የሚያደርግ አእምሮ የሳተ ሰው ይሆን ይሆናል።"

220 የክርስቶስ ልብ ካላችሁ ግን፡ ክርስቶስ በእናንተ በኩል ስለ ራሱ፡ እሱ መሆኑን እና... እናንተም አእምሮአችሁ እንዳልሳታችሁ ያሳያል።

221 አንዳንድ ሰዎች፡ በነገሮች ቅዠት፡ ወደ ውጭ ወጥተው ያብዳሉ። አዎን፡ ያ፡ ስህተት እንደሆነ እናውቃለን። እውነተኛውን ነገር ከመምጣቱ በፊት ዲያብሎስ የሚያስመስለው ነገር አለ፡ አያችሁ፡ ሁሌም ፎርጂድ ነው። አያችሁ?

222 እውነተኛ ሰው ግን የራሱን አሳብ እና አስተሳሰብ ለማጣት! እንደዚያ በጭፍን አይመጣም። ኖ፡ ሰር። እስከነ ትክክለኛ ሰሜትህ ትመጣለህ፡ ክርስቶስ ይረከብሃል ከዚያ እራሱን ይተርካል። ከእንግዲህ ወዲያ፡ ለዓለም እብድ ሰው ናችሁ።

223 እንግዲያውስ፡ አብዶች ከሆናችሁ፡ አብዳችኋላ፡ የቀረ ነገር የለም… ዲያብሎስ ሊቆጣጠራችሁ አይችልም። ከዚህ ቃል ጋር የሚቃረን ነገር ሁሉ እንድታደርጉ ያደርጋችኋል።

224 ክርስቶስ ሲረከብህ ግን፡ እርሱ ቃል ነውና፡ እሱ ራሱ ያን ቃል በአንተ በኩል ይተርከዋል። እሱ ቃል ነው! አያችሁ? እና ከዚያ ክርስቶስ ሲተረክ ማየት ትችላላችሁ። የሆነ ዓይነት ቅዠት ሳይሆን፡ እውነተኛ እና ትክክለኛ ክርስቶስ በእናንተ በኩል ራሱን የሚገልጽ ይሆናል። እንዴት ድንቅ ነው!

225 እንግዲህ አስተውሉ፡ እየጠየቀ ያለው ቤተክርስትያኑን ነው፡ አስራ ሁለቱን "ማን ነው ትሉኛላችሁ?" ይላቸዋል። በዚያ ዘመን ከነበሩት ከሚሊዮኖች መካከል፡ አስራ ሁለቱን፡ ማለት ቤተክርስቲያኑን ጠየቃት።

በኖህ ዘመን ከነበሩ ከሚሊዮን መካከል፣ ስምንቱን ጠየቃቸው። ኧረ-እህ። አያችሁ?

226 እርሱም፡ "በኖኅ ዘመን እንደ ሆነ፡ የሰው ልጅ ሲመጣም እንዲሁ ይሆናል አላቸው፡ ተመልከቱ፡ ስምንት ነፍሳት የዳኑበት ነው።"

227 በስህተት እንዳትረዱኝ። ስምንት ነፍስ ብቻ ይድናል አላልኩም። በፍጹም ብየ አላውቅም። ጥቂት አባላት ባሉባት፡ የመጨረሻዋ፡ የንጥቀት ዕለት——ስንቶች እንደሚድኑ… እኔ አላውቅም። ግን እላችኋለሁ፡ ጥቂት ሰዎች ብቻ ይሆናሉ። "ደጁ ጠባብ፡ መንገዱም ጠባብ ነውና፡ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።"

228 ነገር ግን በየዘመናት ውስጥ የነበረው ታላቁ የተቤዠ አካል ሲገለጡ፣ ያኔ በዚያ ታላቅ ዙፋን ይሆናል! ራእይ ዮሃንስ 7 ሲገልጻቸው፡ "ማንም ሊቆጥራቸው የማይቻላቸው ብዙ ህዝብ፡" በተገለጠላቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ብርሃን የተመላለሱትን ሁሉ፡ ከየዘመኑ ሁሉ ተውጣጥተዋል። የዌስሊ ብርሃን ከሉተር የበለጠ እንደነበረ እናውቃለን። የጴንጤቆስጤም፡ ከዌስሊ የበለጠ እንደሆነ እናውቃለን። አያችሁ? በትክክል፡ ይበልጠዋል።

229 ምክንያቱ፡ በነቢያቱ በኩል እና የመሳሰሉት በኩል፡ ቀስ በቀስ ወረደ፡ ይህም "መለኮት በአካል በክርስቶስ፡" ሙሉ በሙሉ እስኪታወቅ ድረስ ነው።

230 እና አሁን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ክርስቶስ ገና እየተነገረ ነው። ነገሩ ሁሉ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው፣ ከባሏ ጋር እንደገና ወደ ትክክለኛው ቦታዋ እንድትመልሰ ሔዋንን መውሰድ ነው። አስተውሉ፣ እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን ባል ነው፣ ቤተ ክርስቲያንም ሙሽራው ነች።

231 አሁን፡ ጴጥሮስም፡ ሲጠራ፡ "አንተ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ፡" አለው።

232 አሁን ተከታተሉ። "**የዮና-ልጅ፡** ስምኦን ሆይ ብጹዕ ነህ፡" አለው፡ ማለት፡ (የዮና ልጅ።) አያችሁ? "ይህን ስጋ እና ደም አልገለጠልህምና፡ ብጹእ ነህ። ከማንም ትምህርት ቤት አልተማርከውምና። በሰማያት ያለው አባቴ ገልጦልሃል እንጂ።" የተናገረውን አስተውሉ፡ "በዚህ አለት ላይ… " እሱ'ማ ይህንን ብርሃን የበራለት፡ የመንግስቱን ቁልፎች የተሰጠው ቀድሞ የተወሰነው የእግዚአብሔር ዘር የሆነው፡ ጴጥሮስ ነው። "ኢየሱስ ክርስቶስ ማን እንደ ሆነ በሚገለጥበት በዚህ ዓለት ላይ፡" እርሱ በሙላት የተገለጠ፡ እግዚአብሔር

አምላክ ራሱ ነው። "በዚህች አለት ላይ... " ሁለተኛው አካል ሆኖ የተገለጠ፡ አባት፣ ልጅ፣ መንፈስ ቅዱስ ላይ አይደለም። "በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራታለሁ፣ የገሃነም ደጆችም ፈጽሞ አያይሏትም፣ በፍጹም አያሸንፉአትም።" አያችሁ? "በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ" የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ላይ።

233 ተመልከቱ፡ ክርስቶስ በእናንተ መሆኑ እርሱን የመገለጥ ህይወት ማእከል ያደርገዋል። አያችሁ? የክርስቶስ ህይወት በእናንተ ዘንድ መሆኑ እርሱ የመገለጥ ማእከል እንዲሆን ያደርጋል። ክርስቶስ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘንድ መሆኑ፣ መጽሐፍ ቅዱስን የክርስቶስ ሙሉ መገለጥ አድርጎታል። ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ እናንተን እግዚአብሔር ሊያደርገው የሚፈልገውን ሁሉ፡ የመገለጡ ሙላት ያደርጋችኋል፡ አያችሁ።

234 ታዲያ አዲስ ልደት ምን ማለት ነው? ትሉኛላችሁ፡ "ንገረን፣ ወንድም ብራንሃም ሆይ፣ አዲሱ ልደት ምንድን ነው? " በእናንተ ዘንድ የኢየሱስ ክርስቶስ በግል መገለጥ ነው። አሜን! አያችሁ? የቤተ ክርስትያን አባል በመሆናችሁ፣ እጅ በመጨባበጣችሁ፣ የተለየ ነገር በማድረጋችሁ፣ ስርዓተ ሐይማኖት በመድገማችሁ፡ እኖርበታለሁ በማለት ቃል በገባችኋቸው—ሕጎች አይደለም። ነገር ግን ለእናንተ የተገለጠው ቃል፡ ክርስቶስ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ማንም ምንም ቢናገር፡ ምንም ቢሰራ፡ ፓስተር፡ ቄስ፡ ሌላው ሁሉ ምንም ቢሆን፡ ዋናው ክርስቶስ ነው። ቤተ ክርስትያን የተገነባችበት ያ መገለጥ፡ ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው።

235 "እኔ'ማ፡ ሉተራን ነኝ። እኔ ባፕቲስት ነኝ። እኔስ ፕሪስባይቴርያን ነኝ፡" ትላላችሁ። ያ በእግዚአብሔር አምላክ ዘንድ [ወንድም ብራንሃም በጣቶቹ አንቃጨለ—አርታዒ።] ዋጋቢስ ነው፡ ዋጋ የለውም፡ ጣታችሁን ማንቃጨልም አያክልም።

236 ታዲያ ምንድነው? ክርስቶስ እሱም መገለጡ ነው፡ እርሱም ቃል ነው። ቃሉ ሲገለጥ፡ ራሱን በራሱ ይተረካል። አያችሁ? ለኢየሱስ ክርስቶስ የነበረው የእግዚአብሔር አላማ፡ ራሱን መተረክ ነበር፡ የራሱን ህግ ወሰዶ በገዛ ህጎቹ በመኖር፡ ኰነ-... በሞትም፡ የገዛ ሕጉን ፈጸመ። ክርስቶስም፡ እግዚአብሔር፡ በሥጋ ሞተ በሥጋ፡ ይህም ኃጢአትን በስጋ ይኰንን ዘንድ፡ በእግዚአብሔር ቃል ብቻ የምታምን፡ ዳግም የተዋጀችውን፡ ክብርት ሙሽራ ለራሱ ያመጣ ዘንድ ነው፡ እሷም እንደ ሔዋን ለሰው ልጅ ምሁራዊ ፅንሰ ሀሳቦች፡ የማትገዛ ትሆናለች። አያችሁ? የክርስቶስ አሳብ ይህ ነው። የእግዚአብሔር አሳብ ይህ ነው። አዲሱ ልደት ይህንን ይገልጣል።

237 ሰውም ዳግመኛ ተወልጃለሁ ካለ፡ እነዚህን የመጨረሻ ዘመን የክርስቶስ ተስፋዎች፡ ለሌላ ዘመን ሊተካቸው ከከጀለ፡ ክርስቶስ የትናንትና ብቻ እንጂ የዛሬ እንዳልሆነ ካደረገው፡ ያ ሰው ወይም ያ አካል—በሰይጣን ማታለል የሚኖር ነው። ያ ሰው ይህን አምናለሁ እያለ፡ በእርሱም ይህ ካልተተረከ?

238 ኢየሱስ በማርቆስ 16፡ "ወደ ዓለም ሁሉ፡ ወደ እያንዳንዱ ዘመን ሂዱ፡ ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፡" ብሏልና። አጋንንትን እንዲያወጡ፡ በልሳን እንዲናገሩ፡ እና—እናም፡ እነዚህ ሁሉ ታላላቅ የሰጦታዎች መገለጫዎች እንዲከተሏቸው "ወደፊት ይከተሏቸዋል!" "**ምናልባት**፡

ሊከተላቸው **ይችላሉ**፡” አይደለም። “በርግጥ ይከተሏቸዋል!” ቃሉ ከሚያልፍ፡ ሰማይ ኣና ምድር ቢያልፍ ይቀላል።

239 በግለሰቡ ላይ ራሱን እየተረከ ያለው ክርስቶስ ነው፡ በምሁር ሰውም ይሁን—ወይም ሀሁ ባልቆጠረ ሰው ራሱን ይተርካል። ግማሾቹ ሐዋርያት ያልተማሩ ሰዎች ነበሩ፡ ክርስቶስን ግን ያውቁት ነበር፡ በትክክል። ከአንዳንድ ሴሚናሮች እንደወጡ አሰበው፡ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ከቁብ አልቆጠሯቸውም። እንዲህ አሉ፡ “ከክርስቶስ ጋር እንደነበሩ ልብ ብለዋቸዋል፡” በደጅ የነበረውን፡ አንካሳ ሲፈውሱ፡ አያችሁ። ከክርስቶስ ጋር የነበሩ እንደሆኑ—አውቀዋቸዋልና።

240 አዲሱ ልደት ክርስቶስ ነው፡ መገለጥ ነው። እግዚአብሔር ይህን ታላቅ ምስጢር ለእናንተ ገልጦታል፡ አዲስ ልደት ያ ነው። ያ ቡድን ሁሉ በአንድነት ተሰብስቦ ባያችሁ ጊዜስ ምን ታደርጉ ይሆን? መገለጡ ፍጹም በሆነ አንድነት ሲቀናጅ፡ እግዚአብሔር አምላክም በቃሉ በተመሳሳይ አሰራሩ ይተርካል፡ ያኔ ያደረጋቸው ተመሳሳይ አሰራሮች፡ ቃሉ እንዲተረክ ያደርጋሉ። አቤት፡ ቤተ ክርስቲያን አቋሟን ብታውቅ ኖሮ! አንድ ቀን ግን፡ ይሆናል። ያኔ፡ ምን እንደሆነ ስታውቁት ንጥቀት ይሆናል። አሁን አስተውሉ።

241 “አይደለም—ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ያኮ... ” ትሉ ይሆናል፡ ኦህ፡ የሰ፡ ይሄኛውም፡ ያው ነው። እውነቱ ይህ ነው።

242 አስተውላችኋል? ጳውሎስ፡ ኢየሱስን በስጋ አያውቀውም ነበር። ጳውሎስ ፈጽሞ አያውቀውም። ጳውሎስ እርሱን የሚያውቅበት ብቸኛው መንገድ በመገለጥ፡ በራእይ ነው። ልክ ነው? [ጉባኤው፡ “አሜን” አለ።—አርታዒ።] ጳውሎስ ኢየሱስን የሚያውቀው፡ ልክ እንደ ጴጥሮስ በመገለጥ ብቻ ነው።

243 ጴጥሮስ በሥጋ አይቶት ነበር፡ በሥጋ ግን አላወቀውም፡ ኢየሱስም ይህን ተናግሯልና። “ሥጋና ደም አልገለጡልህም። የራሴ ህይወት እንኳን አልገለጠልህም። ነገር ግን በሰማያት ያለው አባቴ ነገሩን ገልጦልሃል፡” እርሱ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ፡ “በዚችም ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ።” ጴጥሮስ በሥጋ አላወቀውም። ሰዎች ተራምደው፡ እሱን ዳሰሰው፡ እና ሌላ ሌላ ሁሉ አድርጓል።

244 ጳውሎስ ግን ከሐዋርያት ሁሉ የሚበልጥ አንዳች ነገር ነበረው። አያችሁ?

245 እነርሱ እንዲህ አሉ፦ “ጳውሎስ ሆይ፡ እኔ—እኔ'ኮ፡ ከአንተ የበለጠ መገለጥ አለኝ፡ ምክንያቱ፡ ታውቃለህ፡ ከእርሱ ጋር ሄጀለሁና። አንድ ቀን ከእሱ ጋር ዓሣ ለማጥመድ ሄጀለሁ። ሲናገር ሰምቼዋለሁ። ከእኔ ጋር በጀልባ ውስጥ ተቀመጠ፡ በእውነቱ፡ 'ወደዚህ እንሂድና በዚያ ቦታ እናጥምድ፡ ብዙ ዓሦችን እናገኛለን' ብሎኛል። ሄደን አጥምደናል።” አየህ? አየህ? “ሲሰራ አይተነዋል።”

246 ጳውሎስ ግን ከሞተ በኋላ፣ ተቀብሮ፣ ከተነሣ በኋላ፡ የእስራኤልን ልጆች በመራበት በእሳት ዓምድ ውስጥ ራሱን ሲተርክ አየው። ጳውሎስ አይሁዳዊ ሆኖ፡ እርሱ ሲተረክ ካላየው በቀር፡ “ጌታ” ብሎ በፍፁም እንደማይጠራው፡ እያወቀ... ያኔም፡ ትናንትና እና ለዘላለም ያው ነውና። “ጳውሎስ፡” አለው፡ በሌላ አባባል፡ “ትናንት የነበርኩ ዛሬም ያው አምላክ ነኝ። እነሆ እኔ፣ በሚቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ፡ ሙሴን ያነጋገረው የእሳት ዓምድ፡ ያው ብርሃን

ነኝ አለ።" በዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ፡ ሕግን ከጸጋ መለየት መቻሉ አያስደንቅም፡ ያንኑ የእሳት ዓምድ አግኝቶታልና። "አንተ የምታሳድደኝ፡ እኔ ኢየሱስ ነኝ፡" አለው።

247 እነሆ እርሱ ዛሬም፡ ያው ነው፡ በዛው የእሳት ዓምድ፡ እራሱን እየተረከ እና ያው መሆኑን እራሱን በማረጋገጥ፡ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወረውን የእግዚአብሔርን ምሥጢር ይገልጣል። አያችሁ?

248 ጳውሎስ እሱን የሚያውቀው—በመገለጥ ነው። ጴጥሮስም እንዲሁ በመገለጥ አወቀው።

249 አብሮት የሄደው፡ ከእርሱ ጋር የተነጋገረው። እናንተም፡ ቃሉ ውስጥ ማረፍ ትችላላችሁ። አሁን፡ እሱ ቃል ነበረ ብያለሁ። አሁን፡ አንድ ምሁር ሰው የተማረ ስለሆነ የእናንተ አእምሮ በወደደው መንገድ ማስር እስኪችል ድረስ ቃሉን ሊያነብላችሁ ይችላል፡ አያችሁ፡ ማድረግ ከፈለገ፡ ሊቅ ስለሆነ፡ ቃሉን ሊያነብላችሁ ይችላል። የካቶሊክ ካህን ውሰዱ፡ እንደው፡ ያን ያህል፡ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ፡ በሰነ መለኮት ትምህርት ያልገፋ። ወንድም፡ ባፕቲስት፡ ወይም ፕረስባይተርያን፡ ወይም የሆነ ሌላ፡ አያችሁ፡ ሰትነጋገሩ፡ ምንም እንደማታውቁ እንዲሰማችሁ ሊያደርጋችሁ ይችላል። ለምን? ምክንያቱ፡ ቃሉን፡ በሰጋው ላይ ስላወቀው። [ወንድም ብራንሃም መጽሐፍ ቅዱሱን መታ አደረጋት—እርታዒ።]

250 የምትድኑበት ብቸኛው መንገድ ግን በመገለጥ እርሱን በማወቅ ነው!

251 ከፈለግኩ፡ በፕሬስባይቴሪያን ትምህርት እናንተን ጴንጤቆስጤዎች እስከማታውቁ ድረስ ላስራችሁ እችላለሁ። የባፕቲስት ትምህርት ወሰጄ እናንተ ጴንጤቆስጤዎች የማታውቁት አንድ ሚልዮን ነገሮችን ላሳያችሁ እችላለሁ። አዎን፡ ይሁን እንጂ ያ ዋናው ነገር አይደለም። ቤተ ክርስቲያኑ እንዲህ አይደለችም። ቤተ ክርስቲያኑ እንደዚህ አይደለችም።

252 ቤተ ክርስቲያኑ እርሱ ሲገለጥ፡ እና እርሱ አምላክ እንደሆነ፡ በገዛ ቃሉ እራሱ ሲተረክ ናት። አያችሁ? (አሜን! ታያላችሁን? )

253 እንዴትስ፡ "አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ፣" ነው እያላችሁ፡ በእርሱ ትጠመቃላችሁ? እሕዛብ! አዎን! በመጽሐፍ ቅዱስ፡ አንድ ቦታ እንኳን በሌለ ሰም እየተጠመቃችሁ፡ ኢየሱስ ክርስቶስን አውቀዋለሁ እንዴት ይባላል፡ እርሱ ቃል ነው፡ "በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ" ሰም የተጠመቀ አንድም ሰው ሳይኖር፡ እንዴት አውቀዋለሁ ትላላችሁ?

254 እናንተ—ለመጠመቅ "የኢየሱስ" ሰም ብቻ የምትጠቀሙ፡ የኦንሊ-ጂሰስ ሰዎች ሆይ! እኔ በግሌ፡ አራት ወይም አምስት ኢየሱስ የተባሉ ሰዎችን ተዋውቄአለሁና። ተቋማችሁ ወደ ምን እንደሚመራችሁ አታዩምን? ደም ከማቅረብ ይልቅ፡ ፍራፍሬ እንዳቀረበ እንደ ቃየን የጨለማ ትርጉም ነው። አያችሁ?

255 መገለጡ የሚመጣው ግን፡ አያችሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በደሙ፡ ማለት በእግዚአብሄር ደም፡ በማርያም ማሕጸን ውስጥ በተፈጠረው የሚመጣ ነው። ጳውሎስም በመገለጥ አውቆታልና። እኛም ዛሬ እሱን የምናውቅበት መንገድ ይህ ነው፣ እሱን ማወቅ የምትችሉበት ብቸኛው መንገድ ይህ ነው። "እኔ ሜቶዲስት ነኝ፡" አትበሉ። ትርጉም የለውም። "ባፕቲስት ነኝ።"

ትርጉም የለውም። "እኔ ካቶሊክ ነኝ።" ትርጉም የለውም። ነገር ግን እምላክ ቃሉን ለእናንተ በገለጠበት መገለጥ ይሁንላችሁ! እርሱ ቃል ነውና። ቃሉ፡ መገለጡንስ እንዴት አድርጋችሁ ታውቃላችሁ? እርሱ ራሱ በእናንተ ስለሚኖር ማንነቱን በእናንተ ይተርክዋልና። ኦ!

256 አብያተ ክርስትያናቶቹ ታላቁን መገለጥ ከረሱ ሰነባብተዋል። አዎ እውነት ነው። የእውነቱን መገለጥ፡ ረስተዋል። በቃ ሄድዋል...

257 ያኔ፡ ሉተር በተነሳ ጊዜ፡ ታላቅ ሰው ነበረ። የዚያ ዘመን መግለጥ ይዞ ነበርና። ታድያ ምን ገጠመው? ዛሬ ዛሬ እናታቸው-መሃል የተላጩ ብለን እንደምንጠራቸው፡ እንደነ ሪኪ እና፡ ሌሎች ቅምጥሎች፡ የተለያዩ ነገሮች፡ ከበቡት። እና—እና—እና፡ በመጀመርያ መታወቅ ያለበት ነገር፡ አሁንም መኖራቸው ነው።

258 ያ አገላለጽ። ብቻ—መጽሐፍ ቅዱሳዊ የቁጥር ስሌት ብታውቁ ኖሮ፡ **ኤልቪስ** ወይም—ወይም **ሪኪ** በቅዱስ ቃል ምን ማለት እንደሆነ ታውቁት ነበር! እይ-እህ ለምን፡ ልክ እንደ ኢየሱስ... እናንተም እንደምትሉት፡ "ስማችሁ ፡እንዲህ ብሎ ነገር የለም።" የለምን? ይህ ሰም በመጨረሻው ቀን ውስጥ ለመጨረሻው-ዘመን ሰዎች ብቻ የሚመጣ ነው።

259 ኢየሱስ የአብራምን ስም ወደ አብርሃም፡ ቀጥሎም፡ ሦራን ወደ ሣራ ለምን ለወጠው? ሳኦልን ወደ ጳውሎስ የለወጠው ለምን ለወጠው? ስምዖንን ወደ ጴጥሮስ ለምን ለወጠው፡ ሌሎችም? እያችሁ፡ በእርግጥ ትርጉም አለው።

260 ይህ ሰም እስከ ዛሬ ድረስ የሚያነሣው የለም። ዛሬ በምድር ላይ የደረስብን ገሃነማዊው ነገር የመጣብን፡ በእንደዚህ አይነት ምክንያቶች ነው። የሰው ዘር በሙሉ ተበላሽቷል። ጠ—ጠፍቷል፡ እያችሁ፡ ምክንያቱ ይህ ነው።

261 አሁን አስተውሉ፡ ሉተር፡ በዘመኑ፡ ደህና ነበር፡ መገለጥም ነበረው፤ ልክ እሱ እንደ ሄደ ግን፡ ያደረጉትን ተመልከቱ። ዌስሊ መልእክት ነበረው፤ ያደረጉትን እዩ። ቀደምት ጴንጤዎች መልእክት ነበራቸው፤ ያደረጉትን እዩ። ልክ እንደዚያው ተመሳሳይ ነገር፡ ብዙ ሰዎችን ያዙ...

262 እግዚአብሔር፡ በጸጋው፡ ለእስራኤል የእሳትን ዓምድ፣ ነቢይ፣ እና መሥዋዕት ላከላቸው፡ በመካከላቸውም ተገለጠ፡ ከግብፅም፡ ቀይ ባሕርን አሻግሮ አወጣቸው። እነርሱ ግን መሳፍንት ይኖራቸው ዘንድ፡ በራሳቸውም የሚያደርጉት ያገኙ ዘንድ፡ ሕግ ፈለጉ። እና ምን አደረጉ? ለአርባ ዓመታት ያህል በምድረ በዳ ለመቅበዝበዝ ቀሩ፡ ከዛ ድርጅት መካከል አንድም እንኳ አልተሻገረም።

263 ካሌብና ኢያሱ ጎልተው የወጡት ሁለቱ ብቻ ነበሩ፡ እነርሱም "የእግዚአብሔርን ቃል ለማየትም፡ ለመውረስም እንችላለን፡" አሉ።

264 ሌሎቹ ሁሉ በምድረ በዳ ሞቱ። ኢየሱስ በዘመናቸው፡ በረከቱን እና ኃይሉን ካሳየ በኋላ፣ ለዘለአለም እንደጠፉ ተናገሯል፤ እንደ ሉተር፣ ዌስሊ፣ እና የመሳሰሉት። አይደል?

"አባቶቻችን በምድረ በዳ መና በሉ፡" አሉት።

265 እርሱም "ሁሉንም፡ አንድም ሳይቀር፡ ሞቱ፡" አላቸው። ያ ማለት ደግሞ ከእግዚአብሔር እምላክ ለዘለአለም መለያየት ነው። ሬሳቸው በምድረ

በዳ አለቀ። አያችሁ? “ሞተዋል። እኔ ግን ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጣው የሕይወት እንጀራ ነኝ።” ሊያዩት አልቻሉም። እንደው ሊያዩት አልቻሉም።

266 እንግዲህ፡ ቤተክርስትያንም ከረሳችው ቆየች። የቃሉ የመገለጥ እውነት፡ በመቀበል ፈንታ፡ የዕውቀትን መልዕክት፡ አዋቂዎችን፡ አባልነትን እና ዕውቀትን ተቀበለች።

267 አሁን ዛሬ ወደሚናገሩት፡ ወደዚህ ተመልከቱ። ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ድውያንን ፈውሱ ወንጌልንም ሰበኩ፡ አጋንንትንም አውጡ ብሎ፡ እግዚአብሔር እንዳዘዘን፡ ታምናላችሁ? “ኦህ፡ ኦህ፡ አዎን፣ ትክክል ይመስለኛል፡ ነገር ግን... ” አየህ?

268 በቀደምለት፡ አንዲት እመቤት ከእኔ ጋር እያወራች ነበረች፡ “ግን እኮ፡ አብያተ ክርስትያናቱ አንድ እየሆኑ ነው፡” አለችኝ።

269 “አንዱ ከአንዱ ጋራ ምንም ዓይነት አንድነት የላቸውም፡” አልኳት። ካቶሊኮች ቆመው ነበርና። “እናንተስ? አንቺ ሜተዲስት ነሽ ያም ደግሞ ካቶሊክ፡ እርስ በእርስ ትስማማላችሁን? ” አልኳቸው፡ “ወደ አንድነት ሊያመጣቸው የሚጥረው ጳጳስ፡ ለሱ ዓይነት ሰዎች ያንን መልካም ነገር ነው፡” አልኳቸው።

270 የጌታ ቤተክርስትያን ግን ከእንደዚህ ዓይነቱ ነገር ጋር፡ ምንም ጉዳይ የላትም። ከዚያ ሰብሰብ ውጪ ናት። አይ-እህ። ትክክል። የሰ፡ ሰር።

271 አንድ ላይ ማድረግ ትፈልጋላችሁ፡ አንዱ **በአንድ ነገር** ያምናል ሌላኛውም ሌላ፡ ሜተዲስቶች በመርጨት ያምናሉ፡ ባፕቲስቶች ደግሞ በጥልቅ ውሃ። ሁለቱም ግን የቅዱሰን የሙላት ኃይሉ ይክዱታል። “**ባመንን** ጊዜ መንፈሰ ቅዱሰን ተቀብለናል፡” ይላሉ።

272 መጽሐፍ ቅዱስ ግን “ካመናችሁ **ወዲህ** መንፈስ ቅዱሰን ተቀበላችሁን? ” ይላል፤ ልዩነቱ ግልጽ ነው። አያችሁ? በትክክል። አያችሁ?

273 እነርሱም፡ “እኛ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ነን። ቀደምት ጀማሪዎች ነን። **እንዲህ** አደረግን።” ሜቶዲስቶችም፡ “በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተመሰርተናል” ሲሉ።

274 ኢየሱስ ግን፡- “ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል” አለ። እስኪ አሁን የት አለ? አሃ-ሃህ። አያችሁ? አዋና። “እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ፡” በእርሱ የሚያምን፡ ፍጥረት ሁሉ። ታዲያ ምንድነው? ቃሉ ነው። “ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ ቃሌ ግን ለዘላለም አይወድቅም።” ታዲያ ምንድነው? አያችሁ? ኦህ፡ ታይታ ብቻ ናቸው!

275 ምንድነው? በተዳቀለ ሁኔታ ነው። እዚህ ተመልከቱ፡ የተዳቀለ ትልቅ የበቆሎ እህል ውሰዱ፡ እና ያንን የተዳቀለ በቆሎ ስታዩት፣ ቆንጆ በቆሎ ነው። እሱን ስትዘሩት፡ ምን ታገኛላችሁ? ትንሽ አገዳ **እንዲህ** ይበቅላል፡ ብዙም ሳይቆይ ወደ ቢጫነት ይለወጣል ከዚያ ይረግፋል። የሰውን ቃል ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ተቀላቅሎ፡ ሲዳቀል፡ እያንድናንዱ የሐይማኖት ተቋም እንዲሁ ይሆናል። ወደ ምልክቶችና ድንቆች፡ እና ኢየሱስ ቃሉን ስለማመን የተናገረውን ይመጣል፡

ወደ ቢጫነት ይቀየራል፡ ከዚያ “እኛ ይሄን አንቀበልም፡” ማለት ይጀምራል፡ ወደ ኋላ ይመለሳል።

276 ከነዓን አልፈው እንዳዩአት እንደ ሌሎቹ ሰላዮች ሁሉ ናቸው። ደርሰውም እንዲህ አሉ፦ “ኧረ እኛ በፊታቸው እንደ አንበጣ ነን! እናሸንፋቸውም! አማሌቃውያን፣ እነዚህ ሁሉ፣ የሚያደርጉትን ያደርጉብናል!” ብለው ተመለሱ።

277 ካሌብና ኢያሱ ግን፡ አሜን፡ በእግዚአብሔር ቃል ስለዳበሩ፡ እግዚአብሔር “ምድሪቱን አሳልፌ ሰጥቻችኋለው፡” ብሎ የተናገረውን ያውቁታል። “ይሄን መውረስ እንችላለን፡” ብለው ተናገሩ!

278 የተወለዳችሁበት ሰፍራ ይወስነዋል። ከእግዚአብሔር ቃል ከተወለዳችሁ፡ የእግዚአብሔር ቃል በቤተክርሰቲያኑ ውሰጥ የበላይነት አለው። እርሱም የሞተው ለዚህ ነበርና። ማሳካት የፈለገው፡ ዓላማውም ያ ነው፡ ይህም በቤተ ክርሰትያን የበላይነት ይዞ እንዲሰራ ነው። ምንም አይነት ነገር ቢመሰልም፡ ከሁሉ በፊት፡ የእግዚአብሄር ቃል ይብራ። ምሁራን እና አዋቂዎች **እንዲህ፡ እንዲያ፡** እና **ሌላም** ይበሉ፡ ምንም ለውጥ የለውም። የእግዚአብሔር ቃል ተናግሯልና፡ ወጥተን መውረሰ እንችላለን!

279 አንድ አገልጋይ፡ እንዲህ አለኝ፡ “እኔ በቤተክርሰትያኔ ይህን የምሰብክ ብሆን ኖሮ፡” “ሰብከቴ በቤተክርሰትያን ውሰጥ ላሉት አራት ጉልላቶች ሆኖ ይቀር ነበር አለኝ።”

280 እኔም፡ የሰ፡ ሰር። “ለዚያም እሰብካለሁ።” የእግዚአብሄር ቃል ተናግሯልና። እግዚአብሄር ውረሷት ብሏልና። መውረሰ እንችላለን። አሜን!

281 ኦህ፡ አዎን፡ በዚህ ምክንያት ለራሳቸውን ምክንያትን ያበዛሉ። አያችሁ? በዚህ በመጨረሻው ቀን፣ እግዚአብሔር ራሱን እያረጋገጠ ባለበት ወቅት፣ ለመጨረሻው ዘመን መልእክት ዓይናቸው የታወረበት ምክንያት ለዚህ ነው። በመናፍሰታዊነት መደብ ለመመደብ ይሞክራሉ፡ ወይም አንዳንዶቹ፣ አቤት፣ (ምን ብዬ ልጥራው? ) አንዳንድ አእምሯዊ፣ ቅዠት፣ ወይም በዚያ ምድብ ውሰጥ። አያችሁ፡ ያልሆነውን ነገር ላይ—ሊመድቡት ይሞክራሉ።

282 ያኔ እዚህ በነበረ ጊዜ እንዳደረጉት፡ ኢየሱሰ እዚህ በነበረ ጊዜ፡ “ብዔልዘቡብ፡ ጠንቋይ፡” እንዳሉት፡ አሁንም ምናባዊ የአእምሮ መታለል ነው ይላሉ። አያችሁ? ባለበት ሆኖ፡ ህዝቡን እየተመለከተ በልቦቻቸውን የተሰወረውን ሀሳብ መለየት እንደሚችል እያወቁ። ይላል መጽሐፍ ቅዱሰ።

283 እሺ፡ ዕብራውያን 4ኛ ምዕራፍ፡ ሲናገር፦ “የእግዚአብሔር ቃል ሕያው እና የሚሰራም ሁለትም-አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ ነው፡ የልብንም ሰሜትና አሳብ ይመረምራል”? ያ ቃል እርሱ ራሱ ነበር። እንግዲህ ያን ቃል በሰው ላይ የበላይነቱን ሲይዝ፡ ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል፡ ምክንያቱ ቃል ነውና! አሜን!... ከአሁን በኋላ በዚ ላይ እንዴት እንደምትሰናከሉ አያችሁ። ግልጽ ነው። አያችሁ? እሺ።

284 ክርሰቶሰ በምድር ላይ በነበረበት ዘመን እንደነበረው ሁሉ፡ ዓይነ ሰውር የሆኑትም ለዚህ ነው። ኦህ፡ ማይ! በተመሳሳይ መንገድ ተንገዳገዱ። እርሱንም “ብዔልዜቡብ ነው፡ ቤል-... ” አሉት። ማድረግ ሲችል አይተውት ሰለነበር፡ እንዲህ አሉት፦ “ያለ ጋብቻ የተወለደ... ሕገወጥ ልጅ፡ እና ጎዶሎ ሰው ነው።

በአጋንንቶች የተያዘ ሰው ነው። እሱ'ኮ—ሳምራዊ ነው፡ አጋንንትም አለበት። ስራውን የሚሰራው በነሱ ነው።"

285 ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲህ ብለው በመጥራታቸው፡ አያችሁ፡ ስለ እምላክ ቃል፡ ክፉ መንፈስ ነው በማለታቸው፡ "ለዛ ይቅር እላቹኋለሁ፡" አላቸው። እርሱም አላቸው፦ "ለዚያ ይቅር እላችኋለሁ። መንፈስ ቅዱስ በሚመጣ ቀን ግን፡ በእርሱ ላይ የምትወጣ አንዲት ቃል ከቶ አትሰረይም፡ በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም፡ ወይም በዚያ ታላቅ ቀን። ይቅር አይባልም።" ስለዚህ፡ አያችሁ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በግልጽ የተጻፈ ነው።

286 ሰዎችም በዚያ ቀን ፊት ሲቀርቡ፡ ምንም ያህል ትምህርት ይኑራቸው፡ የየትኛውም ትልቅ የሀይማኖት ተቋም አባላት ይሁኑ፡ የተኮነኑ ናቸው። መሆንም አለባቸው! መንፈስ ቅዱስን ተሳድበዋልና፡ "ሆሊ-ሮለር" ወይም አንዳንድ የማይመች ሌላ ስያሜ፡ የመሳሰሉ ነገሮች ይሰይሙታል። የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያንም ለዘመናት ይህን ተሸክማ ኖራለች።

287 ጳውሎስም በአግሪጳ ፊት "'**መናፍቅነት**፡' ብለው በሚጠሩት መንገድ፡" "ክህደት፡" እንደማለት ነው፡ "የአባቶቻችንን አምላክ የማመልከው በዚህ መንገድ ነው።" "'መናፍቅነት፡' ተብሎ በተጠራበት መንገድ።" ታላቁ ምሁር ወደዚያ መድረሱ ግድ ሆነበት።

288 ለምን? ለእሱ ስለተገለጠለት ነው። በፊቱ የቆመው የእሳት ዓምድ፡ እንዲህ አለው፦ "በምድረ በዳ ከሙሴ ጋር የነበረው ታላቁ አምላክ፡ እኔ ኢየሱስ ነኝ። እኔ እሱ ነኝና፡ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብሰብሃል።"

289 በዚያን ጊዜ ጳውሎስ በዚያ ቆሞ፡ ሕይወቱ በሞት አፋፍ እንደደረሰች አወቀ፡ እና እንዲህ አለ፡ "'መናፍቅነት' ብለው በሚጠሩት መንገድ፡ የአባቶቼን አምላክ የማመልከው በዚያ ነው።" እንደዚያ ተሰየመ። ምክንያቱ ታላቁ የክርስቶስ እውነት ምን እንደሆነ ስለተገለጠለት።

ዛሬም፡ ሰዎች "የሐይማኖት ተቋም፡" ይመስላቸዋል።

290 በእናንተ ውስጥ የተገለጠው፡ አዲሱ ልደት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡ ይህም ቃሉን ይገልፅ ዘንድ፡ የበላይነትንም ያገኝ ዘንድ ነው። እናም በዚህ በመጨረሻው ቀን፡ ቃል የገባለትን ማንኛውንም ነገር፡ እየሰራበት ባለው በሰውነቱ በኩል ሊፈጽመው ይችላል። አሜን! በትክክል የተተረከ የእግዚአብሔር ቃል ነው። አስተውሉ። በጣም ጥሩ።

291 በክርስቶስ ዘመን እንደነበረው ሁሉ፡ እግዚአብሔር ራሱ፡ የዚህን ዘመን የክርስቶስ መገለጥ ቁልፍ ይዟል። ታምናላችሁ? [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—አርታዒ።] የነገረ መለኮት ትምህርት ቤቶች በፍጹም ሊያገኙት አይችሉም። ኢየሱስም እንዲህ አለ። ማንበብ ከፈለጋችሁ በቅዱስ ማቴዎስ 11:25 እና 27። "አቤቱ፡ የሰማይና የምድር አምላክ ሆይ፡ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ዓይን ሰውረህ፡ ለሚማሩ ሕፃናትም ስለገለጥኸው አመሰግንሃለሁ።" አያችሁ? አያችሁ? ሌላው እያስጨንቀኝም...

292 በዘመኑ የነበሩትን ምሁራን፡ አይሁዶችን፡ ተመልከቷቸው፡ እስከነ ፈሪሳዊ፡ ሰዱቃውያን፡ ሄሮድያውያን፡ ድርጅቶቻቸው ወዘተ ድንቅ ሰዎች ነበሩ። አያችሁ? ኢየሱስ ለእነዚህ ታላላቅ ድርጅቶቻቸው ሁሉ፡ እንዲህ አላቸው፦ "ዕውሮችን

የምትመሩ፡ ዕውራን፡ ኢሳያስ ስለእናንተ እውነት ተናገረ፡ ‘ጆሮ አላችሁ፡ አትሰሙም፡ ዓይኖች አሏችሁ፡ አታዩምም።’ ኢሳያስ ይሄን ነገር ሲናገር በመንፈስ ነበረ፡ ስለዚህ፡ የሰማይ አምላክ አይኖቻችሁን አሳውሮታል። የእግዚአብሄርን መንፈስ ነገር ሳትረዱ፡ ሄዋን እንዳደረገችው፡ የዕውቀትን ነገር ብቻ ትቀበላላችሁ። እንግድያውስ፡ መሪና ዕውር ተመራ፡ ተያይዘው፡ ጉድጓድ አይገቡምን? ” መሪው ዕውር ስለሆነ፡ ከእውሩ ጋራ አብሮ ይወድቃል። የመሪ ከወደቀ፡ ዕውርን፡ ዕውር ሲመራው ነው። ሁለቱም ጉድጓድ ውስጥ ይወድቃሉ።

293 ቁልፉ የያዘው ግን እግዚአብሔር አምላክ እራሱ ነው! ቀደም ብዬ ባነበብኩት ጊዜ በቀደመው ቅዱሳት መጽሐፍት ላይም፡ ተመሳሳይ ነገር ገልጿል፡ “ሰው እኔ የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆንሁ ይላል? ”

294 ጴጥሮስም፡ “አንተ ክርስቶስ፡ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ” አለ።

295 እሱም አለው፡- “ሰምኦን የዮና ልጅ ሆይ። ስጋና ደም ይሄን አልገለጠልህምና ብጹእ ነህ። በሰማያት ያለው አባቴ ገለጠልህ! በዚችም መገለጥ ላይ፡ ብቻ፡ ቤተክርስትያኔን እሰራለሁ። የገሃንም ደጆችም በፍጹም አይቋቋሟትም።” አያችሁ? አሁንስ አያችሁትን?

296 ከምታውቋቸው ትምህርት ቤቶች መካከል፡ ይሄንን ጉዳይ በተመለከተ፡ የሚያውቅ ምሁርም ሆነ፡ የቲኦሎጂ አዋቂ የለም። በጭራሽ ሊያውቁት አይችሉም። አንዳች ነገር ማወቅ አይቻላቸውም። እግዚአብሔር የማወቅን ስሜት፡ ከተመረጡት አስተማሪዎች፡ እና ከሌሎቹ ሁሉ ሰውሮታልና።

297 ጉዳዩ ክርስቶስ በግላቸው ስለሚገለጥላቸው ግለሰቦች፡ የግል መገለጥ ነው።

298 ሌላውም “ተገልጦልኛል፡” እያላችሁ፡ ክርስቶስ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚያፈራውን ፍሬ፡ በእርሱ ዘንድ ያለውን ህይወት፡ በእናንተ ዘንድ ከሌለ፡ የተሳሳተ መገለጥ ይዛችኋል።

299 የዱባን ህይወት ወደ ፒር ዛፍ ህይወት ካገባሁት ዱባን ያፈራል። “በፍሬአቸው ታውቁአቸዋላችሁ።” ትክክል ነው። እና የመጀመሪያ... የተከላችሁት ዛፍ፣ ወይን ከሆነ፣ የወይን ዘለላ ካፈራ፤ የመጀመርያው ቡቃያ ሲያድግ፡ የወይን ዘለላ ያፈራል፡ ሁለተኛው ሎሚ ካፈራ፡ ቀጥሎም ፒር ከሰጠ፡ ቀጣዩም አፕል ከአፈራ፡ የራሱን ሕይወት የሚሸከም፡ አንዳች ሌላ መዳቀል እንዳለ ያስረዳል። እያንዳንዱ የሐይማኖት ተቋም እንደየወገኑ ሕይወት ያፈራል። ይሁን እንጂ የመጀመርያው የወይን ሐረግ አፈትልኮ ቢወጣ፡ መጀመርያ ፍሬ የሚያፈራውን አይነት ዘለላ ያፈራል።

300 እንዲሁም የኢየሱስ ህይወት—የሌሎች የአማኞች አካል ከለበሰ፡ መጀመርያዎቹ እንዳፈሩት ፍሬ ያፈራል። ከበስተጀርባ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ይጽፋሉ፡ ምክንያቱ፡ አንድ ዓይነት ሕይወት ይሆናልና። ምን ማለቴ እንደሆነ ገባችሁ? ከዛ ልታመልጡ አይቻላችሁም። ህይወቱን በእናንተ በኩል የሚተርከው፡ መንፈስ ቅዱስ ወደ እናንተ የከተበው፡ የክርስቶስን የራሱ ህይወት ነው።

301 “የታወሩ የዓይነ ስውራን መሪዎች!” አስተውሉ፡ ቁልፋን የያዘው፡ እግዚአብሔር ብቻውን ነው። የትኛውም የሰነ መለኮት ምሁራን ሊነግሯችሁ አይችሉም፡ አያውቁትም። ተደብቆባቸዋል። ስለሱ አንዳች አያውቁም።

302 ስለዚህ ስለ ትምህርት ስትናገሩ፡ “ፒኤች. ኤልኤል.ዲ.፡” አለኝ ስትሉ... ለእኔም ይሁን፡ ለእግዚአብሔር፡ እና ለማንኛውም እውነተኛ አማኝ፡ ይህ ማለት እጅግ ርቃችሁ ጠፍታችኋል፡ ተጠራርጋችሁ ጠፍታችኋል። እግዚአብሔር በትምህርት አይታወቅም። በመብራራት ችሎታ አይታወቅም።

303 እግዚአብሔር የሚታወቀው ዕውቀት ለሌለው ሰው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ እጅግ ቀላል በሆነ መንገድ ነው። አያችሁ? የአንተ ቲዎሎጂ አይደለም። የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነው። “በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ።” ሌላ አለት ተቀባይነት የለውም፡ ሌሎች ነገሮች ተቀባይነት የላቸውም፡ ሌላ የሮማውያን ዓለት፡ ሌላ የፕሮቴስታንት ዓለት፡ ሌላ ትምህርት ቤት፡ ሌላ ምንም የለም፡ ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በአዲስ ልደት መገለጥ ብቻ ነው። በዚያ ይወልዳል፡ የገዛ ህይወቱ ይወጋችኋል፡ ከዛ በኋላ ህይወታችሁ አይኖርም። የክርስቶስም ህይወት፡ በእናንተ በኩል ባለው የበላይነት፡ ለሕዝቡ ይታያል፡ ይህም፡ በእናንተ አልፎ የሚሰራውን፡ ያንኑ ህይወት፣ ስራ፣ ምልክቶች፣ እና ድንቆችን ማየት ይችሉ ዘንድ ነው። ከዛ ውጪ፡ ሌላው፡ በምንም አይጠራም። ታላቁ የእግዚአብሔር መገለጥ ሲከፈት ተመልከቱ!

304 በመገለጥ እጦት ምክንያት፡ በመካከላችን የተለያዩ መከፋፈሎች እና ሰድቦች ያሉ ለዚህ ነው። በመካከላችን ብዙ መለያየት የበዛው፣ ህዝቡ ያ መገለጥ ስላጣ ነው። አያችሁ፡ አስተማሪዎች፡ ያንን መገለጥ ያጥራቸዋል።

305 ጳውሎስ፣ ከክርስቶስ ታላቅ መገለጥ በኋላ፣ በአንደኛ ቆሮንቶስ፣ ምዕራፍ 2 እንዲህ አለ። እየጻፋችሁት እንደምታነቡት እርግጠኞች ሁኑ። ተከታተሉ! ኦህ! እንዲህ አለ፡ “በጥበብ ወደ እናንተ አልመጣሁም።” ይህ ጥበብ የነበረው ሰው ተመልከቱት፡ ወይም፡ ብዙ እውቀት የነበረው ይህ ሰው ተመልከቱት፡ “በሚያባብል ቃል ወደ እናንተ አልመጣሁም።” አንደኛ ቆሮንቶስ፣ የአንደኛ ቆሮንቶስ 2ኛ ምዕራፍ። ኦህ፡ እንደው...

306 እሺ፡ በቃ እናንብበው። እሺ... አንድ ወይም ሁለት ቁጥሮችን ለማንበብ አንድ ደቂቃ ለመቆም ፍቃደኞች ናችሁ? [ጉባኤው፡ “አሜን” አለ።—አርታዒ።] እኔ ራሴ አነበዋለሁ—ምናልባት እናንተ-... በቴፕ ላይ ያሉት ሰዎችም እንዲመለሱ ያደርጋቸዋል፣ ለማንኛውም፣ እድል እንሰጣቸው።

307 አንደኛ ቆሮንቶስ 2ኛ ምዕራፍ። ታላቁ ሐዋርያው ጳውሎስ፡ የተማረ ሊቅ የሆነ የእግዚአብሔር ባርያ፡ የሚለውን አድምጡት፡ ወደዚህ እንመልከት።

> ... እኔም፡ ጳውሎስ፡ **ወደ እናንተ** በመጣሁ **ጊዜ፡ በቃልና በጥበብ ብልጫ፡ ለእግዚአብሔር ምስክርነቴን...** ለእናንተ **እየነገርሁ አልመጣሁም።** በጭራሽ እኔ—ዶር. **እከሌ-ና-እከሌ** እባላለሁ አላልኳችሁም። አያችሁ?
>
> **በመካከላችሁ** ሳለሁ፡ **ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እርሱም እንደተሰቀለ፡ ሌላ ነገር እንዳላውቅ ቆርጬ ነበርና።**

**እኔም በድካምና፡ በፍርሃት፡ በብዙ መንቀጥቀጥም በእናንተ ዘንድ ነበርሁ፡**

**... ስብከቴም—**ልመናዬም **በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም፡ በሰልጣን... መንፈስንና** ኃይልን **በመግለጥ ነበረ እንጂ።**

308 ይኸው፡ እያችሁ፡ ወንጌል ይህ ነው። እያችሁ? ኢየሱስም “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ሰበኩ፡” አለ። “ሄዳችሁ አስተምሩ፡” አላለም። እሱ ያለው፡ “ሂዱ ሰበኩ።” በሌላ ቃል፦ “ኃይሉን አሳዩ፡ እነዚህ ምልክቶችም ይከተሏቸዋል።” እነዚህን ምልክቶች ለማሳየት ትክክለኛው መንፈስ ራሱ ይጠይቃል። እንጂ ትምህርት ምንም አያንቀሳቅሰውም። እያችሁ? ይሄን ሰሙ።

**እምነታችሁም በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ፡ በሰው ጥበብ እንዳይሆን።**

309 ኦ ማይ! እያችሁ፡ ሰውየውን ለመቀየር! ያው ሆኖ ሳለ፡ “ያው አይደለም፡” ብዬ ለመግለጽ፡ የመቻሌም አይደለም። እንዲህ እማ ካደረግኩኝ፡ ለእኔ፡ የሚሰጠኝ ትርጉም፡ አንድ—ሰው... እንዲህ ካደረገ፡ በትክክል፡ መገለጥ እንደሌለው፡ የእምላክን ሦስት መአዝናዊው መገለጥ እንደሌለው ያሳያል። እያችሁ? እና፡ አሁንም...

እኔም በእናንተም... **ፍጹማን በሆናችሁ በመካከላችሁ በድካም፤ ነገር ግን በዓለም ጥበብ ሳይሆን የሚሻሩት የዚህ ዓለም አለቆች ጥበብ አይደለም፤**

**በምሰጢር ግን የእግዚአብሔርን... ጥበብ እንናገራለን፡** (የእግዚአብሔር ሦስት መአዝናዊ ምሰጢር፡ እያችሁ) **ይህም እግዚአብሔር ከዓለም በፊት ለክብራችን ያዘጋጀውን፡ የተሰወረውን ጥበብ ነው፤**

**ከዚች ዓለም አለቆች አንድም እንኳ አላወቀውም፤** ከካህናቱ፡ ከረቢ—ከረቢዎቹ አንዳቸውም፡... (ይቅርታ አርጉልኝ)... ማንኛቸውም፡ ስለዚህ አንዳች ነገር አያውቁም፡ **አውቀውስ ቢሆኑ፡ የክብርን ጌታ** ባልሰቀሉትም **ነበርና።**

310 “ስለ ራባዮቹ እና አስተማሪዎቹ የተናገርከው ተሳስተሀል” በሉ። የሰቀለው ማን ሆነና? አሃ-ሃህ።

311 አቤት፡ እንዲህ እና እንዲያ እና እንዲያ፡ እያልን፡ ልንቀጥል እንችላለን። እና፡ ጊዜ ለመቆጠብ፡ እያችሁ፡ በርግጥ ጊዜ አለን... ገና አልረፈደብንም፡ ጌታ ከፈቀደ ብዙ የምንለው ነገር አለን እና እንብቡት። አሁን፡ የዚህ እጥረት፡ አሁን...

312 ጳውሎስ፣ ይህ ታላቅ ምሁር፣ ታላቅ ሥነ መለኮታዊ ቃላቱን በሰዎች ላይ ለመግለጽ አልሞከረም። የጌታን ቃል በትህትና ተቀብሎ፡ ቃሉ በእርሱ እንዲተረክ በህይወት ኖረ። እንዲህ ኖሯል—ኢየሱስ ክርስቶስን በእርሱ ውስጥ እስኪያዩት ድረስ፡ መህረቡን እስኪፈልጉ ድረስ፡ ወሰደው፡ በሽተኞች ላይ እንስኪያኖሩት እግዚአብሔርን መሰለ። የክርስቶስ ሕይወት ማለት ይህ ነው።

313 አሁን አንዳንዶች ሲናገሩ፡ “ኦህ፡ አዎን፡ አየህ፡ ኤልያስም፡ ከብዙ ዘመናት በፊት፡ እንዲሁ አድርጓል፡ በትሩንም አኖረ፡ ይሁን እንጂ፡ ያ ለኤልያስ ዘመን ነበር።” እንግዲህ፡ ዓለም የምታስበው እንዲህ ነው። በዛ ዘመን የነበሩ የተማሩ ክህናት፡ እና የሀይማኖት ተቋማት እንዲሁም ሌሎች፡ እነኚህን ነገሮች እናውቃለን ብለው ያስባሉ።

314 እነዚያ አማኞች ግን፡ በተለየ መልኩ ያውቃሉ። በኤልያስ የነበረውን የክርስቶስን መገለጥ አይተዋል፣ በጳውሎስም እንዲሁ፡ ነብይ ስለነበር፡ ያንኑ ሕይወት ይተርከው ነበር። አያችሁ? በትክክል የተፈጸሙትን ነገሮች ተንብዮአል፤ እንዲሁም የእግዚአብሔር ነቢይን መለያ ይህ እንደሆነ ያውቁ ነበር። የእግዚአብሔር ነቢይ መሆኑንም ያውቁ ነበርና። በፍፁም፡ ከሱ ልትነቅሏቸው አትችልም። ጴጥሮስም ስለሚሆነው ነገር ሲናገር ባዩ ጊዜ፡ “ብቻ ጥላው ይለፍብኝ” ይሉ ነበር። አሜን! ቤተ ክርስቲያን ማለት ይህ ነው። የሚያምኑት እነዚያ ናቸው። የስ፡ ስር። የተገለጠበት መንገድ ነው...

315 ለምን ጳውሎስ እንዲህ ብሏልን፦ “ፒኤች.፡ ኤልኤል.ዲ.፡ ወዘተረፈ፡ ስላለኝ አመኑኝ አለ ወይ? በጭራሽ፡” “የሰው ጥበብ፡ እና ሌላው ሁሉ ንቄአለሁ፡” አለ፡ እንዲህ አለ፦ “እናም በትንሣኤው ኃይል አውቀው ዘንድ፡ መሞት አለብኝ፡ የእግዚአብሔርን ኃይል በማሳየት ወደ እናንተ የምመጣው በዚህ ነው።”?

316 ምን ነበር? ኢየሱስ ክርስቶስን ትናንትና፣ ዛሬ፣ እና ለዘላለም ያው አደረገው። ኢየሱስ ያደረጋቸውን ሥራዎች፣ ጳውሎስም እንዲሁ አድርጓል። በሚቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ የተገለጠውን፡ ታላቁን አባት እግዚአብሔርን አዩት፡ ጳውሎስ ፊት ተገልጦ ነበርና፡ አሁንም እየታየ ይገኛል።

317 በእያንዳንዱ ዘመን ተመሳሳይ ነው። የእግዚአብሔር ሦስት መአዝናዊ አደራረግ፡ “ትናንት ዛሬ፡ እና ለዘላለም።” ምንድን? በቤተክርስቲያኑ ውስጥ፡ ቤዛ፡ በሚመጣው መንግሥት ውስጥ፡ የበላይ። አሜን! አያችሁ? በተቻለ መጠን ፍጹም!

318 ኦህ፡ አስተውሉ! መንፈስ ቅዱስ ብቸኛው የክርስቶስን መለኮታዊ መገለጥ ገላጭ ነው። ይሄን ማድረግ የሚችል ትምህርት ቤት የለም። ትምህርት ቤት አይችለውም። ማንም ሰው፣ ምን ያህል የተማረ፣ የቱን ያህል አምላካዊ ወይም ሌላ ነገር ይሁን፡ መግለጥ አይችልም።

319 እዚህ ላይ ግልጽ ልሁን። ዳግም የተወለዳችሁ ትክክለኞች ክርስትያኖች ስንቶች ናችሁ? (እጆቻችሁን ከፍ አድርጉ) በመንፈስ ቅዱስ የተሞላችሁ? መልካም። ይሄው እንግዲህ። መልካም። እንግዲህ አስተውሉ።

320 አስቀድመው ለተወሰኑቱ ብቻ ያደርግላቸዋል። በትክክል። “አብ የሰጠኝ ሁሉ ይመጣል፤ አብ አስቀድሞ ለእኔ ካልሰጠው በቀር ማንም ሊመጣ አይችልም።” አያችሁ?

321 ካህናቶቹ፡ የሚሉትን ሰሙአቸው፡ “ጠምቋይ ነው። ዲያብሎስ ነው። ይህ ሰው ቡኤልዘቡብ ነው።”

322 ከሰድስት ባሎች የነበሯት፡ ያቺ ምስኪን አሮጊት ሴት ግን፡ አምስቱ ጋር ኖራለች፡ ሰድስተኛውም አብሯት ይኖር ነበር። ኢየሱስም እንዲህ አላት፡ “ሂጂና፡ ባልሽን ጠርተሽ ነይ።”

እሷም “ባል የለኝም፡” አለችው።

323 “አዎ ሰድስት አሉሽ፡ አምስት ባሎች ነበሩሽ፡ አሁን አብሮሽ ያለውም ሰድስተኛው፡ ባልሽ አይደለም።” አላት።

“ጌታ ሆይ!” አለች፡ ለምን? ብርሃኑ ያንን ዘር ስለ ነካው።

324 ካህናቱን በነካቸው ጊዜ፡ “ይህ ሰው ጠንቋይ ነው፡” አሉ። አያችሁ፡ ህይወት የላቸውም። አንዴ ድርጅት ከሆነ በኋላ፡ ተዳቅሏል፡ ያኔ ይሞታል።

325 ግን ይህች ሴት ግን ድቅል አልነበረችም፡ “ጌታ ሆይ፡ አያለሁ!” አለችው። ትልልቅ ቆንጆ አይኖቿ እንደዛ ሲያበሩ፣ እንባዋ በጉንጯ ላይ ሲወርድ ይታየኛል። “ጌታ ሆይ፡ አንተ ነቢይ እንደሆንክ አያለሁ። እኔም መሲሑን እየጠበቅኩት ነው። እና ያ መሲህ ሲመጣ፣ ይህንኑ ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል። እነዚህን ነገሮች ይነግረናል።”

እሱም “እኔ እርሱ ነኝ፡” አላት።

326 “እግዚአብሔር ሆይ!” እንስራዋን ትታ ሄደች። “ይሄውላችሁ! ያደረግኩትን ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩት።” ምን ነበር? ያ ብርሃን ያንን ዘር ነካው። ሕይወትም በዚያ ስለ ነበረች። በቀለች።

ዛሬም ያው ነው!

327 ሰነ መለኮታውያን ግን እንዲህ ይላሉ፦ “ቆይ እማ ቆይ። **እከሌ-ና-እከሌ** በዚ ጉዳይ ላይ፡ ፓስተር ሙዲ ምን ይላል፡ ልሰማው… ”

328 በዚ ዘመን ከፓስተር ሙዲ ጋር ምን ያገናኘዋል? ፓስተር ሙዲ በዘመኑ የኖረ ሰው ነው፡ አሁን ግን የለም። በትክክል። ሉተር በዘመኑ ኖረ፡ በዌስሊ ዘመን ግን አልነበረም። ዌስሊ በዘመኑ ኖረ፡ በጴንጤቆስጤ ዘመን ግን አልኖረም። ጴንጤቆስጤ በዘመናቸው ኖሩ፡ ከዚች ሰዓት ግን ወደኋላ የራቁ ናቸው። እኛ የመጨረሻው ሰዓት ላይ ነን። አዎ።

329 ድርጅቶቻቸው፡ እና አቋም አለመኖራቸው፡ እንደሌሉ ያረጋግጣል። ቃል በጉልበት ብቻ እንጂ፡ በትክክለኛው መንገድ ተገልጦላቸው አያውቅም። ዘሮች፡ የሀይማኖት ተቋማት… የሐይማኖት ተቋም ይመሰርታሉ፡ ከዚያ ከትክክለኛው ሰንዴ ጋራ ያረጀ ጂምሰን ዊድ ዘር ይቀላቅሉበታል፡ ወድያውም ይሞታል። ሰብሉ፡ ወድያው ወደ ጂምሰን አረም ይመጣል፡ እሾሃማ ሳማ፡ ወደ መሆን ይመለሳል። አይ-አህ፡ አያችሁ፡ ወድያውም ይሞታል። ከዛም በኋላ እንደገና ማሳው ያርሱት እና እንደገና ይጀምራሉ፡ ጥቂት እውነተኛ ዘር ይዘራሉ፡ ጥቂቶቻቸው ይበቅላሉ ወድያውም ይታነቃል።

330 እግዚአብሔር ግን፡ በዚህ በመጨረሻው ዘመን፡ በደሙ የታጠበውን ሕዝብ አወጣለሁ አለ፡ እነርሱም ለመምጣት አስቀድመው የተወሰኑ ናቸው። መምጣታቸው የማይቀር ነው። እግዚአብሄር ተናግሯልና። ይህም ይገለጣል… ዋና ምልክቱ፡ “ማንን እልካለሁ-… ” ሚልኪያስ 4፡ ምን ለማድረግ፡ “እንደገና ለማቃናት፡” በመጨረሻ ዘመን፡ እንዲፈጸሙ ቃል የገባቸው ነገሮች፡ ይመልሳቸዋል፡ ይህም መገለጡን ያስመጣል። በሚልኪያስ 4… ምን ይሰራል፡

ምንድነው? የአባቶችን እምነት፡ ወደ ልጆች መመለስ ነው። አያችሁ? እውነት ነው፡ ያንን ተመሳሳይ ነገር፡ ተመሳሳይ የእሳት አምድ፡ ተመሳሳይ ምልክት፡ ተመሳሳይ ድንቅ፡ ያው ኢየሱስን ወደ መድረክ መመለስ፤ ያው እንዲሆን ማድረግ፡ ያው እንዲሆን መሰበክ፡ ትላንትና፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው መሆኑን ማረጋገጥ።

331 "እመልሳለሁ፡" ይላል ጌታ፡ "በሜቶዲስት ትላትል፡ እና በደጎብያ ትል የተበላው ዓመታት ሁሉ፡ በባፕቲስት፣ በካቶሊክ፤ እና ያቺን—ትሎች የበሏት እምነት እመልሳታለሁ፡" ዘር አልባ የሐይማኖት ተቋም ግንድ ሆና እስክትቀር ድረስ ተበላች። "እንደገና ግን፡" "ዓመታትን ሁሉ እመልሳለሁ፡" ይላል ጌታ፡ ምን? "የተረሱትን ምልክቶች እና ድንቆች ሁሉ። እንደገና ወደ መጀመሪያው ዛፍ እመልሰዋለሁ፣ እቃናዋለሁ፡" ይላል ጌታ። ነቢይውም የተረጋገጠ ነቢይ ይሆናል። ስለዚህ ቃሎቹ መፈፀማቸው የማይቀር ነው። ኣሜን።

332 መንፈስ ቅዱስ፡ ብቻውን፡ በዘመናት ሁሉ ላይ፡ ብቸኛው የክርስቶስ መሎኮታዊው መገለጥ ገላጭ ነበር። በዘመናት ሁሉ፡ አስታውሱ! የጌታ ቃል በማን በኩል ሲመጣ ነበር? በነብያት፡ ብቻ። በትክክል። እውነት ነው አይደል? ነቢዩም፡ መጀመሪያ የተረጋገጠ መሆኑ ግድ ነበር። ነብይ ነኝ ስላለ ሳይሆን፡ ነብይ ሆኖ ስለተወለደ፡ ነብይ መሆኑንም ስለተረጋገጠ፡ የተናገራቸውም ሁሉ ከቃሉ ጋር ተስማምተው ስለተፈጸሙ፡ ሌላው ሁሉ ይቀጥላል። አያችሁ? የጌታ ቃል፡ በመንፈስ ቅዱስ ብቻ ይመጣል። መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፡ "ቃሉን፡ አባቶች፡ በመንፈስ ተነድተው፡ እንደጻፉት ይናገራል።"

333 ተመልከቱ። መጥምቁ ዮሃንስ እኮ መንፈስ ቅዱስ ባያመላክተው ኖሮ ኢየሱስን ፈጽሞ ማወቅ ባልተቻለው ነበር። ልክ ነው? [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—አርታዒ።]

334 መጥምቁ ዮሃንስ፡ ይህ ታላቅ ነብይ፡ መጥቶ እንዲህ አለ፦ "አሁን በመካከላችሁ አንድ አለ። እንደ ተራ ሰው በዙርያችሁ ይገኛል፡ እርሱም የእግዚአብሔር በግ ነው።" ዮሐንስም አለ፦ "እኔም መሰክሬአለሁ። መሰከርኩ። የእግዚአብሔር መንፈስ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ እንደ ርግብ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፣ በእርሱ ላይ ወረደ። ድምፅም፡ 'በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ።'"

ምን ነበር? መንፈስ ቅዱስ፥ "እመላክተዋለሁ።"

335 ዛሬም እሱን የምታውቁበት ብቸኛው መንገድ ይህ ነው፡ የአምላክን ሦስት መአዝናዊ መገለጥን ለማወቅ የምትችሉበት መንገድ፡ መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። ይህም ሊሆን የሚችልበት ብቸኛው መንገድ፡ አስቀድሞ የተወሰናችሁ ከሆናችሁ ብቻ ነው። ካልሆናችሁ፡ ፈጽማችሁ አታዩትም። ይሄን እንድታዩ አስቀድሞ የተወሰናችሁ ካልሆናችሁ፡ በጭራሽ አታዩትም፡ ምክንያቱ ያ ብርሃን ቢበራም ሄዳችሁ ልታሾፉበት፡ በሌላ መንገድ፡ በዕውቀት መንገድ ልታብራሩት ትችላላችሁና። እራሱ፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ ተገልጦ ያረጋገጠ ቢሆንም እንኳ፡ አስተውሉ፡ ቢሆንም፡ ማየት ከሌለባችሁ፡ አታዩትም።

336 እግዚአብሔር ዝም ብሎ፡ "**ይህንን** መርጫለሁ፣ **ያንን** መርጫለሁ አላለም፡" ነገር ግን በምን አወቃቸው... አስቀድሞ ሊወስን የቻለበት ምክንያት፣ እሱ ወሰን የለው ስለሆነ ነው፣ በዚህም—ሁሉንም ያውቃል... ወሰን የሌለው

ነው፡ ስለዚህ ሁሉንም ያውቃል። መጨረሻውን ያውቀዋል፣ መጨረሻውንም ከመጀመሪያው ማወቅ የሚችል ነው። አምላክ ስለሆነ። ይህን ማድረግ ካልቻለ ግን፡ አምላክ አይደለም። የሱ፡ ስር። ፍጻሜ የሌለው ነው። በጣም ጥሩ።

337 መንፈስ ቅዱስ ባይነግረው ኖሮ፡ ዮሐንስ በፍጹም ባላወቀው ነበር፡ የሱ፡ ስር። እግዚአብሔር እራሱን ከታላላቆች፣ ከተማሩት እና ከሌሎች እንዴት እንደሚሰውር እያችሁ? ተመልከቱ፡ ሰዎች ሁሉ ሲናገሩ... ያይ ዘንድ አስቀድሞ ለወሰነው ራሱን በተናቀ ነገር ይገልጥለታል። ወደዚህ ተመልከቱ! ሌሎች ሰዎች አጠገቡ ቆመዋል እርግቡን በጭራሽ አላዩም፡ ድምጽም አልሰሙም፡ አስቀድሞ ለተወሰነ ዘር ብቻ የተላከ ነውና። አስቀድሞ የተወሰነ! በትክክል፡ አስቀድሞ ተወስኗል!

338 ኢሳይያስ፡ ከመወለዱ፡ ከሰባት መቶ አሥራ ሁለት ዓመታት በፊት፡ በመንፈስ፡ ከሰውነት ስሜት ወጥቶ፡ እንዲህ አለ፦ "'የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያን ጥረጉ' እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ አለ... "

339 ያኔ ኢሳይያስ ሊያየው ከቻለ፡ ሚልክያስ አስቀድሞ ለተወሰነው ስለ መጨረሻው ነቢይ ተመሳሳይ ነገር ማየት አይችልም ነበርን፡ የብሉይ ኪዳን ነብያቶች መደምደሚያ የሆነውን፡ ያንን ታላቅ... ዋናው ነብይ በዘመኑ መጨረሻ እንደሚቆም ማየት አይችልምን? እያችሁ? አስቀድሞ ተወስኗል እያለን ነው። በእርግጥ እንዲሁም ነበርና። ሚልክያስም፡ አይቶታልና።

340 ኢየሱስም፡ "ልትቀበሉት ብትወዱስ፡ 'መልዕክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ፡' ተብሎ የተነገረለት ይህ ነው፡ ሚልክያስ 3፡ 'መንገድን በፊቴ ያዘጋጃል።" እያችሁ? እዎን፡ ያንን መልእክት ለማየት አስቀድሞ ተወስኗል። ወደዚያ አይቶ ያቺን ርግብ ስትወርድ ማየቱ ምንም እያስደንቅም፡ ያም ደግሞ በምድረበዳው ከእስራኤል ጋር፡ የተመላለሰው፡ ይጓዝ የነበረው ብርሃን ነው።

341 እግዚአብሔር ራሱ እንዲህ አለ፡ "በእርሱ ዘንድ ልኖር የምወደው ልጄ ይህ ነው።" አምላክና ሰው አንድ ይሆናሉ።

342 "እኔ ምስክር ነኝ፡" ዮሐንስ እንዲህ አለ፡ "እርሱን አየሁት፡ የአብ አንድያ ልጅ። እኔ ምስክር ነኝ።" አሜን!

343 ቀለል ያለ! ማለት ይኸው ነው። አባቱ፡ ታውቃላችሁ፡ አባቱ የእድሜ ባለጸጋ፡ ከትምህርት ቤት የወጣ፡ ታላቅ የሰነ መለኮት ሰባኪ ነበረ። እሱም ወደ አባቱ የሐይማኖት ተቋም መግባት የነበረበት ይመስላል። ያ ቢሆን ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ አይሆንም ነበር።

344 ያኔ በተወለደ ጊዜ እና ከመወለዱ ከሦስት ወር በፊት፡ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ነካው። የሱ፡ ስር። ማርያም ወደዚያ በወጣች ጊዜ፡ ታናሹ ዮሐንስ በእናቱ ማኅፀን ውስጥ፡ የስድስት ወር ልጅ ነበረ፡ ገናም አላደገም ነበር... ትንንሽ ጡንቻዎቹ እስካሁን ተንቀሳቅሰው አያውቁም ነበር። ማርያምም ሰግታ ነበር... እናቱ፡ ኤልሳቤጥ ማለቴ ነው፡ ትንንሽ ጡንጫዎቹ ገና እድገት ላይ ነበሩ፡ ከዚያ በፊት ግን የህያውነቱ ስሜት ተሰምቷት አያውቅም ነበር። ማርያምም መጥታ በነካቻት ጊዜ፣ ባቀፈቻት ጊዜ፣ ክንዶቿን ባሳረፈችባት፣ እጇን በጫነችባት ጊዜ ነው። እያችሁ? "እግዚአብሔር ተናገረኝ፡ እኔም፡ ልጅ ልወልድ ነው፡" ብላ ነገረቻት።

“አንቺ እና ዮሴፍ ተጋብታችኋል እንዴ? ”

“አይ።”

“ማርያም፡ ይህ እንዴት ይሆናል? ”

345 “መንፈስ ቅዱስ ይጋርደኛል፣ በውስጤም ልጁ ይፈጠራል። ስሙንም ‘ኢየሱስ’ እለዋለሁ። የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል።”

346 ‘ኢየሱስ’ የሚል ድምጽ ባሰማቻት ቅጽበት፡ ዮሐንስ በእናቱ ማኅፀን ውስጥ መወራጨት መጮህ እና መዝለል ጀመረ።

347 እሷ አለች፡ “ጌታ እግዚአብሔር ይባረክ! የጌታዬ እናት ከወዴት መጣች? ” የጌታዬ እናት! ኦህ፡ ማይ! “የጌታዬ እናት ከወዴት መጣች? ሰላምታሽ ወደ ጆሮዬ በደረሰ ጊዜ፡ ልጄ በማኅፀን ውስጥ በደስታ ዘለለ።”

348 እሱን የሚያስተምር ሴሚናሪ፡ ወይም ሌላ የሆነ ነገር አለመፈለጉ፡ ምንም አያስደንቅም። አንድ አስፈላጊ ሥራ ነበረው። የምድረ በዳ ሰው ነው፡ ወደ ምድረ በዳ ወጥቶ ይጠባበቅ ነበር። እግዚአብሔርም፡ በዚያ ተናገረው፡ ራሱንም ገለጠለት። ኦህ፡ እነሆ ሌላ መገለጥ! “ማን እንደሆነ እነግርሃለሁ። አንተ ነብይ ነህ። ቃልም ለአንተ ነው። አንተ ማን እንደሆንክ ታውቃለህ ወይ። መምጣት አለብህ።” ይህም ባለፈው እሁድ ለቀረበ ጥያቄ መልስ ይሰጣል። አያችሁ? “ማን እንደሆንክ ታውቃለህ፡ ዮሐንስ። አንተ ዝም በል፡ ምንም አትናገር። አንተም ወደዚያ ትወጣለህ። ይህንንም ታያለህ፡ ምልክት ከሰማይ ይመጣል፡ እንደ ብርሃንም፡ ርግብ ከሰማይ ትወርዳለች። ይህን ባየኽ ጊዜ እርሱ ያ ነው።”

349 ለዚህም ነው ኢየሱስ ወደ ውሃው በወረደ ጊዜ፡ ዮሐንስም ዙርያውን ቃኘ እነሆም ርግብም ስትወርድ አየ፡ እንዲህም አለ፦ “እነሆ የዓለምን ሐጥያት የሚያስወግድ! የእግዚአብሔር በግ! ይህ ነው።”

350 ኢየሱስ በቀጥታ፡ ወደ እርሱ ወደ ውኃው ሄደ። ሁለቱም የዮሐንስ ዓይኖች ሁለት የኢየሱስ አይኖች አዩአቸው። በሥጋ ሁለተኛ የአጎት ልጆች ነበሩ። ማርያም እና ኤልሳቤጥ የመጀመሪያዎቹ የአጎት ልጆች ነበሩ። ዓይኖቻቸው እርስ በርሳቸው ተያዩ። እግዚአብሔርና ነቢዩ፡ በዚያ ቆመው ነበር፡ አሜን።

351 ዮሐንስም “እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል። ለምን ወደ እኔ ትመጣለህ? ” አለው፡

352 ኢየሱስም፡ “አሁንስ እንደዚህ ይሁን፣ ነገር ግን፣ ስለዚህም ጽድቅን ሁሉ መፈጸም እንዳለብን፡ አትርሳ አለው።”

353 ዮሐንስ ለምን እንደዛ አደረገ? እርሱ መስዋዕት ስለነበረ። ዮሐንስ ነብይ ስለነበረ፡ መሰዋዕት ከመቅረቡ በፊት መታጠብ እንዳለበት፡ ጠንቅቆ ያውቃል። አቤት! አቤት! እርሱም ፈቀደለት፡ አጠመቀውም።

354 ባጠመቀውም ጊዜ፡ እነሆ፡ ሰማይ ተከፈተ፡ ኦህ፡ ማይ፡ ርግብ በርሱ ላይ ወረደ፡ ድምጽም እንዲህ አለ፦ “በእርሱ ዘንድ ለማደር የምወደው ልጄ ይህ ነው።” ኪንግ ጀምስ “በእርሱ ዘንድ ለማደር የምወደው” በማለት አስቀምጦታል። “ለማደር፡” ወይም… በፈለጋችሁት በኩል ብታዩት፡ ያው ነው፡ “በእርሱ አድር ዘንድ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው” ወይም፣ “ለማደር” የፈለጋችሁትን ብትሉት፡ ያው ነው። እሺ እንግዲህ።

355 ያን ጊዜም ለእርሱ ሲገለጥለት አይተነዋል። በዚያ የቆሙት ሌሎች ምንም አልሰሙም። የገለጠለት፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ብቻውን ነው።

356 ለጳውሎስ እና ለሌሎች አስቀድመው ለተወሰኑ ሁሉ፡ ራሱን በገለጠ ጊዜም ተመሳሳይ ነው።

357 ጳውሎስ ከቦታ ቦታ እየዞረ በነበረ ጊዜ፡ እንዲህ ብሎ ሊሆን ይችላል፦ "እነዚያን ሰዎች ይዤ፡ ካልሰባበርኳቸው፡ ዶ/ር ሳኦል አይደለሁም። እኔ'ኮ በገማልያል ሰር ነው ያደግኩት። ከሙዲ መጽሐፍ ቅዱስ ነው የተመረቅኩት... " ወይም ሌላ አይነቶች፡ አያችሁ። "እኔ'ኮ፡ ምሁር ነኝ። የምናገረውን አውቃለሁ። ያን የሆሊ-ሮለር መንጋ እሰባብረዋለሁ። እውነት እሎታለሁ፡ ብጹዕነትዎ፡ ብቻ እርሶ ከቦታ ቦታ የምንቀሳቀስበት ፈቃድ ይስጡኝ እንጂ፡ እያንዳንዳቸውን እዚያ ያሉ አዋኪዎችን አስራቸዋለሁ። መለኮታዊ ፈውስ የሚሉትን ነገሮች፡ እናስቆማለን።"

ኪሱ ውስጥ ከተተና፡ "ሄድኩኝ፡" እያለ ወረደ።

358 በዚያ ቀን፡ እቤት፡ ከቀኑ አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ፡ ብ——ብርሃን በፊቱ አንጸባረቀ፡ በምድር ላይም ወደቀ።

359 ለምን? አስቀድሞ የተወሰነ ዘር ስለ ነበረ። እግዚአብሔር እንዲህ አለ፦ "አዎን። መርጬዋለሁ። ስለ ስሜም መከራ እንደሚደርስበት ታላላቅ ነገሮች አሳየዋለሁ። ወደ አሕዛብ እልከዋለሁ፥ በሚችሉትም መንገድ ሁሉ አዋርደዋለሁ——በመዋረዱ ግን፡ እርሱ ስሜን ይሸከማል።"

360 ከዚያ በኋላ፡ ጳውሎስ፡ በላዩ ላይ የነበሩትን የክህነት አሸንክታቦች ሁሉ፡ ለሶስት አመት ተኩል፡ ወደ ምድረ በዳ ወርዶ ሰባበራቸው። ቃሉን ተምሮ፡ እሱ ራሱ ቃል እስኪሆን ድረስ፡ ወደ አረብ ምድር ወረደ። ከዚያ በኋላ በፍቅር ስንሰለት ተይዞ፡ እስረኛ ሆነ! "በትምህርት ያካበትኳቸው ልምምዶቼ ሁሉ ጠፍተዋል! የኢየሱስ ክርስቶስ እስረኛ ሆኛለሁ። አሜን! ፊልሞና፣ ወንድሜ ሆይ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ እስረኛ ሆኛለሁና። እሱ በል የሚለኝን ብቻ እናገራለሁ።"

361 እግዚአብሔር ዛሬ እራሳቸውን ወደ ፈቃዱ፡ ወደ ቃሉ የሚታሰሩ እስረኞችን ይፈልጋል።

362 ጳውሎስም የነበረው ያ ነው። የቱንም ያህል ዕውቀት ቢማርም'ኳ፡ እግዚአብሔርን ያወቀው ግን በመገለጥ ነው። የሰ፡ ሰር። በዚህች አለት ላይ ቤተክርስትያን እንደተሰራች፡ የሚናገር መገለጥ ሲመጣ፡ ያኔ፡ አዋቂ ነኝ ባይ ሁሉ ተጠራርጎ ይሸሻል። የሰ፡ ሰር። አስተውሉ፡ እሱ አስቀድሞ የተወሰነ ዘር ነበረ።

363 እርሱ ማን እንደሆነ ሊያሳያችሁ የሚችለው፡ ራሱ መንፈስ ቅዱስ፡ ብቻ ነው። ሌላ ማንም የለም፡ ሌሎቹ'ማ፡ ከዚህ ውስጥ "አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ" ወዘተረፈ፡ ያደርጉባችኋል። አያችሁ? ነገር ግን ይህ፡ የተገለጠው እርሱ፡ የሰማዩ አምላክ ጌታ እግዚአብሔር እንደሆነ፡ መንፈስ ቅዱስ ይገልጠዋል፡ ኦህ!

364 አሁን አስተውሉ። ነቢያት አይደሉም፣ ነገሥታት አይደሉም፣ ሌሎችም አይደሉም፡ ነገር ግን፡ እግዚአብሔር ራሱ ለመጀመርያ ጊዜ፡ የመለኮቱ ሙላት በአካል፡ በክርስቶስ ላይ፡ በሰው ስጋ ተገለጠ። መገለጡ ይህ ነው። እቤት፡ እቤት! አሁን አንድ አዝማች እዘምርላችኋለሁ፡

መንግስታት ፈረሱ፣ እስራኤል ነቅታለች፣ (አይደለም’ዴ? )
ነቢያት ያሉት ምልክት ሁሉ፡
የአህዛብ (ቤተ ክርስቲያን ተቋም ውስጥ ነች፡) ቀናቸው ደርሰዋል፡ በደንቃራ ተሰናክለዋል፡
(ከመካከላቸው የተባረራችሁ ሁሉ።) “የተበተናችሁ ሆይ፡ ወደ ራሳችሁ፡ ተመለሱ።”

የቤዛው ቀን ቀርቧል።
የሰዎች ልብ በፍርሃት ወድቋል፡

365 የሆሊውድ ቀልዳ ቀልድ የሚሸፍኑት አይደለም። በመቃብር ሰፍራ በጨለማ እያፏጨ እንደሚያልፍ፡ እንደ ህጻን ልጅ ሆኗል። አያችሁ?

መንፈስ ተሞሉ፡ መቅረዛችሁ ንጹህ ይሁን ይስተካከል፡
አይናችሁን እንነሡ ተመልከቱ! ቤዛችሁ ቀርቧል።

ሐሰተኛ ነቢያት ይዋሻሉ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ይክዳሉ፡
ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካችን አይደለም ይላሉ (አዎን።)
ይህ ትውልድ የእግዚአብሔርን መገለጥ ያቃልላል፡
እኛ ግን ሐዋርያት በረገጡበት ቦታ እየሄድን ነው።

የቤዛው ቀን ቀርቧል፡
የሰዎች ልብ በፍርሃት ወድቋል፡
መንፈስ ይሙላቹህ፡ መቅረዛችሁ ንጹህ ይሁን ይስተካከል፡
አይናችሁን እንነሡ ተመልከቱ! ቤዛችሁ ቀርቧል።

366 ወንድሜ ሆይ፡ መገለጡን ያዘው። ይህ ትውልድ፡ የእግዚአብሔርን መገለጥ የሚጠላ ትውልድ ነው! ተመልከት? ይህን የሚያደርጉት ሐሰተኛ ነቢያት ናቸው። “በፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።” የተዳቀሉ—ናቸውና። በእግዚአብሔር ቃል ፈንታ፡ ወደ ድርጅት የተዳቀሉ ናቸው፡ የእግዚአብሔር መገለጥ ራሱን የሚገልጠው፡ ቃል በሆነው በክርስቶስ ነው። ኦህ፡ ማይ!

367 እዚህ ማቆም እንችላለን፡ እንዲሁም… ከፈለጋችሁ፡ እንደገና ሰመለሰ ይሁን። እንግዲህ ይሄኛው… መቀጠል ከፈለጋችሁም፡ ምርጫው የእናንተ ነው። [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።] እሺ። ጥቂት ብቻ… እፈጥናለሁ፡ ስለዚህ፡ ከዚህ በኋላ፡ ለማረፍ የተወሰነ ጊዜ ታገኛላችሁ… የምትፈልጉትን ያክል በቂ ጊዜ ውሰዱ። እሺ።

ተመሳሳይ፡ አስተውሉ፡ ያ አስቀድሞ የተወሰነው ዘር!

368 እሱ ማን እንደሆነ፡ መንፈስ ቅዱስ ብቻውን፡ ያሳያችኋል፡ ነቢያት ወይም ነገሥታቱ አይችሉም። እዚህ ጋር ደግሞ እግዚአብሔር በሥጋ ተገለጠ። ሙላቱ ይህ ነው። ሙሉ በሙሉ ተገለጠ ለዓለምም ታወቀ። ኦህ፡ ማይ!

369 ታቦር ተራራ ላይ፡ የራሱ የእግዚአብሔር ምስክርነትን ተመልከቱ፡ “የምወደው ልጄ ይህ ነው። እርሱን ሰሙት!” ሙሴ ሕጉን ወክሎ ቆሞ ነበር። ኤልያስም ነቢያትን ወክሎ ቆሞ ነበር። እርሱም… እሱም እንዲህ አለ፡ እነርሱ ሁሉ ስለ ሞቱ፡ “የምወደው ልጄ ይህ ነው። እርሱን ሰሙት!” ሕግን፣ ነብያትን፣

እና-... ክርስቶስን በመወከል፡ ሶስት ሰዎች ቆመው ነበር። እሱ ግን፦ “**ይህ** ነው” አላቸው። በነቢያት በሙላት ያልተገለጠው፡ በሕግ ያልተገለጠው፡ በክርስቶስ ግን፡ በሙላት የተገለጠው፡ እግዚአብሔር፡ እርሱ ነው።

370 ሕግ እስር ቤት ያወርዳችኋል፡ ከእስር ሊያስወጣችሁ ግን አይችልም። ምሕረት የያዘው ግን ክርስቶስ ነው። ነቢያትም እናንተን ለመኮነን እና ለመግደል፡ የእግዚአብሔር ፍርድ ናቸው። ትክክል። ኢየሱስ ግን እናንተን እንደጠራችሁ፡ አስቀድሞ ለተመረጠ ዘር ለማሳወቅ፡ የእግዚአብሔር ፍቅር እና መገለጥ ነበር። “ይህ እርሱ ነው። እርሱን ስሙት!”

371 እወቁ! የመለኮት ሙላት የታወቀ ሆኗል። ይህ የተሰወረው ምስጢር አሁን ተገለጠ፣ ይህም እግዚአብሔር እርሱ መገለጡ ነው። የተቀባው ሰው፡ ክርስቶስ! አምላክና ሰው አንድ ሆኑ፡ **ክርስቶስ** ማለት ምን ማለት ነው? “የተቀባው፡” በመለኮት ሙላት በአካል ላይ በሙላት የተቀባው። ኧረ፡ ወይኔ! ሰዎች እንዴት ሊጠራጠሩ ይችላሉ?

372 ያኔ ድሮ፡ ሙሴ፡ በከፊል ያየው፡ ዳዊት፡ በከፊል ያየው፡ ኦህ፡ ማይ፡ አሁን ግን አምላክ ራሱ በሙላት ተገልጦ፡ በምድር ላይ ቆመ። እግዚአብሔር፡ በሙላቱ፡ ለቤተ ክርስቲያኑ የተቀደሰ ሕይወትን ይሰጥ ዘንድ፡ ስለ ሰዎች ኀጢአት ሞተ፣ ይህም በገዛ ቤተ ክርስትያኑ፡ በሙላት፡ የበላይነት ይኖረው ዘንድ፣ ለመጨረሻዎቹ ቀናት የገባውን፡ ቃል ኪዳን በእነዚህ በመጨረሻዎቹ ቀናት ይፈጽም ዘንድ ነው። አያችሁ? ምን ነበር...

373 አሁን አድምጡ። እሺ? ትንሽ እራሳችሁን ቆንጠጥ አርጉ። ተከታተሉ።

374 ኢየሱስ የተገለጠው ለምን ነበር? እግዚአብሔርን ለማሳየት። እርሱ አምላክ ነበር። አምላክ መሆንም ነበረበት፡ ሌላ ሊሞት አይገባምና፡ ነቢይ ሊሞት አይቻለውምና። እርሱ አምላክ ነበር። እርሱ የነቢያት አምላክ ነበር። እርሱ ራሱ ነቢያት ነበረ። እሱ ራሱ ነገሥታት ነበረ። እሱ ታሪክ ነበር። ሊመጣ የነበረውም እርሱ ነበር። የነበረው፣ ያለው፣ በዚህ ቀን ያለው፣ ትላንትና፣ ዛሬ፣ እና ለዘላለም ያው ነው። የተገለጠው ለዚሁ ዓላማ ነው።

375 በዚህ ዓላማም ቤተ ክርስቲያንን አገኘ፡ ይህም፡ የእግዚአብሔር ሙላት የሆነው እርሱ፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለውን የበላይነት ቦታው፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ የበላይነቱን፡ ቦታውን በያዘ ጊዜ፡ በእነዚህ በመጨረሻ ቀናት የተገባውን፡ የእግዚአብሔርን ቃል ሁሉ እንዲፈጽም ነው። ኢየሱስም፡ “በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፡ እኔ ወደ አባቴ እሄዳለሁና፡ ከዚህም በላይ ያደርጋል።” አያችሁ፡ ዓላማው ያ ነበር። ያኔም መገለጫ ነበረ። አሁንም፡ ዛሬ፡ ይህን በትክክል ማየት የሚችል፡ ቃሉንም እንዲሰራ የሚያደርግ ሰው ይፈልጋል...

376 አያችሁ፡ ኢየሱስ በደንብ አርጎ አይቶታል፡ እያንዳንዷን የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ በሱ እስኪገልጽ ድረስ፡ ፍጹም ለዚያ ቀን የተወለደ ነበረ። እርሱ የእግዚአብሔር መገለጥ ነበረ፡ እግዚአብሔር፡ ተገለጠ።

377 በዚህ በመጨረሻው ቀን፡ ቃል ኪዳንን ሁሉ፡ ይገልጥ ዘንድ፡ በመንፈሱ እና በደሙ ቤተ ክርስቲያንን ቀደሰ። አሁን፡ እነሆ፡ እሱ ተመልሶ ሄዶ እነዚህ ሌሎች ሰዎች በዚህ በመጨረሻው ቀን የረሱትን፡ እያነሣ፡ በመንፈስ ቅዱስ የሰባቱን ማኅተሞች ምስጢር ሁሉ መግለጥ ይችላል። አያችሁ፡ ራሱን እየገለጸ

ነው። አላማው ያ ነው። የሞተው ለዚህ ነው። ይህ ማለት ሁለተኛው የሦስተኛ መአዝናዊ መገለጫው ዘርፍ ነው። በመጀመሪያ፡ በክርስቶስ ራሱን መግለጽ፡ ከዚያም በቤተ ክርስቲያን በኩል ራሱን መግለጽ። ክርስቶስ ራሱ፡ ቃል እንደነበረ ሁሉ፡ ቤተክርስቲያንም ቃል የምትሆነው ቃሉ በእነሱ በኩል እንዲሰራ ስትፈቅድ ነው።

378 የተዳቀለ የእምነት ተቋም ከተቀበሉ ግን፡ ቃሉ እንዴት ሊሰራባቸው ይችላል? ግራውንድ ተደርጓል፡ ከዛ ሾርት ያደርጋል ከዛ በኋላ ፊውዙን ያቃጥለዋል። አያችሁ?

379 የኤልክትሪክ ኃይሉ፡ ማለት የእግዚአብሔር ቃል በነጻነት ሲፈስ ግን፡ እራሱን ይገልጻል። "እኔ የማደርገው ሥራ፡ እናንተም ትሆናላችሁ።" በመጨረሻው ዘመንም እንዲሁ ይሆናል፡ "እነሆ ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ፡ እርሱም የልጆቹን ልብ—ወደ አባቶች እምነት ይመልሳል።"

380 በዚያ ውስጥም፡ አምላክነቱን፡ አምላክነትን ራሱን በገዛ ቤተ ክርስትያኑ በሙላት የሚገልጽበት፡ በገዛ ቤተ ክርስትያኑም፡ የበላይ የሚሆንበት ጊዜ ይመጣል። ኦህ፡ ማይ! ምን? የተቀባው ሰው፡ አሁን የተቀባ ህዝብ ነው፡ ኦህ፡ ማይ፡ ይህም የተቀባች ሙሽሪት እና ሙሽራ ለማቅረብ ነው። የተቀቡት (ለምን? ) ሔዋን እና አዳም የናቁትን በመቀበል፡ የቃሉን ቅባት እየያዙ ይመጣሉ፡ "ቃሌ መንፈስ ነው" ብሏልና። አያችሁ፡ በቃሉ የተቀቡ ናቸው። ሔዋን የናቀችው፡ እሱ እንደገና መጣ እኛም ተቀበልነው።

381 ያ የተዳቀለ ሁኔታ፡ ያኔ ሄዋን ላይ እንዳደረገ፡ እንደገና እዩት።

382 ለሔዋን እንዲህ አላት፡ "**እንዲህ** ወይም **እንዲያ** አድርጊ እንጂ፡ **እንዲህ** አታድርጊ፡ **እንዲያም** አታድርጊ።"

383 ሰይጣንም "ኧረ! ይኸውልሽ፡" አላት... እሷም እርሱን ለመሰማት ዞር አለች።

384 በመጨረሻው ቀን ያለችው ሔዋን ግን ይሄን አታደርገውም፡ እንዳታደርገው አስቀድማ ተወስናለችና። የሰ፡ ሰር። እግዚአብሔር ራሱ ያውቀዋል። ይፈጽመዋል። የራሱ ያደርጋታል። እርሱ እንዳለው፡ የፊት... "የፊት መጨማደድ እና ጠባሳ የሌለባት ቤተ ክርስትያን ናት።" እሷም በግርማ ሞገሱ ውስጥ፡ በተገለጠው ቃሉ ውስጥ ትቆማለች።

385 ለአለም ምልክት ትሆናለች። የተለየች ትሆናለች-... ለዓለም የተለየች ትሆንባቸዋለች፡ ማለት፡ ሌላው ዓለም ሁሉ እሷን አይቶ እንዲህ ይላታል፡ "አይ፡ እቺ ደግሞ ሆሊ-ሮለር ነች። ሁለተኛዋ የአጎት ልጅ ነች። ከእኛ ዘንድ አይደለችም።" አያችሁ፡ ይህም ጥሩ ነገር ነው። አውቃለሁ። እሷ—እሷ **ከእነኚያ** ቡድኖች ጋር ነች።

386 በቀደም አንድ ሰው፡ ቆመን ስናወራ፡ እንዲህ አለኝ፡ "አንተስ፡ የየትኛው እምነት ተቋም አባል ነህ፡" አለኝ?

"የማንም፡" አልኩት።

"ምን? "

"የማንም፡" "እኔ የመንግስቱ ነኝ።" አልኩት።

“እሺ፡ እንዴት ተቀላቀልካቸው? ”

“በውስጧ የምትወለድባት እንጂ። መጥተህ የምትቀላቀልባት አይደለችም።” ኧሃ-ሃህ።

“ምን አይነት መንግሥት ናት? ”

“የኢየሱስ ክርስቶስ ምስጢራዊ አካል ናት፡” አልኩት።

387 “በአንድ መንፈስ ወደዚህ አካል እንጠመቃለን፡” ከመንፈሱ ተወልደን፣ የመንግሥት ልጅ እንሆናለን። በህይወታችን አሜሪካውያን አይደለንም፣ ጀርመኖች አይደለንም፣ ምንም አይደለንም፡ ክርስቲያኖች ነን። የተረጋጉ፡ በመንፈስ የሚመላለሱ፡ የፍቅር-ባሪያዎች ነን። ከዓለም ነገሮች፡ እና በዓለም ያሉን መብቶች ሁሉ፡ ሽጠን ይህንን ታላቅ ዋጋ ያለው ዕንቁ ገዝተናል፡ መንፈስ ቅዱስ እንዲገለጥ ፈቅደን እየተመላለስን ነን። እውነተኛዋ ቤተክርስቲያኑ ይህች ነች። የሐይማኖት ስርዓት በሚለው ሳይሆን፡ በገዛ ቃሉ፡ እያገለገላችሁ ከኖራችሁ፡ እናንተም እንዲሁ ናችሁ፡ እኔም እንዲሁ ነኝ።

388 አስተውሉ፡ ይህ የተቀባው ሰው፡ ክርስቶስ ራሱ፡ ኧረ አምላክ፡ የታወቀ ሆነ። አሁን ግን፡ ተመልከቱት፡ አሁን—አሁን ግን (ዋው!) የበላይነቱ ተቆጣጥሯል። እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ የተገለጠው፣ የእግዚአብሔር የመገለጡ ምስጢር በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

389 ይህ ታላቅ የመገለጥ ብርሃን ከድሮ ጀምሮ የዚህን ዓለም ጥበብ አሳውሯል።

390 በኢየሱስ ክርስቶስ ዘመን፡ እዚህ ምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፡ ታውረው—ነበር። “አንተ፡ እራስህን አምላክ ታደርጋለህን! ራስህን ከእግዚአብሔር ጋር ታስተካክላለህ!” አሉት፡ እሱ ግን ራሱ አምላክ ነበር እንጂ፡ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ብቻ አልነበረም። እያችሁ፡ አልገባቸውም ነበር። በነገራችን ላይ፡ አንዳንዶቻችሁ...

391 በአንድ ወቅት ከሃዲዎች ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ አላለም ሲሉኝ ሰምቻቸዋለሁ። እሱ ግን በትክክል ብሏል። በርግጠኝነት ብሏል። መጽሐፍ ቅዱሳችሁን ያላወቃችሁት እናንተ ናችሁ። በውኃ ጉድጓድ ውስጥ ለነበረችው ሴት ምን አላት? እያችሁ? ምን ነገራት?

392 “መሲህ እንደሚመጣ አውቃለሁ። እርሱም ሲመጣ፡ እነዚህን ነገሮች ያደርጋል።”

“የሚናገርሽ እርሱ፡ እኔ ነኝ፡” አላት።

እንዲሁም፡ ለጳውሎስ፡ እና ለተለያዩ ሰዎች ተናገረ።

አስተውሉ። አሁን ግን የበላይነቱን የያዘች ቤተ ክርስትያኒቱ ናት።

393 የእግዚአብሔር ታላቅ ምስጢር ሁል ጊዜ የዓለምን ጥበብ አሳውሯል። ሊያገኙት አይችሉም። በቃ ሊረዱት አይችሉም። ሰይጣን ይሄንን አይረዳም። ሊረዱት አስቀድሞ ከተወሰነላቸው ብቻ በቀር፡ እግዚአብሔር እና ክርስቶስ እንዴት አንድ እንደሆኑ፡ ማናቸውም ቢሆኑ ይሄን መረዳት አይችሉም። በየዘመኑ ሶስት ያደርጉታል። እያችሁ? በርግጥም ያደርጉታል።

394 አስተውሉ፡ ቀጥሎ፣ በሁለተኛ ደረጃ፣ የክብር ተስፋ የሆነውን ክርስቶስ፡ በእናንተ መገለጡ ነው። ያ ታላቅ፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ ተገለጠ፡ አሁን ክርስቶስም በእናንተ ተገለጠ።

ቶሎ እንላለን።

395 ተመልከቱ! በአንድ ወቅት ታላቅ የነበረው የእግዚአብሔር ምስጢር፣ በልቡ ውስጥ የነበረው ታላቅና የተሰወረ ምስጢር፡ አሁን በአማኞች ልብ ውስጥ እኑሮታል፡ ይህም፡ የክርስቶስ አካል ነው። በአንድ ወቅት ዓለም ሳይፈጠር በፊት በልቡ ውስጥ የነበረው፡ ይህ ታላቅ የእግዚአብሔር ምስጢር፡ አሁን ተገለጠ። አሰበው፡ ወዳጄ። ኦህ፡ ኦህ፡ እንጃ…

396 እንዳልገባን፡ እንዳልተረዳነው እርግጠኛ ነኝ። መቼም፡ እኔ—ማየት እንደሚጠበቅብኝ—ማየት አልቻልኩትም፡ እናንተም እንዲሁ እንደሆናችሁ እርግጠኛ ነኝ። አያችሁ?

397 የዘላለም አምላክ ምስጢር የሆነው፡ የእግዚአብሔር ታላቅ ምስጢር ግን፡ አሁን በኢየሱስ ክርስቶስ ተገለጠ፡ ከዚያም ለቤተክርስቲያኑ ተሰጠ። በአንድ ወቅት በእግዚአብሔር አሳብ የነበረው አሁን በክርስቶስ አካል ውስጥ አለ። ኢየሱስ ከቤተ ክርስትያኑ ጋር፡ ከሙሽራይቱ ጋር ፍቅር እየተጫወተ፡ ምስጢሮችን ሹክ ይላታል።

398 ታውቃላችሁ፡ ነገርን ለሚሰትህ፡ ልታገባት ለወደድካት ቆንጆ ሴት፡ እንዴት እንደሚነገር ታውቃላችሁ። በጣም ሰለምትወዳት፡ ምስጢሮችህን ታጫውታታለህ፡ ከጎንህ ታመጣታለህ፡ ታፈቅርሃለች ወዘተ። እንዴት እንደሆነ ታውቁታላችሁ።

399 ክርስቶስ፡ እግዚአብሔር፡ ለቤተ ክርስቲያን እያደረገ ያለው ይህንኑ ነው። አያችሁ? ያሉትን ምስጢሮች፡ የተሰወሩ ነገሮች እንድታውቅ ያደርጋታል። ቅምጥሊቱን አላልኩም፡ የገዛ ሚስቱን ነው (አያችሁ? በጣም ጥሩ፡ አሁን ተመልከቱ።) በጸጋው፡ የምስጢሩን መገለጥ እንዲያውቁት በማድረግ፡ ያውቃል! አቤት የእግዚአብሔር ጸጋ! ሰዎች፡ አውቀዋለሁ… የ—የሰዎች ስብሰባ፡ ወይም **ይህና፡ ያ፡** የግል ጉዳይ ነው ብላችሁ እንዳታስቡት ተስፋ አደርጋለሁ፣ ነገር ግን ሊቀበሉት ቢወዱ፡ እግዚአብሔር ለመላው ቤተክርስቲያን የሚያካፍለው ምስጢር ነው። አያችሁ? ወደ ውስጥ ለመግባት እየሞከረ—ማለት ለእኔ፡ ወይም ለአንተ ማለት አይደለም። ቤተ ክርስትያን ማለት ነው።

400 አንተም "እሺ፡ ታዲያ ለምን አይቀበሉትም?" ትለኝ ይሆናል፡ ሊቀበሉት አይችሉም። ራሱም ተናግሯልና፡ ዳግመኛም ብሏልና። "ምን ቢሆኑ ነው?" ኢሳያስ ማየት አይችሉም ብለዋቸዋል። አያችሁ? ድሮም እንዲሁ ነው…

401 ነቢዩ ጳውሎስ እንዲህ አለ፡ "በመጨረሻው ዘመን ሰዎች ችኩሎች፡ በትዕቢት የተነፉ፡ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ፡ ዕርቅን የማይሰሙ፣ ሐሜተኞች፣ ራሳቸውን የማይገዙ፣ መልካም የሆነውን የማይወዱ፡ ችኩሎች፡ በትዕቢት የተነፉ፡ አያችሁ፡ የአምልኮት መልክ አላቸው፡ ኃይሉን ግን ክደዋል፡ ከእንዲህ ዓይነቱ ራቅ። ወደ ቤቶች ሾልከው እየገቡ፡ ስነፎችን ሴቶች የሚያስቱ፡ በልዩ ልዩ ምኞትም የሚወሰዱ፡" ጸጉራቸውን የሚቆራርጡ፣ አጫጭር ቁምጣዎች የሚለብሱ፣ ወዘተረፈ። "በልዩ ልዩ ምኞት ተወስደው፡ 'ምንም

አይደለም። ኸረ፡ ዝም በሏቸው። እነሱ እብዶች ናቸው፡’” ይላሉ… አያችሁ? “እውነትን ወደ ማወቅ ፈጽሞ ሊመጡ አይችሉም። ኢያንበሬስና ኢያኔስ ሙሴን እንደ ተቃወሙት፡ እነዚህ ሰዎችም ተቃወሙት፡” ቤተክርስቲያንን መመስረት፡ እና ሰዎችን መሰብሰብ ይችሉበታል። የስ፡ ሰር።

402 ኢየሱስ ሙሽራውን ወስዶ እዚህ ባቆማት ጊዜ፡ “ይህች ናት፡” በማለት፡ ከእርሷ ጋር በሄደ ጊዜ ግን፡ “ስንፍናቸው **ያኔ** ይገለጣል።” እውነት ነው። ስንፍናቸው የተገለጠ ይሆናል።

403 ተመልከቱት፡ የዚህን ምስጢር መገለጥ በጸጋው ስለገለጠላቸው! ተመልከቱ! ይህ የተገለጠ ምስጢር፡ ታላቅ መገለጥ ሲገለጥላችሁ፡ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ሲሆን፡ የዓለም የሆነውን ሁሉ ትንቃላችሁ።

404 አሁን እንደገና እመለሳለሁ። ምናልባትም ይህን እላለሁ፡ ወደ ብዙ አገሮች ስለሚዘረጉ፡ ስለ ቴፖቹ ስል፡ ይህን እጠቁማለሁ፡ ይህ ቴፕ በመላው ዓለም ይሄዳል። አያችሁ?

405 እናንተ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቄአለሁ የምትሉ፡ ፀጉራችሁ እንዲያድግ ግን ድፍረት የሌላችሁ ሴቶች ሆይ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሴት ጸጉር ሲያወግዝ… አንድ ሰው ሚስቱ ፀጉሯን ብትላጭ በፍቺ የመፈታት መብት አለው። ይህን በማድረጉ፡ በእግዚአብሔር ፊት የተከበረ ነው። ፀጉሯን ብትቆርጥ፡ ራሷን ታዋርዳለች፡ ይላልና መጽሃፍ ቅዱስ። ይሄ’ኮ ተራ ነው፡ እናንተም፡ አንድ ሴት ጸጉሯን ቆርጣ ስትጸልይ፡ ተራ ነገር መሆኑን በትክክል ታውቃላችሁ። አያችሁ?

406 አጫጭር ቁምጣዎች፡ ሱሪዎች፡ ወዘተረፈ! መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር “እንዲህ የምታደርግ ሴት፡” (አቤት፡ በል እስኪ… ) “የወንድን ልብስ የምትለብስ፡ በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ ነው፡” የሆነ ቦታ ላይ እንዳለች ያረጀች ግም መታጠቢያ፡ የገማ፡ የቆሸሸች ናት። አያችሁ? ኸረ፡ ወይኔ! በእግዚአብሔር አፍንጫ ውስጥ ግም ነው! እና እንዲህ ባለው ሁኔታ ሆናችሁ ለመጸለይ ወይም ጸሎት ለማቅረብ ትሞክራላችሁ? እግዚአብሔር አይቀበለውም፡ ይንቀዋል። ትክክል ነው።

407 “እንዴ፡” ብላችኋል፡ “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ እስኪ ቆይ፡ አንተ የምትናገረው’ኮ ስለ ብሉይ ኪዳን ነው።”

408 እርሱ ትናንትናም፣ ዛሬም፣ እስከ ዘላለም ድረስም ያው ነው። የእግዚአብሔር ሙሉ መገለጥ ነው። እግዚአብሔር አንዴ የተናገረው ነገር፡ ሁልጊዜ ያጎላል እንጂ፡ አይለውጠውም። ሊለውጠውም አይችልም። ህጉ ጎልቶ ወጣ እንጂ፡ አልተለወጠም። ጎላ!

409 “‘የሚያመነዝር ሁሉ የሞት ፍርድ ይገባዋል፡’ ነገር ግን፡” አሁን አጎላውና፡ “ሴትን አይቶ የተመኛት አደረገው!” ትዕዛዙን አጎላው እንጂ። በጭራሽ አልለወጠውም።

410 “‘የሰንበትን ቀን ቀድሱት፡ የሚለውን አስታውሱ፡’” በሳምንት አንድ ቀን ነበረ፡ አሁን ግን ጎልቶ፡ የእግዚአብሔርን መንፈስ ከመጠባበቅ የሚመጣ “እረፍት” ነው። “ትእዛዝ በትእዛዝ፡ ሰርዓት በሰርዓት ላይ፡ እዚህ ትንሽ፣ እዚያም ትንሽ ነው። መልካም የሆነውን አጥብቃችሁ ያዙ። በባዕድ አፍ በልዩም

ልሳን ለዚህ ሕዝብ እናገራለሁ። ዕረፍት ይህች ናት እላለሁ። ይህ ከጌታ መገኘት ደስ የሚያሰኝ ነው።”

411 እነርሱ ግን መስማትን እምቢ አሉ፡ እራሳቸውን እያወዛወዙ ወደ ሐይማኖት ተቋማቸው ሄዱ። እህ-ሃህ። “ደስ ይላል፡” እያችሁ፡ የሰንበትን ቀን አጎላ፡ በተለይ ደግሞ የሰንበት ቀን አክባሪዎች፡ እና ሌሎች። ኦህ፡ ማይ! እሱ አይለወጥም። ያጎላዋል እንጂ። ልትቀበላቸው ሲኦል አፏን ከፍታለች።

412 አሁን፣ የመጨረሻው-ዘመን መልእክት፣ ለምን ውድቅ እንደተደረገ፡ ይታያችኋል። ይታያችኋል? [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።] ይህ ማለት፡ የምስጢሩ መገለጥ እንጂ፡ የሀይማኖት ተቋም አይደለም። እያችሁ፡ የሐይማኖት ተቋም አይደለም። መገለጥ ነው! እግዚአብሔር በሐይማኖት ተቋም አይታወቅም። የሚታወቀው በመገለጥ ነው።

413 ተመልከቱ! እግዚአብሔር በገዛ አካሉ ውስጥ ማለት፡ ክርስቶስ ነው፡ ክርስቶስ በገዛ አካሉ ማለት፡ ሙሽራይቱ ናት። ኧረ-ረ-ረ፡ እንዴ! እግዚአብሔር በክርስቶስ ተገለጠ፡ ክርስቶስ በሙሽሪት ውስጥ ተገለጠ! እግዚአብሔር ሴቲቱን፡ ከአዳም ሥጋ ወሰደ፡ እንደ ወደቀች፡ እንግዲያስ እግዚአብሔር ከክርስቶስ አካል፡ ቃል የሆነውን ሥጋውን፡ አካሉን ውሰዶ፡ በሐይማኖት ተቋምም ይሁን በስርዓቶች የማትወድቅ ሙሽራን እያመጣ ነው። ኧረ፡ አትወድቅም። ይሁን እንጂ፡ በንጹህ እና በማይበረዘው በእግዚአብሔር ቃል ዳግም እየተመለሰች ናት።

414 ይህንን ካሴት የሚሰማ ወንድ እና ሴት ሁሉ እንደሚረዱት ተስፋ አደርጋለሁ። እያችሁ?

415 ሁለተኛዋ ሔዋን ይህች ናት፡ ይሁን እንጂ የባልዋ ብቻ የሆነው፡ የጽሕና እና የቅድስና ቀሚሷ አታበላሸውም—አትሰብረውምም። ማንም ምንም ይበል ከቃሉ ጋር ትቆያለች። የፈለጋችሁትን ያክል የኢኪመኒካል እንቅስቃሴዎች እና ወገናዊነት ሊኖራችሁ ይችላል።

416 በዚህም በቅርብ ጊዜ፡ ሰደት መቀሰቀሳችሁ፡ ቸርቾች ሁሉ መዘጋታችሁ የማይቀር ነው። ታዩታላችሁ። ሐይማኖታዊ ተቋም ያልሆኑት፡ እንደዚህች የመሳሰሉ አብያተ ክርስትያኖችም፡ ለመጋዘን እና ለሌላ ይጠቀሙባቸዋል። በዚህም ምክንያት የኢኪመኒካል እንቅስቃሴ አባል ላልሆነ ግለሰብ ጸሎት ለማድረግ የሚሄድ ሁሉ፡ ወድያውኑ በጥይት ይገደላል። ሁሉም ተዘጋጅተዋል። የሉተራኑ፡ የበላይ መሪም፡ እንዲሁ ተናግሯል። ይኸው እዚሁ አለ፡ መጽሔታችሁ ውስጥ ማንበብ ትችላላችሁ። በትክክል።

417 እነሱ ምንም ቢሉ ለውጥ የለውም፡ ቤተ ክርስቲያን በትግሉ ውስጥ ጸንታ ትቆማለች። አስቀድማም በማረጋገጫ አሳይታለች፡ አሁንም ቢሆን በማንም ፊት ትደግመዋለች። የእግዚአብሔር ቃል ነው። ሁሉም የኢኩሜኒካል እንቅስቃሴዎች እና ሌሎች ነገሮች ሁሉ ይጥፉ። እሷ ግን ያለ ፊት መጨማደድ ወይም ያለ ጠባሳ ትሆናለች። በትክክል። በሰፍራዋ ትጸናለች።

418 እስተውሉ፡ እግዚአብሄር የገዛ ሰውነቱ በሆነው በክርስቶስ ላይ፡ ራሱን ተረከ። አሁንስ የሚያምረውን፡ ሦስት መአዝናዊ ዘርፍን አይታችኋልን?

419 እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል እንዳደረገው፡ ክርስቶስም በሰውነቱ፡ ማለት በቤተ ክርስቲያን በኩል፡ አስቀድሞ የገባውን ቃል ይተርካል።

420 "ስለ ኃጢአት የሚኮንነኝ ማን ነው? የአብን ሥራ አላደረግኩምን፡ ታዲያ—ውድቀቴ ምኑ ነው? እንግዲህስ እኛ በትክክል ሰርተናል የምትሉ ሆይ፡ እናንተ የሀይማኖት ተቋም ሆይ፡ እስኪ አሳዩኝ። አዎን። መሲህ ከመሆን የወደቅኩበት እስኪ አሳዩኝ። እግዚአብሔር መሲሑ ያደርጋል ብሎ በተናገረው በአንድ ምልክት ላይ የወደቀሁበትን፡ ማድረግ የተሳነኝ ካለ አሳዩኝ፡" አላቸው። አያችሁ? እግዚአብሔር በገዛ ሰውነቱ።

421 አሁን ክርስቶስም፡- "እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ።" እዩት፡ እዩት፡ ያው አምላክ ነው። አያችሁ? "እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ፡ ወደ አባቴ እሄዳለሁና፡ ከዚህም ይልቅ ታደርጋላችሁ፡" ቤተ ክርስቲያን በብርሃን ውስጥ ትንሽ ትቆያለች፡ አያችሁ። እርሱ የገባውን ቃል ትተርከዋለች። እግዚአብሔር የገባውን ቃል በክርስቶስ ሰውነት እንዳደረገ፡ ክርስቶስም የክርስቶስ አካል በሆነች በቤተ ክርስቲያን፡ ተመሳሳይ ሥራውን እየሰራ ነው፡ አያችሁ፡ በመጨረሻው ቀን በዛፉ ላይ እንደነበረው የመጀመርያው ፍሬ በመስጠት፡ የሙሽሪቱ ዛፍ ምስጢሩን እንድታውቀው አሁን እየሰጣት ነው።

422 ተመልከቱት፡ ዛፉ ቅርንጫፍ አወጣ፡ ሉተራን። ምን ሆን? ዛፉ መውጣት ሲጀምር፡ ፍሬው አብሮ ወጣ። ምን ሆነ? ተቋም አደረጉት። ከዚያ ቆራጩ ይመጣል፡ ባለቤቱ፡ አባትዬው መጥቶ፡ "ሞቷል፡" ይላል፡ ከዚያ ቆርጦ ይጥለዋል።

423 በመቀጠል ዌስሊያውያን መጡ፡ በመምጣታቸውም መልካም አደረጉ። ከዛስ ምን ሆነ? ፍሬውም ዳግመኛ ወደ ዛፉ ገባ፣ ወይኑንም ቈረጠው፣ ሞተም።

424 እስኪ አንድ፣ አንድ ቤተ ክርስቲያን አሳዩኝ... ማወቅ እፈልጋለሁ። የሰላሳ-ሶስት አመት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አለኝና። የትኛውም ቦታ ተደራጅታ፡ በተደራጀችበት ጊዜ ያልሞተች፡ ቤተ ክርስቲያን ካለች አሳዩኝ። ሪቫይቫል ከሌለው፡ ከቁጥር እና ከአሸንክታብ በቀር፡ እንደገና የተነሱበትን አንድ ቦታ አሳዩኝ። አያችሁ? የለም። ኖ፡ ሰር። ጨርሳ ትጠፋለች።

425 ስለዚህ ባለቤት ሲመጣ ምን ያደርገዋል? መጥቶ ይቆርጠዋል። አያችሁ? የእምነት ተቋም ፍሬ ያፈራል፡ በብርቱኳን ዛፍ ላይ የሎሚ ፍሬ ያፈራል፡ ስለዚህ መጥቶ ይቆርጠዋል፡ አያችሁ። አምጥቶ፡ ያስቀጥለዋል።

426 የዛፉ ልብ ግን የት ነው? መሃል ላይ። እና ከላይ እስከ ታች ድረስ፡ ሁሉንም ይቆርጠዋል...

427 እዚህ ሰሩ ላይ ዘር አለው። በውኃ ወንዞች ዳር እንደተተከለች ዛፍ፣ የእግዚአብሔርን ሕግና ፍቅር በልቡ የሚይዝ። "በውሃ ዳር እንደተተከለ፡" መዝሙር 1፡"እርሱም ቅጠሎቹም እንደማይረግፍ፡ በየጊዜውም፡ ፍሬውን የሚያፈራ ዛፍ ይሆናል።" እርሱም እነሆ...

428 ፍሬ በቶሎ የሚበስለው የት ነው? ዛፉ እናት ላይ። ለምን? ብርሃን በላዩ ላይ ነውና። አሜን! ትክክል ነው። በዚህ በመጨረሻ ቀናት ውስጥም፡ የሙሽራዋ ዛፍ፡ በዛፉ እናት ላይ ያፈራል።

429 አሁን እዩ፡ እርሱን አሰቡት፡ እርሱ "ከእባቡ ዘር፡" በተቃራኒ፡ የሕይወት ዛፍ ነው። በኤደን ገነት የነበረው የሕይወት ዛፍ፡ ያ ዘር "የሴቲቱ ዘር፡" እርሱ ነው። "እጆቻቸውን ዘርግተው ይህን ዛፍ ባይነካኩ ኖሮ፡ ዛፉን በልተው ለዘላለም መኖር ይችሉ ነበር።" ከእርሱ ዘንድ በልታችሁ ለዘላለም ትኖሩ ዘንድ፡ ሊበላ የተገባው ብቸኛው ዛፍ እርሱ ነው። ቃሉ ህይወት ነውና። ሔዋንም በኤደን ገነት የጣለችው የእግዚአብሔር ቃል፡ እንግዲህ ይህ ቃል ሲሆን፡ እንግዲያውስ፡ ይህ የተገለጠው ቃል፡ ማለት ክርስቶስ ይህ ነው።

430 ወደ ምድርም በመጣ ጊዜ እርሱ የሕይወት ዛፍ ነበር። ይህን ታምናላችሁ? [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ከዚያስ ሮም ምን አደረጉት? መቆረጥ ነበረበት። በውርደትም ዛፍ ላይ ተንጠለጠለ፡ "በእንጨት ላይ የሚሰቀል ርጉም ነውና፡" ስለ ሰው ልጅ እርሱ እርግማን ሆነ።

431 ስለዚህም ደግሞ በዚህ ምክንያት፡ የሙሽራይቱ ዛፍ አሳደገ፡ ይህም ዛፍ ደግሞ ወደሱ የተቃናች የሕይወት ዛፍ ናት፡ እንደ ባል እና ሚስት በኤደን ገነት ይሆናሉ፡ (ኦህ፣ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን) ያው ቃል እና ያው አምላክ ባልና በሚስት ሆነው እንደተገለጡ፡ ያው የሙሽራይቱ ዛፍ ዳግም ተመልሳ መጣች።

432 አስተውሉ፡ እራሱን በማስተዋወቅ! እንዴት... አቤት፡ እዚህ ውስጥ ብዙ ነገር አለ፣ ዝም ብለን መቀጠል እንችላለን። አስተውሉ፡ በኤደን ገነት ያለው፡ የክርስቶስ ሰውነት የሆነው፡ ይህ ዛፍ። ምን አደረገ፡ ምስጢሩን ለሙሽራይቱ ዛፍ እንዲታወቅ እያደረገ ነው።

433 ተመልከቱ፡ ሁለተኛው አዳም በሆነው፡ በክርስቶስ ተዋጀች። እርሱ እንዲሁ መሆኑን ታምናላችሁ? [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ከውድቀት ከተዋጀች ከሚስቱ ጋር እንደገና ወደ ቤት መጡ፡ ወደ ኤደን፡ ወደ ቤት ተመለሱ። ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ክርስቶስ፡ ሚስቱን እየመለሰ ነው። ሦስት መአዝናዊ ምስጢሩን እያችሁት አሁን? ["ኣሜን።"] እግዚአብሔር በክርስቶስ ተተረከ፡ ክርስቶስ በቤተክርስቲያን ተተረከ፡ ይሁ ሁሉ፡ የመጀመሪያውን አዳምና ሔዋን፡ አንድ የሆኑትን፡ ከአንድ መንፈስ እና ከአንድ ደም የተሰሩትን፡ በሌላም ሁሉ አንድ የሆኑትን፡ ወንድ እና ሴት እንደገና ለመመለስ ነው።

434 በመንፈስ፡ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ደም ናት፡ ምክንያቱ—ሕይወት ያለው በደም ውስጥ ነው። ወደ አካሉ የሚያጠምቀን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ ሰውነቱን፣ ሥጋውን፣ ቃሉን ብቻ የሚያውቅ ያ ነው። [ወንድም ብራንሃም መጽሐፍ ቅዱሱን መታ—አርታዒ።]

435 የሐይማኖት ተቋም፡ ይህን ፈጽሞ አይነካውም። መገለጥ ነው። እሷ ታውቀዋለች። ሔዋንም ይህን እውቃ፡ ወደቀች፡ ይህችኛዋ ግን ታውቀዋለች፡ በጭራሽ አትወድቅም። ለዚሁ ተጠርታለች! ሃሌሉያ! አቤት! ላለመውደቅ የተጠራች ናት። በጭራሽ አትወድቅም። ለዚህም አስቀድማ የተወሰነች ናት። "እግዚአብሔር ኃጢአት የማይቆጥርበት ሰው ብጹዕ ነው።" ሁለት ደርዘን ያህል ሆናችሁ እዚህ የተቀመጣችሁ እናንተ አገልጋዮች ሆይ፡ እኔ የምናገረውን ታውቃላችሁ። እያችሁ? "እግዚአብሔር ኃጢአትን የማይቆጥርበት ሰው ብጹዕ ነው፡" ዳዊት።

436 አስተውሉ፡ እርሱ ጋር፡ እንደገና ተዋጅታ፡ በሰው ሰውነት ውስጥ፡ እየበሉ፡ እየጠጡ፡ ዘላለም ለመኖር፡ ወደ ቤት ወደ ወደ ዘለአለም ህይወት አብረው

ይመለሳሉ። ኢሰያሰም አለ፦ “ቤት ይሠራሉ ይቀመጡባቸዋል፡ ወይንንም ይተክላሉ ፍሬውንም ይበላሉ። የሚሰሩት ቤት ሌሎች አይወርሱትም።” ከዘሮቻቸው ጋር አብረው ይቀመጡበታል እንጂ፡ ልጆቻቸው አይወርሱትም። እሱ ይገነባዋል ይቀመጥበታል። አሜን። “እርሱ የሰራው፡ ሌላ አይበላውም፡ ይሰራል፡ ራሱ፡ ይመገባል።” አሜን! ይህ ምንድነው? ሙሽራው ከእርሱ ጋር ትመለሳለች፡ እንደገና ወደ መጀመሪያው አዳምና ሔዋን ተዋጅታለች፡ ሞት ወደ ኋላ ቀርቷልና። መሰቀሉን መለስ ብለው አይተው ሞት እንደተከፈለ ያያሉ።

437 እና አሁን፡ በእምነት፡ ከእርሱ ጋር ተነስተን፡ አሁን በሰማያዊ ሰፍራ ተቀምጠናል፡ የተቤዠንን ወደ ኋላ ዞረን በመመልከት፡ ከእርሱ ጋር ወደ ቤት እንድንጓዝ፡ ባልየው እንዲመጣ በመጠባበቅ ላይ ነን።

438 በአዳምና በሔዋን፡ እና በእያንዳንዱ ነቢይ፡ በእያንዳንዷ ዘመን የተገለጠው፡ በሚመጣው፡ በነበረው፡ ባለው፡ እርሱም—ሊመጣ ባለው የእግዚአብሔር ሦስት መዝናዊ ዓላማ ተገለጠ። ሙሉ መገለጥ፣ የእግዚአብሔር ቃል መገለጥ፣ አዳምና የሔዋን፡ እንደገና ተዋጅተው፡ ወደ ቤታቸው መመለስ፡ የእግዚአብሔር ራሱን ማስተዋወቅ!

439 ያኔ በዳዊት ዙፋን ላይ ይቀመጣል (በትክክል? ) አሕዛብን ሁሉ፡ በብረት በትር ይገዛል። በሁለቱም ዳር ላይ—ዛፍ ይሆናል፡ ለሚገቡባት ሰዎች ሁሉ፡ ይህ ፈውስ ይሆናቸዋል... ቅጠሎቹም ለአሕዛብ ሁሉ ፈውስ ይሆናል። ነገሥታቱ ክብራቸውን ወደ እርሰዋ ያመጣሉ። ሊያረክሳት ወደ እርሷ የሚገባ ምንም ነገር አይኖርም። የጽዮን ተራራም፡ ቀንና ሌሊት በእሷ ላይ ብርሃን ይሆናል፡ የዳኑትም በብርሃኗ ይመላለሳሉ። ኦህ፡ ሃሌሉያ!

440 ስታስቡት፡ የተረት ታሪክ አይደለም፡ የሆነ የስነ መለኮት ጽንሰ ሐሳብም አይደለም። በቃሉ፡ ጎልቶ የሚታይ፡ በሁሉም ዘመናት እውነት የነበረው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነው። በዚህ ዘመንም እውነት ነው። አሁንም እዚህ እውነት ነው። በእኔ ዘንድ እውነት ነው፡ በእናንተም ዘንድ፡ ይህን መገለጥ በያዙ ወንድ እና ሴት ሁሉም እውነት ነው። ኣሜን።

441 እግዚአብሔርንም እዩት ራሱን እየገለጠ፡ በዚህ የሕይወት ደም ስር ውስጥ ምት ይመታል፡ ይህም እናንተ የእርሱ እስረኞች ስለመሆናችሁ ነው። እናንተ የፍቅሩ-እስረኞች ናችሁና። ዓለም ይስቃል፣ ያሾፍባቸዋል፣ “ና ውጣ፡” ሊላችሁ ይችላል። ልትሄዱ ትችላላችሁ፡ ይሁን እንጂ እስረኞች ናችሁ። እያችሁ? ሌሎች ሴቶች የሆሊውድ ድርጊትን ሊከተሉ ይችላሉ፡ በአንቺ ዘንድ ግን አይሆንም። እስረኛ ነሽ። ኣሜን። አየሽ፡ አንቺ የክርስቶስ እስረኛ ነሽ። ሌሎች ወንዶች ከፈለጉ፡ ማጨስ እና መጠጣት፡ እራሳቸውን ክርስቲያኖች፣ ዲያቆናት፣ ሰባኪዎች ሊሉ ይችላሉ፣ በእናንተ ዘንድ ግን አይሆንምን። እስረኞች ናችሁ፡ የቃሉ እስረኞች ናችሁ። የስ፡ ስር። የስ፡ ስር።

442 ምስጢሩን ለሙሽራይቱ ዛፍ እያስታወቀ፡ በሁለተኛው አዳም፡ በክርስቶስ ተዋጅታ፡ ከሞት ነጻ ወጥታ ከበሽታ፡ ከሐዘን ከውርዴት ወጥታ፡ ወደ መጀመርያው ገነት፡ ወደ ቤት፡ ለምትመለሰው፡ ምስጢሩን፡ የታወቀ ያደርጋል።

443 አሁን ሰሙኝ፡ ብዙ ሰዎች፡ የተሳሳተ ግንዛቤ አላቸው። የ—የ... ሰዎችን ክርስትያኖችን ማድረግ፡ እና ወደ ሰልጣኑ መለወጥ፡ የእግዚአብሔር ሃሳብ በፍጹም አይደለም። እናንተም “በሰልጣኑ ሰዎችን ክርስትናን እናስቀብላለን፡”

ትላላችሁ። ስሕተት ነው። "እሺ፡ መጠጥ ሊጠጡ አትየገባቸውም። ውሸት ሊዋሹ አይገባቸውም።" ሙሐመዳውያን በዚህ እንደሚበልጧችሁ ታውቃላችሁን? በአፍሪካ ውስጥ ያሉትን አረማውያን፡ ጥቁር ሰዎች፡ እናንተ በክርስትና ከምትፈበርኩት ሕግ አብዝቶ የሚሻል ሕጎች በጎሳዎቻቸው መካከል አላቸው።

444 ለምን፡ ሻንጋን የሚሉት ጎሳ ዘንድ እኔም ሄጄ ነበር። አንዲት ወጣት ልጃገረድ በተወሰነ የዕድሜ ክልል ውስጥ ካላገባች፡ የጎሳውን መዋብያዎችን ከላይዋ አስወግዳ፡ ጎሳውን ትታ—እንድትወጣ ትገደዳለች። ወደ ከተማ ገብታ፡ ተራ የቀን ስራ ትሰራለች። እንዲሁም... ወይም ከማግባትዋ በፊት፡ ድንግል መሆንዋን እና አለመሆንዋን ትፈተሻለች። ከአንድ ሰው ጋር ዝሙት ፈጽማ ከተገኘች፡ ሰውዬው... ማን እንደሆነ ትናገራለች፡ ሁለቱም በአንድነት፡ ይገደላሉ። አህ-ሃህ። ኦህ፡ እነዚህ ሁሉ—ነን-በሚሉት ፊት የተሻሉ ናቸው...

445 ክርስቲያን ነን-በሚሉ ሰዎች ውስጥ ይህ ብታወርዱትስ? ዘጠና-ዘጠኝ በመቶ የሚሆኑት በጠራራ ጸሐይ ይገደሉ ነበር። ትክክል ነው። ትክክል ነው፡ ወንዱም ሴቱም ሁሉ። ይህ እውነት እንደሆነ ታውቁታላችሁ።

"ምን? " "እኔ ንጹሕ ነኝ፡" ትላላችሁን!

446 "ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።" ይሄስ ምን ትይዋለሽ? አንቺስ እህት ሆይ፡ እራስሽን በሰዎች ፊት በዚያ መልኩ የምታቀርቢስ? ልክ እንደፈጸመችው ዓይነት ሴት ጥፋተኛ ነሽ። ገባሽ?

447 "ኦህ፡ ምን ችግር አለው።" ፓስተሩ ይህን ለመናገር ይፈራል፡ ለምን? እንዲህ አይነቱ የጸና አቋም ከያዘ'ማ የሐይማኖት ተቋሙ ታሰወግደዋለች። የተዳቀሉ ናቸው። ቃሉን አይቀበሉትም። ቃሉም እውነት ነው ይላል። ኢየሱስም እውነት ነው ይላል፡ እርሱም ራሰ ነውና።

448 አሁን አስተውሉ፣ እግዚአብሔር ራሱን እያሳወቀ ነው። አይደለም፡ ሰዎችን በስልጣን ወደ ክርስትና እምነት ተከታዮች ማድረግ አንችልም፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በክርስቶስ እንደነበረ፡ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ በመኖሩ፡ ባለው በመገለጥ እንጂ። እግዚአብሔር በክርስቶስ እንደነበረ፡ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ! ያኔ፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ ያደረገውን፣ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ያደርገዋል! እግዚአብሔር በክርስቶስ ያደረጋቸው ምልክቶች ሁሉ፡ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ያደርጋቸዋል! አቤት፡ ደስ ይላል አይደል? አሃ! ኦህ፡ ማይ! ይህ ደስ ይለኛል።

449 ኢየሱስም "በዚያን ቀን፡" አለ፡ ቀኑም ይህ ነው። "በዚያን ቀን፡" ይህ መገለጥ ሲታወቅ፡ "እኔ በአብ እንዳለሁ፡ አብም በእኔ እንዳለ፣ እኔ በእናንተ፡ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ ታውቃላችሁ።" መገለጡ በታወቀ ጊዜ፡ "እኔና አብ አንድ እንደ ሆንን በዚያን ቀን ታውቃላችሁ፡ እኔ በአብ ውስጥ፡ አብም በእኔ ውስጥ አለ።" ከዚያም መገለጡ በመጣ ጊዜ፦ ያኔ፡ "እኔ በእናንተ፡ እናንተም በእኔ ትሆናላችሁ።" ይኸው ነው። የመገለጥ ዘርፍ፡ ሦስት መአዝናዊ መገለጥ-... ለምን? መልሶ ለማምጣት ነው። ያ መሆን አለብን...

ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደመሆኑ መጠን ያንኑ አረጋግጧል።

450 እርሱ——ቃል ባይሆን ኖሮ፡ ቃሉን ባልተረከው ነበረው፡ አንድ ታላቅ ቲኦሎጂያን በሆነ ነበር። ዓለም የምትጠባበቀው እውነተኛው መሲሕ በሆነ ነበር። አያችሁ? የስ፡ ሰር፡ እርሱ ይሆን ነበር።

451 ዛሬም የሚፈልጉት ያ ነው፡ ቢሊ ግራሃምን የሚበልጥ——አንድ——አንድ ሰው፡ ወይም ከድርጅታቸው ጋር በትክክል የሚመሳሰል አንድ ሰው፡ መጥቶ ባፕቲስቶች የቆሙበትን ሰፍራ እንደማያውቁ የሚያሳቸው ይጠብቃሉ። በእውነት። የሚጠብቁት ያ ነው። ቤተ ክርስትያኒቱ ግን የሕያው አምላክ ምልክቶች እና ትሕትና እየተጠባበቀች ትገኛለች።

452 ኢየሱስ ታላቅ የሰነ መለኮት ምሁር አልነበረም። እሱ ተራ ገበሬ፣ የአናጺ ልጅ፣ ተብሎ-የሚጠራ ነበር። አያችሁ? ከቦታ ወደ ቦታ ተጉዟል፡ እግዚአብሔር ግን… “እንዳንዶቻችሁ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ታደርጋለህ ብሎ ሰለ እኔ የተናገረው፡ እኔም ሳልተርከው የቀረሁት ነገር ካለ አሳዩኝ፡” አላቸው።

453 ስለዚህ ቤተክርስቲያን ዛሬም ተመሳሳይ ነገር ማድረግ ትችላለች። ክርስቶስ ያደረገውን አሁን ቤተ ክርስቲያንም ታደርገዋለች። “እኔ በአብ እንዳለሁ፣ አብም በእኔ እንዳለ፣ እኔ በእናንተ፣ እናንተም በእኔ በዚያ ቀን ታውቃላችሁ።” አያችሁ? ጉዞ ወደ ጽዮን፡ ይኸው ነው፡ (ወዴት?) ወደ መንግስት! “እኔ በእናንተ እንዳለሁ በዚያ ቀን ታውቃላችሁ።”

454 አሁንም ይሄኛው ተከታተሉ። ይሄኛው፡ ደስ ይላል። ይህ እንዲያመልጣችሁ አልፈልግም። አሁን ሁላችሁም፡ እናንተ በቴፕ የምታዳምጡ፡ ጫካ ውስጥ ወይም የትም ሆናችሁ የምትሰሙ፡ አሁን አድምጡኝ።

455 “አብ እንደ ላከኝ፡ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ፡” ኢየሱስም አለ። አያችሁ? አሁን ተመልከቱ። የላከው አብ ራሱን በትክክል ይተርክ ዘንድ፡ ወደ እርሱ ገባ፡ እርሱ ቃል ነበርና። እናንተን የላካችሁ ኢየሱስም፡ ይህንን አምላክ ራሱ ለመተረክ፡ ከእናንተ ጋር ሆኖ እና በውስጣችሁ ገብቶ ይኗዛል። “አብ እንደ ላከኝ፡ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደሆንኩ፤ ስለዚህ እኔም እልካችኋለሁ፡ እናንተም ከእኔ የተነሣ ሕያዋን ትሆናላችሁ።” እሱ ምንድነው? እሱ ቃሉ ነው። የምትኖሩት በቃሉ ነውና። ኦህ፣ እንዴት በዚህ ላይ ርዕስ ወስጄ፡ ለሁለት ሰዓታት ያህል ብሰብክበት ደስ ባለኝ ነበር፡ አያችሁ፡ በዚያ ላይ፡ እሱ እንዴት ነበር… በዛ ላይ። አስተውሉ፣ አስተውሉ፣ “የላከኝ አባቴም፡” አብሮት ገብቷል። የሚልክ አባት… የላከን ኢየሱስም ገባ።

456 “ጥቂት ጊዜ አለ ከዚህም በኋላ ዓለም አያየኝም፡ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፡ እኔን፡” የግል ተውላጠ ስም፡ “እኔ፡” ግለሰቡ፡ ኢየሱስ፡ “እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡ በውስጣችሁም እኖራለሁ። እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ።” ወደኋላችሁ ተመልክታችሁ የሰራውን እዩት፡ የእናንተ ሰራም ተመልከቱት፡ ከዚያ በኋላ እራሳችሁን አወዳድሩ።

457 “በኖኅ ዘመንም እንደ ሆነ፡ በሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል። በሎጥ ዘመንም እንደሆነ፡” ዘመናዊው ቢሊ ግራሃም እና ኦራል ሮበርትስ ወደ ሶዶም ወርደው ሶዶማውያንን ሰበኳቸው፡ አይኖቻቸውንም፡ በወንጌል አሳወሩአቸው፡ አያችሁ። አንደኛው መልአክ ግን፡ መልዕክተኛው ከአብራሃም እና ከተመረጡት ወገን ጋር፡ ወደ ኋላ ቀረ፡ እና ምን አይነት ምልክት አደረገ? ተመልከቱ? አብርሃምስ ምን ብሎ ጠራው? ኤሎሂም፡ በሥጋ የተገለጠ

አምላክ አለው። አምላክ በእርሱ ዘንድ የሆነው፡ ኢየሱስ እርሱ ራሱ፡ በመጨረሻው ቀን በሙሽራይቱ ውስጥ እንደሚገለጥ አሳይቷል! ኧረ፡ እንደው፡ እንደው! የእግዚአብሔር አምላክ መገለጥ፡ ማለቂያ የለውም! ዘላለማዊ ነው፡ ይሄዳል ይቀጥላል ይቀጥላል።

458 እንግዲህ፡ አስተውሉ፡ እንደ መጀመሪያው አዳምና ሔዋን፡ ኃጢአት በሞት ከመለየታቸው በፊት እንደነበረ፡ አሁን አንዱ ክርስቶስ፡ ማለት ሁለተኛው አዳም፡ ሙሽራይቱን፡ በህይወት ከሞት ዋጃት፡ እንግዲህ አሁን ወደ ኦሪጂናል ኤደን ገነት እየተመለሰ ባለ ጊዜ፡ ሙሽራይቱን ከእግዚአብሔር ጋር፡ በኤደን ገነት ውስጥ፡ እንደ ባል እና እንደ ሚስት፡ ሕብረት ይኖራት ዘንድ አቃንቷታል፡ ክርስቶስ እና ሙሽራይቱ።

459 እግዚአብሔርም፡ በዚያ ቀን፡ "ሁሉ በሁሉ እርሱ ይሆን ዘንድ፡ መንግሥቱ ለአብ ይሰጣል።" "እሱ የሚናገረውን፡ እኔ እሰማለሁ።" ዳዊት፡ ክርስቶስ፡ ዳዊት በዙፋን ላይ ተቀምጦ፡ በሰው ዘር ሁሉ ዘንድ ነገሠ። "ገና እያሰቡ፡ አሳባቸውን አውቃለሁ። ከመናገራቸው በፊትም፡ እመልስላቸዋለሁ። ተኩላና በጉ አብረው ይሰማራሉ። አንበሳ እንደ ወይፈን ገለባ ይበላል፡ አብረው ይሰማራሉ ይተኛሉም። በተቀደሰው ተራራዬ ሁሉ አይጐዱም አያጠፉምም፡" በትክክል መሄድ የሚቻለውን ያህል፡ ወደ ኤደን ተመለሰ!

460 ሦስት መአዝናዊ ዓላማው ይህ ነው። አምላክ ሆይ፡ እንድናውቅ እርዳን! እንድናውቀው እርዳን!

461 አሁን ወደ መጀመሪያው ኤደን እየተመለስን ሳለን፡ አሁንም በድጋሚ በደንብ ያዳምጡ።

462 ከዚያም ከእርሱ ስንወለድም፡ በእርሱ እንሞላለን። ህይወታችሁን፡ እዩት፡ ህይወቱ በእናንተ ውስጥ ነው። እንግዲያውስ፡ ስራዎቻችን ሁሉ እርሱን የሚተርክ ሊሆን ይገባል።

463 የአንደኛው ዛፍ ህይወት—ወደሌላኛው ዛፍ እንደ መውሰድ ነው። ከፒር ዛፍ የዛፉን ህይወት ወስዳችሁ በአፕል ዛፍ ውስጥ ብትጨምሩት፡ ፒር ያፈራል። መሆንም አለበት፡ ምክንያቱ ጭማቂው፡ ማለት በውስጡ ያለው ህይወት፡ ህዋሱ የፒር ዛፍ ነው። በጣም ጥሩ።

እንግዲያውስ፡ ስራዎቻችን ሁሉ እርሱን የሚተርክ ሊሆን ይገባል።

464 ሰሙን ተሸክመናል። ልክ ነው? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ሰሙን መሸከም አለብን።

465 አሁንም አስታውሱ፡ እኛ አሁን፡ እንደ ሙሽራይቱ፡ በመንፈሱ ጸንሰናል። ኦህ፡ ማይ! ቤተ ክርስቲያን፡ ልጆችን እየወለደች ናት፡ አያችሁ፡ በሰሙ ከመንፈሱ ፀነሰች፣ ሰሙን በመሸከም ህይወቱን ታፈራለች፡ የበላይነቱ ምስክር፡ የትንሳኤው ምስክር በመሆን፡ እርሱ ለዘለአለም ሕያው ሆኖ የሚኖር እንጂ፡ ሙት እንዳልሆነ፡ የሕይወቱ ምልክቶችን ፍሬ በማፍራት ትመሰክራለች። የተመሰከረለት፡ የዘላለም ሕይወት ይህ ነው፣ ይህም እኛ በእርሱ ሆነን ሕያዋን መሆናችንን ለዓለም ያረጋግጣል። ዊው!

466 እንዴት ታውቃለህ፡ የቤተክርስቲያን አባል ስለሆንክ ነው? ምክንያቱ፡ ክርስቶስ በእናንተ በኩል እየኖረ፡ እናንተም ለሌሎች ነገሮች ሁሉ እስረኞች

ትሆኑለት ዘንድ——በመንፈሱ እጅግ ጸንሳችኋል። ኡህ፡ ማይ፡ ስለወንጌል ታስራችኋል፣ ስለ ቃሉ ታስራችኋል፡ እናንተ ራሳችሁ እስረኞች ስለሆናችሁ፡ የምታፈሯቸው ልጆች ሁሉ እንዲሁ ናቸው።

467 አስቀድማችሁ ስላረገዛችሁ፡ ምንዝርና መፈጸም አትችሉም። ክብር ይሁን! ሌላ ነገር አይዝም። የሕይወት ማሕፀን ለሌላ ነገር የተዘጋ ነው። አስቀድሞ በመወሰን፡ በቃ የርሱ ተደርጋችኋል። ያ ዘር ወደ ሕይወት መጥቷልና፡ ዓለም መግባት አይችልም። አቤት! አቤት፡ በዚህ ላይ ለአንድ ሰዓት ያህል መቆየት ብንችል እንዴት ደስ ይላል! እንደተረዳችሁት እርግጠኛ ነኝ። አያችሁ? አስቀድሞ ጨርሶታል፡ ክርስቶስ፡ እና የእርሱ የሆኑት ብቻ። ዘሩ ቀድሞም ነበረ። ዘሩ አስቀድሞ ነበር። መቼ ነው እዚያ የተቀመጠው? “ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ ለዘለዓለም ሕይወት አስቀድሞ ወሰኖናል።” እና ሕይወት-ሰጪ የሆነው እንደፈሰሰ፡ እዚያው የወደቀችው ያቺ ዘር... የሚገቡ ሌሎች ዘሮች ሁሉ፡ አይጸኑም፡ እንደው፡ አይሆንላቸውም። ያ ዘር በገባ ጊዜ ግን፡ ማኅፀኑን ፈጥኖ ይዘጋል፡ የቀረው ዘር ሁሉ ይባረራል፡ አያችሁ፡ እንደዛ ነው።

468 እናም በክርስቶስ፡ የተማረከ፡ እስረኛ ትሆናላችሁ። ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ፡ ህይወቱ ምስክር ያፈራል፡ ምልክቶቹን። ኡህ፡ ማይ፡ ማይ፡ ማይ! ተመልከቱ፡ የትንሳኤው ምስክር ይሆን ዘንድ የሕይወቱ ምልክቶች ማሳየቱ፡ ያ የዘለአለም ሕይወት ለዓለም ማረጋገጫ ሰጠ፡ ይህም እኛ ሕያዋን መሆናችንን ለዓለም መተረኩ ነው። አሰቡት እስኪ፡ ከቤዛችን፡ ከእግዚአብሔር ጋር ሕያዋን አደረገን፡ ለተመሳሳይ ዓላማ ፈጠረን፡ በቤተ ክርስቲያን፡ በእኛ ውስጥ ያለው የመፍጠር ህይወቱ ጋር ሕያዋን ነን።

469 ማለትም፡ ሙሴ በእግዚአብሔር ቃል፡ “ይሁን” ባለ ጊዜ፡ ዝንቦች ሆኑ። ዝንቦችን የሰራ አምላክ ሽኮኮዎችም ይሰራል። አያችሁ?

470 የፈለገውን ማድረግ ይችላል። መፍጠር ይችላል። ማንኛውንም ነገር ማድረግ ይችላል። አምላክ ነው። ያ ፈጣሪ የሆነ ሕይወት፡ በእናንተ ዘንድ የሚኖር፡ ያው አምላክ፡ አያችሁ፡ እንዲህ ማድረግ ይችላል... እስረኞች ናችሁና፡ ተናገር እስኪላችሁ ድረስ አትናገሩትም። ከተናገራችሁ፡ ግን፡ የእግዚአብሔር ቃል ነው። እንዲሁ እንዲሆን ተርኮታል። ሌላው ሁሉ እውነት ነው፡ እርሱም ያውቀዋል፡ እርሱ ሲናገር፡ የተናገረው ሊሆን ይገባል። አያችሁ?

471 እግዚአብሔር “እንቁራሪቶች ይውጡ፡” ሰላለ፡ ሙሴም በትሩን አንሥቶ፡ “እንቁራሪቶች ይውጡ፡” አለ። በቃ ወደ ውጭ አስተላለፈው። ትክክል ነው። እንቁራሪቶችም በሁሉም ነበሩ፡ በሁሉም ቦታ እንቁራሪቶች ነበሩ። ከየት መጡ? ማንም አያውቅም። ከዚህ በፊት አልነበሩም። ፈጣሪ እግዚአብሔር ግን በሰው በኩል እየሠራ፣ ነገሮችን፣ ሕያዋን ፍጥረታትን ፈጠረ።

472 የመጀመሪያውን እንቁራሪት የፈጠረው አምላክ ሁለተኛውን እንቁራሪት ማድረግ ይችላል። ሁሉንም እንቁራሪቶች ይሠራል። ኡህ፡ ማይ! ምን ለማለት እንደፈለኩ አያችሁ? በመጀመሪያ ሽኮኮ የሠራ፡ ሁለተኛውን ሽኮኮም ይሠራል፡ ሽኮኮዎች በሌሉበት ቦታ፡ ሽኮኮዎች ማድረግ ይችላል። የፈለገውን ማድረግ ይችላል! እርሱ አምላክ ነው! እርሱ አምላክ ነው! ኡህ፡ ማይ! ሕይወቱ! ሳስበው፡ ያንቀጠቅጠኛል! አህ-ሃህ።

473 አቤት፡ ከእርሱ ጋር መኖር፣ ከእርሱ ጋር ወደ ቤት እየሄድን ነን። ከእርሱ ጋር ለመኖር! ዘላለማዊ ህይወት ይዘን አብረን ዘለአለም ለመኖር፡ ከእርሱ ጋር ወደቤት እየሄድን ነው!

474 ይህ እግዚአብሔር እና ሰው አንድ የሆኑበት፡ የእግዚአብሔር ታላቅ የፍቅር ምስጢር ነው። አያችሁ? መላ ነገሩ፡ ሰውና እግዚአብሔር አንድ መሆናቸው ነው። ሰውና እግዚአብሔር በዚያ አንድ ነበሩ፤ ሰው እና እግዚአብሔር፡ እዚህ፡ አንድ ናቸው። አያችሁ? ይሄ ምንድነው? እርሱ የበላይ ሆኖ፡ በእርሱ መንፈስ መሞላት ነው። ያ የእግዚአብሔር ሰኬት ያ ነበር፡ የእግዚአብሔር ዓላማ ይህን ለማድረግ ነው። እርሱ በክርስቶስ ዘንድ፡ ክርስቶስም በእኛ ዘንድ፡ ሁላችንም በአንድነት፡ አንድ እንሆን ዘንድ ነው። መንፈስ ቅዱስም፡ ያው ነው፡ ለክርስቶስ ገለጠው፡ እዚህም ገለጠው፡ መለኮታዊ የሆነ የመፍጠር ኃይል ነው። ኦህ፡ ማይ!

475 በሙሴ በኩል ይህ ሁሉ መናገር የቻለ—ያው አምላክ፡ "እንቁራሪቶች ይውጡ፡" ያለው ያ ሰው በዚያም ቆሞ "ይህ ውሃ ወደ ወይን ጠጅ ይለወጥ፡" ያለው እርሱ ነው። አያችሁ? ኣሜን። ልክ ነው? [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።] እርሱ ያው አምላክ፡ አንዱ እርሱ ነው።

476 እሱ አይለወጥም። እግዚአብሔር በሰው ውስጥ እርሱ ነው። ያ መገለጫው ነው። የሚገልጠው ይህንን ነው። ለማድረግ እየሞከረ ያለው ይህንን ነው፡ የእግዚአብሄር ቃልም እየገለጠው ይገኛል። ፈጣሪ እግዚአብሔር እንጂ፡ ሰው መፍጠር እንደማይችል ያሳያል። ከዚያ በኋላ ሰው አይደለም፡ በሰው ውስጥ ያለው፡ ፈጣሪ እግዚአብሔር አምላክ ነው፡ ይህም አሁን ቤተክርስቲያኑ ነው። አሜን!

477 ከእርሱ ጋር፡ ለዘላለም ለመኖር፡ ወደ መንግሥተ ሰማያት እየሄድን ነን። እግዚአብሔርም ለቤተክርስቲያን ዘላለማዊ ፍቅሩን ይገልፃል።

478 አዳምጡኝ፡ አሁን በድንብ ስሙኝ። ይሄን እንዳያመልጣችሁ እፈልጋለሁ። ከዚህ ውጪ ሌላ ቸርች፣ ሌላ ምልክት፣ ሌላ ሕብረት፣ ሌላ ሰልጣን፣ ሌላ ምስክርነት፣ ሌላ ሰርዓት፣ ሌላ ተቋም፣ ተቀባይነት የለውም። እግዚአብሔር ከዚህ በቀር ሌላ አይቀበልም፡ "ይህም የክብር ተሰፋ ክርስቶስ በእናንተ መሆኑ ነው፡" እግዚአብሔር የሚያውቀው ብቸኛው ነገር ይህ ነው። ሌላው ሕብረት፣ ሌላው ቸርች፣ ሌላው ሰርዓት፣ ሌላው ተቋም፣ ምንም ይሁን፡ ሌላው ሁሉ ሙት ነው። ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ የበላይ ሆኖ ይኖር ዘንድ፡ እነዚህ ሁሉ ከነገሩ ተከርክመው፡ መቆረጥ ያለባቸው ክፍሎች ናቸው።

479 ወደ ኋላ መመለስ የለም! "የእኔ ድርጅት ነው፡" የምትል፡ አንድ ቅርንጫፍ ካለች፡ ያቺ ደግሞ፡ መቆረጥ አለባት። "የራሴ **እከሌ-እና-እከሊት** ይዣለሁ። **ይሄኛው** እንዲህ ይላል። እናቴም ሆሊ-ሮለር ትለኛለች።" ይህ ደግሞ፡ መቆረጥ አለበት። አያችሁ? "እይ፡ ባለቤቴ እነዚህን ቁምጣዎች እንድለብሳቸው እንደሚፈልገኝ አውቃለሁ።" ይህም፡ ይቆረጥ። አያችሁ? አንተ እና ክርስቶስ ብቻ እስክትሆኑ ድረስ፡ ተቆርጦ መከርከም አለበት። አያችሁ? እህ!

480 አሰቡት! በሕያው ቃል ሕያው የሆነው ክርስቶስ በህያው መገኘቱ፡ ኦህ፡ ሕያው ክርስቶስ፣ ሕያው መገኘት፣ ሕያው ቃል! ተከታተሉ! በገዛ ራሱ፡ በገዛ ራሱ ማሳያ ቤተክርስቲያኑን ያትማል።

481 በአባላት አይደለም! በሙሴ ዘመንም፡ አላደረገም። በሌላ በማንም ዘመን አላደረገም፡ በዓለም መጨረሻ፡ ጥፋት ወደነበረበት ሁኔታ ሲመጣም አላደረገውም። በሎጥ ዘመን፡ እግዚአብሔርም በሥጋ በነበረ ጊዜ፡ አባልነት አልነበረም። በግሉ ማሳያ ነበር፡ እያችሁ፡ በግል ማሳያ ነው።

482 አስታውሱ! ከመንፈሱ የተወለዱትን፡ እነዚያ ሰዎች፡ አሰቡ፡ እንዲህ ባለ ዘመን፡ እኛ አሁን እየኖርንበት ባለው በታላቁ በሐይማኖት ተቋም ዘመን፡ ሕያው እግዚአብሔርም—ሕያው ቃሉን፡ በቃሉ ያለውን ሕይወት፡ በዘሩ ውስጥ ያለውን ህዋስ ወሰዶ፡ በግል ደረጃ ያረጋግጠዋል! ቃሉም ዘሪ ሊዘራ ይዞት የወጣ ዘር ነው። ሕይወት፡ በቃል ውስጥ፡ በአንተ በግልህ ውስጥ ክርስቶስ ነው፡ አንተ ማድረግ የማትችለውን እርሱ ይተርከዋል፡ ይህም እርሱ እንጂ፡ አንተ አለመሆንህን ለማረጋገጥ ነው። ይህም ደግሞ፡ አንተ የእርሱ ሙሽራ ትሆን ዘንድ፡ ለእርሱ የ—የ—የፍቅሩ-ባርያ ያደርግሃል።

483 ሰማያትንና ምድርን በመካከላቸውም ያለውን ሁሉ የፈጠረ ሕያው አምላክ ይመስገን! እያስገርምም፦ "እርሱ አልፋና ኦሜጋ፡ መጀመሪያውና መጨረሻው፡ የነበረውና፡ ያለው፡ የሚመጣውም፡ የዳዊት ሥርና ሐረግ፡ ብሩህ የማለዳ ኮከብ መሆኑ አያስደንቅም።" ሁሉ-በሁሉ-እርሱ ነው።

484 የመገኘቱ፡ በግለሰቡ ውስጥ፡ እራሱን በራሱ የሚተርክበት ከግሉ ማሳያ ጋር፡ ለዘመኑ በተሰጠው የተሰፋው ቃል፡ በእናንተ ዘንድ እራሱን ይተርክበታል፡ ይህም የእግዚአብሔር ታላቅ መገለጥ ማሳያ ነው። እዩት፡ በግለሰብ ደረጃ እንጂ፡ በጭራሽ በቡድን አይደለም! ግለሰብ፡ በቡድን አይደለም! የእሱ መለያ ከግለሰብ ጋር ነው። ገብቷችኋል? [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ከመቶዲስቶች ጋር አይደለም፣ ከባፕቲስቶች ጋር አይደለም፣ ከፕሬስባይቴሪያኖች ጋር አይደለም፣ እንደ ሉተራን ሳይሆን፣ እንደ ጴንጤቆስጤ ሳይሆን። እንደ ግለሰብ!

485 "አንዱን ወሰጄ አንዱን እተወዋለሁ፡ እለያቸዋለሁ።" ትክክል ነው። "በእርሻ ላይ ሁለት ይሆናሉ፡ አንዱን ወሰጄ አንዱን እተወዋለሁ። በአልጋ ላይ ሁለት ይተኛሉ፡ አንዱን ወሰጄ አንዱን እተወዋለሁ።"

486 ቡድን አይደለም። በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ለእግዚአብሔር ሰለተገዛ ሰለ ሌላው ግን ምንም ደንታ ሰለ ሌለው፡ ሰለ አንድ የእግዚአብሔር ልጅ የተጸነሰ የግል ማሳያ ነው። መንፈስ ቅዱሰም በእርሱ ደም ሰር እየመታ ሕይወቱን ይኖራል፡ ይህም ቃሉ ራሱ፡ ለህዝብ እና ለዓለም የመተረኩ፡ የግሉ—የግሉ ማሳያ ነው።

487 አለም በጭፍን እንደዚህ ባለ ነገር እንዴት መኳዝ ይችላል? ልክ እንደ ካቶሊኮች ቅዱስ ፓትሪክ ትዝ እንዳላላቸው እሰከሞተበት ጊዜ ድረስ እውቅና አልሰጡትም። በሴንት ማርቲንም ያደረጉት ተመሳሳይ ነገር ነው፡ አላወቁትም። በሁሉም ዘመናት ውስጥ ያደረጉት ተመሳሳይ ነገር ነው።

488 ጆአን ኦፍ አርክ ያደረጓትም ተመሳሳይ ነገር ነው። እሷ መንፈሳዊ ስለነበረች፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፡ ጠንቋይ ሴት ናት በማለት አቃጠለቻት። ከመቶ ሃምሳ ዓመታት በኋላም፡ የእነዚያን ካህናት አጽም ቆፍረው በማውጣት ንስሐ እንዲገቡ፡ ወረወሯቸው።

489 በአጠገባቸው ያልፋል እንጂ፡ ትቷቸው እስኪሄድ ድረስ በጭራሽ አያስተውሉትም። ምድር ከመፈጠሩ በፊት እግዚአብሔር አስቀድሞ የወሰነውን ዘር ብቻ ነው የሚያነሳው። በኖኅ ዘመን የሆነውም፡ በሙሴ ዘመን የሆነውም ይኸው ነው፡ የኤልያስ ዘመን፡ የነቢያት ዘመን፡ የኢየሱስ ዘመን፡ በእያንዳንዱ ዘመን እስከዚህም ሰዓት ድረስ ያው ነው። የእግዚአብሔር ቃል በጸነሰ ግለሰብ ላይ፡ ለእግዚአብሔር ፈቃድ፡ ራሱን ባስማረከ፡ እስር በሆነው ግለሰብ ላይ፡ ቃሉ ብቻ፡ ይተረክ ዘንድ፡ ቃል በሰው እራሱን ይተርካል።

490 "የእኔ ቤተ ክርሰቲያን... " አትበል፡ አሁን፡ "የእኔ ቤተ ክርሰቲያን" ከዚህ ጋር ምንም ህብረት የለውም።

491 የግል ጉዳይ ነው፡ አንድ ሰው! ሲኦል ሁሉ ግን ይህን ትምህርት ይቃወመዋል። ገሃነም ሁሉ ይህን እውነት ይቃረናል፡ ግን እውነት ነው።

492 ኢየሱስ በፍጹም እንዲህ አላለም፦ "አሁን፡ ጴጥሮስ፡ አንተም ዮሐንስ፡ ሌሎች ሰዎች ሁላችሁ፡ መገለጡን አግኝታችኋል፣ አሁን ቤተ ክርሰቲያን ሁሉ ድኗል።" አላለም።

493 ለእርሱ ብቻ፡ ለግሉ ነበረች። "እኔም እልሃለሁ፡ እልሃለሁ፡" እላችኋለሁ አይደለም፡ "አንተ፡ ጴጥሮስ ነህ፡ በዚህች ዓለት ላይ ቤተክርሰቲያኔን እሠራለሁ።" **ጴጥሮስ** የሚለው ቃልም "ድንጋይ" ማለት ነው። **ድንጋይ** ማለት "የተናዘዘው፡" ወይም፡ "የተለየው፡" ማለት ነው።

494 በተለየው ድንጋይ ላይ፡ በአንድ ነገር ላይ፡ ማለት፡ በተጥሩት-ላይ፡ በተጠራች ቤተ ክርሰትያን ላይ፡ በዚህ **ድንጋይ** ላይ፡ በዚህ "መገለጥ" ላይ ነው። "ሥጋና ደም ፈጽሞ አልገለጸልህም። ነገር ግን በዚህ መገለጥ ላይ፡ በተጠሩት-ቡድን ላይ፡ በእነርሱ ላይ ቤተ ክርሰቲያኔን እገነባለሁ። የገሃነም ደጆች ሁሉ ደግሞ ሊቋቋሙት አይችሉም።"

495 "ከራስህ አንዲት ጠጉር አንዲት እንኳ አትጠፋም። አንተ የእኔ ነህ! በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ፡ የዘላለም ህይወት እሰጠዋለሁ፡ በዘመን ፍጻሜም አሥነሳዋለሁ።" መገለጡ፡ ይህ ነው። እነርሱን አላለም፡ "እርሱን" እንጂ፡ ግለሰብ እንጂ! ቡድን አላለም፡ ግለሰብ! ገሃነም ሁሉ ይቃወመዋል።

496 ምሥጢሩ የተገለጠው ለምትወደው ሙሽራ ብቻ ነው። ሊያየው የሚችለውም ያ ብቻ ነው።

497 እንዲህ አላቸው፡ "እናንተ ግብዞች፡ የሳር ውስጥ እባቦች፡ ኢሳያስ ሰለእናንተ መልካም ተናገረ። ወጥታችሁ እንዲህ የምትሉ፡ 'ኦህ፡ የቅዱሳን ነብያት! መቃብራቸውን አሳመረናል። ቀለም ቀብተናል የምትሉ።'" "መቃብር ውስጥ የከተታችኋቸው እናንተ ራሳችሁ ናችሁ፡" አላቸው። አላለምን?

498 በዘመናቸውም ለካቶሊክ አብያተ ክርሰቲያናትም እንዲሁ ተመሳሳይ ነገር ይላቸዋል፡ ከኒቂያ በፊት፡ በሮም ዘመን፡ ከመምረጣቸው በፊት፡ የብሉይ ኪዳን—የብሉይ ነብያቶች በተላኩ ጊዜ። የብሉይ ነብያት ከመሬት የወዳደቁትን እየበሉ፡ በመጡ ጊዜ፡ ልብስ ሳይለብሱ፡ የበግ ለምድ በላያቸው አርገው፡ ስለመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ለመጽናት ይሞክሩ ነበር። የካቶሊክ ቤተ ክርሰቲያን ግን ምሁራዊ ፅንሰ ሐሳባቸውን ፈለገች። ከዚያም ወጡ... ከዚያም ቅዱስ ኢራኔዎስ፣ ፖሊካርፕ፣ ማርቲን፣ የቀሩትም መጡ። እና ምን አደረጉ? ጀእን

ኦፍ አርክን፡ ቅዱስ ፓትሪክ፡ እና የቀሩትን ሁሉ፡ መቃብር ውስጥ አስገቧቸው። መቃብር ውስጥ ከተው፡ አሁን መጥተው ለጆአን ኦፍ አርክ እንዳደረጉባት መቃብሮቻቸውን ያሳምራሉ። ምን አደረጉ? መቃብር ውስጥ ከተቷቸው!

499 መንፈሱ ስለ እናንተ እንደተናገረ፡ እነሆ እኔም እላችኋለሁ፡ “የተለሰኑ ግድግዳዎች! ቃሉን እየተዋችሁ፡ የሰውን ምሁራዊ ፅንሰ ሀሳብ የተቀበላችሁ፡ ለራሳችሁ ስም የምታወጡ፡ ግብዞች። በእናንተ ዘንድ በሚኖረው በቃሉ፡ በእግዚአብሔር ዘር ጸንሣችሁ ከመምጣት ይልቅ፡ ሌላውን ዲቃላ ሁሉ ተቀብላችኋል።” “እንደ ጋለሞታ” መቀምጥዋ አያስደንቅም፡ ምክንያቱ “መንፈሳዊ ምንዝርናዎች ትፈጽማለችና፡” የእግዚአብሔርን ሳይሆን የሰውን ነገር ለሕዝቡ ታስተምራለችና።

500 እርሱ ግን “ታናሽ መንጋ ሆይ፡ አትፍራ፡ መንግሥቱን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ነው፡” አለ። ትክክል ነው። በእርግጠኝነት። አሁን እነሆ አግኛተናታል።

501 መጽሐፍ ቅዱስ፡ በራዕይ ላይ፡ እንዲህ ይላታል፡ “በምድር ነገሥታት ሁሉ ላይ የነገሠች ታላቅ ከተማ።” “ጋለሞታ” ተብላለችና። ምን ማለት ነው? እመቤት ነኝ እያለች ዝሙትን የምትፈጽም ሴት ማለት ነው። ለዓለም፡ ቺርስ የምትልበት፡ “ጽዋ በእጇ የያዘች፡” “ይህም... በዝሙትዋም ርኩሰት የተሞላ ግማት ነው።” ሴቲቱም ሴት ልጆች አሏት፡ እነዚህም ተመሳሳይ የሐሰት ትምህርቶች ይዘው የወጡ፡ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርትያናት፡ ተመሳሳይ ጥምቀት፣ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ይልቅ፡ በእጅ መጨባበጥ፡ እና የሙሽራውን ስም ከመጠቀም “አባት፣ ልጅ፣ መንፈስ ቅዱስ፡” ወዘተረፈ፡ የሚሏቸው የሐሰት ትምህርቶቻቸው... ሙሽራይቱ፡ ወዘተረፈ።

“ምንም ለውጥ አያመጣም፡” ትላላችሁ አይደል። ያመጣል።

502 ሰሜን በቼክ ላይ፡ “ለተከበሩ፡” ለ “አገልጋዩ፡” ወይም ሌላ ሌላ፡ ብዬ ካስፈርኩት፡ ያንን ገንዘብ ማንም አያወጣም። ይህ እውነት ነው። ባንክ ቤቱ ላይ ይወገዳል። እሀ-ሃህ። አስተውሉ። በጣም ጥሩ።

503 ይህ ሁሉ ምስጢር የሚገለጠው ግን፡ ለሙሽራይቱ፡ ቃል እንደገባለት ብቻ ነው። ገሃነም ይህን እውነት፣ እና የዚህን ምስጢር መገለጥ ይቃወማል። ሙሽራይቱ ግን በዚህ ላይ ጸንታለች። ያ አቋምዋ ነው።

504 ቤተ ክርስትያን ሆይ፡ ለምን ተራብሽ፡ ለምንስ ተጠማሽ? እብ ይህን የተደበቀ ምስጢር ሊገልጥላችሁ ነው። እናንተ ግን ከሰውነታችሁ ብዙ ነገር አስወግዱ። ስራችሁን ካዱ፡ ሚስታችሁን ካዱ፡ ባላችሁን ካዱ፡ ልጆቻችሁን ካዱ፡ የዓለም አሳብ ሁሉ ካዱ፡ አንዳንድ ፓስተርን ካዱ፡ አንዳንድ ሰዎችን በህይወታችሁ ላይ ካዱ፡ ይህ ሁሉ ግን በጥልቅ በልባችሁ ውስጥ ረሃብ፡ እና መጠማት መኖሩ ስታውቁ ይሁን። አያችሁ፡ እግዚአብሔር፡ መገለጡን ለእናንተ ሊሰጥ እየፈለገ ነውና። የመጨረሻው ዘመን ደርሷል። አሁን አስተውሉ።

505 እንደገና ወደ ኋላ እንመልከተው። ይህንን ሁሉ ማለፍ አልችልም። አያችሁ? አሁን አንድ ደቂቃ ብቻ ወደዚህ እንድትታዩ እፈልጋለሁ፣ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እንዘጋለን። ታርፋላችሁ... ለአንድ ደቂቃ ያህል ያልተከፋፈለ ትኩረት ብቻ ስጡኝ።

506 አስተውሉ፡ የቆላስይስ ሰዎች፡ 18ኛ ቁጥር ላይ። በቆላስይስ መጽሐፍ ላይ፡ 18ኛ ቁጥር።

> እርሱም **የአካሉ ማለት** የቤተ ክርስቲያን **ራስ ነው፡ መጀመሪያ ከሙታንም በኵር ነው፡ እርሱም እርሱ—በሁሉ** የበላይ **ይሆን ዘንድ ነው።**

507 "እርሱ የቤተክርስቲያን ራስ ነው፣ እርሷም አካሉ ናት፣ እናም እሱ የበላይነቱን ይፈልጋል።" አሁን አዳምጡ፣ አሁን ስንቀጥል አዳምጡ። ምን? እርሱ ልክ እንደ አዳም፡ ከእርሱ ዘንድ እንደተወሰደች፡ ስጋ እና አጥንት፡ እንደ፡ ሙሽራራዋ፡ የአካሉ፡ የሙሽራይቱ ራስ ነው።

508 "ከሙታን መወለድ፡" አያችሁ፡ ከአለማመን ኃጢአት፡ ከሙታን መወለድ፡ ያ ነው።

509 ሄዋንን ምን ገደላት? አለማመን። ልክ ነው? በምን አለማመናቸው? በምን፡ በእግዚአብሔር አለማመን-... ነውን? አይደለም። በእግዚአብሔር'ማ እምነት ነበራት። በትክክል። "እግዚአብሔር የለም" ብላለችን? ኖ፡ ስር። ከሃዲ አልነበረችም። "እሺ፡" "ይኸውልህ፡ እኔ ቃሉን በሙሉ አላምንም" ብላለችን? ኸረ፡ በጭራሽ። ከአንዲት ትንሿ በቀር ሁሉንም አምናለች። አያችሁ?

510 አሁን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ በራእይ መጽሐፍ፡ ኢየሱስ ራሱ ተናግሯል፡ "እኔ—እኔ ኢየሱስ ስለዚህ ነገር እንዲመሰክርላችሁ መልአኬን ላክሁ"? "ማንም ከእርሱ አንዲት ቃል የቀነሠ፡ ወይም በእርሱ ላይ አንዲት ቃል የሚጨምር።" ስለዚህ ይህ ሁሉ የልብ ህመም እና ሀዘን አንዲት ሴት አንዲት የእግዚአብሔር ቃል ከመጠራጥርዋ የተነሣ ብቻ የመጣ ከሆነ፡ አሁንስ አንዷን ቃል ተጠራጥረህ ዝም ይልሃልን? ዝም ካለህ ጻዲቅ አይሆንም። አህ-ሃህ። አያችሁ? አየህ፡ ልክ አይደልም። የተወገዘ ነውና...

511 እነሆ አንድ ሰው ቆሞ፡ በተጠራጠረው በአንድ ቃል ምክንያት ይህን ሁሉ የልብ ህመም አመጣ፡ ከዚያም ወደ ፊት ሄዶ የዓመታት ልምድ እና መጽሐፍ ቅዱስ እና የመሳሰሉትን ቀሰሞ፡ ሌሎች ህይወታቸውን የሰጡበትን፡ ለአንተ እንዲህ "ኦህ፡ ሄደ መብላት ትችላለህ። ችግር የለውም፡ ዞሮ ዞሮ፡ እመልሥሃለሁ፡" ይልሃልን? ኦ! እግዚአብሔር የሰው ፊት አይቶ አያደላም፡ ስለዚህ... ? ... አያችሁ? አያችሁ? እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያዳላም። አሁን አስተውሉ።

512 አሁን አስተውሉ። "እርሱ የአካሉ ራስ ነው" በእግዚአብሔር ቃል፡ በአለማመን ሐጢያት የተውለደ ነው። ያ አባባይ-... እያንዳንዱን ቤተ እምነት፡ እያንዳንዱን እምነት የሚያባብል ነው፡ አያችሁ። በቃሉ አለማመን፡ እርሱም የሕይወት ቃል፡ ራሱ ነው። አያችሁ? ሕይወት ያለው፡ ቃሉ፡ ብቻ ነው። ሌላ ማንኛውም ቃል ድቅል ነው። ምንም ያህል ቢመሳሰልም፡ ቃል አይደለም።

513 ሔዋን ለግል ዕውቀት የቀየረችውን ቃል፡ የራሱን ሕይወት ያወጣል። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እደሆነች፡ አያችሁ? በአንዳንድ ሰዎች አመለካከት። ሙሴ የሚነደውን የቁጥቋጦ ልምምድ እስኪያገኝ ድረስ ስለ እግዚአብሔር የራሱ ታላቅ አመለካከት ነበረው፡ ከዚያም ውድቀቱን አየ። ሙሴ የጎደለው የሚነደውን የቁጥቋጦ ነበር። ቃሉም የሐይማኖት ተቋም የሌላቸው ነገር ይዟል።

"እርሱ፡ ራስ፡ የትንሣኤ ፍሬዎች መጀመሪያ ነው።"

514 ከፈቀዳችሁ፡ ስለዚህ ስለ "መገለጥ"፡ ትንሽ ሰፋ አርገን፡ ወጣ እንላለን። [ጉባኤው ሁሉ "አሜን፥" አለ።—አርታዒ።] እሺ እንግዲህ። በጣም ጥሩ፡ እሺ፡ ትንሽ ብቻ።

515 "እርሱ የትንሣኤ ፍሬዎች መጀመሪያ ነው።" ልክ ነው? [ጉባኤው ሁሉ "አሜን፥" አለ።—አርታዒ።] ተመልከቱ። ታዲያ፡ እሱ ምንድን ነው? "እርሱ የአካሉ ራስ፡ ቤተክርስቲያኑም፡ ሙሽራ ነው።" እህ-ሃህ።

516 ከዚያም፡ የሙሽራዋ-አካል ጭንቅላትን መከተል አለበት፡ ምክንያቱም የምስጢሩ አካል የትንሣኤውም አካል ነውና። ይህ አለመሆን የማይቻል ነው። ኡህ፡ ማይ! እግዚአብሔር ራሱን የገለጠበት መንገድ እና በቃሉ ያስነሳበት መንገድ፣ የእግዚአብሔር ምስጢር አካል ነው፡ ስለዚህም ቤተክርስቲያኑን ገልጦ በዚያው ቃል ያስነሣታል። የሦስት መአዝናዊ ምስጢር አካል ነው።

517 ራስ ከመቃብር እንደተወሰደ ሁሉ፡ አካሉም ወደ ኤደን ሊከተለው ይገባል። የቤተሰብ ራስ የሆነው፡ ሰውዬው፡ ሙሽራው፡ ባለበት ሁሉ፡ ሙሽራዋ የሙሽራው ሰውነት ስለሆነች፡ እርሱም የሙሽራዋ፡ ራስ ስለሆነ፡ ትከተለዋለች። ራሰም ተገልጦ፡ ከዘላለም ሕይወት ጋር መጥቷል፡ ሰውነትም እሱን መከተል ይጠበቅበታል፡ ምክንያቱ የባል እና የሚስት ህብረት ነውና። አሜን! እና አካሉ በሆነው፡ ተመሳሳይ ቃል እስከፀነሳችሁ ድረስ፡ ቃሉን በወሰዳችሁ ጊዜ፡ አካሉን ተቀብላችሁ፡ በእርሱ ዘንድ ሆናችኋል። ቃሉ እንጂ፡ የሃይማኖት ሰርዓት አይሰራውም! ኡህ፡ ማይ!

518 ዛሬ ከሰአት በኋላ እንድንቀጥል የሚያስችል ርዕስ ማውጣት አያስችለንምን? ኧረ? አቤት፡ አያምርም ወይ? አያችሁ? እሰኪ ምን እንደሆነ፡ አሰቡት።

519 ስለዚህ፡ አካሉ... ይህን እንዳትረሱ ከራስ በቀር ሌላ አያውቅም። ስለዚህ፡ ይህ አካል፡ ከቃሉ በቀር ሌላ አይነት ራስ ማወቅ አይችልም። ምክንያት፡ ራ— ራስ ከአካል ጋር የተገናኘ ነውና፡ ራሰም ቃል ነው፡ ቃሉም ያው ቃል ነው፡ አንድ ራስነት! ስለዚህ፡ የሐይማኖት ተቋማት፡ ብጹዓን አባቶች፡ እና ሌላው ሁሉ፡ የሞተ እበት ነው። አንድ ራስ አለ፡ እርሱም ክርሰቶስ ነው። አካሉ የሚያውቀው አንድ ነገር ነው፡ ቃል ብቻ!

520 አሁን በዚህ በአካል ውስጥ፡ "በአባት፣ በልጅ፣ በመንፈስ ቅዱስ" ሰም፡ የተጠመቀ አንድ ሰው ካለ አሳዩኝ? የምታስታውሱት ካለ? አያችሁ፡ እንደምታውቁት፡ በዓለም ዙርያ ሁሉ የቴፕ አገልግሎት አለንና፡ አሁን ሰናገር፡ በቴፕ ከሺዎች ጋር ነው። እናንተ የተጠመቃችሁት በማን ሰም ነው? "ሰው ይድንበት ዘንድ፡" "ከሰማይ በታች የተሰጠ ሌላ ሰም የለምና፡" ይላል ቃሉ። በክርስቶስ ላይ ያለህን እምነት ለማሳየት ከተጠመቅህ፡ ከዚያም የሐይማኖት ሰርዓት ሰም ከተቀበልህ፡ እንግዲያውስ የተዳቀልህ ነህ። ልክ እንደዚያች ቤተ ክርሰቲያን እና ልክ እንደ ትምህርታቸው ካልሆናችሁ...

521 እንግዲህ፡ እናንተ የካቶሊክ ሰዎች ሆይ፡ ተመልከቱ፡ በጳጳሱ ከክርሰቶስ፡ ማለት ከጴጥሮሰ ጀምሮ-... በሐዋርያዊ መተካካት፡ የተተካ አልጋ ወራሽ ነው የምትሉት ጳጳሰና ይህች ቤተ ክርሰቲያን፡ እግዚአብሔር በምልክት እና በድንቅ፡ ቤተ ክርሰትያኔ ብሎ ካወቀው ከመጀመሪያው ቃል፡ እጅግ በተቃራኒ

ያስተምራሉና፡ እንዴት በጳጳሱ ስልጣን ስር ልትገዙ ትችላላችሁ? ይህ ቃልም በዚያም ጊዜ የነበረውን ያንኑ ትንሣኤ አሁንም በማሳየት፡ ያው ቃል አሁንም ሲገለጥ፡ እግዚአብሔርም ያው ተመሳሳይ ስራ እየሰራ፡ በሕዝቡ መካከል ሲመላለስ እያያችሁ፡ እንዴት የሮም ራስ ትመለከታላችሁ?

522 የእኛ ራስ በሰማይ ነው። እኔ ሰሞት ወደ ሰማይ እንጂ፡ ወደ ሮም አልሄድም። እያችሁ? እያችሁ? ራስ ያለው በሰማይ ነው።

523 ሚስት ባልን እንደምትከተል፡ ሰውነትም ራስን መከተል አለባት። አዳም ሳይታለል፡ ከሔዋን ጋር አብሮ ወጣ። የተታለለች ሔዋን ናት፡ የተተላለፈችው እሷ ነበረች፡ ባይሆን ግን በጌታ በኢየሱስ ቀን እርሱ ከመቃብር በወጣ ቀን የሰውነቱ መላ ትንሳኤ ያኔ መፈጸም ይችል ነበር። ነገር ግን አካሉ የሆነችውን፡ እርሷን መዋጀት ነበረበት። ወደ እሱ መምጣት እንድትችል መዋጀት ነበረባት። ገብቷችኋል? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—እርታዒ።] ኦህ፡ ማይ! እያችሁ፡ ያኔ ሊከሰት አይችልም ነበር። መዋጀት አሁን እየተፈጸመ ነው።

524 አሁንስ ማሕተሞቹን ታያላችሁን? መካከለኛ ሆኖ በሚሰራ ጊዜ፡ ያኔ እየዋጀ ነው፡ አንድ ቀን ግን ይህን የተቤዠውን መጽሐፍ ለመውሰድ ይመጣል። ያኔ በዚህ መጽሐፍ የተገኘ ሁሉ እሱ ይሆናል፡ በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ ቃላት፡ ያ አማኝ ራሱ ነውና፡ ቃሉም እርሱ ነው። እናም በዚህ ውስጥ ያለው ሁሉ፡ ለዚህ የቤዛነት መጽሐፍ ይመጣል፡ ዓለም ሳይፈጠር በፊት እንደበግ በታረደ ጊዜ፡ ሰሞቻቸው በዚህ መጽሐፍ ተጽፏልና።

525 እነሆ ዛሬም፡ ያኔ ያደረገውን ተመሳሳይ ስራ እየተረከ፡ በቃሉ ውስጥ ተገኝቷል። ለሌላ ራስ እውቅና አትሰጥም። ኖ፡ ስር። ቢሾፕ የለም፡ ሌላም የለም። አንድ ራስ ታውቃለች፡ እርሱም ክርስቶስ ነው፡ ክርስቶስም ቃል ነው። ኦህ፡ ማይ! ዊው! ተመቸኝ። አቤት! የስ፡ ስር።

526 ራስ ከመቃብር እንደተወሰደ፡ ሰውነቱም ወደ ዔደን ሊከተለው ይገባል። ስለዚህም፡ አካል የቃሉን ራስነት እንጂ፡ ሌላ ራስነት ሊያውቅ አይችልም።

527 የትኛውም ተቋም ምንም ነገር ሊያስቀምጥበት አይችልም። "አንዲትን ቃል የሚቀንስ ወይም በእርሱ ላይ አንዲት ቃል የሚጨምር ሁሉ፡ የሚቀንስ ሁሉ።" ወዲያው፡ ተዳቅለህ፡ ሞተሃል። ይህ ምስክርነት በእጆቿ ላይ ይዛ፡ ወደዚህ ተመልሳለች፡ "የዝሙትዋ ርኩሰት፡ መንፈሳዊ ምንዝርና በመፈጸም፡" እምነዋለሁ በምትለው ቃል ላይ አመጸች። እያችሁ?

528 ስለዚህ፡ ከቃሉ በቀር፡ ሌላ የለም። ትክክል ነው። ቃል የሆነው፡ እርሱ! ትክክል እንደሆነ እንዴት ታውቃላችሁ? እርሱ፡ ያ ቃል፡ ማሳያ አለው። እያችሁ? እርሱ፡ ያ ቃል፡ ራስ ሆኖ፡ የቤተ ክርስትያን ራስ እንደሆነ፡ በትክክለኛ ታይቷል። ራስ የሆነው ቃል፡ እርሱ ነው። እርሱ ራሱ በገዛ መንፈሱ በቤተ ክርስትያን፡ ያንን ሰው እንደሆነ፡ በትክክል ተለይቶ፡ ታውቋል፡ ታይቷል። እራሱን በማሳያ፡ ማሳየቱ፡ ለመላው አካሉ ቀጥተኛ ማረጋገጫው ነው። እንዲህ ከሆነ፡ የሐይማኖት ስርዓት አያስፈልጋችሁም። የሐይማኖት ተቋሞች ጠተዋል። ራስ መሆኑ ግን፡ በግል መታወቂያዎች በአካሉ ላይ የታወቀ ሆኗል፡ እያችሁ፡ እራሱን ማስተዋወቁ፡ ለአካሉ ራስ መሆኑን ያረጋግጣል። ስለዚህ፡ በማሳያ በተረጋገጠው በአንድ ራስነት ሥር አንድ ነን፣ እርሱም፡ በክርስቶስ፡ በእግዚአብሔር ቃል ነው [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—እርታዒ።] እንጂ በየትኛውም ቤተ ክርስቲያን ሥር አይደለም።

529 እንግዲያውስ፡ የእኛ ራስ መንግስት ነው። "የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና፡" ይላል መጽሐፍ ቅዱስም፡ ኢየሱስም። መንግሥቱ! እኛ የሐይማኖት ተቋም አይደለንም። እኛ የአንዲት መንግሥት ነን፡ ይህ መንግሥትም በሕይወታችን ውስጥ መንፈስና ሕይወት የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ነው፡ ይህም ቃልና እግዚአብሔር አንድ በነበሩበት በዚያ ዘመን እንዳደረገ፡ በዚህ ቀን የተሰፋውን ቃል ሁሉ እየፈጸመ ነው። ዛሬም ቃልና እግዚአብሔር በቤተክርስቲያኑ አንድ ነው፡ ይህም በመጨረሻው ቀን መልእክቱን ለማድረስ፡ ለተቤዣት አካል ራስ በመሆን፡ በትንሳኤው፡ ከሙታን በመነሣት፡ አዳም እና ሔዋን እንደነበሩት እንደ መጀመርያው፡ ወደ ኤደን ገነት ለማቃናት፡ እንደገና ለመመለስ ነው። ሦስት መአዝናዊ የእግዚአብሔር ምስጢር፡ አካሉ! ኦህ፡ ማይ!

አሁን በደንብ ተከታተሉኝ፡ እንደ ጥንቷ እስራኤል፡ በጥላ፡ [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]

530 ብዙ ጊዜ እየወሰድኩባችሁ ነውን? [ጉባኤው "አልወሰድክም፡" አሉ።—አርታዒ።] እጅግ ርቄ እንድሄድ፡ አትፍቀዱልኝ... አሁን ስሙኝ። ከሀያ ገጾች በላይ ሌላ የለንም። እያችሁ? እያችሁ? አሁን ግን... አሁን ትኻሽ ጊዜ ብቻ፡ እንጂ—እንጂ እስከ በጋ ድረስ፡ ወይም ጌታ ቢፈቅድ፡ ለተወሰኑ ቀናት እተዋችኋለሁ። እያችሁ?

531 አሁን ተመልከቱ። አስተውሉ፡ በአንድ ራስነት ሥር አንድ ላይ መሆናችን፡ በተመሳሳይም መልኩ፡ የጥንቷ እስራኤል ዓይነት ጥላ ነው። አሁን እየገባችሁ ነው? እንደ ጥንቷ እስራኤል፡ እርሱ ቃል መሆኑ፡ በእሳት ዓምድ የተረጋገጠ፡ እና በነቢይ በኩል ራሱን የገለጠ፡ አንድ አምላክ ነው። ያው አምላክ፡ ያው የእሳት ዓምድ፡ በተመሳሳይ መንገድ፡ መንገዱን መለወጥ አይችልም። መሆን የቻለውን ያህል... ግልጽ ነው። አይደለም'ዴ? እያችሁ? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።]

532 አንድ አምላክ! እስራኤል ስንት አምላክ ነበራት? [ጉባኤው "አንድ፡" አለ።—አርታዒ።] ሙሽራይቱስ ስንት አላት? ["አንድ."] ወደ ፊትስ ስንት ይሆናል? ["አንድ።"] በትክክል። በትክክል።

533 እያችሁ፡ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት፡ በታላቁ ነቢይ፡ በሙሴ ዘመን የእሳት ዓምድ ነበረ። እርሱም በእሳት ዓምድ እተመራ። ልክ ነው? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] አዎን። ወደ ተሰፋይቱ ምድር ተጓዙ።

534 በክርስትና ዘመንም በእሳት ዓምድ አምሳል፡ ጳውሎስ ለተባለ ነብይ፡ ስለ ስሙም አንድ ሕዝብ ለመውሰድ፡ ወደ አሕዛብ ለተላከ ሰው፡ የተገለጠ አንድ አምላክ ነበረ። ልክ ነው? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።]

535 በመጨረሻው ቀንም፡ በተመሳሳይ መልኩ፡ ራሱን በማሳያ እያረጋገጠ፡ እያችሁ፡ ያው ምልክት፡ ያው ድንቅ፡ ያው የእሳት አምድ፡ ያው ወንጌል፡ ያው ቃል፡ ያው ማሳያ ጋር ወርዷል።

536 አካሉም እንደ ማርቆስ 16፡ እና የመሳሰሉትን፡ የገባውን ቃል ስራ ይሰራል። አካሉ በመቃብር ውስጥ አልተያዘምና፡ ነገር ግን በትንሣኤ ከእርሱ ጋር የታወቀ ሆነ። ገባችሁ? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ያኔም፡ የአማኞች ልጆቹ አካልም እርሱ ሲመጣ ከእርሱ ጋር ይታወቃል እንጂ፡ በመቃብር አይያዝም፡

ምክንያቱም እርሱ የሞተው ሙሽራውን፡ አካሏን ለማስነሣት ነው። የገዛ አካሉ ነውና፡ ማለትም ቃል ነውና፡ የታወቀች ሆነች። ከሐይማኖት ተቋም ነገሮች፡ ሙሉ በሙሉ ወደ እርሱ ተማረከች፡ እሱም ቃል ነው። አያችሁ? የትንሣኤያችን የመጀመሪያ ፍሬ ስላለን በእርሱ ዘንድም የታወቀ ነው፡ በዚህም ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን፡ የእርሱ እስረኞች እንደ ሆንን እወቁ። እግዚአብሔርም፡ በዚያን ጊዜ ያደረጋቸውን አሁን በቤተክርስቲያን በኩል በማድረግ፡ ትናንትናና ለዘላለም ያው እንደሆነ በግል ራሰነቱ አረጋግጦልናል፡ "እርሱ በእኔ፣ እኔም በእርሱ፣ በእናንተም፣" ይህን ሁሉ፡ አውቃችኋል። ትክክል ነው።

537 አካሉ በመቃብር አልቀረም። በትንሳኤው ከእርሱ ጋር እውቅና አግኝተዋል፡ ይህ ማለት እንዲህ ነው፡ ሰሙኝ፡ አሁንም ያው ነው፡ እርሱ ራሱ፡ የሆነው ቃሉ፡ አሁንም መነሣት ጀምሯል ማለት ነው። ቃሉ፡ በሉተር፡ በዌስሊ ዘመን ሁሉ፡ ወደ ኃይሉ መነሳት ጀምሯል፡ አያችሁ፡ ያኔ መንቀሳቀስ ጀመረ፡ ከዚያም ትንሽ ጨመረ፡ አሁን ወደ ፍጹም መታውቅ ደርሷል። አያችሁ? ተመልከቱ። አሁን፡ የህይወት በአካሉ መሆን፡ ንጥቀት በደጅ የመሆኑ ማሳያ ነው። የእርሱ የመገለጡ ሙላቱ ልክ፡ እንዲሁም ራሰነት እና አካል አንድ ሆነው ሰታዩ፡ አካል ወደ ራስ ለመወሰድ መዘጋጀቱን ያሳያል።

አሕዛብ ተበታተኑ፡ እስራኤል ግን ነቃች።

538 ምን ለማለት እንደፈለግኩ አያችሁ? ለአካሉ ሕይወት መሰጠት ጀምሯል፣ (ለምን?) የዋጃት ስለሆነች። የመካከለኛ ሰራው ተሰርቷል፡ የመነጠቅ ማረጋገጫ ማሳያ እንዲሆን፡ ህይወቱን ወደ አካሉ እያመጣ ነው። አስታውሱ፡ አሁን፡ በመጨረሻው ቀን...

539 እ—እ፡ ጥቂት ጊዜ ብቻ፡ ከፈቀዳችሁልን፡ አሁን—አሁን፡ ይበራላችኋል። እንድትሰቱት አልፈልግም። ይ—ይህን፡ ካሴትም—አሁን ማዳረስ አለብኝ፡ እስካሁን የጀመርኩት ስለሆነ። በጥቂቱ መቀጠል ካለብኝ፡ አንድ ተጨማሪ ጥሩ አስተያየት ማድረግ እፈልጋለሁ።

540 አሁን አስተውሉ። ይሄን አዳምጡ። ትልቁ ነገር ይህ ነው። ማየት ያለብን አሁን ነው። አስታውሱ፡ በመጨረሻዎቹ ቀናት፡ በትክክል ወደ ኋላ ተመልሶ የመጀመሪያውን ቀን ያሳያል፡ አያችሁ፡ አዳም እና ሔዋን፡ ባል እና ሚስት፡ ያለ ምንም ሐጥያት፡ ሕያዋን ነበሩ፡ ከዛ ውድቀት መጣ። ተከታተሉኝ፡ በደንብ ተከታተሉ።

አጣመማት። አህ-ሃህ።

541 አስተውሉ። ይህን ያደረገ ማን ነው? ሉሲፈር! መጀመርያው እንዳደረገ አሁን እንዲሁ እያደረገ ነው።

542 ልክ የአሕዛብ መንግሥት፡ ከንጉሥ ናቡከደነፆር ጋር እንደገባ፡ ያልታወቀ ቋንቋን፣ ራዕይን፣ ሕልምን ሊተረጉም በሚችል ነቢይ የአሕዛብን ዘር በማረጋገጫ አሳየ። በሜዶ-ፋርስና፡ በብረትና በመሳሰሉት፡ ያለ ምንም ነገር፡ በአሕዛብ በኩል ወረደ፡ በእግሮቹም ስር በተመሳሳይ መልኩ፡ የአሕዛብ መንግስት ቀጠለ።

543 በመጨረሻው ቀን፡ ሉሲፈር፡ መጀመሪያ ያደረገውን ስራ እያደረገ እንዳለ አስተውሉ። ያኔ ሉሲፈር ምን አደረገ? ሉሲፈር የእግዚአብሔርንና የሰውን

ኅብረት ለመለየት ያደረገው የመጀመሪያው ነገር፡ ታላቅ ግርማ ሞገስ፡ እና የተሻለ ዝማኔ ያለው የሚመስለው፡ ለሚካኤል፡ ለክርስቶስ ከነበረው የሚበልጥ አንድ መንግሥት ሊገነባ ፈለገ።

544 ገብቷችኋል? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] አሁን፡ አሁን ይህ ካመለጣችሁ፡ ይኸውላችሁ፡ እጃችሁን ከፍ አርጉ፡ እንደገና እንደግመዋለሁ። አያችሁ?

545 ሉሲፈር፡ መጀመሪያ ላይ፡ የልቡ ውስጥ ዓላማ በገነት ውስጥ ከክርስቶስ የበለጠ ብሩህ እና ታላቅ ነገርን መገንባት ነበር። ልክ ነው? ከክርስቶስ መንግሥት ይልቅ የበለጠ ዝማኔ ያለው፡ የሚያምር፡ ባለ ግርማ ሞገስ የሚመስል ነው። በሺህ አመት መንግስ ውስጥ አውቶሞቢሎች እና አውሮፕላኖች ይኖረናል ብላችሁ ታስባላችሁን? ተመልከቱ? ሉሲፈር ምን እየሰራ እንደሆነ ተመልከቱ?

546 አሁን፡ ትልልቆቹ የምሁራን የሐይማኖት ተቋማት ተመሳሳይ ነገር በማድረግ ላይ ናቸው፡ ተመሳሳይ ነገር ለማድረግ ራሳቸውን አንድ እያደረጉ ነው። አያችሁ? እራሳቸውን ተቋም ለማድረግ እየተሰበሰቡ፡ አንዱ ሌላኛውን ለመምታት እየጣረ ነው። ስለዚህ አሁንም እጅግ የበዛ ግርማ ይዘዋል፡ ከካቶሊክ ቤተ ክርስትያን ጋር አንድ ለማድረግ ካልሆነ በቀር ምን ማድረግ እንዳለባቸው አያውቁም። አያችሁ? ሉሲፈር እንደገና ታላቅ መንግስት በመገንባት ላይ ነው፡ ይህም በሐይማኖት ተቋም የማያምኑ ሰዎችን ገፍቶ ለመጣል፡ የቸርች ህንጻዎቻቸውን በመንጠቅ መጋዘኖች ያደርጋቸዋል፡ እንደዚህ ያሉ ፓስተሮች ሁሉ በፍጹም መብት አይቀርላቸውም።

547 እግዚአብሔር የላከው-ሰው ይህን ሰምቶ ወይም ካየ በኋላ በሐይማኖት ተቋም ውስጥ አይቆይም፡ እርሱም—ወጥቶ ለማየት ብቃት ያለው ከሆነ ነው። በትክክል። አያችሁ? ይህን የምለው ለትችት ብዬ አይደለም፡ አያችሁ፡ ይህን ተገልጦ ለማየት፡ ከልቤ እናገራለሁ እንጂ።

548 አስተውሉ፡ በዚህ በመጨረሻዎቹ ቀናት፡ ሉሲፈር ተመሳሳይ ነገር እያደረገ ይገኛል። ይታያችኋልን? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ዲያብሎስ ተመሳሳይ ነገር እያደረገ ነው፡ በመዳቀል በተዳቀሉ አባላት፡ የተዳቀለች ቤተ ክርስቲያንን እየገነባ ነው፣ ከቃሉ ይልቅ በእውቀት የተዳቀሉ፣ ዳግመኛ-ከመወለድ ይልቅ በአዋቂዎች ጽንሰ ሐሳብ፡ ከትንሿ የክርስቶስ መንጋ የሚበልጥ የምሁራዊ ጽንሰ ሐሳብ መንግሥት እየገነባ ነው። አያችሁ? ይህን እያደረገ ያለው ምንድነው? የወደቁ መላዕክቶች።

549 መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ወቅት የራሳቸው ከነበረ ክርስቶስን ከመስማት ይልቅ፡ ሉሲፈርን አዳምጠው የወደቁ መላእክት ናቸው ይላል። ልክ ነው? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።]

550 አሁን በደንብ ስሙኝ፡ "የወደቁ መላዕክት።" ምን አይነት መላዕክት? ሉተር፣ ዌስሊ፣ ካቶሊክ፣ ጴንጤቆስጤዎች፣ እንደ መላእክት የመጀመሪያ ርስታቸውን ያልጠበቁ፣ እና በኒቂያ ላይ እንደ ሉሲፈር ዋና ምሽግ፡ በድርጅት ውስጥ የወደቁ ናቸው። እና ያደረጉትስ ምንድነው? መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው "ለአውሬው ምስል፡" ይሰሩ ዘንድ፡ ዓለም አቀፍ ታላቅ የአገልጋዮች

ማኅበር አደራጁ። እናም የዚህን ቤተክርስትያን እና ሌሎች መሰሎቹን በሮች የሚዘጋ የክርስቲያን አንድነት ገነቡ። ሉሲፈር ስራውን ሲሰራ አያችሁ?

551 ሦስት መአዝናዊ ወይም ምስጢራዊ የእግዚአብሔር መገለጥ ወደ እናንተ ለማምጣት እየሞከርኩ ነው።

552 ምን አደረጉ? ሔዋን እንዳደረገች፣ የወደቁ መላዕክትም እንዳደረጉት፡ ለጥበብ እና ለምክንያት እንዲሁም ለትምህርት ተሸጡ። ዌስሊ የእግዚአብሔር ሰው ነበር፡ ግን ምን ተከተለው? የወደቁ መላእክት ገቡበት። መላእክት፡ በመጀመርያ ምን ነበሩ? የእግዚአብሔር ህያው ፍጡራን ነበሩ፡ ነገር ግን በሉሲፈር ጥበብ ወደቁ፡ ለሉሲፈር—ለሉሲፈር ጥበብ ተገዙ። ምን እንደሆኑ ታያላችሁን? የወደቁ መላእክቶች። ድርጅቶች፡ በምድር ላይ እውነትን ለመትከል ከወጡ የእግዚአብሔር ሰዎች ውስጥ፡ እውነት ሰፍታ ከመታወጁ በፊት እና ወደ እውነተኛው የክርስቶስ መገለጥ ከመድረሷ በፊት፡ የወደቁ መላእክት ገብተው ወሰዷትና እና የሐይማኖት ተቋም አድርገው ሰሯት።

553 የሰባት-ማህተም ምስጢር መገለጥ ያለበትም ለዚህ ነው።

554 አሁንስ አያችሁትን? ያቋረጡት ነገር፡ ሉተር ቀጥሎበት ቢሆን ኖሮ፡ ይህ ይሆን ነበር። ዌስሊ ቀጥሎ ቢሆን፡ ጴንጤቆስጤ ቢቀጥል ኖሮ፡ ምን ያደርጉ ነበር?

555 አሁን ሊሆን የሚችል ግን አንድ ነገር ብቻ ነው። በመጨረሻው ዘመን ማንም የማይከተለው፡ የሚመጣ መልእክት መኖር አለበት። ዓለም አቀፉ ድርጅትም እንዲህ አይነት ሰርዓት አዘጋጅቷል የትኛውም የሐይማኖት ተቋም ይሁን ወይም ሌላ ምንም ይሁን አልከተለውም የማይለው ነገር ነው፡ ትከተላለህ ወይስ አትከተልም ነው። ፍሬው በዛፉ እናት ላይ ነው፡ ብርሃኑ አስቀድሞ በተወሰነ ፍሬ ላይ ይበራል። እሷም ክርስቶስን-ወደሚመስል ፍሬ እየበሰለች፡ በእርሱ ዘንድ የነበረው ያ ጣዕም እና የጎመራ ነገር፡ እንዲሁም ያው መንፈስ ታፈራለች። አይታችሁታል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ! አያችሁ?

556 አንድ ቀን ብዙ ነገር ለማሳየት—ሞከርኩ። አደከምኳችሁ። [ጉባኤውም "አላደከምከንም፡" አሉ።—አርታዒ።]

557 ስለዚህ፡ ተመልከቱ፡ ለምክንያት ተሸጡ፡ ለሐይማኖት ጠቋም ምክንያቶች ተሸጡ። "እኔም **የዚህኛው** አባል ልሁን! ከንቲባው'ኮ—እዚህ ቸርች ይገባል።" አያችሁ? "ሜቶዲስት ብሆን፡ ወይም ፕረስባይተሪያን።" የት እንደገቡ ብቻ ተመልከቱት። አሁን፡ በደንብ አብራርቼዋለሁ፡ እነዚያ ቅርንጫፎች ተከርክመዋል። ሞተዋል። ከእንግዲህ ወዲህ ከክርስቶስ ጋር ሕብረት የላቸውም፡ ቢሆኑ ኖሮ ተመሳሳይ ህይወት ያፈሩ ነበርና። ሕብረት የላቸውም።

558 እነዚህ ግን—እንደ ሆምጣጤ ፍሬ ናቸው። የትኛውም የሆምጣጤ ፍሬ በሆምጣጤ ዛፍ መኖር ይችላል፡ የሚያፈራው ፍሬ ግን የራሱ ፍሬ ነው። የወይን በ—በብርቱካን ዛፍ ውስጥ ትከሉት፡ በብርቱካን ዛፍ መኖር ይችላል፡ ፍሬው ግን ወይን ነው። ሎሚም በዚያው ላይ ጨምሩት፡ ሆምጣጤ ስለሆነ፡ የቀድሞ ሆምጣጤ ሎሚውን ያፈራል፡ የሚኖረው ግን በዚያኛው ህይወት ነው። የሐይማኖት ተቋማትም፡ በቤተ ክርስቲያን ስም እየሰሩ ያሉት ይህንኑ ነው።

559 ኦሪጂናል ዛፍ፡ እና ኦርጂናል መንፈስ ሙሽራይቱ ናት። መገለጡ የመጣው ከክርስቶስ ነው እንጂ ከሐይማኖት ተቋም አይደለም። ከክርስቶስ ነው! አስተውሉ።

560 የሐይማኖት ተቋም ምን ለማድረግ እየሞከረች ነው? እንደ ሉሲፈር፡ ራሷን ከፍ ከፍ ለማድረግ። ራሳቸውን "ቤተ ክርስቲያን፡ ሙሽራይቱ" ተብለው-ይጣራሉ። በራዕይ 17 ላይ፡ እንደተገለጸው፡ ስለ ሐሰተኛዋ ሙሽራ፡ ይናገራል። ከክርስቶስ ትንሽ መንጋ ሙሽራዋ፡ በላይ፡ በመገለጥ እውቀት ሉሲፈር ከትሑት የእግዚአብሔር እውነት ቃል በላይ እራሱን ከፍ ከፍ ያደርጋል ያስባል፡ እራሳቸውን ከፍ ከፍ እስኪያደርጉ ድረስ፡ እራሳቸውን በቲኦሎጂ እና በሰሚናሪ ትምህርት ላይ አስፍረዋል። ከቡድናቸው ውስጥ ካልሆናችሁ፡ ተጠርገ-የወጣህ ነህ።

561 ልክ መጀመርያ ሉሲፈር እንዳደረገ፡ አሁንም ያኔ ለሔዋን የተናገራት ነገር እየተናገራቸው ነው፡ "በእርግጥ እግዚአብሔር ይቀበለናል! ድሆችን እናበላለን።" ጥሩ ነው። "እርሱ በእርግጥ ይቀበላል። እኛ ታላቅ የተደራጀ የሐይማኖት ተቋም ነን። ቆንጆ ቤተ ክርስቲያን ነን። እንዴ፡ ታላላቅ ህንጻዎቻችንን እዩት! ታላላቅ አባሎቻችን እዩ። በሚልዮኖች ተቆጥረናል። እግዚአብሔር አምላክ ይህችን ቡድን በእውነት አይጥላትም።"

562 ቃየን ያደረገው ያው ነው፡ እርሱም መሬት አርሶ፡ አለሳልሶ ቆንጆ ፍራፍሬ አመጣ፡ ሠራ፡ ፍራፍሬም አመጣ፡ ትሑቱ የበጉ ደም ግን አክፋፋ።

563 እግዚአብሔር ሆይ አደራ፡ ወንዶችም ሴቶችም ይህን የምለው አንድ የግሌ ነገር ከፍ ከፍ ለማድረግ ወይም አንድ የግሌ መገለጥ፡ ወይም የሆነ ነገር ነው ብለው እንዳያስቡብኝ አደራ። እውነት ብቻ እላችኋለሁ። የሚሰሩትን ነገር አይታያችሁምን? አያችሁ? አጠንክሬ እና ጮኬ ተናግሬአለሁ፡ ሊጠቅማችሁ ከፈለጋችሁ ግን፡ ይኸውላችሁ፡ እስክታዩት ድረስ፡ ሚስማሩን ጠበቅ ማድረግ የእናንተ ፋንታ ነው። አያችሁ?

564 አሁን፡ ለሕዝቡ እንዲህ እላለሁ፡ "በእውነት! ይህን ሁሉ ጊዜ የቆመችው፡ ታላቋ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያናችን፡ ታላቁ ሜቶዲስት፡ እና ስለ ሁሉም፡ አንተ ልትነግረኝ ትሞክራለህን? አባቶቻችንን ተመልከት!" አያችሁ? እነርሱ'ማ የጌታን ቃል አፈረሱ። ሔዋን'ማ የእግዚአብሔር፡ የእርሱ አንዲት ነገር ናት፡ ለእርሱም... የአዳም የአካሉ-ትርፍ ነበረች፡ እና አንድ የእግዚአብሔርን ቃል ስለተጠራጠረች፡ ይህ ሆነ።

565 እዚህ ደግሞ ዛሬም እንደገና ሉሲፈር በስራ ላይ ነው። ደግሞም፡ ስለ ኮሚኒዝም፡ ጸረ ክርስቶስ እንዳልሆነ አስታውሱ። ጸረ ክርስቶስ ለእውነተኛው ነገር እጅግ ቅርብ ነው፡ "የሚቻል ቢሆን ኖሮስ የተመረጡት እንኳ እስኪያስት ድረስ፡" ነው፡ በማቴዎስ 24 ላይ ኢየሱስ ሲናገር "የሚቻል ቢሆን ኖሮስ የተመረጡትን።" ሉሲፈር፡ በድጋሚ፡ ሉሲፈር የእግዚአብሔርን አንድነት በሰው ልጅ እየጣሰ ነው፡ ይህም—የእግዚአብሔርን ቃል በራሱ ምክንያቶች በመገደብ ነው። እሱ ትክክል ነው ብሎ የሚያስበው፡ እና የእግዚአብሔርን ቃልን ይሰብራል፡ ብሎ በሚያስበው።

566 በኢየሱስ ዘመንም እንዲሁ አደረገ። ኢየሱስም አለ፡ "እናንተ ስለ ወጋችሁ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ከንቱ አድርጋችኋል።"

567 የሐይማኖት ተቋማትም፡ በገዛ አእምሯዊ ጽንሰ ሀሳባቸው እና ምክንያቶቻቸው፡ የእግዚአብሔርን ቃል በሰዎች ላይ የማይሰራ አድርገውታል። ይህ እውነት ነው። ሊያዩት አይችሉም። ከዚያም "የመጽሐፍ ቅዱስ አምላክ የት አለ፡" ይላሉ? ይኸው እዚህ ነው። እሱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡ እርሱ ያ ነው።

568 አሁን አስተውሉ፡ ሉሲፈር በኤደን እንዳደረገ፡ የሰውን እና የእግዚአብሔርን አንድነት እንዳበላሸ፡ አሁን፡ በተንኮሉ መጥቷል፡ ይህም የራስ-ስልጣን እና ታላቅነት በሚሉ ፈታኝ ተሰፋዎች ተገልጧል። "እንዴ፡ ከእኛ ጋር ከሆንክ'ኮ ቢሾፕ ትሆናለህ። የወረዳው አቡን ትሆናለህ። ለምን ወደ እንደዚህ ያለ ነገር ትሄዳለህ? " ይኸውላችሁ፡ ጴንጤ፣ ካቶሊክ፣ እና የመሳሰሉት ማለት ይህ ነው፡ ይህ፡ ከእግዚአብሔር ቃልና የተሰፋ ቃል ውጭ ኃይልን ለመቀበል ለሰዎች የቀረበ ታላቅ የሐሰት ተስፋ ነው። ኃይልን የምትቀበሉት፡ መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ነው እንጂ አንተ ቢሾፕ ስትሆን፡ ወይም ዲያቆን ስትሆን፡ ወይም ምንም ቢሆን አይደለም። አያችሁ? ሉሲፈር ግን አሁንም በስራው ላይ ነው።

569 ይህች ቤተ ክርስቲያን ይህን ተረድታለችን? ያንን እንዳየው እጅ ይነሣ። [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።] እሺ። ከአሁን በኋላ፡ በዚህ ላይ ጊዜ አላጠፋም።

ከእግዚአብሔር ቃል ተለይታለች፡ ወጣች! አያችሁ?

570 በኒቂያ፡ ሮምም እንዲሁ አድርጓል። ቆስጠንጢኖስ የሰጣቸው ታውቃላችሁ? የቤተ ክርስቲያን ዘመንን አንብባችሁታል። እሱ የሰጣቸው... በመጀመርያ ከክርስቶስ በቀር፡ ምንም ነገር አልነበራቸውም። በትንንሽ ያረጁ ህንጻዎችን በቻሉት ቦታ ሁሉ፡ በጠንካራ ድንጋይ ላይ ቁጭ ይሉ ነበር። **የኒቂያ ጉባኤን፡** እና **የቅድመ-ኒቂያ ጉባኤን** ካነበባችሁ፡ ታውቁታላችሁ፡ እና **የኒቂያ አባቶች**፡ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፡ የመሳሰሉት ካነበባችሁ። ምንም አልነበራቸውም። ይህን ጉባኤ ካደረጉ በኋላ ግን አንዳንድ የሮማውያን ጣዖት አምልኮዎች ወደ ክርስትና አስገብተው፡ ቅዱሳን ሰዎች ቢሾፖች፡ ጳጳሶች፡ እና ሌላ ሌላ፡ ትርጉም አልባ ነገሮች ከጨመሩ በኋላ ግን፡ ቆስጠንጢኖስ ምን ሰጣቸው? ማንኛውም የቲኦሎጂ ምሁር እንዲነግረኝ እጠይቃለሁ። ንብረት ሰጣቸው። ነፃነትንና የፈለጉትን ሁሉ ሰጣቸው።

571 እናም የእግዚአብሔርን ቃል በሰው ጥበብ እና በሰው ወግ ቀየሩት! ሉሲፈርም ያኔ ያደረገው ተመሳሳይ ነገር፣ በኤደን ገነት ያደረገውም ይህ ነው፡ በዚህም ወዲያው ሞቱ። የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን በኒቂያ፡ ሮም ሞተች፡ ይህ ግን በመጨረሻው ዘመን በሙሽሪት ዛፍ ውስጥ ለመነሳት ነው።

572 አስተውሉ፡ ተንኮለኛው፡ ሉሲፈር፡ እንደዚያን ጊዜ አሁን ገባ፡ ይህም በፈተናና በውሸት፡ ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ፡ ባለው ኃይል ተስፋዎች ነው። በኒቂያ፡ ሮምም እንዲሁ አድርጓል። ዛሬም በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ሕብረት ተመሳሳይ ነገር እያደረገ ነው።

573 ጳጳሱም "ሁሉም አንድ ይሁኑ፡" አለ። "ሁሉም ዓለም አቀፍ ሕብረት ወንድሞቼ ከእኔ ጋር እንዲተባበሩ እፈልጋለሁ። አዎን አንድ ነን።" ትክክል ነው፡ በድርጅቶች ውስጥ አንድ ናችሁ። ያ ግን ከክርስቶስ ሙሽራ ጋር ምንም

ግንኙነት የለውም፡ ወንድሜ፡ ምንም የለውም። እንደዚህ ባሉ ነገሮች በጭራሽ አትወሰዱትም።

574 አሁን በመጨረሻው ቀን፡ የመጀመሪያው እምነት፡ በተመሳሳይ በሙሽሪት ዛፍ ጊዜ... ወደ እግዚአብሔር ልጆች እንዲቃናላቸው ቃል ተገብቶላቸዋል። ሚልክያስ 4፡ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡ “ዓለም በእሳት ሳይቃጠል፡ እነሆ እኔ ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ፡ እርሱም የልጆችን እምነት ያቃናል።” ይህ ማለት፡ ከዚህ በፊት የመጣው የመጀመሪያው ኤልያስን አይደለም። አይ፡ አይደለም።

575 እዚህ፡ ስለ ኤልያስን መጎናጸፊያ እና ስለ ኤልያስ ብርድ ልብስ፡ እነዚህን የመሳሰሉ ነገሮች አናስተምርም። እኛ የምናስተምረው የእግዚአብሄርን ቃል ብቻ ነው። እሺ? እርሱም ያለው ያ ነው። አያችሁ፡ ኤልያስ **ይሄኛው** እና ኤልያስ **ያኛው** የሚባል ብዙ ነገር አለ፡ ይህ ሁሉ ከንቱ ነው። ያ ከሆነ—ያ ሁሉ... እናውቀዋለን። እኔም... ስለዚያ አላልኩም፡ መንፈሳዊ-አስተሳሰብ ያላችሁ ሰዎች ይገባችኋል። አያችሁ፡ መሽቷል፡ እየረፈደም ስለሆነ፡ ነገሩ ሁሉ በዚህች ቴፕ ውስጥ ማስቀመጥ፡ እርግጥ አይቻልም።

አሁን፡ በመጨረሻው ዘመን የገባው ቃል ነው። እንዲህ ከሆነ...

576 ኢየሱስም፡ በ—በማቴዎስ ይመስለኛል፡ 11ኛ ምዕራፍ፡ ወይም 6ኛ ምዕራፍ፡ እና 11ኛ ሲናገር... አይደለም፡ 11ኛው ምዕራፍ 6ኛ ቁጥር አካባቢ ነው። ዮሐንስ በእውነት እርሱ ራሱ እንደ ሆነ ለማየት ወደዚያ ደቀ መዛሙርቱን በላካቸው ጊዜ፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ “ማንን ለማየት ወጣችሁ? በ—በ—በንፋስ... በነፋስ የሚወዛወዝ ሸምበቆ? **እንዲህ-እና-እንዲህ** የመሳሰሉትን ለማየት ወጣችሁን? ” “ወይስ ነቢይን ልታዩ ሄዳችሁን? ” አላቸው፡ “ከነብይ በላይ፡” ነው። ዮሐንስም የቃል ኪዳኑ መልእክተኛ ነበርና፡ ከነብይ በላይ ነበር። እርሱም አላቸው፡ “ልትቀበሉት ብትወዱስ፥ በነቢያት የተነገረለት፡ ‘መልእክተኛዬን በፊቴ እልካለሁ’ የተባለው ይህ ነው።’”

577 ያ ማለት፡ ሚልኪያስ 3 ላይ ነው፡ ሚልኪያስ 4 አይደለም። ምክንያቱም፣ ሚልክያስ 4 ሊመጣ ያለው ኤልያስ፡ ምድር በትልቅ ትኩሳት ልትቃጠል ስለሆነ ነው፡ ያ ጻድቃንም በሺ ዓመት መንግስት የኃጥኣን አመድ የሚረግጡበት ጊዜ ነው። አያችሁ? ስለዚህ ያ አይደለም። ገባችሁ?

578 አሁን የተሰፋው ቃል ሲፈጸም አይተነዋል። እውነተኛው፡ ራስ የሆነው ክርስቶስ፡ ወደ ሙሽራይቱ ለመግባት ሲሄድ፡ ያኔ በመጀመርያ ያደረጋቸው ስራዎች አሁን ሲያደርጋቸው፡ ቃሉን ለመፈጸም፡ በመጀመርያ፡ በዮሃንስ 14:12 ያዘጋጀውን ቃሉ በመፈጸም ላይ ነው፡ “በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል።” ያኔ፡ ራስ እና አካሉ በመጨረሻው ቀን፡ እግዚአብሔር በገባው ተሰፋ ቃል፡ በተረጋገጠ ማሳያ በስራ እና በምልክት እና በህይወት አንድ ይሆናሉ። በመጨረሻው ዘመን ይህን ቃል ገብቷል። እናንተም፡መንፈሳዊ ከሆናችሁ፡ ይገባችኋል።

579 ከዚያም፡ የሰርጉ እራት እንደቀረበ ማየት እንችላለን። አሁንም፡ ዳግመኛ ካላየኋችሁ፡ የሰርጉ እራት እንደቀረበ፡ ይህን እወቁ። እንደ ተሰፋው ቃል ይመጣል የተባለው ታላቁ የሺህ አመት መንግስት፡ የቤተክርስትያኒቱ መወሰድ፡ እንዲሁም የአምጸኞች መጥፋት፡ ለመጀመር ተዘጋጅቷል። ይህም ዓለም በስድስተኛው

ማኅተም ሥር በእሳተ ገሞራ እንዲነጻ፡ ክፋትን እና ሐጥያትን ሁሉ ከዓለም በማስወገደ ዳግም ቅርጽ እንዲያሰይዛት፡ እና ለሚመጣው ዘመን ብሩህ አዲስ የሺህ አመት መንግስት ያገባ ዘንድ ነው።

580 እነኚህ ሦስት መአዝናዊ መገለጦች፡ ማለት እግዚአብሔር በክርስቶስ፣ ክርስቶስም በቤተ ክርስትያን፣ እና የመንግስቱ መምጣት፡ በምናያቸው ጊዜ። አዳምና ሔዋን በክርስቶስ እና በሙሽራይቱ ምሳሌ፡ ወደ ኤደን ገነት ተዋጅተው ይመለሳሉ፡ ያኔ እንደ ተሰፋው ቃል መንግስቱ ይታደሣል። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን! አሁን፡ ይህም የምስጢሩ፡ በሦስት መአዝናዊ ምስጢር መገለጥ፡ እና በመጀመርያው ራስነት በሚረጋገጠው የግሉ የቃሉ ማሳያ ይሆናል!

581 "መልካም፡ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን፡ እንጮኻለን፡ ሃሌሉያ እንዘምራለን፡ እንጮሃለን፡" አትበሉ። አይደለም፡ ያ አይደለም። እኔ ራሴ ሚሰዮናዊ ነኻና። ሰባት ጊዜ፡ በተግባር፡ ዓለምን ዞሬአለሁ። አያችሁ? ጠንቋዮች፡ አጋንንቶች፡ እና ሌሎች ነገሮች ሁሉ፡ ሲጨፍሩ እና ሲጮሁ አይቻለሁ። ሁሉንም ዓይነት ሥጋዊ መገለጫዎችን አይቻለሁ። ሥጋዊ ነው።

582 እኔ ግን የማወራው ስለ ክርስቶስ ራስነት ነው። አስተውሉ፡ ከኦሪጂናሉ ራስነት ጋር በግላችን በመታወቅ፡ ለዲያብሎስ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ ይኖረናል። አሜን! ክብር ይሁን! ለዲያብሎስ ጥያቄ መልስ አለን። እርሱ፡ ክርስቶስ፡ ዋጋ ከፍሎ ተነሥቷል፡ በዚህም ራስ... ወይም አካልን አስነሥቷል።

583 ዲያቢሎስ ሊቋቋመው አይችልም። ለዚህም ነው እነዚህ ኢኩሜኒካል መንግስታት ቦታ ቦታ የያዙት። አሁን ወደሚያደርጉት ነገር እየደረሱ ያሉትም ለዚህ ነው። ዲያቢሎስ፡ አሁን እንደሚያደርገው የሚጮህበት ምክንያታቸው ይህ ነው። ክፋቱ ሁሉ... አጭበርባሪነቱ ሁሉ በትንሳኤ በተነሣው፡ በአካሉ ራስነት በተነሣው ክርስቶስ፡ ተጋልጧል። ክብር ይሁን!

584 እኔ ብቻየን እመሰላችኋለሁን? አይደለሁም። ለዲያብሎስ መልስ አግኝተንለታል። "በእኔ የሚኖረው ቃል የሆነው ክርስቶስ ነው እንጂ፡ እኔ አልኖርም።" የእኔ ሀሳብ አይደለም፡ ኃይሉ ነው። የእኔ ሀሳብ አይደለም፡ ቃሉ ነው። እርሱ ቃል ገባ፡ ይኸው ተፈጸመ። ይመጣል አለ፡ ይኸው መጣ። መልሱን ይዘናል።

585 ክርስቶስ ተነስቷል ስለ ቤዛችንም ዋጋ ከፍሏል። እግዚአብሔር በክርስቶስ በገለጠው ነገር፡ ያን ሥጋ፡ ያን ደም ሰጠ፡ ይህም በደሙ ህይወት ይመጣ ዘንድ፡ ስጋውም ይዋጅ ዘንድ ነው፡ ይህም—እግዚአብሔር ያኔ በዚያ ቀን እንዳደረገ በተዋጀው ስጋ ውስጥ ለዚህ ዘመን የመደበው ቃሉ በዚያ ስጋ ያሳይ ዘንድ ነው። ዊው! ክብር ይሁን!

586 አያችሁት? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ኦህ፡ ማይ! መቼ ላቁም? አስቡት። ["ቀጥል ቀጥል!"]

587 ከዚያም፡ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ሆነን እንገኛለን። የቀለም ጠብታ ወደ በ—በ—በበረኪና ወደ ተሞላ ገንዳ ቢረጭ፡ የቀለሙ ህብር ፈማችሁ አታገኙትም። ወደ ሆነ ቦታ ይሰወራል። ዳግም አይመለስም። ይህን አይቶ ለሚቀበል አስቀድሞ የተወሰነ ዘር፡ በእውነት ሲዋጅም፡ ኃጢአቱ ፈጽሞ ይጠፋል። ሄዷል። ተለይቷል። ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ደም—ስልተረጨ፡ መታሰቢያው ፈጽሞ ይጠፋል። እግዚአብሔር ይረሳዋል። በእግዚአብሔርም

ፊት፡ እንደ እግዚአብሔር ወንድ ልጅና ሴት ልጅ ይቆማል። አሜን አሜን! “አሁን እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ነን።” ገና **እንሆናለን** አይደለም፡ አሁን ነን! የተዋጀን ነን።

588 ለሰይጣን መልስ አለን። እግዚአብሔር ራሱን በማሳያ አረጋግጧል። እግዚአብሔር በዚህ ቀን ለገባው ቃል፡ ራሱን አሣይቷል። ሃሌ ሉያ! ራስነቱ እዚህ አለ። አሜን! ከሙታን የተነሳው ጌታ፡ ክርስቶስ፡ እንደ ጥንቱ ራሱን እየገለጠ አሁንም በዚያው በትንሳኤ ሃይሉ፡ እዚሁ አለ። ለዲያቢሎስ መልስ አለን።

589 ለዚህ ነው ይህ ሰው፡ በቀደም ለት፡ በተቀመጠበት ወድቆ በሞተ ጊዜ፡ “ወደ ሕይወት ተመለስ!” ብለን ለመናገር፡ የደፈርንበት ምክንያት፡ መንፈስ ቅዱስ ስላለ ነው።

590 ለዚያም ነው በሜክሲኮ ውስጥ፡ ለአሥራ አምስት ሰዓታት ያህል የሞተ ሕፃን ላይ ይህን ሊያደርግ የተቻለው፡ ራእዩ መጥቶ “ወደ ሕይወት ተመለስ-... በለው፡” ስላለኝ ነው። እኔም “ህጻኑ ልጅ በሕይወት ይኑር፡” አልኩኝ። ሕጻኑ በዚያ ማለዳ በዘጠኝ ሰዓት መሞቱ የሚገልጽ፡ ዶክተሮች ደብዳቤ ጽፈውበት ነበር፡ ከምሽቱ አሰራ አንድ ሰዓት ላይ ወደ ህይወት ተመለሰ፡ ዛሬ በሕይወት አለ።

591 ምንድነው ይሄ? ሰዎቹ አይደሉም። ራስ እና አካል በሕበረት አንድ ስለሆኑ ነው እንጂ። በሕዝቡ ውስጥ የተገለጠው እግዚአብሔር ነው። ባልና ሚስት ከአሁን በኋላ ሁለት አይደሉም፡ አንድ ናቸው። የእግዚአብሔር ታላቅ መገለጥ “ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ” መሆኑ፡ እግዚአብሔር እና ቤተክርስቲያኑ አንድ ናቸው። ክብር ለእግዚአብሔር! ይህም ሰሙን ለመሸከም፡ ሰሙ ኢየሱስ፡ የተቀባ ነውና። ኢየሱስ የተባለበት ምክንያት፡ እርሱ የተቀባ ነው። ያ ሰውነት እግዚአብሔርን በመተረክ፡ እንደተረጋገጠ፡ ይህ ሰውነትም የተቀባ የክርስቶስ ሰውነት ነው። እናም ያ አካል እነዚህን ሁሉ፣ እነዚህን አካላት ሁሉ ዋጀ፡ በዚያም እግዚአብሔር፡ ወደ መንግስቱ እየሄደ ሦስት መአዝናዊው መገለጫው ሰራበት። ዋጋ ከፍሎ፡ ተነሥቷል! እኛም ተዋጅተናል። እግዚአብሔርም በማሳያ በማረጋገጥ፡ መሰክሯል። አያችሁ?

592 እኛም በክርስቶስ ጸድቀን፡ በፊቱ ቆመናል። ይህም፡ እኔም ጭምር የአካሉ ብልት የሆንሁለትን፡ ያንን አካል ፈርዶበታልና፡ ሌላ ፍርድ አያስተላልፍም። ምን፡ እንዴት የአካሉ ብልት ሆንኩ? **ይኸው**፡ በእኔ ውስጥ ስለሆነ ነው። “እናንተ... በእኔ ብትኖሩ፡ ቃሌም በእናንተ ቢኖር፡ የትናገሩትን ሁሉ... አብን በሰሜ ማንኛውንም ነገር ጠይቁ፡ እርሱ በዚያ ስለሚኖር፡ ይፈጸማል።” ጻድቅ! ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!

593 አቤት፡ ዓለም ይህን እንዲያየው ማድረግ በቻልኩ! ለምን? ይኸው እናንተው ናችሁ። ህያው የሆነው፡ የተዋጀው የቆመው ክርስቶስ አካል ይህ ነው። የተዋጀ! ኦህ፡ ማይ!

594 በፊቱ የጸደቀ! የጸደቅነው ለምንድነው? ድሉ እኛ ስለሆንን። ቤተ ክርስትያን የእርሱ ድል ናት። እኛም ድሉን እያሳየን፡ በዚህ ከተከበረው ወንጌል ጋር አብረን ወጥተናል። እሱ የሞተው ለዚህ ዓላማ ነው፡ እኛም የድሉ ምስክር ነን። አሜን! ወርዶ በቤተ ክርስቲያን መካከል ሲኖር ሰናየው፡ ያ ድሉ ነው። እርሱን በመቃብር ውስጥ ማቆየት እንደማይችል ያሳያል፡ እኛንም ማቆየትም

አይችሉም። ትክክል ነው። በትክክል ታሰረናል። እኛም ከሙታን፡ ማለት፡ ቃሉን ካለማመን፣ ከሕይማኖት ተቋም ሰርዓት፡ ዘላለማዊው ወደ ሆነው አምላክ፡ ዘለአላምዊው ቃሉ ይህም እርሱ ነው፡ ራሱም ትላንትና እና ዛሬም፣ እስከ ዘላለም ድረስ፡ ያው መሆኑ እየተረከ፡ በእኛ እንዲሰራብን ሰለተነሣን፡ አሁን፡ ያለጥርጥር፡ ተነሰተናል።

595 ከዚያም ቃሉ ከላይ ከራስ ጀምሮ፡ ወደ ታች ወደ አካሉ ይሄዳል። ይሄስ ምንድነው? ያው ቃል ነው። አንዳች ሊጨመርበት ወይም ሊቀነሰበት አይችልም። ሰለዚህ ያ ቃል ከራስ ተንቀሳቅሶ፡ ቀኑ ሲቃረብ፡ ሁለቱ አንድ መሆናቸውን፡ በማሳያ እያረጋገጠ፡ ወደ አካሉ ይወርዳል። ባልና ሚስት ናቸው። የሥጋው ሥጋ፣ የቃሉ ቃል፣ የህይወቱ ህይወት፣ የመንፈሱ መንፈስ ናቸው። አያችሁ? አሜን! እንዴት ታውቁታላችሁ? አንድ አይነት ምስክርነት፣ አንድ ፍሬ፣ አንድ ቃል ሰለሚያፈራ። አያችሁ? ክርስቶስን ይተርካል፡ አንድ ዓይነት ሕይወት፣ አንድ አምላክ፣ አንድ መንፈስ፣ አንድ ቃል፣ አንድ መጽሐፍ! አሜን! "እኔ የማደርገው እናንተም ደግሞ ታደርጋላችሁ፡" ተመሳሳይ ምልክቶች። ኦህ፡ ሃሌሉያ! ማይ!

596 አስተውሉ፡ በገዛ አካሉ በማሳያ የተገለጠ ቃል የሞቱ ምክንያት የሆነው ዋነኛ ድሉ እርሱ ነው። አያችሁ፡ እርሱ ሲሞት፡ ሞቱ፡ በሰጋ ብቻ ሞተ እንጂ፡ በመንፈስ አይደለም። መንፈሱ ወደ ሲኦል ሄዶ በእስር ላይ ላሉ ነፍሳት ሰበከ። ልክ ነው? ሥጋው፡ ብቻ፡ ሞተ፡ ከዚያም አስነሣው ሕያውም አደረገው። **ሕያው ማድረግ** ማለት ሰጋውን፡ ማለት አካሉን "ሕይወት መስጠት" ማለት ነው። ያም ደግሞ ቃል ነው። ለዓመታት ሙት ነበረች፡ ቀሰ በቀስ ግን በተሃድሶ መምጣት ጀመረች፡ አሁን በሁለት እግሮቿ ቆማለች!

597 አቤት፡ ወደ ሕዝቄል ተመልሼ፡ "የደረቁት አጥንቶችን፡" ማውጣት በቻልኩና ባሳየኋችሁ። "እነዚህ አጥንቶች እንደገና መኖር ይችላሉን፡" አለውና?

"ትንቢት ተናገርባቸው!" አለ፡

598 ትንቢት የሚመጣው እንዴት ነው? በነቢዩ በኩል ብቻ። የጌታ ቃል ነውና። "እናንተ፡ የደረቁ አጥንቶች ሆይ፡ የጌታን ቃል ሰሙ!" ጅማት፡ እና ቆዳ በላያቸው መጣ፡ ኃይለኛ ሰራዊት ሆነውም ቆሙ፡ ወደ ጽዮንም መገሰገስ ጀመሩ። ክብር ለእግዚአብሔር! ድሉ፡ ይሄ ነው። ይሄው ነው።

> እግዚአብሔር ቤዛ የሆናቸው ወደ ጽዮን በደስታ ይመጣሉ፡
> በተቀደሱ ተራሮቹ የሚጎዳቸው ወይም የሚያፈርሳቸው ነገር የለም። (እሃ።)

599 እርሱ ራሱን በሚያሳይበት ጊዜ የትንሣኤውን ህይወት ምስክር ይሰጣል። እሷም፡ ሽራይቱ፡ ከሌላው ነገር ሁሉ ነጻ ነች። ነፃ የሆነች ሴት ነች፡ ከሌሎች አእዋፋት ሁሉ ይልቅ የተዋበች ታላቅ ዥንጉርጉር ወፍ ነች። ሰለ "ታላቅ ዝንጉርጉር ወፍ" መጽሀፍ ቅዱስ ታስታውሱታላችሁ። እሷ ግን፡ ሰሙ ተጠርቶባታል፡ ህይወቱም ይዛ ነበር። ምክንያቱ...

600 ወፏን ዝጉርጉር የሚረጨባት እንዴት ነበር? በመጀመርያ ሁለቱም ነጮች ናቸው፡ በመቀጠል የአንደኛዋ ወፍ አንገት ሰብረው ደሙ በሁለተኛዋ ላይ እስከ

መጨረሻ ድረስ ያንተባጥቡታል። ሁለተኛውም ወፍ በቀይ ደም ዝንጉርጉር ትረጫለች፡ ክንፎቿም **እንዲህ** ታራግበዋለች፡ ደሙ መሬት ላይ በሚንተባጠብ ጊዜ “ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ፡” እያለ ይጮኻል።

601 ክርስቶስም፡ እንደ ሞተ አጋር፡ የገዛ ደሙን፡ ከሕይወቱ የመጣ ደሙ፡ በእኛ ላይ፡ በመርጨት-... ደሙን ተሸክሞ፡ “ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅድስና፡ ለእግዚአብሔር!” እያለ ይጮኻል፡ ሲታይ ደም-ግባት አልባ ወፍ ነው። አዎን፡ እንዲሁ ነውና። እሷ ግን፡ ሙሽራይቱ፡ በእርሱ—የታወቀች፡ ከሌሎች ሁሉ ነፃ የሆነች ናት። “አብራችሁ በሕይወት እስካላችሁ ድረስ ለእሷ ብቻ ተጠበቅ። አንቺም ራስሽን ለእሱ፡ ማለት ለቃል ተጠበቂ፡” ምንም፡ ዝሙት አይኑር፡ ምንም አይነት የሐይማኖት ተቋም ምልክት፣ ምንም አይነት የስርዓቶች ምልክት፣ ምንም አይነት ምንዝርና አይኑር። ቃሉና፡ እሱ ብቻ!

602 “ሌሎች ሁሉ የሚያስምጡ አሸዋዎች፡ እኔ ግን ቆምኩኝ በክርስቶስ በጠንካራው ዓለት፡” አለ ኤዲ ፔሮኔት። አህ-ሃህ።

603 ቃል የሆነው፡ ክርስቶስ፡ ይህ ነው! ቃል ነበረ፡ አሁንም ቃል ነው። እርሱ ቤተ ክርስትያንን የእርሱ አካሉ በማድረጉ ምክንያት፡ እሷ ቃል ትሆናለች፡ አሁንም ይህ ቃል ነው። በእርሱ ዘንድ በግል በመታወቅ፡ የግል ገንዘቡ ትሆናለች! የራሱ ገንዘቡ ትሆናለች! ከእርሱ፣ በእርሱ፣ ለእርሱ፣ ለእርሱ ብቻ ትሆን ዘንድ የተዋጀች ናትና። ትክክል ነው። ስለዚህ፡ ዲያቢሎስ የሚንጫጫበት ምክንያት፡ አሁን ግልጽ ነው።

604 አደገኛ ጊዜ ላይ ደርሰናል። አስታውሱ፡ ቅዱሳት መጻሕፍት፡ እነዚህ ነገሮች መከሰት ሲጀምሩ፡ “ጊዜ አይኖርም” ብለዋል። መገለጫዎች ሁሉ ሰናያቸው፡ ቀስ በቀስ ትደበዝዛለች።

605 “በመሬት መንቀጥቀጥ።” ባለፈው ቀን ሺዎች ሲገደሉ አያችሁ? “በተለያዩ ቦታዎች የመሬት መንቀጥቀጥ።”

606 “በሰማይ አስፈሪ ድንቆች፡ የእሳት አምዶች፡” ይባላል፡ እንደ፡ ተንሳፋፊ፡ የማይታወቁ በራሪ ነገሮችም። ምን እንደሆኑም አያውቁትም። አያችሁ? ይህ ነው የሚሉት ነገር የላቸውም።

607 ሰዶም ከመጥፋቷ በፊት፡ ሰዶምን የሚመረምሩ መላእክት መውረዳቸው ታስተውላላችሁን? ታስታውሳላችሁ? [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።] ሦስት ሆነው፡ ተሰብስበው ወረዱ። አንደኛው ከአብራሃም ጋር ቀረ። ታስታውሱታላችሁ? [“አሜን።”] እነዚህም በፍርዱ ምርመራ ላይ፡ ከሰማይ የወረዱ ብርሃናት ነበሩ። አንዴ...

608 ሁሉም የት እንደሚገኙ ተመልከቱ። በፔንታጎን ዙርያ፡ ወዘተረፈ፡ ነው። የዓለም፡ የሶዶም ፍርድ ነው። አንድ ተወካይ አለ፡ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ይወከላል፡ እርሱም በማሳየት፡ የሚያረጋግጥ፡ ክርስቶስ ራሱ ይሆናል። አያችሁ? “በላይ በሰማይ... ድንቆች፡ በታች በምድርም ምልክቶች ይታያሉ።” በትክክል።

609 የታወቀች ናት! አቤት፡ ዲያብሎስ በዚህ ነገር እየተንጫጫ ነው፡ በቃሉ ተሰፋ የተገለጠው እውነት በእሷ ዘንድ ብቻ ነው።

610 መልሱ የላቸውም። ኢየሱስ ሲመጣ፡ እነዚያ ፈሪሳውያን ለምን አቃታቸው? እንዲህ አላቸው፡ “እኔ በእግዚአብሔር ጣት አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፡ እናንተ በምን ታወጣላችሁ? ” አያችሁ? ብቻውን ጸንቶ ቆሞ ነበርና።

611 አሁንም ቤተ ክርስትያኑ ብቻዋን ጸንታ ትቆማለች። ከሌላ ነገር አትዛመድም። እርሱ ግን እግዚአብሄር የሚኖርበት መኖርያ በመሆኑ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ ነበረ፡ ቤተ ክርስትያንም ያንኑ ሰራ እየሰራች፡ በገዛ አካሉ ትታወቃለች። እሷ በመጨረሻው ቀን የተገለጠው የቃሉ እውነት የሆነች፡ የእርሱ አካል ናት። እሷ፡ ብቻዋን፡ ከጎኑ ትቆማለች። ዲያብሎስ እነዚያን ታላላቅ ድርጅቶችን በማደራጀት፡ እሷን ለመዝጋት የሚንጫጫው፡ በዚህ ምክንያት ነው። በጭራሽ አይሳካላቸውም። ትወሰዳለች እንጂ አትዘጋም። ስለዚህ በተገባላት የተሰፋው ቃል ማሳያ እየተገለጠች፡ አሁን ተነስታለች። አሜን!

612 ሙሽሪት ቃል ኪዳኗን የምትጠብቀው እንዴት ነው! “አንድ ቀን እንደሚመለስልኝ ተናግሮኛል። እኔም አምነዋለሁ።” እህ-ሃህ። አያችሁ? የስ፡ ሰር። ይህም ራሷን፣ ቤዛዋን፣ ባሏን፣ ንጉሷን፣ ጌታዋን ፍቅረኛዋን፣ አዳኟን፣ በተዘጋጀላት መገናኛ ሰፍራ፣ ለማግኘት ነው!

613 ከእርሱ ጋር የሚገናኙበት ሰፍራ አላቸው። ይኸውላችሁ፡ ሙ—ሙ... ሙሽራው አንዳች ነገር አያሰቀርም። መታወቂያው፡ ማለት ቀለበቱን አዘጋጅቷል። የምትለብሰው ልብሷን፡ መጎናጸፍያዋን ይዟል። አያችሁ? ከእሷ ጋር የሚገናኝበት የተለየ ሰፍራም መድቧል፡ ያም አየር ላይ ነው። ሁሉም ነገር ተዘጋጅቷል። የሰርጉ እራት ተሰተካክሏል፡ እንግዶች ተጠርተዋል፡ አሰቀድሞ ተመርጠዋል። መላእክቱ፡ አገልጋዮቹ በዙርያው ሁሉ በተጠንቀቅ፡ ከበዋል። አቤት፡ አቤት፡ አቤት፡ አቤት፡ አቤት!

> እነሆ፡ በደመናት የተቀጠረ ጉባኤ ላይ፡
> እጅግ በሚያምረው፡ በሚያምረው ሰማይ፡
> አያችኋለሁ፡ ተገናኝተን ከላይ
> በዚያ ቤት ማዶ ከህዋው በላይ፡
> በሟች ጆሮ ተሰምቶ የማያውቅ፡ ውብ ዜማ፡
> አውጃለሁ፡ እያልኩኝ ይሁን ባለ ግርማ!
> የእግዚአብሔር ልጅ፡ እርሱ መሪያችን፡ (የእግዚአብሔር
> የሙላት መገለጫው።)
> በአየር ላይ ባለው ጉባኤያችን። (ኦህ፡ ማይ!)

614 ማሳያዎቹ አሁን ተመልከቱ።

> ሰምታችኋል—የቁጥቋጦው ታሪክ ሰምታችኋል ስለ
> ሙሴ፡
> ሰምታችኋል ወንጭፍ ይዞ የማይፈራው ስለ ዳዊት፡
> ሰምታችኋል ስለ ህልሙ የዮሴፍ ታሪክ፡
> ሁሌ ምንዘምረው የዳንኤል የአንበሶቹ መዝሙር።
> ኧረ፡ ብዙ፡ በመጽሐፍ የተመሰከረላቸው ብዙ አሉ፡

ሁሉንም ለማግኘት እንዴት እንደምጓጓ፡ እውጃለሁ!
ያኔ ጌታ እንድናገኛቸው ይረዳናል፡
በአየር ላይ በዚያ ስብሰባ ላይ።

ስብሰባ አለ በላይ አየሩ ላይ፡
እጅግ በሚያምረው፡ በሚያምረው ሰማይ፡
አገኛችኋለሁ፡ ስንገናኝ ሰላምታ አቀርባለሁ
በዚያ ቤት ማዶ ከህዋው በላይ፡
በሟች ጆሮ ተሰምቶ የማያውቅ፡ ውብ ዜማ፡
እውጃለሁ፡ እያልኩኝ ይሁን ባለ ግርማ!
የእግዚአብሔር ልጅ፡ እርሱ መሪያችን
በአየር ላይ ባለው ጉባኤያችን። (ኦህ፡ ማይ!)

615 ደስ አይላችሁም? አሁን የታላቁ ምስጢር ሦስት መአዝናዊ ዓላማ መገለጥ አሁን ተገልጧል። ዋናውም ያ ነው። አንደኛው ያ ነው። ኦህ፡ ማይ! እስኪ እንዘምር። በጣም ደስ ብሎኛል። ከዚህ በላይ መሰበክ አልችልም፡ አያችሁ።

እነሆ፡ በደመናት የተቀጠረ ጉባኤ ላይ፡
እጅግ በሚያምረው፡ በሚያምረው ሰማይ፡
አያችኋለሁ፡ ስንገናኝ ሰላምታ አቀርባለሁ
በዚያ ቤት ማዶ ከህዋው በላይ፡
በሟች ጆሮ ተሰምቶ የማያውቅ፡ ውብ ዜማ፡
እውጃለሁ፡ እያልኩኝ ይሁን ባለ ግርማ!
የእግዚአብሔር ልጅ፡ እርሱ መሪያችን
በአየር ላይ ባለው ጉባኤያችን።

616 ትሄዳላችሁ? አሜን! በእግዚአብሔር ጸጋ፣ በእግዚአብሔር ጸጋ! አያችሁ? ኦህ፡ ማይ!

የቁጥቋጦው ታሪክ ሰምታችኋል ስለ ሙሴ፡
ወንጭፍ ይዞ ስለ ማይፈራው ስለ ዳዊት ሰምታችኋል፡
(እነዚያ ሁሉ ጥላዎች ናቸው።)
ሰምታችኋል ስለ ህልሙ ስለ ዮሴፍ ታሪክ፡
ሁሌ ምንዘምረው የዳንኤል የአንበሶቹ መዝሙር።
ኧረ፡ ብዙ፡ በመጽሐፍ የተመሰከረላቸው ብዙ አሉ፡
(ይህም ራሱ ነው)
ሁሉንም ለማግኘት እንዴት እንደምጓጓ፡ እውጃለሁ!
ያኔ ጌታ እንድናገኛቸው ይረዳናል
በዚያ ስብሰባ ላይ...

617 አንዱና ዋነኛው ግን አለ!

አቤቱ፡ ስብሰባ አለ በላይ አየሩ ላይ፡
እጅግ በሚያምረው፡ በሚያምረው ሰማይ፡

አገኛችኋለሁ፡ ስንገናኝ ሰላምታ አቀርባለሁ
በዚያ ቤት ማዶ ከህዋው በላይ፡
በሚች ጀሮ ተሰምቶ የማያውቅ፡ ውብ ዜማ፡
አውጃለሁ፡ እያልኩኝ ይሁን ባለ ግርማ!
የእግዚአብሔር ልጅ፡ እርሱ መሪያችን
በአየር ላይ ባለው ጉባኤያችን።

618 አሁን እዚያ ውስጥ እርስ በርስ እንገናኛለን። እስቲ ሁላችንም፡ ሜቶዲስቶች፡ እና ባፕቲስቶች እና ምንም ብትሆኑ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ዳግም የተወለዳችሁ፣ መዝሙሩን እየዘመርን ተጨባበጡ።

አቤቱ፡ ስብሰባ አለ በላይ አየሩ ላይ፡
እጅግ በሚያምረው፡ በሚያምረው ሰማይ፡
አገኛችኋለሁ፡ ስንገናኝ ሰላምታ አቀርባለሁ
በዚያ ቤት ማዶ ከህዋው በላይ፡
በሚች ጀሮ ተሰምቶ የማያውቅ፡ ውብ ዜማ፡
አውጃለሁ፡ እያልኩኝ ይሁን ባለ ግርማ!
የእግዚአብሔር ልጅ፡ እርሱ መሪያችን
በአየር ላይ ባለው ጉባኤያችን።

619 አቤት፡ አቤት፡ አቤት! አቤት፡ ድንቅ ነው፡ አያችሁ፡ ምን እንደሚሆን አያችሁ። አሁን እዩት።

620 ወዳጆች ሆይ፡ አሁን ሁለት ሰዓት ሊሆን ነው፡ ይኸውላችሁ፡ እራት ሰዓት ላይ—እዚህ መገናኘታችን ስለሆነ፡ አሁን እንዝጋው። እንደምታዩት፡ ገና ብዙ ገጽ ይቀራል፡ መቋጫ የለውም። ስለዚህ ዝም ብለን መዝጋት አለብን።

621 መገለጥ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ዘላለማዊ እንደሆነ ሁሉ ዘላለማዊ ነው። ይኸውላችሁ፡ የእግዚአብሔር ሦስት መአዝናዊ ታላቅ ምስጢራዊ ዓላማ ግን ተገልጧል! እግዚአብሔር በክርስቶስ ተገለጠ፣ ክርስቶስም በቤተክርስቲያን ተገለጠ፡ ይህም በኤደን ገነት የጠፋችውን ሔዋንን ወደ ቀድሞ ሁኔታው ለመመለስ ነው። ኦህ፡ ማይ!

622 አቤት፡ ያኔ ታላቅ ቀን ትሆናለች! አዎን። አይዘገይም። እኛም እናምናለን። አታምኑበትምን? ያን መዝሙር ባሰብኩ ቁጥር ትዝ ይለኛል።

623 በዳንኤልም፣ በሙሴም፣ በኤርምያስም ራሱን አሳይቷል። እነርሱ ምን ነበሩ? ይኸውላችሁ፡ እነዚያ ታላላቅ ሰዎች፡ ቃሉ ወደ እነርሱ የተላከላቸው ነቢያት ነበሩ። ይኸውላችሁ፡ ስለ ህልም አላሚው ዮሴፍ ሰምታችኋል፡ አያችሁ፡ በአንበሶች ጉድጓድ ስለገባው ዳንኤልም፡ እንዲሁም፡ የምታውቋቸው ሌሎች ሁሉ። እነርሱ፡ ያስ፡ ምን ነበሩ? ነብያት። ገባችሁ? ዋናው ግን… በዚህኛው እግዚአብሄር፡ በጊዜአዊነት፡ በእነርሱ ዘንድ በጥላ ይታይባቸው ነበር።

624 ትክክል የሆነውን እያወቀ፡ በአዳም ላይ ራሱን በጥላ አሳየ፡ ሚስቱን ግን ጠፍታበት ነበርና፡ ሊቤዣት ወጣ። ክርስቶስ ሃጢያት መሆን አላስፈለገውም፡ የጠፋውን ልጁን ለመቤዠት ግን፡ ወጥቶ ኃጢአትን ወሰደ። አያችሁ? አያችሁ? እራሱን በጥላ አሳየ።

... ሙሴም በጫካው ውስጥ፡
ሰምታችኋል ወንጭፍ ይዞ ስለ ማይፈራው ስለ ዳዊት፡
ሰምታችኋል ስለ ህልሙ ስለ ዮሴፍ ታሪክ፡ (ነብይ።)
ሁሌ ምንዘምረው የዳንኤል የአንበሶቹ መዝሙር።
ኧረ፡ ብዙ፡ በመጽሐፍ የተመሰከረላቸው ብዙ አሉ፡
እኔም...

625 እነዚህ፡ እነዚህ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ ናቸው።

እኔም...

ሁሉም ግን፡ በእርሱ ተገለጡ። አያችሁ? ያለ እርሱ፡ ሁሉም ሙታን ናቸው። አያችሁ? እኔም እርሱ እሆን ዘንድ፡ አካሉ መሆን አለብኝ። አሜን! አያችሁ?

ሁሉንም ለማግኘት እንዴት እንደምጓጓ፡ አውጃለሁ። (ትክክል ነው።)
የእግዚአብሔር ልጅ፡ እርሱ መሪያችን
በአየር ላይ በሚደረገው ጉባኤያችን።

626 ዕብራውያን 11፡ "ያለ እኛ ፍጹም ሊሆኑ አይችሉም፡" ይላል። ያለ ራስ፡ ያለ እውቀት፡ ያለ ጭንቅላት፡ እጆች እና እግሮች ፍጹማን ሊሆኑ አይችሉም። አያችሁ? እኛ ሁላችንም በእርሱ ፍፁማን ተደርገናል፡ "ስለዚህ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል፡" ከፍርድ ነፃ፡ ከኃጢአት፡ ከሞት ተሻገርን... አሜን! "አየር ላይ በሚደረገው ጉባኤያችን የእግዚአብሔር ልጅ መሪያችን ይሆናል።" ትወዱታላችሁን?

እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
እርሱ እኔን...

627 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት በእነዚህ መሃረብ ላይ ይምጣና፣ ጌታ ሆይ፣ የታመሙትንም ይፈውስ። ይህ በሚዳሰሳቸው ጊዜ፡ እንዲሁ ይሁንላቸው። እንዲሁ እንደምትፈጽምላቸው፡ በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ። አሜን።

... በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

628 እስቲ አስቡት፡ "ክርስቶስ ተገለጠ፡" አሁን በእኛ ውስጥ፡ አሁን በእኛ ውስጥ ተገልጧል። እንዴት፡ የተገለጠው እንዴት ነው? ቀድሞ ስለወደደኝ። ምንስ አደረገ?

መዳኔንም ገዝቶልኛልና
በ...

629 ክብር! ከሙሴ ጋር በምድረ በዳ የነበረው፡ ያ ታላቅ የቃል ኪዳን መልአክ፡ በደማስቆ መንገድ ወደ ጳውሎስ የመጣው እርሱ፡ ከእና ጋር አብሮ ፎቶ ግራፍ እንዲነሣ ፈቀደ፡ ይህም ምስል በቀደምለት **በታይም** መጽሔት የወጣው ምስል ራሱ ነው፡ ያው ቃል፣ በአንዱ አምላክ፣ በተመሳሳይ መስመር፣ በተመሳሳይ መንገድ፣ በተመሳሳይ የተሰፋ ቃል! "ሁለት ወይም ሦስት በሰሜ በተሰበሰቡበት እኔ በመካከላቸው እገኛለሁ።" ከዚያ እሱ በዚያ ይገኛል። "የእግዚአብሔር መላእክት በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራሉ፡" በቃሉ ብቻ በሚታመኑ ዙርያ።

ማንም ሰው እግዚአብሄርን ሳይፈራ ቃሉን ማክበር አይችልም። ገባችሁ? እርሱም፡ በመንፈስ ሰናመልከው፡ ዛሬ ጠዋት፡ ከኛ ጋር እዚህ አለ።

630 ኧረ እንደው፡ ከእንደዚህ አይነት ከባድ መልእክት በኋላ፣ በመንፈስ እሱን በጥቂቱ ማምለክ ያለብን ይመስለኛል። እንደው፡ አይናችሁን ጨፍናችሁ ያን መዝሙር በድጋሚ እንዘምርለት፡ "እወደዋለሁ፡ እኔ እወደዋለሁ፡" እንደው፡ እጆቻችሁን—ሁላችሁ፡ ወደርሱ ዘርጉና።

እወደዋለሁ፡ እኔ እወደዋለሁ
እርሱ እኔን... ቀድሞ ወዶኛልና
መዳኔንም ገዝቶልኛልና
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

ኦህ፡ ማይ፡ አቤት ሰንወደው!

እምነት በአባት ላይ፡ እምነት በልጅ ላይ፡
እምነት በመንፈስ ቅዱስ፡ ሦስቱ አንድ ናቸውና፡
አጋንንት ይንቀጠቀጣሉ፡ ኃጢአተኞችም ይነቃሉ፡
ጆሆቫን ማመን ሌላውን ሁሉ ያናውጣልና።

631 አሜን! ክብር ለእግዚአብሔር! አቤት ሰንወደው! አምልኩት፡ ከልባችሁ ቀድሱት አሁን፡ የሰራውን መልካም ነገር—አሁን አሰቡት። ያደረግልንን ተመልከቱ። እነዚህ የራዕይ አመታት ሁሉ፡ አንዳቸውም አልወደቁም። ይሆናል ያለው ሁሉ፡ ይሆናል እንዳለው ተፈጽሟል።

632 እኔ እወዳችኋለሁ። ልጆች ሆይ፡ የታዘዛችሁትን የእግዚአብሔር ትዕዛዝ አትርሱ፡ "እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ።" ሁሉንም ውደዱ። ትክክል ይሁን ሰህተት፡ ኃጢአተኛ ይሁን ቅዱስ፡ እንዲሁ፡ ውደዷቸው። ካልቻላችሁ፡ እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ ጸልዩ፡ እግዚአብሔር ሐጥያተኛውን ይወዳልና። ያኔ የእግዚአብሔር ባሕርይ በእናንተ ነው። ሰውዬው ቢሳሳትም፡ እንዲሁ፡ ውደዱት። ሐጥያቱን አትካፈሉ። አያችሁ? ከሐጢያቱ ግን አትካፈሉ። በተወደደች መንገድ በእናንተ ዘንድ ሰላለው የሕይወት ተሰፋ ንገሯቸው፡ ይህ ግን በግሳጼ አይሁን፡ በመራራነትም አይሁን፡ በተወደደች መንገድ ይሁን፡ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ለእናንተ ተገለጠ።

የኢየሱስ ሰም ካንተ ጋር ውሰድ፡
የሀዘንና የዋይታ ልጅ፡
ደስታ እና ምቾት ይሰጥሃል፡
ኦህ፡ በምትሄዱበት ሁሉ ውሰዱ። (ይሄን አትርሱ።)

ኦህ፡ ውድ... (ያ ሰም!)... ኦ...

633 ሰሙ አለን። የተጠራነው በሰሙ ነው።

የምድር ተሰፋ የሰማይ ደሰታ፡
ውድ ሰም፣ ኦ ድንቅ ሰም!
የምድር ተሰፋ የሰማይ ደሰታ።

634 አሁን እንደገና እስክንገናኝ ድረሰ፡ ትንሽ ሚሰጥር እሰጣችኋለሁ፡ አስታውሱ፡ እንደቆምን፡ ይህን አስታውሱ፡

በኢየሱስ ስም ስገድ፣
በእግሩ ስር ውደቅ፡
የነገስታት ንጉስ ሰማይ ላይ እናከብራለን፡ (ዘውድ እንጭንበታለን!)
ጉዟችን ሲጠናቀቅ።

ውድ ስም፡ (የተከበረ ስም!) (እንዴት ጣፋጭ ነው!)
የ ክብር ተስፋ...

635 ምን? ሦስት መአዝናዊ መገለጥ! በርሱ ዘንድ የተገለጠ፡ ሰማያዊ ተስፋ ነው።

ውድ ስም፡ (የተከበረ ስም!) እንዴት ጣፋጭ ነው!
የምድር ተስፋ እና ደስታ...

636 ምንድን? የምድር ተስፋ እና የገነት ደስታ፣ ሁሉም ነገር በክርስቶስ ተገልጧል። እግዚአብሔር፣ ቤተ ክርስቲያን፣ ሌላው ሁሉ በክርስቶስ ተገልጧል። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈ ቃል ነው። ይህም፡ እርሱ ቃል ነው። መገለጡም ወደ ቃሉ ሥጋ የመጣ፡ የሕይወት ምስክርነት ነው። ኦህ፡ አይደንቅም ወይ!

የኢየሱስን ስም ውሰድ...

አሁን በደንብ ስሙት።

(ይሄን አትርሱ።)... ከወጥመድ ሁሉ... እንደ ጋሻ;
ፈተናዎች ሲከቧችሁ፡ (ምን ይውጣሃል ሲላችሁ? )

በጸሎት ቅዱስ ስሙን ተንፍሱ።

ውድ ስም፡ (ውድ ስም!) እንዴት ጣፋጭ ነው! (እንዴት ጣፋጭ ነው!)
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ውድ ስም፡ (ውድ ስም!) እንዴት ጣፋጭ ነው!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

637 አዎን... እናንተ ሳታውቁት፡ መንፈሳዊያን ስለሆናችሁ ብቻ፡ መንፈሳዊ ነገሮችን ታያላችሁ። እናንተ ሳታውቁት፡ እግዚአብሔር ግን ያውቀዋል። አሁን ግን ዞር ብላችሁ ወደ ሰዓታችሁ ከተመለከታችሁ፡ አሁን ሁለት ሰዓት፡ እናቱ ላይ ሆኗል፡ ይህም የሁለተኛው ስሕበት ፍጻሜ ጊዜ ነው። ስሦስተኛው ስሕበት በደጅ ነው! እያችሁ?

በኢየሱስ ስም ስገድ፡
በእግሩ ስር ውደቅ፡
የነገሥታት ንጉሥ በሰማይ እናከብራለን፡
ጉዟችን ሲጠናቀቅ።

ውድ ስም...

ሁለተኛው ስሕበት ጨርሶ ተገልጧል!

የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ውድ ስም፣ ኦ ድንቅ ነው!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

638 መንፈሱ ይህን ዝማሬ ወስዶ ከዚህ ኦክታቭ ይልቅ ከፍ ወዳለው እንዳነሳው አስተውላችኋል? ቅቀጣይ ስሕበት በደጅ ነው! አሜን! አሀ-ሃሀ።

የኢየሱስ ስም ካንተ ጋር ውሰድ፡

ካሰብከው በላይ ረፍዷልና፡

... የሐዘን እና የዋይታ፡
ደስታ እና ምቾት ይሞላሃል፡
ኦሀ፡ በሄድክበት ቦታ ሁሉ ውሰደው።

ውድ ስም፡ (ውድ ስም!) እንዴት ድንቅ ነው!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ውድ ስም፡ ኦ ድንቅ ነው!
የምድር ተስፋ እና ደስታ...

አሁን ፈተናዎች ቢመጡ፡ ምን ታደርጋለህ?

የኢየሱስን ስም ካንተ ጋር ውሰድ፡
ከወጥመድ ሁሉ ጋሻ ይሆናል፡
ፈተናዎች ሲመጡብህ... (እምነትህን የሚያጎድል ሲመጣብህ)... ጠንከር በል፡
ቅዱስ ስሙን በጸሎት መተንፈስ፡ አትርሳ።

ውድ ስም፡ ኦ ድንቅ ስም!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ውድ ስም፡ (ውድ ስም!) እንዴት ድንቅ ነው!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

639 አሁን ሁላችንም በአክብሮት፡ ራሶቻችንን ዝቅ እናደርጋለን። አሁን ተመልከቱና።

በኢየሱስ ስም ስር ሰገድ...

640 [ልሳኖች እና ትርጓሜዎች ተሰጠ—እርታዒ።] አሁን ከተረዳችሁ፡ የጌታ መንፈስ ባልታወቁ ቋንቋዎች፡ በሰብሰባው ላይ ወርዷል፡ የጌታ ቃል! በማያውቀው ሰው የተነገረውን፡ በሌላ በማያውቀው ሰው ተተረጎመ። ጠላት መጥቶባቸው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያላወቁ ጊዜ ትዝ ይላችኋል? የጌታ መንፈስ በአንድ ሰው ላይ ወረደ፥ መደረግ ያለበትን ገለጠላቸው። ኦሀ፡ ማይ!

641 አሁን በትሕትና፡ ራሶቻችሁን ዝቅ አድርጉ፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

እሰክንገናኝ! እሰክንገናኝ!
በኢየሱስ እግር ላይ እሰክንገናኝ፡
እሰክንገናኝ!

እሺ፡ ፓስተር።

## **ክርሰቶሰ የተገለጠ የእግዚአብሔር ምሰጢር ነው** AMH63-0728

(Christ Is The Mystery Of God Revealed)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ ሐምሌ 28 ቀን፡ 1963፡ እሁድ ጠዋት፡ በዩ.ኤሰ.ኤ.፡ ጀፈርሰንቪል ኢንዲያና፡ ከሚገኘው ከብራንሃም ተበርናክል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይሰ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግሰ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2023 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org